# አማርኛ

## እንደአፍመፍቻ ቋንቋ

### የተማሪ መጽሐፍ

6ኛ ክፍል

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የትምህርት ሚኒስቴር

ISBN: 978-99944-2-049-0
ዋጋ ብር 25.00

አማርኛ
እንደአፍ መፍቻ ቋንቋ
የተማሪ መጽሐፍ 6ኛ ክፍል

# አማርኛ

## እንደአፍ መፍቻ ቋንቋ

### የተማሪ መጽሐፍ

6ኛ ክፍል

ማዳመጥ

መጻፍ



መናገር

ማንበብ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር




**ውድ ተማሪዎች!**
**ለዚህ መማሪያ መጽሐፍ ተገቢውን እንክብካቤና ጥበቃ አድርጉ!**

ይህ መማሪያ መጽሐፍ የትምህርትቤታችሁ ንብረት ነው፡፡ መጽሐፉ እንዳይበላሽ ወይም እንዳይጠፋ በጣም መጠንቀቅ አለባችሁ፡፡ መጽሐፉን በጥንቃቄ ለመያዝ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን 10 መመሪያዎች ተግባራዊ አድርጉ፡፡

1. መጽሐፉን ከጉዳት ለመከላከል በላስቲክ ወይም በወረቀት ሸፍኑት፡፡
2. መጽሐፉን ሁልጊዜ በደረቅና በንጹህ ቦታ አስቀምጡት፡፡
3. መጽሐፉን ለመጠቀም ስትዘጋጁ በቅድሚያ እጃችሁ ንጹህ መሆኑን አረጋግጡ፡፡
4. በመጽሐፉ ሽፋን ወይም የውስጥ ገጾች ላይ አትጻፉ፡፡
5. በመጽሐፉ ገጾች መካከል እልባት ለማድረግ ስትፈልጉ ብጣሽ ወረቀት፣ ክር ወይም ካርድ ተጠቀሙ፡፡
6. በመጽሐፉ ውስጥ ያሉትን ሥዕሎች ወይም ገጾች በፍጹም አትቅደዱ፡፡
7. በመጽሐፉ ውስጥ የተቀደደ ወይም የተገነጠለ ገጽ ሲኖር በሙጫ ወይም በሌላ ንጹህ ማጣበቂያ አጣብቁት፡፡
8. መጽሐፉን ከቦርሳችሁ ስታስገቡ ወይም ስታወጡ ጥንቃቄ አድርጉ፡፡
9. መጽሐፉን ለሌላ ሰው ስታቀብሉም ሆነ ከሌላ ሰው ስትቀበሉ ተገቢውን ጥንቃቄ አድርጉ፡፡
10. መጽሐፉን ለመጀመሪያ ጊዜ ስትጠቀሙ ሽፋኖቹና ገጾቹ እንዳይገነጠሉ መጽሐፉን በጀርባው ጋደም አድርጋችሁ አስቀምጡት፤ ከዚያም ጥቂት ገጾችን ቀስ እያላችሁ በየተራ ግለጡ፤ በግራና በቀኝ እጃችሁ የያዛችሁትን የመጽሐፉን ክፍል በኃይል አትጫኑት (አትመንጭቁት)፡፡

# አማርኛ

## እንደአፍ መፍቻ ቋንቋ

## የተማሪ መጽሐፍ

## 6ኛ ክፍል


### አዘጋጆች

ፀጋዬ በየነ አሸናፊ

አበበች ተስፋዬ ዳምጤ

ፋሲል መኳንንት ያለው

ሙሉ ብርሃን ጠገናው

### አማካሪ

ጌታቸው እንዳላማው አስፋው (ረ/ፕ)

### የቡድን መሪ

ቻላቸው ገላው ሰጠኝ



የኢፌዴሪ የትምህርት ሚኒስቴር እና አብክመ ትምህርት ቢሮ

ይህ መጽሐፍ የተዘጋጀው ከአሜሪካ ህዝብ በአሜሪካ ዓለማቀፍ የልማት ድርጅት (United States Agency for International Development (USAID) በኩል በተገኘው የገንዘብና የቴክኒክ ድጋፍ፣ በትምህርት ሚኒስቴር፣ በክልሉ ትምህርት ቢሮና በREAD TA ፕሮጀክት ትብብር ሲሆን የህትመቱ ወጪ በሁለተኛው የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማረጋገጫ ፕሮግራም (General Education Quality Improvement Program (GEQIP II) ተሸፍኗል።

የመጽሐፉ ህጋዊ የቅጂ ባለቤት ©2007 ዓ.ም. በኢ.ፌዴ.ሪ ትምህርት ሚኒስቴርና የአማራ ክልል ትምህርት ቢሮ ናቸው።

ISBN: 978-99944-2-049-0

# የይዘት ማውጫ


መግቢያ (ለወላጆች ማስታወሻ) ............................ iv

ምዕራፍ አንድ

ባህላዊ ልብስ ............................ 1

ምዕራፍ ሁለት

የህይወት ታሪክ ............................ 23

ምዕራፍ ሦስት

ቃላዊ ግጥሞች ............................ 43

ምዕራፍ አራት

ልጅነት ............................ 67

ምዕራፍ አምስት

ቱሪዝም ............................ 89

ምዕራፍ ስድስት

ተወዳጅ ታሪኮች ............................ 109

ምዕራፍ ሰባት

ኤች አይቪ. ኤድስ በኢትዮጵያ ............................ 136

ምዕራፍ ስምንት

ባህላዊ፣ ክንዋኔዎች ............................ 159

ምዕራፍ ዘጠኝ

ሴቶችን ማብቃት ............................ 184

ምዕራፍ አሥር

ተውኔት ............................ 207

ሙዳየ ቃላት ............................ 234

ዋቢዎች ............................ 238

# መግቢያ (ለወላጆች ማስታወሻ)

ይኽ መጽሐፍ ከ5ኛ እስከ8ኛ ክፍል ድረስ በአፍ መፍቻ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎች በቋንቋዉ በብቃት ማንበብ፣ መጻፍ፣ ማዳመጥና መናገር እንዲችሉ ለማድረግ ተሻሽሎ የተዘጋጀው የአፍ መፍቻ ቋንቋ ሥርዓተትምህርት አካል ነው። የመጽሐፍ ዝግጅቱም፣ ተማሪዎች እንዴት ማንበብና መጻፍ እንደሚችሉ፣ መማር ፈጠራዊና አስደሳች እንዴት እንደሚሆን፣ የትምህርትቤት ውስጥ ተግባራት እንዴት መማርን እንደሚያግዙና እንደሚያጐለብቱ በተደረጉ ጥናቶች ላይ የተመሠረተ ነው።

ከዚህ በተጨማሪም መጽሐፉ ስለነዚህ የክፍል ደረጃዎች ሥርዓተትምህርትና ስለሚሰጡ ትምህርቶች ሽፋን መረጃ ይሰጣል። በመሆኑም ተማሪዎችና ወላጆች በትምህርትቤት የተከናወኑ ተግባራትን ለማስቀጠልና ይበልጥ ለማዳበር በጋራ ለመሥራት ያስችላቸዋል።

## የሥርዓተትምህርቱ መሠረታዊ መርሖች፤

1. ተማሪዎች በማኅበረሰብ ሕይወት ውስጥ አስፈላጊ ስለሆኑ የምንባብ ይዘቶችና ርዕሰጉዳዮች ይማራሉ (እያንዳንዱ ምዕራፍ አንድ የምንባብ ይዘትና የተለያዩ ርዕሰጉዳዮችን ይሸፍናል።)
2. ተማሪዎች ስለነዚህ የምንባብ ይዘቶችና ርዕሰጉዳዮች የተጻፉ ምንባቦችን ካነበቡና ካዳመጡ በኋላ፣ በእነሱ ላይ በመመሥረት ይናገራሉ፤ ይጽፋሉም።
3. ሁሉም የቋንቋ ትምህርት ከእነዚህ የምንባብ ይዘቶች፣ ርዕሰጉዳዮችና ምንባቦች ጋር የተያያዘ ነው።
4. ተማሪዎች በርካታ የመናገር፣ የማዳመጥ፣ የማንበብና የመጻፍ ተግባራት እንዲያከናውኑ ይጠበቅባቸዋል። ስለሆነም ተግባራቱን በቀላሉ በተገቢ ሁኔታ ለማከናወንና ራሳቸውንም በትክክል ለመግለጽ አይቸገሩም፤
5. ተማሪዎች በግላቸው ብቻ ሳይሆን አብረዋቸው ከሚማሩ ቢጤዎቻቸውና በቡድን አብረዋቸው ከሚሠሩ ተማሪዎች ይማራሉ።
6. ተማሪዎች በምዕራፎቹ ይዘቶችና በርዕሰጉዳዮች ላይ ተመሥርተው የቀረቡ ጽሑፎችን በሚያዳምጡበት፣ በሚያነቡበትና አዳዲስ ቃላትን በሚተዋወቁበት ጊዜ የቃላቱን ፍቺዎች ይማራሉ፤ ይረዳሉ፤ ይጠቀሙባቸዋልም። እነዚህን አዳዲስ ቃላት በሚጠቀሙበት ጊዜም የበለጠ ይረዷቸዋል፤ የቋንቋ ችሎታቸውንም የበለጠ ያበለጽጋሉ።

## በቤት ውስጥ ከቤተሰብ ጋር በጋራ መማር

ተማሪዎች በትምህርትቤት የሚቀስሟቸውና በቤታቸው ከወላጆቻቸው ጋር የሚሠሯቸው በርካታ ትምህርታዊ ተግባራት አሉ። ስለዚህ ወላጆች ከእነዚህ በርካታ ተግባራት ቢያንስ የተወሰኑትን ከልጆቻቸው ጋር በጋራ እንዲሠሩ ይጠበቃል።

1. ወላጆች የሳምንቱን ወይም የዕለቱን የምንባብ ይዘት ወይም ርዕሰጉዳይ ልጆቻችሁን በመጠየቅ ተረዱ።
2. በትምህርትቤት ያነበቧቸውን ምንባቦች በጋራ አንብቡ። ይኼንንም ልጆች ወይም ወላጆች ለብቻ ወይም በየተራ በማንበብ ሊተገብሩት ይችላሉ።
3. ልጆቻችሁን የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ስለምንባቡ ተወያዩ፤
    - ምንባቡ ምን ዓይነት የምንባብ ይዘት ይሸፍናል?
    - በምን ዓይነት ርዕሰጉዳይ ላይ ያተኩራል?
    - ከዚህ የምንማረው ምንድን ነው?
    - ስለርዕሰጉዳዩ በተጨማሪ ምን እናውቃለን? ስለርዕሰጉዳዩ በዜና ወይም ሌሎች ሰዎች ሲናገሩ የሰማነው ምንድን ነው? ስለርዕሰጉዳዩ በሌላ ቦታ ምን አንብበናል?
    - ስለርዕሰጉዳዩ ወይም ርዕሰጉዳዩ በምንባቡ ውስጥ በቀረበበት መንገድ ላይ በግል ያለን አስተያየት ምንድን ነው?
    - በምንባቡ ውስጥ ከተጠቀሰው ሌላ ስለርዕሰጉዳዩ ምን ማወቅ እንፈልጋለን?
    - ስለርዕሰጉዳዩ በተለየ ሁኔታ ምን ለመሥራት እንፈልጋለን?
4. በምንባቡ ውስጥ ስላጋጠሟችሁ ቃላት የሚከተሉትን ዓይነት ጥያቄዎች በመጠየቅ ተወያዩ፤
    - የዚህ ቃል ፍቺ ምንድን ነው?
    - ቃሉስ ምንባቡን ለመረዳት ረድቶኛል?
    - በተለያዩ መንገዶች በጥቅም ላይ ውሏል?
    - እንዴትስ በሕይወቴ ውስጥ ልጠቀምበት እችላለሁ?
5. ስለርዕሰጉዳዩ የሚያወሱ ሌሎች ጽሁፎችን ከመጻሕፍት፣ ከጋዜጦች ወይም ከመጽሔቶች ፈልጋችሁ አንብቡ።
6. በግል ያንብቡ (ልጆች ራሳቸውን ችለው በግላቸው እንዲያነቡ አበረታቱ)፤ ከዚያም ስላነበቡት ጉዳይ ተወያዩ።
7. ከቴሌቪዥን፣ ከሬዲዮ ወይም ከድረገጽ ስለርዕሰጉዳዩ አዳምጡ ወይም

ተመልከቱ።

8. ልጆች በክፍል ውስጥ ምን ምን እንደተማሩ ደብተራቸውን በጋራ ተመልከቱ፤ ስለምን እንደተማሩና ምን እንደተሰማቸው የሚከተሉትን ዓይነት ጥያቄዎች በማንሳት ተወያዩ።
    - ትምህርቱ ከባድ ነው/ነበር?
    - ትምህርቱ ቀላል ነው/ነበር?
    - ለቋንቋ ትምህርቱ ጠቃሚ ነው/ነበር?
    - ልጆቹ ቀጥሎ ምን መማር ይፈልጋሉ?
9. የመጻፍ ችሎታቸውን ለማዳበር የተማሯቸውን ዝርዝር ክሂሎች በመረዳት ምን እንደተማሩ ለማወቅ የሚከተሉትን ዓይነት ጥያቄዎች ልጆቹን ጠይቋቸው፤ ለምሳሌ፣ የቃላቱ ፊደላት በተገቢ ሁኔታ ተጽፈዋል/ተሰድረዋልወይ? በዓርፍተነገሮች ውስጥና/ወይም መካከል ያሉት ሥርዓተነጥቦች (አራት ነጥብ፣ ነጠላ ሰረዝ፣ ድርብ ሰረዝና የመሳሰሉት) በተገቢ ቦታቸው ገብተዋልወይ? ወዘተ.
10. ልጆች የተሰጣቸውን የቤትሥራ ሲሠሩ፣ ራስን ወይም ሌሎች የቤተሰብ አባላትን በቃለመጠይቅ፣ ንግግርን በመጻፍ ወይም በንግግር ልምምድ ወቅት በመሳተፍ አብሮ መሥራት ተገቢ ነው።
11. ልጆች አጫጭር ደብዳቤዎች (ለምሳሌ፣ ለቤተሰብ አባላት ወይም ለጓደኞች) እንዲጽፉ ወይም በዕለቱ ወይም በሳምንቱ ስለተከሰቱ ጉዳዮች ወይም ስለአንድ ጉዳይ ያላቸውን አስተያየት ወዘተ እንዲጽፉ አበረታቷቸው።

## የመጽሐፍ ይዘቶች አደረጃት

### ትምህርቶች

በመጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት ይዘቶች በምዕራፍ ተደራጅተው ቀርበዋል። እያንዳንዱ ምዕራፍ የራሱ የምንባብ ይዘት፣ እያንዳንዱም የምንባብ ይዘት ሦስት ርዕሰጉዳዮችና አራት አራት ምንባቦች አሉት። የምንባብ ይዘቶቹና ርዕሰጉዳዮቹ ተማሪዎች በቋንቋቸው እንዲናገሩ፣ እንዲያዳምጡ፣ እንዲያነቡና እንዲጽፉ እንደመነሻ ያገለግሏቸዋል።

ተማሪዎች በእያንዳንዱ ምዕራፍ የሚያዳብሯቸው ክሂሎች ከላይ የተጠቀሱት ናቸው። ወላጆች ምናልባት ስለነዚህ ክሂሎች ጥያቄዎች ካሏችሁ ልጆቻችሁን ወይም መምህሮቻቸውን ጠይቃችሁ ማብራሪያ ማግኘት ትችላላችሁ። በተጨማሪም ልጆቻችሁን እንዴት መርዳት እንደምትችሉ ከመምህራን ጋር ተወያዩ።

## የቃላት ጥናት

ተማሪዎች አዳዲስ ቃላትን፣ የቃላቱን የተለያዩ የመዋቅር አካላት፣ ለተለያዩ አጠቃቀሞች የሚያሳዩትን የቅርጽ ለውጦች ይማራሉ።

## አንብቦ መረዳት

ተማሪዎች የሚያነቡትን ጽሑፍ እንዴት ትኩረት ሰጥተው እንደሚያነቡና እንደሚረዱ ይማራሉ። ከዚህም በተጨማሪ ባነበቡት ጽሑፍ ላይ ተመሥረተው በሚዘጋጁ የመናገርና የመጻፍ ተግባራት ላይ ይሳተፋሉ። እነዚህም ተግባራት የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ፤

- ምንባቡ ስለተመሠረተበት ይዘትና ርዕሰጉዳይ መነጋገር፣
- ከማንብብ በፊት መገመት፣
- አስፈላጊ ቃላትን መማርና ስለእነሱ መነጋገር፣
- የቅድመንባብ፣ የማንበብ ሂደትና የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን መጠየቅና መመለስ፣
- ከሌሎች ጋር በምንባቡ ላይ በክፍል ውስጥ መወያየት፣
- ስለምንባቡ፣ ስለርዕሰጉዳዩና ስለምንባቡ ይዘት መጻፍ፣
- ስለምንባቡ እንዲናገሩ፣ የግል ሀሳባቸውንም እንዲያቀርቡ ማድረግ፣
- በምንባቦቹ ይዘቶች ወይም በርዕሰጉዳዮች ላይ ያተኮሩና በክፍል ውስጥ ሊከወኑ የሚችሉ ታሪኮችን፣ ግጥሞችን፣ የተውኔት ጽሑፎችን ስጥቶ እንዲከውኑ ማድረግ።

## ቃላት

ተማሪዎች በሚያነቧቸውና በሚያዳምጧቸው ምንባቦች ውስጥ የሚያጋጥሟቸውን አዳዲስ ቃላት ተምረው ይጠቀማሉ። ለምሳሌ፡-

- የቃላትን ንበት፣ ፍቺና የተለያየ አጠቃቀም ይማራሉ፤
- ተመሳሳይ ፍቺ ያላቸውን ሌሎች ቃላት ይማራሉ፤
- በክፍል ውስጥና ከክፍል ውጪ (ለምሳሌ በቤት ወይም በማኅበረሰብ አካባቢ) በሚፈጸሙ የመናገርና የመጻፍ ተግባራት ላይ ቃላቱን ይጠቀማሉ።

## መጻፍ

ተማሪዎች ስለሚያነቧቸው የምንባብ ይዘቶችና ርዕሰጉዳዮች በግል ወይም በቡድን ይጽፋሉ። የሚጽፏቸውም ጽሑፎች የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ፤

- የተለያዩ የጽሑፍ ዓይነቶችን፣ ለምሳሌ ተራኪ፣ ገላጭና አወዳዳሪ ወይም አነፃፃሪ ጽሑፎችን መጻፍ፣
- ሃሳባቸውን እንዲጽፉ፣ እንዲከልሱ (እንዲያርሙ) እና ለኅትመት ዝግጁ እንዲያደርጉ ማድረግ፣
- የጽሑፍን የተላያዩ ቁምነገሮች፣ ለምሳሌ በቃላት ውስጥ ፊደላትን በአግባቡና በትክክል መጻፍ፣ ቃላትን በትክክል ማንበብ፣ አጥረው የተጻፉ ቃላትን ወዘተ መረዳት።

## አቀላጥፎ ማንበብ

ተማሪዎች ጽሑፎችን ለደረጃቸው ተገቢ በሆነ ፍጥነት፣ በትክክልና በተገቢ አገላለጽ ማለትም የምንባቡን መልዕክት በሚገልጽ ስሜት ደረጃ ድምፅ በማሰማት ያነባሉ።

## ቃላዊ ክሂሎች፣ ማዳመጥና መናገር

ተማሪዎች በሚያነቡትና በሚያዳምጡት ጽሑፍ ላይ ትኩረት ማድረግንና መረዳትን ይማራሉ። በተጨማሪም በሚያዳምጡትም ሆነ በሚያነቡት ጽሑፍ ላይ በተመሠረቱ ተግባራት ላይ ይሳተፋሉ። የሚሠሯቸውም ተግባራት የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ፤

- የማዳመጡ ምንባብ ስለተመሠረተበት ይዘትና ርዕሰጉዳይ መነጋገር፣
- ከማዳመጥ በፊት መገመት፣
- ቍልፍ ቃላትን መማርና ስለእነሱ መነጋገር፣
- የቅድመማዳመጥ፣ የማዳመጥ ሂደትና የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎችን መጠየቅና መመለስ፣
- ከሌሎች ጋር በማዳመጥ ምንባቡ ላይ በክፍል ውስጥ መወያየት፣
- ስለማዳመጥ ምንባቡ፣ ስለርዕሰጉዳዩና ስለማዳመጥ ምንባቡ ይዘት መጻፍ፣
- ስላዳመጡት ምንባብ መናገር፣ የግል ሀሳብን ማቅረብ፣
- በማዳመጥ ምንባቦቹ ይዘቶች ወይም በርዕሰጉዳዮች ላይ ያተኮሩና በክፍል ውስጥ ሊከወኑ የሚችሉ ታሪኮችን፣ ግጥሞችን፣ ተውኔቶችን መከወን።

## ሰዋስው

ተማሪዎች የቋንቋውን የተወሰኑ መዋቅራዊ ክፍሎች ለምሳሌ፣ ነጠላና ብዙ ቍጥር ስሞችን፣ የአሁንና የኃላፊ ጊዜ ግሶችን፣ ቅጽሎችን፣ ተውሳከግሶችን፣ ነጠላና ድብልቅ ዓረፍተነገሮችንና አጠቃቀማቸውን ይማራሉ።



# ባህላዊ ልብስ

## ምዕራፍ 1

### የሠርግ አለባበስ

1ኛ ሳምንት 1ኛ ቀን

## የቃላት ጥናት

### መነጠልና ማጣመር

**ተግባር**

የሚከተሉትን ውስብስብ ቃላትና ሐረጋት ነጣጥላችሁና አጣምራችሁ አንብቡ።

| | ነጣጥሎ ማንበብ | አጣምሮ ማንበብ |
|---|---|---|
| ሀ | አንባር-ኦች-ሽ | አንባሮችሽ |
| ለ | እጅጌ-ዎች-ኡ | እጅጌዎቹ |
| ሐ | ተኸርጎርጉረው-ኣል | ተኸርጎርጉረዋል |
| መ | ያብለጨልጭ-ኣል-ኡ | ያብለጨልጫሉ |
| ሠ | ተጫምቶ-ኣል | ተጫምቷል |
| ረ | ባት-ኧ-ሁለት | ባተሁለት |
| ሰ | እየ-ተ-ጠቃቀሱ | እየተጠቃቀሱ |
| ሸ | ተንጠልጥሎ-ኣል | ተንጠልጥሏል |

## ማንበብ

### ሙሽሮቹ

### ቅድመንባብ

### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

**ተግባር 1**

ምንባቡን ከማንበባችሁ በፊት ለሚከተሉት ቁልፍ ቃላት ፍቺ ስጡ።

ሀ. ጥበብ ለ. እጀጠባብ ሐ. ጌጣጌጥ

## ተግባር 2

ሥዕሉን በመመልከት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. ሙሽሮቹ የትኞቹ ይመስሏችኋል? ለምን?

ለ. በሥዕሉ ውስጥ የምታዩአቸው ሰዎች ምን ምን ዓይነት ልብሶች ለብሰዋል?

## የማንበብ ሂደት

## ተግባር

መምህራችሁ በሚያመቻቹላችሁ ሁኔታ “ሙሽሮቹ” በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ በለሆሳስ አንብቡ።

### ሙሽሮቹ



ወሩ ጥር ነው። በአንድ የገጠር ሠርግ ሥነሥርዓት ላይ ታድሜያለሁ። የአካባቢው ባህል በሚፈቅደው መሠረት ዶቃና ከረሜላ ሰጥቼ ሙሽሮቹን የማየት ዕድል አገኘሁ። በቀጫጭን እንጨቶች፣ በጭድ፣ በወይራና በባህርዛፍ ቅርንጫፎች ወደተሠራው ጫጉላ ቤት ገባሁ።

ከባሏ በስተቀኝ የተቀመጠችውና በባህላዊ መንገድ የተዋበችው ሙሽራ ተመልካችን ታማልላለች። በጭንቅላቷ ዙሪያ በአግባቡ ከተከረከመው ጋሜዋ መካከል ቁንጮዋ

ሸሩባ ተሠርቶ ወደኋላ ተንጠልጥሏል። ከሹሩባዋ ዘለላዎች ጫፍ ዛጎሎች ተቋጥረዋል፤ ጭንቅላቷን ባንቀሳቀሰች ቁጥር ዛጎሎቹ እርስበርስ እየተጋጩ ድምጽ ያሰማሉ። በአደስ ተለውሶ የተቀባችው ቅቤ እየቀለጠ በግንባሯ ሊወርድ አስቧል። መልካም መዓዛውም ከሩቅ ያውዳል። ዓይኖቿ ደግሞ በኩል ተውበዋል። እጆቿና እግሮቿ በእንሶስላ ደምቀዋል። በሁለቱ ክንዶቿ ላይ የሚታዩት አንባሮች በእንሶስላ ከደመቁት እጆቿ ጋር እየተጠቃቀሱ ተመልካችን ያፈዛሉ። በግራ እጅ ጣቶቿ ያጠለቀቻቸው ቀለበቶች ያብለጨልጫሉ። ቀይ ጃንጥላ ከጎኗ ግድግዳውን ተደግፎ ይታያል።

የለበሰችው ጥበብ ቀሚስ የሀገራችንን ሸማ ሠሪዎች ችሎታ አጉልቶ ከማሳየቱም በላይ ለሙሽራዋ ልዩ ውበት አጎናጽፏታል። የቀሚሷ ፊት ለፊት በሚያምር ጥልፍ አጊጧል። የእጅጌዎቹ ጫፍ ዙሪያውን በተመሳሳይ ጥልፍ አምሯል። ቁርጭምጭሚቷን ተንተርሰው የተቀመጡት አልቦዎች ከቀሚሷ ጥለት ጋር የተለየ ውበት ፈጥረዋል። ባለቀይ ጥለት ነጠላዋም ውበት ጨምሮላታል። ከነጠላዋ በላይ የተደረበው በወርቅ ቀለም የተንቆጠቆጠ ካባ ንግስት አስመስሏታል። በአንገቷ ላይ ያጠለቀቻቸው ማርዳ፣ ድሪ፣ እርባንና ጠልሰም በነጠላዋ ተሸፍነው በከፊል ይታያሉ። በቀጭኑ በተፈተለ የሀር ክር ያሰረችው መስቀል ከደረቷ ላይ ይፈልቃል።

ከግራ ወደቀኝ ስዞር ዓይኔን በሙሽራው ላይ አሳረፍኩ። ቀይ ጥለት ያለው ነጭ ኩታውን ከግራ ወደቀኝ አጣፍቶ ከሙሽራዋ በስተግራ በኩል በኩራት ተኮፍሷል። ከኩታው ሥር ተመሳሳይ መልክ ያለው ኮትና ሱሪ ለብሷል። ጭንቅላቱን በአረንጓዴ፣ በቢጫና በቀይ ጥለት በተኸጎረጎረ ፎጣ ሁለት ዙር አስተካክሎ ጠምጥሞታል። ጠይም ፊቱ ጋብቻው በፈጠረለት ደስታ ወዝቷል። ፈገግ ባለ ቁጥር እንደበረዶ ነጥተው የሚታዩት ጥርሶቹ ልብን ያሸፍታሉ። ሰማያዊ ሸራ ጫማ ተጫምቷል። በሸራ ጫማው ጎንናጎን የሚታዩት ነጫጭ ክብ ጌጦች እግሮቹን ባንቀሳቀሰ ቁጥር ድምቀት ሰጥተውታል።

ሁለት አጫዋቾች እንደሙሽሮቹ ተውበው ተቀምጠዋል። ልዩልዩ ቀልዶችን እያወሩ ሙሽራዎቹን ያዝናናሉ። የሚያስፈልጋቸውን ምግብና መጠጥ በማቅረብም ይንከባከቧቸዋል። ከጫጉላ ውጪ ሌሎች ልጆች እንደእኔ ሙሽሮቹን ለማየት ዶቃና ከረሜላ ይዘው ተራቸውን ይጠባበቃሉ። እኔም በአጫዋቾቹ የተፈቀደልኝ ጊዜ በመጠናቀቁ ጫጉላ ቤቱን ለቅቄ ወደትልቁ ዳስ አመራሁ።

የዳሱ መግቢያ ለማስተናገድ ከላይ ከታች በሚሉ አስተናባሪዎችና በተጋባዥ እንግዶች ተጨናንቋል። የዘፋኞችና የተጋባገሮች ድምጽ ያስገመግማል። አንዱ ከሌላው ጋር የሚደማመጥ አይመስልም። በአጠቃላይ በዳሱ ውስጥ የሚታየው ትርዒት የደራ ገበያ ይመስላል። ትልቅ ወርቃማ የጠላ ማንቆርቆሪያ የያዘ አስተናጋጅ የቀዳልኝን ጠላ ተቀበልኩ። በአለላ በተዋበ መሶብ ከሌሎች ሰዎች ጋር እንድበላ ማዕድ ተሰራልኝ። የቀረበልኝን እየተመገብኩ የዳሱን የውስጥ ክፍል ማስተዋል ጀመርኩ።

ከዳሱ በአንደኛው ጥግ ከላይ ነጭ ጋቢ፣ ከውስጥ ደግሞ እጀጠባብ፣ ባተሁለት ሱሪ የለበሱና ባርኔጣ ያደረጉ ሰባት ሰዎች የደራ ጨዋታ ይዘዋል። ከመተጫጨት ጀምሮ እስከጋብቻው ቀን ድረስ በሽምግልና ስለተሳተፉ በልዩ እንክብካቤ የሚስተናገዱ ይመስላሉ። በዘፈኑ ውስጥ የምሰማቸውን ግጥሞች እያሰላሰልኩ የቀረበልኝን ተመግቤ "ይውለዱ፣ ይክበዱ" በማለት መርቄ ወጣሁ።

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. ጫጉላ ቤቱ የተሠራው ከምን ከምን እንደሆነ ግለጹ።

ለ. ለሙራሽዋ ውበት የሰጧት ጌጣጌጦች ምን ምን ናቸው?

ሐ. ሙሽራው ምን ዓይነት ልብስ ለብሷል?

መ. የአጫዋቾች ተግባር ምንድን ነው?

ሠ. ለጋብቻ ሽምግልና የሚላኩ ሰዎች ምን ዓይነት ሰዎች ይመስሏችኋል? ለምን?

ረ. ተመልካቹ/ቿ ግለሰብ (ተራኪው/ዋ) "ይውለዱ ይክበዱ" ያለው/ችው ለምንድን ነው?

ሰ. ሠርጉ የተከናወነበት አካባቢ ገጠር ነው ወይስ ከተማ? ምክንያቱን ግለጹ።

ሸ. በእናንተ አካባቢ ሙሽሮች ምን ምን ዓይነት ልብሶችን ይለብሳሉ?

## 2ኛ ቀን

## ቃላት

### ጥቅል ቃላትንና ሐረጋትን መዘርዘርና ለቃላት ዐውዳዊ ፍቺ መስጠት

### ተግባር 1

በምንባቡ መሠረት የቢጋር ሠንጠረዡን በተገቢ ቃላት አሟልታችሁ ጻፉ።







## ተግባር 2

ለሚከተሉት ቃላት በምንባቡ መሠረት ዐውዳዊ ፍቺ ስጡ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሀ. አስተናባሪ | ሐ. ማዕድ | ሠ. ተኾጎረጎረ | ሰ. አለላ |
| ለ. ጫጉላ | መ. ዳስ | ረ. ሽምግልና | ሸ. ጋሜ |

## መጻፍ

### 4ሀ. ድርሰት መጻፍ

### ድርሰት ለመጻፍ የሚያስችል የቢጋር ሠንጠረዥ ማዘጋጀት

## ተግባር 1

የሚከተሉትን ሀሳቦች መነሻ በማድረግ ሙሽራዋንና ሙሽራውን የሚገልጽ የቢጋር ሠንጠረዥ አዘጋጁ።

## ሙሽሮች

| ሙሽራው | ሙሽራዋ |
|---|---|
| • በኩራት ተኮፍሶ ተቀምጧል | • ሹርባ ተሠርታለች |
| • | • |
| • | • |
| • | • |
| • | • |
| • | • |

### ተግባር 2

ያዘጋጃችሁትን የቢጋር ሠንጠረዥ በመጠቀም ባለሦስት አንቀጽ ገላጭ/ሥዕላዊ/ ድርሰት ጻፉ።

## የአጻጻፍ ሥርዓት

## ቃላትን አዳምጦ መጻፍ

### ተግባር

መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን ቃላት አዳምጣችሁ በትክክል ጻፉ።

# 3ኛ ቀን

## አቀላጥፎ ማንበብ

## ሙሽሮቹ

## ቅድመንባብ

### ተግባር

"ሙሽሮቹ" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ከማንበባችሁ በፊት በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ።

ሀ. የምንባቡን ዋና ሀሳብ አስታውሳችሁ ግለጹ።

ለ. በገጠር አካባቢ ሙሽራዋ የምታጌጥባቸው ጌጦችና የምትለብሳቸው ልብሶች

ምን ምን ናቸው?

## ማንበብ

### ተግባር

“ሙሽሮቹ” በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ መምህራችሁ በሚያመቻቹላችሁ መሠረት የምንባቡን አንድ አንቀጽ ፊደል ሳትገድፉ በፍጥነት አንብቡ።

## ማዳመጥ

## የቆቲ ሥነሥርዓት



### ቅድመማዳመጥ

### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

### ተግባር

“የቆቲ ሥነሥርዓት” በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ከማዳመጣችሁ በፊት

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. “የቆቲ ሥነሥርዓት” በሚለው ርዕስ ሥር የቀረበው ሥዕል ስለምን የሚገልጽ ይመስላችኋል?

ለ. በእናንተ አካባቢ የቀለበት ሥነሥርዓት የሚከናወነው እንዴት ነው?

## የማዳመጥ ሂደት

### ተግባር

“የቆቲ ሥነሥርዓት” በሚል ርዕስ የቀረበ ምንባብ መምህራችሁ ያነቡላችኋል። በጥሞና አዳምጡና በማዳመጥ ሂደት ለሚጠይቋችሁ ጥያቄ ትክክለኛ መልስ መልሱ።

## አዳምጦ መረዳት

### ተግባር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. የቆቲ ሥነሥርዓት ማለት ምን ማለት ነው?

ለ. ዕድሜው ለጋብቻ የደረሰ ወንድ ትዳር መፈለጉን እንዴት ይገልጻል?

ሐ. ሽማግሌዎቹ የወይራና የውላጋ ዝንጣፊ የሚይዙት ለምን ይመስላችኋል?

መ. በቆቲ ሥነሥርዓት መሠረት አንዲት ልጃገረድ የታጨች መሆኗ በምን ይታወቃል?

ሠ. የሴቷ ወላጆች ሽማግሌዎቹን በመጀመሪያው ቀን መስተንግዶ ሳያቀርቡ የመለሷቸው ለምን ይመስላችኋል?

ረ. የእናንተ አካባቢ የቀለበት ሥነሥርዓት ከቆቲ ሥነሥርዓት በምን ይለያል?

# ሰዋስው

## የተጸውዖና የወል ስሞችን መለየት

### ተግባር 1

የሚከተሉትን ስሞች የወል ወይም የተጸውዖ በማለት በሁለት ምድብ ለይታችሁ በደብተራችሁ ጻፉ።

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ራሔል | ሰዓዳ | ዋቢሸበሌ | በግ | አባይ | ላም |
| ፍራፍሬ | ተማሪ | ምንተስኖት | ፖሊስ | ወንዝ | ድሬዳዋ |

ስሞች

| የተጸውዖ | የወል |
|---|---|
| | |
| | |
| | |
| | |
| | |
| | |

## ተግባር 2

በተግባር "1" ከተሰጡት ስሞች የተለዩ አምስት የተጸውዖ ስሞችንና አምስት የወል ስሞችን ጻፉና ለመምህራችሁ አሳዩ።

## ማንበብ

### ዐውዳመት

### ቅድመንባብ

### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

#### ተግባር

ምንባቡን ከማንበባችሁ በፊት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. በዐውዳመት ዕለት ትላላቅ ሰዎች ምን ምን ዓይነት ልብሶችን ይለብሳሉ?

ለ. በዐውዳመት ዕለት ምን ምን ነገሮች ይከናወናሉ?

### የማንበብ ሂደት

#### ተግባር

"ዐውዳመት" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ በለሆሳስ አንብቡ። በምታነቡበት ጊዜ ግልጽ ያልሆነላችሁ ቃል/ ሐረግ ሲያጋጥማችሁ ደጋግማችሁ በማንበብ ሀሳቡን ለመረዳት ሞክሩ።

### ዐውዳመት

የ18 ዓመት ታዳጊ ናት። የተወለደችው አዲስ አበባ ቢሆንም ከሰባት ዓመቷ ጀምሮ ያደገችው በአሜሪካ ነው። ፍቅርተ በኢትዮጵያዊነቷ ትኮራለች፤ ወገኖቿንም ትወዳለች። በተለያዩ ጊዜያት ከወላጆቿ ጋር ወደኢትዮጵያ መጥታለች። በርካታ ሰውሠራሽና ተፈጥሯዊ መስህቦችንም ጎብኝታለች። ዛሬ ደግሞ የጥምቀትን በዓል አከባበር ለመጎብኘት ጎንደር ከተማ ገብታለች።

ፍቅርተ የጥምቀት በዓል በድምቀት በሚከበርበት ቦታ ከወላጆቿ ጋር ተገኝታለች። በዚህ ዐውዳመት ላይ የታደሙት ሰዎች በተዋቡ ባህላዊ አልባሳት አሸብርቀዋል። ሕፃናት፣ ወጣቶችና አዋቂዎች በቡድን በቡድን እየሆኑ ይጨፍራሉ፤ ይዘፍናሉ። ፍቅርተ በምትመለከተው ነገር ሁሉ በጣም ተደንቃለች፤ ተደስታለች። በተለይ ባህላዊ ልብሶቹና ጌጣጌጦቹ በማንነቷ እንድትኮራ አድርገዋታል። በእያንዳንዱ የጭፈራ ቡድን በመዘዋወር የሰዎቹን የዐውዳመት አለባበስ በትኩረት ማጤን ጀመረች።

በቅድሚያ ያመራችው ሕፃናት ወደሚገኙበት አቅጣጫ ነው። ሴቶች ሕፃናት ነጭ

ጥበብ ቀሚስ ለብሰዋል። አንዳንዶቹ የተለያዩ ጌጣጌጦች ባሏቸው ጥልፍ ቀሚሶች ተውበዋል። ከቀሚሳቸው በላይ በተለያዩ ጥለቶች የተዋቡ ነጠላዎች ደርበዋል። ፀጉራቸውን በቀጭኑ ቁጥርጥር ተሠርተው በአምፖል ቅርፅ በነጭ የፀጉር ጌጥ አስይዘውታል። ከብር የተሠሩ የሚመስሉ ትንንሽ ነጫጭ ጉትቻዎች በጆሮዎቻቸው ላይ ይታያሉ። ወንዶች ልጆች ደግሞ የመብሩቅ እጀጠባብና ወንጨሬ (ጠባብ ሱሪ) ለብሰዋል። በቀይ፣ በቢጫና በአረንጓዴ ቀለማት የተሠራ ጥብጣብ በደረታቸው ላይ በሰያፍ አስረዋል። አልፎ አልፎ ሙሉ ኮትና ሱሪ የለበሱና ክራባት ያሰሩ ሕፃናት ይሯሯጣሉ። በተለያዩ ቀለማት የተሽለመለሙ አጫጭር በትሮችንም ይዘዋል። ፍቅርተ በልጆቹ አለባበስ በጣም በመደሰቷ ኢትዮጵያዊነቷን ይበልጥ ወደደችው።

ወደሌላኛው አቅጣጫ ስትዞር ደግሞ ልዩ የወጣቶች ጭፈራ ተመለከተች። አብዛኛዎቹ ወጣት ሴቶች እንደሕፃናት ሴቶች በጥልፍ የተዥጎረጎረ ነጭ ጥበብ ቀሚስ ከነጠላ ጋር ለብሰዋል። በነጭ ሻሽ ፀጉራቸውን አንድ ዙር አስረውታል። እጆቻቸውንና እግሮቻቸውን በእንሶስላ አስውበዋል። ከዶቃና ከብር የተሠሩ አልቦዎች በእግሮቻቸው አጥልቀዋል። ክንዶቻቸው ላይ አምባር ያሰሩ ጥቂት ወጣቶች ከጭፈራው መካከል እየተጋፉ ያጨበጭባሉ። ሌሎች ደግሞ ከብር የተሠሩ ጌጣጌጦችን እንደአምባር በክንዶቻቸው ላይ አስረዋል። በጣቶቻቸውም ላይ የተለያዩ ፈርጦች ያሏቸው ቀለበቶች ተሰድረዋል። ወጣቶቹ በኩል በተዋቡ ዓይኖቻቸው ሰረቅ አድርገው ሲመለከቷት ዓይን ለዓይን ተገጣጠሙ። ፍቅርተ ጠጋ በማለት ውበታቸውን አደነቀች፣ የሀገሯ ሴቶች ደምግባትም እጅግ ማረካት።

ፍቅርተ ከሩቅ የሰማችው የወጣት ወንዶች ጭፈራ ቀልቧን ስለሳበው ወደዚያው አመራች። አብዛኞቹ ወጣት ወንዶች በእሳት ተለብልቦ በነጭና በጥቁር ቀለም የተሽለመለመ ቀጭን ዘንግ ይዘዋል። ዘንጋቸውን ወደላይ አንስተው እየዘለሉና ሽብረክ እያሉ ይጨፍራሉ። አለባበሳቸውን ለመቃኘት ሞከረች። ጥቂቶቹ ባሕላዊ፣ በርካታዎቹ ደግሞ ዘመናዊ ልብስ ለብሰዋል።

በመጨረሻም አዋቂዎች በብዛት ወደሚገኙበት አካባቢ አመራች። አዋቂ ወንዶችም ሆኑ ሴቶች በባህል አልባሳትና ጌጣጌጦች አምረውና ደምቀው ተመለከተች፤ ሴቶቹ በቀጭኑ ሹርባ ተሰርተዋል። አንዳንዶቹ በሹርባቸው ረድፍ መካከል የብር ቀለበት ሰክተዋል። አልፎ አልፎ ከቀሚሳቸውና ከነጠላቸው ጋር ተመሳሳይ የሆነ ጥለት ባለው ነጭ ሻሽ ጸጉራቸውን በሙሉ አስረዋል። ሌሎቹ ደግሞ በአንድ ዙር ብቻ ሸብ አድርገዋል። የለበሱት ጥበብ ቀሚስና ነጠላ ልዩ ውበት አጎናጽፏቸዋል። በአንገታቸው ላይ ድሪና እርባን ወይም ጠልሰም፣ መስቀልና ማርዳ ሕብር ፈጥረው ያብረቀርቃሉ። በወገባቸው ላይ ሸብ ያደረጉት ትፍትፍ መቀነት ቀሚሳቸውን ሰብስቦ ላለባበሳቸው የተለየ ቅርጽ ሰጥቶታል። በክንዶቻቸው ላይ ከብር የተሰሩ አምባሮች አጥልቀዋል፤ በጣቶቻቸውም ላይ ቀለበቶች ደርድረዋል። ፍቅርተ በምታየው ሁሉ በደስታ ሲቃ ተዋጠች።

ፍቅርተ ብዙ ሳትቆይ ጉዞዋን ታቦታቱ ወደሚገኙበት አቅጣጫ አደረገች። ወደቦታው

ስትጠጋ አዛውንቶቹ በርጋታ እያዘገሙ ተመለከተች። አንዳንድ አዛውንቶች ነጭ እጀጠባብና ባተሁለት ለብሰዋል። ሌሎቹ ደግሞ ነጭ እጀጠባብ በወንጨሬ ለብሰው ከላይ በተለያዩ ጥለቶች ያሸበረቁ ነጠላና ኩታ አጣፍተዋል። አልፎ አልፎ በርኖስ ደርበዋል። ሌሎች አዛውንቶች ደግሞ ረዘም ያለ ዘንግ ይዘው ነጭ ጭራቸውን ከወዲያ ወዲህ በስልት ያወዛውዛሉ። አባት አርበኞች ጦርና ጋሻ ይዘው በረድፍ ይጓዛሉ። ቀሳውስቱ ካባቸውን ደርበውና ክባሳቸውን አሳምረው ይወርባሉ። ፍቅርተ በምታየው ነገር እጅግ ደስ አላት። በሀገሯ በምትቆይባቸው ጊዜያት ሌሎች አካባቢዎችን ለመጎብኘት ለራሷ ቃል ገባች።

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. ሕፃናት በደረታቸው ላይ በሰያፍ ቅርጽ በአረንጓዴ፣ በቢጫና በቀይ ቀለማት የተሠሩ ጥብጣቦች ያሠሩት ለምንድን ነው?

ለ. ፍቅርተ በአሜሪካ መኖር ከጀመረች ስንት ዓመት ሆኗታል?

ሐ. ፍቅርተ ኢትዮጵያዊነቷን እንድትወድ ያደረጓት ነገሮች ምን ምን ናቸው?

መ. አባት አርበኞች በበዓሉ ዕለት ጦርና ጋሻ መያዛቸው ምንን ለማመልከት ነው?

ሠ. ፍቅርተ በመጨረሻ ለራሷ ቃል የገባችው ምን ለማድረግ ነው?

ረ. ከምንባቡ ውስጥ እናንተን ይበልጥ ያስደሰታችሁ የዐውዳመት ውሎ የትኛው ነው? ለምን?

ሰ. ፍቅርተ ለራሷ ቃል በገባችው መሠረት የትኞቹን አካባቢዎች የምትጎበኝ ይመስላችኋል? ለምን?

## 5ኛ ቀን

## ቃላት

## ለቃላት ዐውዳዊ ፍቺ መስጠት

### ተግባር

ለተሠመረባቸው ቃላት ዐውዳዊ ፍቺ በጽሑፍ ግለጹ።

ሀ. ቀሳውስቱ በዐውዳመት ዕለት ካባ ይደርባሉ።

ለ. አዛውንቶቹ በጥምቀት ዕለት በርኖስ ደርበው ለብሰዋል።

ሐ. ባርኔጣ ስላደረጉ የፀሐይ ሙቀት አላቃጠላቸውም።

መ. ሽማግሌዎች ባተሁለት ሱሪ መልበስ ያዘወትራሉ።

ሠ. ዘውዲቱ ትፍትፍ መቀነት አሠራች።

ረ. በአንገቷ ላይ ያደረገችው ጠልሰም ከሩቅ ያብረቀርቃል።

ሰ. በጥምቀት በዓል ልጆች በአንገታቸው ላይ ማርዳ ማድረግ ደስ ይላቸዋል።

ሸ. የቀሳውስቱ ክባስ በጭንቅላታቸው ላይ ልዩ ውበት ፈጥሯል።

## መጻፍ

### ድርሰት መጻፍ

### የቢጋር ሠንጠረዥ ማዘጋጀት

#### ተግባር 1

የሚከተሉትን ሀሳቦች መነሻ በማድረግ ስለአንድ ዐውዳመት በዓል አከባበር የሚገልጽ የቢጋር ሠንጠረዥ አዘጋጁ።




#### ተግባር 2

ያዘጋጃችሁትን የቢጋር ሠንጠረዥ በመጠቀም በገላጭ የአጻጻፍ ስልት አንድ አንቀጽ ጻፉ።

### የአጻጻፍ ሥርዓት

### በአንቀጽ ውስጥ ቃላትንና ሐረጋትን አስተካክሎ መጻፍ

**ተግባር**

የተሠመረባቸውን ቃላትና ሐረጋት በማስተካከል አንቀጹን እንደገና ጻፉ።

ሰው በህወቱ ሲኖር የማያገኘውን መልከም ነገር ሁሉ የመቀበለው ከተወለደበት ሀገር ነው። ስለሆነም አፈላጊ ምክንየት በመጣ ገዜ ያለውን መልካም ነገር ሁሉ ህወቱን እንካ ሳይቀር ሳይመነታ ለሀገሩ ሲል ሊሰዋ ይገባዋል።

## 6ኛ ቀን

## አቀላጥፎ ማንበብ

**ዐውዳመት**

### ቅድመንባብ

**ተግባር**

“ዐውዳመት” የሚለውን ምንባብ ከማንበባችሁ በፊት ዋና ሀሳቡን አስታውሳችሁ በቃላችሁ ተናገሩ።

### ማንበብ

**ተግባር**

“ዐውዳመት” በሚል ርዕስ ከቀረበው ምንባብ አንድ አንቀጽ በአንድ ደቂቃ ውስጥ ድምጽ በማሰማት በትክክል አንብቡ።

## መናገር

### ሀሳብን በንግግር መግለጽ

**ተግባር**

የምታውቁትን ዐውዳመት በመምረጥ ስለአከባበሩ በቡድን በመወያየት በክፍል ውስጥ ንግግር አቅርቡ።

## ሰዋስው

### የዋህ ኃላፊ ግስን መለየት

### ተግባር 1

የሚከተለውን ሠንጠረዥ በምሳሌው መሠረት በደብተራችሁ አሟልታችሁ ጻፉ።

| የዋህ ሃላፊ ግስ | ጾታ | መደብ | ቁጥር |
|---|---|---|---|
| ወደቀ | ተባዕት | 3ኛ | ነጠላ |
| መጣች | | | |
| ሠራን | | | |
| በላሽ | | | |
| ደረስህ | | | |
| መጣሁ | | | |
| ሄዳችሁ | | | |

### ተግባር 2

በሚከተሉት የዋህ ኃላፊ ግሶች ዓረፍተነገር ሠርታችሁ አሳዩ።

ምሳሌ፡- ፍቅርተ አዲስ ልብስ ለበሰች።

ሀ. አጠቡ

ለ. ቆረጠ

ሐ. ፈቀደች

መ. አጠናን

ሠ. ጻፋችሁ

ረ. ዘለልኩ

## የቃላት ጥናት

### መነጠልና ማጣመር

#### ተግባር

የሚከተሉትን ውስብስብ ቃላትና ሐረጋት በመነጠልና በማጣመር አንብቡ።

| | ነጣጥሎ ማንበብ | አጣምሮ ማንበብ |
|---|---|---|
| ሀ | የ-ዕደ-ጥበብ | የዕደጥበብ |
| ለ | እንዲዋብ-ብ-ኣቸው | እንዲዋብባቸው |
| ሐ | ሠርግ-ኧኛ-ኦች-ኣችን | ሠርገኞቻችን |
| መ | ቱሪስት-ኦች-ም | ቱሪስቶችም |
| ሠ | ተፈጥሮ-አዊ-ነት | ተፈጥሯዊነት |
| ረ | ጥልፍ-ኦች-ኣቸው | ጥልፎቻቸው |
| ሰ | ዓለም-አቀፍ-አዊ | ዓለማቀፋዊ |
| ሸ | ኢትዮጵያ-ኣዊ-ነት-ኣችን-ን | ኢትዮጵያዊነታችንን |

## ማንበብ

## ባህላዊ ልብሶቻችን

### ቅድመንባብ

### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

#### ተግባር

“ባህላዊ ልብሶቻችን” በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ከማንበባችሁ በፊት በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያይታችሁ በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. “ባህላዊ ልብሶቻችን” ለምን ባህላዊ ተባለ?

ለ. ኢትዮጵያውያን ከሌሎች ሀገር ሰዎች ተለይተው የሚታወቁባቸውን ባህላዊ ጉዳዮች ግለጹ።

## የማንበብ ሂደት

### ተግባር

የሚከተለውን ምንባብ በለሆሳስ አንብቡ፤ ግልጽ ያልሆነላችሁ ሀሳብ ካለ በማንበብ ሂደት ስለምትረዱት ማንበባችሁን ቀጥሉ።

### ባህላዊ ልብሶቻችን

እኛ ኢትዮጵያውያን እንደየባህላችን በተለያየ ቅርፅና ቀለም ያሸበረቁ የባህል ልብሶች አሉን። እነዚህ የባህል ልብሶች የማንነታችን መግለጫዎች ናቸው፡ ውብ አለባበሳችን ኢትዮጵያውያንን ከሌሎች የዓለም ህዝቦች የተለየን ያደርገናል። ወደተለያዩ የውጪ ሀገራት ብንሄድ እንኳ በአሸብራቂ የባህል ልብሶቻችን አማካይነት ኢትዮጵያዊነታችንን እንገልጻለን።

እነዚህ የባህል ልብሶቻችን የራሳችንን የዕደጥበብ ፈጠራ ያሳያሉ። ለልብሶቹ የሚውለው ጥሬ እቃ የሚመረተውና ወደልብስነት የሚቀየረው በራሳችን ጥበበኞች ነው። እንደየባህሉና እንደየወቅቱ የሚለበሱ ልብሶች የሀገራችንን ሸማ ሠሪዎች ችሎታ አጉልተው ያሳያሉ። በልብሶቹ ላይ የሚታዩት ጥልፎች፣ ጌጣጌጦችና ጥበቦች ህብር ፈጥረው ቀልብ የሚስቡት በእኛው ጥበበኞች ተሠርተው ነው። አልባሳቱ በእኛው ተሠርተው ለእኛው ስለሚቀርቡ በራሳችን ዕደጥበብ እንድንተማመን ያደርጋሉ።

የባህል ልብሶቻችን ከጊዜ ወደጊዜ ዓለማቀፋዊ ተወዳጅነታቸው እየጨመረ መጥቷል። በየጊዜው ወደኢትዮጵያ የሚመጡት ቱሪስቶችም አለባበሳችንን እንደወደዱት በተለያዩ አጋጣሚዎች ይገልጻሉ። ባህላዊ ልብሶቻችንን ገዝተው የሚለብሱት የውጪ ዜጎች ቁጥርም ቀላል አይደለም። ምክንያቱም አብዛኛዎቹ ተፈጥሯዊ በሆነ መንገድ ከጥጥ ስለሚዘጋጁ ምቾትና ውበት አላቸው። በማንኛውም ጊዜ ሊለበሱ ይችላሉ። በሥራ ቦታ፣ በሠርግ፣ በበዓላት፣ በልዩ ልዩ አጋጣሚዎች ወዘተ እንዲለበሱ ሆነው ስለሚዘጋጁ ተመራጭነታቸው የጎላ ነው።

ስለሆነም ኢትዮጵያውያን በእነዚህ አስደሳች የባህል ልብሶቻችን ልንኮራ ይገባል። የባህል ልብሶቻችን የኢትዮጵያዊነት መለያ እንዲኖረን ያደርጋሉ። እንደየባህሉ ለወንዶችም ሆነ ለሴቶች የሚዘጋጁት የተለያዩ ልብሶች የየባህሉ አሻራ ይታይባቸዋል። ውበታቸውም ቢሆን ከውጪ ሀገራት ከሚመጡት ዘመናዊ ልብሶች የተሻለ ነው ማለት ይቻላል። በጥበበኞቹ ኢትዮጵያውያን ሸማ ሠሪዎች ስለሚዘጋጁ የሀገር ውስጥ ገቢን ከፍ ያደርጋሉ። የሀገራችንንም የጥበብ ፈጠራ ደረጃ ያሳድጋሉ። ሁላችንም ብንለብሳቸው ደግሞ አምረን ከመታየት በተጨማሪ በየጊዜው እንድናሻሽላቸው ዕድል ይፈጥራሉ። የማንነታችን መገለጫ የሆኑትን ባህላዊ ልብሶቻችንን ለቀጣዩ ትውልድ ማስተላለፍ የምንችለውም እኛው ራሳችን ስንለብሳቸው ነው። በባህላዊ ልብሶቻችን ተውበን መጪው ትውልድ እንዲዋብባቸው ልናስረክብ ይገባል። “ባለቤት ያቀለለውን አሞሌ፣ ባለዕዳ አይቀበለውም”

እንደሚባለው ባህላዊ ልብሶቻችንን ሌሎች እንዲቀበሏቸው እኛ ልናከብራቸውና ልንቀበላቸው ይገባል።

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር 1

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. ባህላዊ ልብሶች የምንላቸው ምን ምን ናቸው?

ለ. ባህላዊ ልብሶቻችን የኢትዮጵያዊነት መለያ በማድረግ ረገድ ያላቸው ፋይዳ ምንድን ነው?

ሐ. ባህላዊ ልብሶቻችን የራሳችንን የዕደጥበብ ፈጠራ የሚያበረታቱት እንዴት ነው?

መ. ባህላዊ ልብሶቻችን በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ተወዳጅነታቸው እንዲጨምር ምን መደረግ ያለበት ይመስላችኋል?

ሠ. ባህላዊ ልብሶቻችንን ለተተኪው ትውልድ የምናስተላልፈው ለምንድን ነው?

ረ. "ባለቤቱ ያቀለለውን አሞሌ ባለዕዳ አይቀበለውም" የሚለው አባባል ምንን ያመለክታል?

ሰ. የምንባቡ ዋና መልዕክት ምንድን ነው?

### ተግባር 2

ባህላዊና ዘመናዊ የሆኑ ልብሶችን ለይታችሁ በሚከተለው የቢጋር ሠንጠረዥ ውስጥ ጻፉ።



## 8ኛ ቀን

## ቃላት

### ቃላትን በተገቢ ዐውድ በመጠቀም ዓረፍተነገሮችን ማሟላት

#### ተግባር

የሚከተሉትን ቃላት በትክክለኛ ቦታቸው በመጻፍ ዓረፍተነገሮችን አሟሉ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሀ. ቀለም | ሐ. ባህላዊ | ሠ. ቀልብ | ሰ. ህብር |
| ለ. ውበት | መ. ሸማ | ረ. ቁጥር | ሸ. አሻራ |

ምሳሌ

ባህላዊ ልብሶቻችንን ገዝተው የሚለብሱት የውጪ ሀገር ዜጎች ቁጥር ቀላል አይደለም።

ሀ. ባህላዊ ልብሶች የሀገራችንን ——— ሠሪዎች ችሎታ አጉልተው ያሳያሉ።

ለ. ለወንዶችም ሆነ ለሴቶች የሚዘጋጁት ባህላዊ ልብሶች የየባህሉ ——— አርፎባቸዋል።

ሐ. ብሔር ብሔረሰቦች የተለያየ ——— ያላቸው የባህል ልብሶች አሏቸው።

መ. ባህላዊ ልብሶቻችን ከተፈጥሮ ጥጥ ስለሚዘጋጁ ምቾትና ——— አላቸው።

ሠ. ባህላዊ ልብሶቻችን ከጥልፎችና ከጥበቦች ጋር ——— ፈጥረው ——— ይስባሉ።

ረ. በዐውዳመት ጊዜ ብዙዎቻችን ——— ልብስ መልበስ እንወዳለን።

## መጻፍ

### ድርሰት መጻፍ

### በአስረጂ የአጻጻፍ ስልት ድርሰት መጻፍ

#### ተግባር

በአካባቢያችሁ ስለሚሠራ አንድ ባህላዊ ልብስ ከጓደኞቻችሁ ጋር በመወያየት ከምን እንደሚሠራ፣ እንዴት እንደሚሠራና ለምን እንደሚያገለግል በመዘርዘር ባለሦስት አንቀጽ አስረጂ ድርሰት ጻፉ።

## የአጻጻፍ ሥርዓት

### በዓረፍተነገር ውስጥ ሥርዓተነጥቦችን መጠቀም

### ተግባር 1

ሥርዓተነጥቦችን በተገቢ ቦታ በማስገባት ዓረፍተነገሮችን እንደገና ጻፉ።

ሀ. ባህላዊ ልብሶች ከሚባሉት መካከል ጋቢ ኩታ በርኖስ ጥበብ ካባ ሊጠቀሱ ይችላሉ

ለ. ባህላዊ ልብሶቻችን ዓለማቀፋዊ ተወዳጅነት አግኝተዋል ተፈላጊነታቸውም ጨምሯል

ሐ. ታዳሚዎች ከመቀመጫቸው ተነስተዋል ጭብጨባው ደምቋል ሙሽሮቹ ወደዳሱ ሳይገቡ አልቀረም

መ. ባህላዊ ልብሶች መቼ መቼ ይለበሳሉ

ሠ. ባህላዊ ልብሶች ከጥጥ ከበግ ፀጉር ከተልባ እግርና ከቆዳ ይሠራሉ

ረ. የምታደርጉትን አስተውሉ በችኮላ የተሠራ ሥራ ሁሉ ስህተት አያጣውምና

ሰ. ለምን አረፈድክ

### ተግባር 2

የሚከተሉትን ሥርዓተነጥቦች በመጠቀም ዓረፍተነገር ሥሩ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፣ | ፤ | ? | ። |

## 9ኛ ቀን

## አቀላጥፎ ማንበብ

**ባህላዊ ልብሶቻችን**

### ቅድመንባብ

### ተግባር

"ባህላዊ ልብሶቻችን" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ አቀላጥፋችሁ ለማንበብ የሚከተሉትን መመሪያዎች ተግባራዊ አድርጉ።

- ምንባቡን በጣት እየጠቆሙ አለማንበብ
- የፊደል ግድፈትን ማስወገድ

- ሐረጋትን፣ ቃላትንና ፊደላትን በመደጋገም አለማንበብ
- ነጠላ ሠረዝ ካለበት ላይ ትንሽ የቆምታ ጊዜ መውሰድ
- አራት ነጥብ ካለበት ላይ ረዘም ያለ የቆምታ ጊዜ መውሰድ
- ምንባቡን ከቀደመ ዕውቀት ጋር እያገናዘቡ ማንበብና ቀጥሎ ከሚመጣው ሀሳብ ጋር ግንኙነት መፍጠር
- መጠይቃዊ ዓረፍተነገር ላይ በጥያቄ መንፈስ ድምጽን ጎላ አድርጎ ማንበብ
- እንግዳ ቃላት ሲያጋጥሙ ከዐውዳቸው ፍቻቸውን ለመረዳት መሞከር

### ማንበብ

#### ተግባር

"ባህላዊ" ልብሶቻችን የሚለውን ምንባብ ከሁለተኛው አንቀጽ ጀምሮ ተራበተራ አንድ አንድ አንቀጽ ድምጽ በማሰማት በአንድ ደቂቃ ውስጥ በፍጥነት አንብቡ።

## መናገር

### ሀሳብን በንግግር መግለጽ

#### ተግባር

"ባህላዊ ልብሶቻችን ተወዳጅነታቸውና ዓለምአቀፋዊ ተፈላጊነታቸው እንዲጨምር ምን ማድረግ አለብን?" በሚለው ጥያቄ ላይ ተወያይታችሁ የደረሳችሁበትን መደምደሚያ ሀሳብ ለጋራ ውይይት አቅርቡ። ለመነሻ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ተጠቀሙ።

- ባህላዊ ልብስ ሠሪዎች ምን ማድረግ አለባቸው?
- እያንዳንዳችን ምን መሥራት አለብን?
- ነጋዴዎች ምን ማድረግ አለባቸው?
- የባህልና ቱሪዝም ማዕከላት ምን ማድረግ አለባቸው?
- የባህላዊ ልብስ ጥሬዕቃ አቅራቢዎች ምን ማድረግ አለባቸው ?
- ማህበረሰቡስ ምን ምን ማድረግ ይጠበቅበታል?

## ሰዋስው

### የወል ስም፣ የተጸውዖ ስምና የዋህ ኃላፊ ግስን መለየት

#### ተግባር 1

የሚከተሉትን ቃላት የወል ወይም የተጸውዖ በማለት ለይታችሁ ጻፉ።

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| እህል | ቤት | ጊቤ | ደብረብርሃን | ሱዳን | ሻላ | ሠራዊት | ልብስ |




## ተግባር 2

በምሳሌው መሠረት ከዚህ በታች የቀረቡትን የዋህ ኃላፊ ግሶች ከቁጥር፣ ከፆታና ከመደብ አንጻር ጻፉ።

ምሳሌ፡- ሄደ

ሄድኩ → ሄድን → ሄድክ → ሄድሽ → ሄዳችሁ → ሄደች → ሄዱ

ሀ. ሰበረ

ለ. ፈራ

ሐ. ጠራ

መ. ቀዳ

ሠ. ለቀመ

ረ. ገደለ



# ምዕራፍ 2

# ታዋቂ አትሌቶች

## የሠርግ አለባበስ

1ኛ ሳምንት 1ኛ ቀን

## የቃላት ጥናት

### መነጠልና ማጣመር

### ተግባር 1

የሚከተሉትን ቃላት በመነጠልና በማጣመር አንብቡ።

| ነጣጥሎ ማንበብ | | አጣምሮ ማንበብ |
|---|---|---|
| ሀ. | ሱ-ር-ኽ-ስ | ሱርኽስ |
| ለ. | ሜ-ክ-ሲ-ኮ | ሜክሲኮ |
| ሐ. | አ-ት-ሌ-ቲ- ክ - ስ | አትሌቲክስ |
| መ. | ኦ-ሎ-ም-ፒ-ክ | ኦሎምፒክ |
| ሠ. | ኒ-ሻ-ን | ኒሻን |
| ረ. | ሜ-ዳ-ል-ያ | ሜዳልያ |

### ተግባር 2

የሚከተሉትን ሐረጋት በትክክል አንብቡ።

ሀ. የሚለማመደውም

ለ. ከሚታወቅባቸውም

ሐ. እንደሚመለከተው

መ. በአለማቀፍ

ሠ. ከተወዳዳሪዎቹ

ረ. ወዳረፉበት

# ማንበብ

## ማርሸ ቀያሪው ...

### ቅድመንባብ

### ለአዳዲስ ቃላትና ሐረጋት ፍቺ መስጠት

**ተግባር**

ለሚከተሉት ቃላትና ሐረጋት በቃላችሁ ፍቺ ስጡ።

ሀ. ተሞክሮ

ለ. ስመጥር

ሐ. አርአያ

መ. የህይወት ታሪክ

### የማንበብ ሂደት

**ተግባር**

"ማርሽ ቀያሪው..." በሚል ርዕስ የቀረበውን ተራኪ ምንባብ የድርጊቶችን ቅደምተከተል በማስተዋል ድምጽ ሳታሰሙ አንብቡ።

## ማርሸ ቀያሪው ...

ኢትዮጵያ በርካታ ስመጥር አትሌቶች አሏት። ከእነዚህ መካከል አንዱ ምሩፅ ይፍጠር ነው። ምሩፅ በዛሬው የትግራይ ክልል፣ ሱርኸስ በምትባል ቦታ በ1937 ዓ.ም. ተወለደ። 17 ዓመት ሲሞላው ከቤተሰቡ ተለይቶ ወደአሥመራ ሄደና በዚያው መኖር ጀመረ። በሳምንት 20 ብር እየተከፈለው እህል በመመዘን ሥራ ላይ ተሠማራ።



ምሩፅ የሩጫ ፍቅር ስለነበረው ከሥራው ጎንለጎን በግሉ ይለማመድ ነበር። የሚለማመደውም ርቀት ከ5ሺህ እስከ10ሺህ ሜትር ነበር። በልምምዱ ወቅት አበበ ቢቂላ ሮም ላይ በማራቶን ሩጫ አሸናፊ ሆኖ የወርቅ ሜዳልያ ማግኘቱን ሲሰማ የሩጫ ስፖርት ትልቅ ዋጋ እንዳለው ተገነዘበ። ልምምዱን ከቀድሞው በበለጠ አጠናክሮ ቀጠለበት።

በዚህ ሁኔታ ላይ እንዳለ ሜክሲኮ ላይ ለሚደረገው የሩጫ ውድድር ከሚሰለጥኑ ሯጮች ጋር የመገናኘት ዕድል ገጠመው። ወጣቱ ምሩፅ ስፖርተኞቹ ወዳረፉበት ሆቴል ሄደና ከአሰልጣኙ ጋር ተዋወቀ። ከተወዳዳሪዎቹ ጋር አብሮ ለመለማመድ ባቀረበው ጥያቄ መሠረትም የአሰልጣኙን ፈቃድ አገኘ። ይሁንእንጂ ተመራጭ አትሌት ሆኖ ወደሜክሲኮ ለመሄድ አልቻለም። ይሁንና ቁመናውንና ወጣትነቱን ያየው የወቅቱ አሰልጣኝ የአየር ኃይል የስፖርት ክለብ አባል እንዲሆን መረጠው።

ጥር 1 ቀን 1961 ዓ.ም. የአየር ኃይል ሠራዊት አባል ሆኖ ተቀጠረ። ከተቀጠረበት ጊዜ አንስቶ የሩጫ ልምምዱን አጠናክሮ ቀጠለ። በሀገርአቀፍና በዓለምአቀፍ ውድድሮችም መሳተፍ ጀመረ። በአጭር ጊዜ ውስጥም ታዋቂ እየሆነ ሄደ። ከታወቀባቸው የሩጫ መወዳደሪያ ርቀቶች የ10 ሺህና የ5ሺህ ሜትር ዋነኞቹ ነበሩ። በእነዚህ ርቀቶች በ1970 ዓ.ም. በሞስኮ ኦሎምፒክ በሁለቱም ርቀቶች አሸናፊ ሆኖ ሁለት የወርቅ ሜዳልያ አጠለቀ። ይህም የኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን የአፍሪካም ቀደምት አትሌት አድርጎታል። በወቅቱ የበርካታ ሀገር ጋዜጠኞች ይህን ታላቅ ድል በስፋት ስለዘገቡት በዓለምአቀፍ ደረጃ ዝነኛ ሆነ።

ምሩፅ በሞስኮ በሁለቱም ርቀቶች ባሳየው የተለየ የአጨራረስ ብቃት የአፍሪካና የዓለም ኮከብ አትሌት ተብሎ የወርቅ ጫማ ተሸለመ። በተጨማሪ “ማርሽ ቀያሪው” የሚል መጠሪያ ወይም ቅፅል ስም ተሰጠው። ወደሀገሩ እንደተመለሰ የኢትዮጵያ መንግስት ከፍተኛ የክብር ኒሻን ሸልሞታል። በመስሪያቤቱም የሻምበልነት ማዕረግ አግኝቷል። የማርሽ ቀያሪው ምሩፅ፣ የሩጫ ስልት ለበርካታ ተተኪ አትሌቶች አርዓያ ሆኗል። ለምሳሌ ኃይሌ ገብረሥላሴ ምሩፅን እንደአርዓያ እንደሚመለከተው በተለያዩ አጋጣሚዎች ገልጿል። ምሩፅ ውድድር ካቆመ በኋላ በኢትዮጵያ ደረጃ የአትሌቲክስ አሰልጣኝ በመሆን ልምዱን ለወጣት አትሌቶች በማካፈል የበኩሉን አስተዋጽኦ አበርክቷል።

(ከሳቴ ለገሰ። 1999። *የትግራይ ስፖርት እንቅስቃሴ ከየት ወዴት።* ፈንታሁን እንግዳ፣ 2000። *ታሪካዊ መዝገበ ሰብዕ ከጥንት እስከዛሬ።* ለውጥ ተደርጎበት የተወሰደ።)

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር 1

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. ምሩፅ ይፍጠር ለሀገሩ ጥልቅ ፍቅር ያለው መሆኑን እንዴት አስመሰከረ?

ለ. ምሩፅ ይፍጠር "ማርሽ ቀያሪው" የተባለው ለምን ይመስላችኋል?

ሐ. የምሩፅ ይፍጠር የሩጫ ስልት ለሌሎች አትሌቶች ጥሩ ተሞክሮ የሆነው እንዴት ነው?

መ. ምሩፅ ይፍጠር ለሩጫ ትልቅ ዋጋ የሰጠው በምን ምክንያት ይመስላችኋል?

ሠ. ከምሩፅ ይፍጠር ታሪክ ምን ተማራችሁ?

## ተግባር 2

በምንባቡ መሠረት ለሚከተሉት ዓመተምህረቶች የተከናወኑ ተግባራትን ጻፉ።

| ዓመተምሕረት | የተከናወኑ ተግባራት |
|---|---|
| 1937 | |
| 1954 | |
| 1961 | |
| 1970 | |

## 2ኛ ቀን

## ቃላት

### ለቃላት ዐውዳዊ ፍቺ መስጠት

## ተግባር

ለሚከተሉት ቃላት ዓረፍተነገር በመሥራት ዐውዳዊ ፍቺ ስጡ።

ምሳሌ፡- የትምህርትቤታችን የእግር ኳስ ቡድን ልምምዱን ጀመረ።

በዚህ ዓረፍተነገር የተሠመረበት ቃል (ቡድን) ዐውዳዊ ፍቺው የተጫዋቾች ስብስብ የሚል ነው።

ሀ. ሥራ

ለ. ዝና

ሐ. ታሪክ

መ. ማዘውተር

ሠ. ማክበር

ረ. ዕድል

ሰ. መታወቅ

## መጻፍ

### ድርሰት መጻፍ

### በቢ.ጋር ሠንጠረዥ ውስጥ ተገቢ መረጃዎችን መጻፍ

#### ተግባር 1

"ማርሽ ቀያሪው..." በሚል ርዕስ በቀረበው ምንባብ መሠረት የቢ.ጋር ሠንጠረዡን በተገቢ መረጃዎች አሟሉ።




#### ተግባር 2

ስመጥር ከሆኑ አትሌቶች መካከል አንዱን/አንዷን መርጣችሁ የህይወት ታሪካቸውን ከሰው በመጠየቅ ወይም መጽሐፍ በማንበብ ጽፋችሁ በክፍል ውስጥ አንብቡ።

### የአጻጻፍ ሥርዓት

### ቃላትን አዳምጦ መጻፍ

#### ተግባር

መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን ቃላት በማዳመጥ በደብተራችሁ በትክክል ጻፉ።

# 3ኛ ቀን

## አቀላጥፎ ማንበብ

### ማርሽ ቀያሪው ...

**ቅድመንባብ**

**ተግባር**

"ማርሽ ቀያሪው ..." ከሚለው ምንባብ ውስጥ የምታስታውሷቸውን አምስት ዋናዋና ሀሳቦች ተናገሩ።

**ማንበብ**

**ተግባር**

"ማርሽ ቀያሪው..." በሚል ርዕስ ከቀረበው ምንባብ አራተኛው አንቀጽ መምህራችሁ ባሳዩአችሁ የአነባበብ ስልት መሠረት በ1 ደቂቃ ውስጥ ለጓደኞቻችሁ ድምፅ በማሰማት አቀላጥፋችሁ አንብቡ።

## ማዳመጥ

### ቀድሜ የበራች ኮከብ

**ቅድመማዳመጥ**

**የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ፣ የምንባብን ሀሳብ ከርዕስ መገመት**

**ተግባር**

"ቀድሜ የበራች ኮከብ" በሚል ርዕስ የቀረበ ምንባብ ከማዳመጣችሁ በፊት ቀጥለው የቀረቡትን ጥያቄዎች የቀደመ ዕውቀታችሁን በመጠቀም በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. ከምንባቡ ርዕስ ምን ትረዳላችሁ?

ለ. ከምታውቋቸው ሴት አትሌቶች መካከል ምንባቡ ስለማን የሚገልጽ ይመስላችኋል?

**የማዳመጥ ሂደት**

**ተግባር**

"ቀድሜ የበራች ኮከብ" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ በትክክል አዳምጡና በማዳመጥ ሂደት ለሚቀርበው ጥያቄ ምላሽ ስጡ።

### አዳምጦ መረዳት

#### ተግባር 1

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በቃላችሁ በትክክል መልሱ።

ሀ. ደራርቱ ቱሉ ለመጀመሪያ ጊዜ የወርቅ ሜዳልያ ያገኘችው የት ነው?

ለ. ደራርቱ ቱሉ "ቀድማ የበራች ኮከብ" የተባለችው ለምንድን ነው?

ሐ. ደራርቱ ቱሉ በልጅነቷ ቤተሰቦቿን ምን ምን በመሥራት ትረዳ ነበር?

መ. የደራርቱ የጀግንነት ምስጢር የተገለፀው መቼ ነው?

#### ተግባር 2

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. ከደራርቱ ቱሉ የህይወት ታሪክ የተማራችሁትን ቁምነገር በሦስት አንቀጽ ጻፉ።

ለ. እንደደራርቱ ቱሉ ከትምህርትቤት ውጪ ቤተሰቦቻችሁን ምን ምን በመሥራት እንደምታግዙ በዝርዝር ጻፉ።

## ሰዋስው

### ባለቤትና ግሣዊ ሐረግ መለየት

#### ተግባር 1

ከሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ባለቤትና ግሣዊ ሐረግ ለይታችሁ ጻፉ።

ምሳሌ፡-

1. "ደራርቱ ውድድሩን አሸነፈች።" በዚህ ዓረፍተነገር ባለቤቱ "ደራርቱ" የሚለው ቃል ሲሆን ግሣዊ ሐረጉ፣ "ውድድሩን አሸነፈች" የሚለው ነው።
2. "ልጁ ተኛ።" በዚህ ዓረፍተነገር ባለቤቱ "ልጁ" የሚለው ቃል ሲሆን ግሣዊ ሐረጉ፣ "ተኛ" የሚለው ነው።

ሀ. ዓለሙ ሥዕል ሳለ።

ለ. ዘይነባ በጧት ተነሳች።

ሐ. ውሻው ጮኸ።

መ. ፅጌረዳዋ ፈካች።

ሠ. ተማሪዎቹ ክፍላቸውን አፀዱ።

ረ. ሶስና ቁርሷን በላች።

#### ተግባር 2

ባለቤትና ግሳዊ ሐረግ ያላቸው ሦስት ዓርፍተነገሮች ጻፉ።

## ማንበብ

### ጽናት ያላት አትሌት

**ቅድመንባብ**

**ከርዕስና ከሥዕል የምንባብ ሀሳብ መገመት**

**ተግባር**

የሚከተሉትን የቅድመንባብ ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. ከምንባቡ ርዕስ ምን ትረዳላችሁ?

ለ. በርዕሱና በሥዕሉ መካከል ያለው ዝምድና ምን ይመስላችኋል?

**የማንበብ ሂደት**

**ተግባር**

"ጽናት ያላት አትሌት" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ለአዳዲስ ቃላት ከዐውዳቸው ፍቺ እየሰጣችሁ በለሆሳስ አንብቡ።

### ጽናት ያላት አትሌት



ሐምሌ 12 ቀን 1975 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ከተማ ተወለደች። ለወላጆቿ አራተኛ ልጅ ናት። ሦስት እህቶችና ሁለት ወንድሞች አሏት። አባቷ አነስተኛ የወር ደመወዝ ነበራቸው። በዚህ የተነሳ በሕፃንነት እድሜዋ ከትምህርቷ ጎንለጎን የቤተሰቦቿን ችግር ለማቃለል ብዙ ጥረት አድርጋለች። በዕድሜም ሆነ በአካል እያደገች ስትመጣ በግንባታ ሥራ ውስጥ ተቀጥራ ሠርታለች። ጀሪካን ተሸክማ ውኃ በመቅዳት፣ ወደጫካ እየሄደች ለምግብ ማብሰያ የሚሆን ቅጠል በመልቀም ቤተሰቦቿን ትረዳ ነበር። በአጠቃላይ ኑሮን ለማሸነፍ እጅግ ፈታኝ የሆነ ህይወት አሳልፋለች። ይህች ብርቱ ወጣት አትሌት መሠረት ደፋር ትባላለች።

በዚህ ፈታኝ ሁኔታ ውስጥ ያደገችው መሠረት ወደሩጫው ዓለም የገባችው በልጅነት ዕድሜዋ ነበር። የአትሌቲክስ ተሰጥዖዋ ጎልቶ የወጣው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን በመከታተል ላይ እያለች ነው። በወቅቱ በትምህርትቤቱ ውስጥ እንዲሁም በትምህርት ሚኒስቴር በኩል በሚደረጉ የሩጫ ውድድሮች በ800 ሜትር፣ በ1500 ሜትርና በ3ሺህ ሜትር ርቀቶች ተካፍላ በተደጋጋሚ አሸናፊ ሆነች። በሩጫ ያላትንም ተስፋ ተገነዘበች።

ተስፋዋንና ምኞቷን ለማሳካት ከቀድሞው በበለጠ ልምምዷን ማጠናከር ጀመረች። በዚህም ጊዜ ቢሆን ልዩልዩ ችግሮች ያጋጥሟት ነበር። ችግሮቹን ግን በጽናት ተቋቁማ በልምምድ ላይ እንዳለች ለስኬቷ በር ከፋች የሆነ አጋጣሚ ተፈጠረ። በአዲስ አበባ ስታዲዮም ለአበበ ቢቂላ መታሰቢያ በተዘጋጀ ውድድር ላይ በ5 ሺህ ሜትር ተሳትፋ አሸናፊ ሆነች። ይህንን ብቃቷን ያየው የባንኮች አትሌቲክስ ቡድን ዋና አሰልጣኝ የቡድኑ አባል አደረጋት። የባንክ ቡድኑን ከተቀላቀለች በኋላ በእቅድ ላይ የተመሠረተ ልምምዷን በትጋት አከናወነች። ልምምዷን ከልብ በመነጨ ፍላጎት መሥራቷና ጽናቷ ደግሞ በሀገር ውስጥ ውድድሮች በተከታታይ የአሸናፊነትን ክብር ለመቀዳጀት አበቃት።

ካላት ብቃት አንፃር ብዙም ሳትቆይ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ የአትሌቲክስ ቡድን ተመረጠች። ገና በጧቱ ሀገሯን በሩጫ ለማስጠራት የነበራት ምኞትና ቁርጠኝነት በመሳካቱ ተደሰተች። የመጀመሪያዋ የሆነውን ዓለምአቀፍ ውድድር ለማድረግ ሐምሌ 1991 ዓ.ም. ወደፖላንድ አመራች። በ3 ሺህ ሜትር ርቀት ተወዳድራ ሁለተኛ ወጣች። ይህም በዓለምአቀፍ ውድድር የመጀመሪያው አኩሪ ውጤቷ ሆኖ ተመዘገበላት። ከዚህ በኋላ ሀገሯን በመወከል በበርካታ ውድድሮች ላይ ተሳትፋለች። አያሌ አኩሪ ድሎችንም አስመስዝግባለች።

መሠረት በተሳተፈችባቸው በርካታ ዓለምአቀፍ ውድድሮች ማሸነፍ ብቻ ሳይሆን አዳዲስ የዓለም ምርጥ ሰዓቶችንም (ሪኮርድ) አስመዝግባለች። ለምሳሌ በአሜሪካ ኒውዮርክ ከተማ ግንቦት 26 ቀን 1998 ዓ.ም. በተደረገው የ5 ሺህ ሜትር ውድድር ቀደም ሲል የተመዘገበውን ሰዓት አሻሻለች፤ በዓለም የርቀቱ ሪኮርድ ባለቤትም ለመሆን በቃች። ከአንድ ዓመት በኋላም ጃፓን ላይ በተደረገ ውድድር ቀደም ሲል የያዘችውን ሪኮርድ አሻሽላለች። ጥር 26 ቀን 1999 ዓ.ም. በጀርመን ስቱትጋርት

በ3 ሺህ ሜትር የቤት ውስጥ ውድድር ተሳትፋ አዲስ ሪከርድ አስመዝግባለች። ግንቦት 12 ቀን 1999 ዓ.ም. በአሜሪካ ካሊፎርኒያ የሁለት ማይል ሩጫ ውድድር ተካፍላ ፈጥና በመግባት ሪከርድ አስመዝግባለች። ቤልጅየም ላይ ይህንኑ ሰዓት በማሻሻሏ ከዓለምአቀፍ የአትሌቲክስ ፌዴሬሽን "የዓመቱ ምርጥ አትሌት" የሚል ማዕረግ አግኝታለች። መሠረት፣ አሁንም ቢሆን የሀገሯ ሰንደቅዓላማ ከፍ ብሎ እንዲውለበለብ በማድረግ ላይ የምትገኝ ብርቅዬ አትሌት ናት።

(ቅዱስ ሀብት በላቸው። 2014። መጠነኛ ለውጥ ተደርጎበት የተወሰደ።)

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ

ሀ. መሠረት ኑሮን ለማሸነፍ ምን ምን ተግባራትን አከናውናለች?

ለ. የመሠረት ተሰጥዖ ጎልቶ የወጣው መቼ ነው?

ሐ. መሠረት የመጀመሪያ ዓለምአቀፍ ውድድሯን ለማድረግ የሄደችው የት ነበር?

መ. መሠረት ፈጣን ሰዓት (ሪከርድ) ያስመዘገበችው የት የት ነበር?

ሠ. መሠረት የሀገሯ ሰንደቅዓላማ ከፍ ብሎ እንዲውለበለብ ያደረገችው እንዴት ነው?

ረ. ከመሠረት ምን ተማራችሁ?

ሰ. በትምህርትቤቶችና በአትሌቲክስ መካከል ምን ዓይነት ዝምድና ያለ ይመስላችኋል?

## 5ኛ ቀን

## ቃላት

## ለቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ መስጠት

### ተግባር 1

በምንባቡ መሠረት በ "ሀ" ረድፍ ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳያቸውን ከ "ለ" ረድፍ በመምረጥ አዛምዱ።

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ሙያ | ሀ. ምኞት |
| 2. እቅድ | ለ. የሥራ ዘርፍ |
| 3. ተስፋ | ሐ. የዓላማ ጽናት |
| 4. ብቃት | መ. ስልጠና |
| 5. ልምምድ | ሠ. መርሐግብር |
| 6. ቁርጠኝነት | ረ. እንዝላልነት |
| | ሰ. ችሎታ |

## ተግባር 2

በምንባቡ መሠረት በ "ሀ" ረድፍ ለቀረቡት ቃላት ተቃራኒያቸውን ከ "ለ" ረድፍ በመምረጥ አዛምዱ።

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. መሀል | ሀ. ተቃውሞ |
| 2. ድጋፍ | ለ. አልፎ አልፎ |
| 3. ፍቅር | ሐ. ጥላቻ |
| 4. ዘወትር | መ. የማይታወቅ |
| 5. ማግስት | ሠ. ዋዜማ |
| 6. ስመጥር | ረ. ሁልጊዜ |
| | ሰ. ዳር |

## መጻፍ

### ድርሰት መጻፍ

### በማወዳደርና በማነጻጸር ስልት ድርሰት መጻፍ።

## ተግባር

የሚከተለውን ሠንጠረዥ መሠረት በማድረግ «ሁለቱ አትሌቶች' በሚል ርዕስ በማወዳደርና በማነጻጸር ስልት ባለሦስት አንቀጽ ድርሰት ጻፉና ለመምህራችሁ አሳዩ።

ምሩፅ ይፍጠርና መሠረት ደፋር

| ተመሳሳይነት |
|---|
| ሁለቱም ኢትዮጵያውያን ናቸው። |
| ሁለቱም ታዋቂ ናቸው። |
| ሁለቱም ከችግር ተነስተው ለውጤት የበቁ አትሌቶች ናቸው። |
| ሁለቱም አርዓያ ሊሆኑ ችለዋል። |
| ሁለቱም የሀገራቸው ሰንደቅ ዓላማ ከፍ ብሎ እንዲውለበለብ አድርገዋል። |

| ልዩነት | |
|---|---|
| ወንድ አትሌት | ሴት አትሌት |
| 1937 ተወለደ። | በ1975 ተወለደች |
| ትግራይ አካባቢ ሱር'ኸስ ተወለደ | በአዲስ አበባ ተወለደች። |
| በግሉ ሩጫ ጀመረ። | በትምህርትቤት ሩጫ ጀመረች |
| በእህል መመዘን ሥራ ተሠማርቶ ነበር። | በህንፃ ሥራ ላይ ተሠማርታ ነበር። |
| በሞስኮ ሮጧል። | በፖላንድ ሮጣለች። |

## የአጻጻፍ ሥርዓት

### ውስብስብ ፊደላትን በትክክል መጻፍ

### ተግባር 1

የሚከተሉትን ቃላት የተሠመረባቸውን ፊደላት በውስብስብ ፊደላት በመተካት ጻፏቸው።

ምሳሌ፡- ቡዋገተ ⟶ ቧገተ

ሀ. ነገርኩዋቸው  ሐ. ኑሮዋቸው  ሠ. መጉዋጎጥ

ለ. መረጣችሁዋት  መ. ሁዋለኞች

### ተግባር 2

መምህራችሁ የሚጽፉላችሁን ቃላት በተገቢ ፊደላት አስተካክላችሁ ጻፉ።

# አቀላጥፎ ማንበብ

## ጽናት ያላት አትሌት

### ቅድመንባብ

#### ተግባር

"ጽናት ያላት አትሌት" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ዋና ሀሳብ አስታውሳችሁ ተናገሩ።

### ማንበብ

#### ተግባር

በ2ኛው ሳምንት፣ በ4ኛው ቀን "ጽናት ያላት አትሌት" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት በፍጥነት አቀላጥፋችሁ አንብቡ

# መናገር

### ውይይት ማካሄድ

#### ተግባር

በአካባቢያችሁ የምታውቋቸውን ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን በመጥቀስ በተለይ በሴቶች ላይ የሚያደርሱትን ጉዳት በቡድን በመወያየት የደረሳችሁበትን የማጠቃለያ ሀሣብ በተወካዮቻችሁ አማካይነት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።

# ሰዋስው

### ባለቤትና ግሣዊ ሐረግ መለየት

#### ተግባር 1

የሚከተሉትን ዓረፍተነገሮች ባለቤትና ግሣዊ ሐረግ ለይታችሁ ጻፉ።

ሀ. መሠረት አኩሪ ድል አስመዘገበች።

ለ. ኃይሌ የወርቅ ሜዳልያ ተሸለመ።

ሐ. ነጃት መጽሐፍ አነበበች።

መ. ተማሪዎች ክፍላቸውን አፀዱ።

ሠ. ሶስና ደብዳቤ ጻፈች።

ረ. ዘሀራ አባቷን ረዳች።

## ተግባር 2

መምህራችሁ በሚጽፉላችሁ ዓረፍተነገሮች ላይ በመወያየት ባለቤታቸውንና ግሣዊ ሐረጋቸውን ለይታችሁ ጻፉ።

## የቃላት ጥናት

### መነጠልና ማጣመር

**ተግባር**

የሚከተሉትን ቃላት በመነጠልና በማጣመር አንብቡ።

| ነጣጥሎ ማንበብ | | አጣምሮ ማንበብ |
|---|---|---|
| ሀ. | ወዳጅ-ነት-ኣቸው | ወዳጅነታቸው |
| ለ. | ዳኛ-ኦች-ኡ | ዳኞቹ |
| ሐ | ልምድ-ኦች-ኣችን | ልምዶቻችን |
| መ. | ውጤት-ኣማ-ነት | ውጤታማነት |
| ሠ. | ልጅ-ነት-ኣችን | ልጅነታችን |
| ረ. | ኢትዮጵያ-ው-ያን | ኢትዮጵያውያን |
| ሰ. | ጉዳት-ኧኛ-ኦች | ጉዳተኞች |
| ሸ | ወራሽ-ኦች-ኣቸው-ን | ወራሾቻቸውን |

## ማንበብ

### የስኬታማነት ምስጢር

### ቅድመንባብ

### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

**ተግባር**

"የስኬታማነት ምስጢር" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ከማንበባችሁ በፊት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. ስኬት ምንድን ነው?

ለ. ለስኬት የሚያበቁ ነገሮች /ሁኔታዎች ምን ምን ናቸው?

## የማንበብ ሂደት

### ተግባር

የስኬታማነት ምስጢር በሚል ርዕስ የቀረበውን መረጃ ሰጪ ምንባብ በለሆሳስ አንብቡ።

### የስኬታማነት ምስጢር

ኢትዮጵያ የበርካታ አትሌቶች መፍለቂያ ሀገር ናት። እነዚህ አትሌቶች በተለያዩ ጊዜያት ሰንደቅዓላማችን ከፍ ብሎ እንዲውለበለብ አድርገዋል። በዓለም አቀፍ መድረክ ታላቅ ክብርና ዝና አትርፈዋል። በድል ደምቀው አድምቀውናል። ታዲያ የስኬታማነታቸው ምሥጢር ምን ይሆን? ለስኬት ከበቁባቸው አያሌ ምክንያቶች የሚከተሉት ጥቂቶቹ ናቸው።

የመጀመሪያው የስኬታማነታቸው ምሥጢር ጠንካራ ልምምድ ማድረግ ነው። በብዙ የሙያ መስኮች በቂ ልምምድ ማድረግ ለውጤት እንደሚያበቃ ተደጋግሞ የታየ ዕውነታ ነው። ኢትዮጵያውያን አትሌቶችም ለስኬታማነት የበቁበት አንዱ ምሥጢር ተገቢ ልምምድ ማድረጋቸው ነው። በዕቅድ ላይ የተመሠረተና በአሠልጣኝ የታገዘ ልምምድ ለድል አብቅቷቸዋል።

ሁለተኛው የስኬታማነታቸው ምሥጢር ጽናት ነው። ሰዎች በተሰለፉበት የሥራ ዘርፍ የተለያዩ ችግሮች ሊያጋጥሟቸው ይችላሉ። እነዚህን ችግሮች ግን በጽናት መቋቋም ያስፈልጋል። ችግሮች ሲከሰቱ ተስፋ መቁረጥ በፍፃሜ ወደሚገኘው ስኬት አያደርስም። ብዙዎቹ የዓለማችን ስኬታማ ሰዎች ፈተናዎችን በጽናት የተሻገሩ ናቸው። ኢትዮጵያውያን አትሌቶችም ከልጅነት ጀምሮ የገጠሟቸውን ችግሮች በጽናት አልፈዋል፤ ስኬታማ ለመሆንም ችለዋል። ለምሳሌ ያህል አበበ ቢቂላ በባዶ እግሩ በመሮጥ በሮም አደባባይ ላይ የሀገሩ ሰንደቅዓላማ ከፍ ብሎ እንዲውለበብ ያደረገው በጽናት ነው። በተጨማሪም አበበ የመኪና አደጋ ከደረሰበት በኋላ እንኳ በአካል ጉዳተኛ ተሽከርካሪ ወንበር ላይ ሆኖ በቀስት ስፖርት መወዳደር ችሏል። እስከለተሞቱ ድረስ በስፖርቱ ዓለም በጽናት የቆመ ጀግና ለመሆንም በቅቷል። አትሌት ጥሩነሽ ዲባባም በውድድር ጊዜ ሕመም እያስጨነቃት ሆዷን በእጇ ደግፋ በአሸናፊነት ያጠናቀቀችው በጽናት ነው። ሌሎች አትሌቶቻችንም ተመሳሳይ የጽናት መንፈስ ስላላቸው ለአንፀባራቂ ድሎች መብቃት ችለዋል፤ በስኬት ላይ ስኬት ተጎናጽፈዋል።

ሦስተኛው የስኬታማነት ምሥጢር የሙያ ሥነምግባር ነው። ሥነምግባር የሌለው ሰው በተሰማራበት ሙያ ውጤታማ መሆን አይችልም። ሁሉም ስመጥር አትሌቶቻችን በመኖሪያ አካባቢም ሆነ በመሮጫ መም ላይ ተገቢ ሙያዊ ሥነምግባር ስላላቸው እንደፈርጥ ሊያበሩ ችለዋል፤ ተወዳጅነትንም አትርፈዋል። ለምሳሌ ያህል በኮሪያ የዓለም ወጣቶች የ10 ሺህ ሜትር ውድድር ላይ ኃይሌ ገብረሥላሴ ከኋላ ተነስቶ ኬንያዊ ተፎካካሪውን ቀድሞ በመግባት አሸነፈው። አሸንፋለሁ ብሎ ያሰበው ኬኒያዊ አትሌትም በኃይሌ ስለተቀደመ በንዴት ኃይሌን

በቡጢ ነረተው። ኃይሌም አፀፋውን ሳይመልስ በትዕግስት አለፈው። ይህንን ህገወጥ ተግባር የተመለከቱ ዳኞች ኬንያዊው አትሌት ሊያገኝ የነበረውን የብር ሜዳልያ በቅጣት በመከልከል ሦስተኛ ለወጣው ሯጭ ሰጥተውበታል። በዚህም ኃይሌ ተወድሶበታል፤ ኬንያዊው ሯጭ ደግሞ አንገቱን ደፍቶበታል።

አራተኛው የስኬታማነት ምንጭ ከቀደምት ኢትዮጵውያን አትሌቶች ለመማር ዝግጁ መሆን ነው። በማንኛውም የሥራ መስክ የተሻለ አፈፃፀም ያላቸውን ሰዎች ተሞክሮ በመውሰድ መጠቀም ለድል ያበቃል። በሥራ ክንውን፣ በአመጋገብ፣ በአኗኗር፣ በጊዜ አጠቃቀም ከሌሎች ልምድ መቅሰም በጣም ይጠቅማል። ከራስም ሆነ ከሌሎች ሰዎች ስህተት ብዙ መማር ይቻላል። ኢትዮጵያውያን አትሌቶች በስኬት የሚያበሩት ከሌሎች ኢትዮጵያውያን አትሌቶች የአሯሯጥ ጥበብ ልምድ በመቅስም ነው። ለምሳሌ ኃይሌ፣ ጥሩነሽ፣ መሠረት፣ ቀነኒሳ... ከምሩፅ ይፍጠር የአጨራረስ ስልት ልምድ አግኝተዋል። አንጋፋዎቹ አትሌቶቻችን ደራርቱ ቱሉና ፋጡማ ሮባ የተደራራቢ ድል ባለቤት ለሆኑት ወጣት ሴት አትሌቶቻችን አርዓያ ሆነዋቸዋል።

በአጠቃላይ በሩጫው መስክ ስኬታማ የሆኑ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች የበርካታ ችሎታዎች ባለቤት ናቸው። ተከታታይ ልምምዳቸው፣ ሙያዊ ሥነምግባራቸው፣ ጽናታቸውና ከሌሎች መማራቸው ለታላቅ ስኬት አብቅቷቸዋል። በአንዱ ጠንክሮ በሌላው መድከም የታሰበውን ያህል በድል ጎዳና አያራምድም። ስለሆነም ሁሉንም አማራጮች አስተባብሮ ማከናወን ተገቢ እንደሆነ ከአትሌቶቻችን በቀላሉ መማር ይቻላል።

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ለስኬት የበቁባቸው ምክንያቶች ምን ምን ናቸው?

ለ. መሠረትና ጥሩነሽ ልምድ ያገኙት ከእነማን ነው?

ሐ. በሩጫ ጥበብ የአሰልጣኝ ሚና ምን ሊሆን ይችላል?

መ. ከሌሎች ሰዎች ልምድ የምንቀስምባቸው ሁኔታዎች ምን ምን ናቸው?

ሠ. እናንተ በምትማሩበት ትምህርትቤት ከጓደኞቻችሁ ልምድ ቀስማችሁ ታውቃላችሁ? እንዴት?

ረ. በአካባቢያችሁ በግብርና፣ በንግድ፣ በፈጠራ፣ በትምህርት ወዘተ. ለስኬት የበቁ ሰዎችን ጥቀሱ።

# 8ኛ ቀን

## ቃላት

### ለቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ መስጠት

### ተግባር 1

በ "ሀ" ረድፍ ለቀረቡት ቃላት ተመሣሣይ ፍቻቸውን ከ"ለ" ረድፍ በመምረጥ አዛምዱ።

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. አፀፋ | ሀ. ምላሽ |
| 2. ፈርጥ | ለ. ሥራ |
| 3. ተግባር | ሐ. ሽልማት |
| 4. መቅሠም | መ. እንቁ |
| 5. ሜዳልያ | ሠ. መገኛ |
| 6. ፍጥነት | ረ. ቅልጥፍና |
| 7. መፍለቂያ | ሰ. አበላል |
| 8. አመጋገብ | ሸ. መማር |

### ተግባር 2

በ "ሀ" ረድፍ ለቀረቡት ቃላት ተቃራኒ ፍቻቸውን ከ"ለ" ረድፍ በመምረጥ አዛምዱ።

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ስኬት | ሀ. ማንኳሰስ |
| 2. ማትረፍ | ለ. ድካም |
| 3. ብርታት | ሐ. መመለስ |
| 4. ማሸነፍ | መ. መከልከል |
| 5. ማድነቅ | ሠ. መጥላት |
| 6. አንጋፋ | ረ. ማጣት |
| 7. መፍቀድ | ሰ. ጀማሪ |
| 8. መውደድ | ሸ. መረታት |
| 9. መውሰድ | ቀ. ውድቀት |

## መጻፍ

### ድርሰት መጻፍ

### ድርሰትን አስተካክሎ መጻፍ

#### ተግባር 1

ስለአትሌት ምሩፅ ይፍጠርና ስለአትሌት መሠረት ደፋር የህይወት ታሪክ በ2ኛው ሳምንት፣ በ5ኛው ቀን የጻፋችሁትን ድርሰት የፊደላት ግድፈትና የሥርዓተነጥብ አጠቃቀም ስህተቶችን አስተካክላችሁ እንደገና ጻፉ።

#### ተግባር 2

የሚከተሉትን ሀሳቦች መነሻ በማድረግ "ትምህርትቤት የገባሁ ዕለት" በሚል ርዕስ አንድ ተራኪ ድርሰት ጻፉ።

- የተሰማኝ ደስታ
- የለበስኩት ልብስ
- የተዋወቅኳቸው ጓደኞቼ
- የያዝኳቸው የትምህርት መሣሪያዎች
- የትምህርትቤቱ አቀማመጥ(ገጽታ)

መንደርደሪያ ዓረፍተነገር፦ ትምህርትቤት የገባሁ ዕለት የተሰማኝ ደስታ ወሰን የለውም።

### የአጻጻፍ ሥርዓት

### ቃላትን አዳምጦ በትክክል መጻፍ

#### ተግባር

መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን ቃላት አዳምጣችሁ ፊደል ሳትገድፉ በትክክል ጻፉ።

# 9ኛ ቀን

## አቀላጥፎ ማንበብ

### የስኬታማነት ምስጢር

### ቅድመንባብ

#### ተግባር

በ3ኛው ሳምንት፣ በ7ኛው ቀን "የስኬታማነት ምሥጢር" በሚል ርዕስ ያነበባችሁትን ምንባብ ፍሬ ሀሳብ አስታውሳችሁ ተናገሩ።

### ማንበብ

#### ተግባር

"የስኬታማነት ምስጢር" በሚል ርዕስ ከቀረበው ምንባብ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት ሦስተኛውን አንቀጽ በ1 ደቂቃ ውስጥ ድምፅ በማሰማት በትክክልና በተገቢው ፍጥነት አንብቡ።

## መናገር

### ውይይት ማካሄድ

#### ተግባር

ተተኪ አትሌቶችን ለማፍራት በትምህርትቤት ደረጃ ምንምን ተግባራት መከናወን እንዳለባቸው በቡድን ተወያይታችሁ የደረሳችሁበትን ማጠቃለያ በክፍል ውስጥ አቅርቡ።

## ሰዋስው

### ባለቤትና ግሣዊ ሐረግ መለየት

#### ተግባር 1

የሚከተሉትን ዓረፍተነገሮች ባለቤትና ግሣዊ ሐረግ ለይታችሁ ጻፉ።

ሀ. ልጆቹ ኳስ ተጫወቱ።

ለ. አልማዝ ጥያቄ መለሰች።

ሐ. ሰውዬው ሽንኩርት ገዛ።

መ. ተማሪዎቹ ችግኝ ተከሉ።

ሠ. ዘሀራ አባቷን ጠራች።

#### ተግባር 2

ባለቤትና ግሣዊ ሐረግ ያላቸው ሦስት ዓረፍተነገሮች ጻፉ።



# ቃላዊ ግጥሞች

## ምዕራፍ 3

ሠርግና ሞት

1ኛ ሳምንት 1ኛ ቀን

## የቃላት ጥናት

### መነጠልና ማጣመር

**ተግባር**

የሚከተሉትን ውስብስብ ቃላትና ሐረጋት ነጣጥላችሁና አጣምራችሁ አንብቡ።

| | ነጣጥሎ ማንበብ | አጣምሮ ማንበብ |
|---|---|---|
| ሀ | አል-ዋለ-ም | አልዋለም |
| ለ | አስ-ኣሰረ | አሳሰረ |
| ሐ | አል-ጨበጠች-ም | አልጨበጠችም |
| መ | ተከሳችሁ-ኣል | ተከሳችኋል |
| ሠ | የሚ-መስል-ኧ-ው | የሚመስለው |
| ረ | መደሰቻ-ኣቸው | መደሰቻቸው |
| ሰ | እየ-ኣዋለለ-ች-ው | እያዋለለችው |
| ሸ | እየ-ኣጫወተ-ች | እያጫወተች |
| ቀ | የ-ወረብ-ሽ | የወረብሽ |

## ማንበብ

### ዘመናይ ማርዬ

**ቅድመንባብ**

ከሥዕል የምንባብን ሀሳብ መገመትና አዳዲስ ቃላትን ማስተዋወቅ

**ተግባር 1**

"ዘመናይ ማርዬ" ከሚለው ርዕስ ሥር የቀረበውን ሥዕል ተመልከቱና የሚከተሉትን

ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. በሥዕሉ ላይ የምታዩአቸው ሰዎች የተደሰቱ ይመስላችኋል? ለምን?

ለ. በሥዕሉ ላይ የሚታዩት ሰዎች የተሰባሰቡት ምን ዓይነት ሥርዓትን ለማከናወን ይመስላችኋል? ለምን?

## ተግባር 2

“ዘመናይ ማርዬ” የሚለውን የሠርግ ግጥም ከማንበባችሁ በፊት ለሚከተሉት ቃላት በቃላችሁ ፍቺ ስጡ።

ሀ. ሸገነ ለ. ወረብ ሐ. ወይባ መ. ወለባ

## የማንበብ ሂደት

## ተግባር

“ዘመናይ ማርዬ” በሚል ርዕስ የቀረበውን የሠርግ ግጥም መምህራችሁ በሚያነቡላችሁ አነባበብ ስልት መሠረት አንብቡ።

### ዘመናይ ማርዬ



አምሯል ሸገኑ <u>አምሯል ሸገኑ፣</u> (2)

መደሰቻቸው <u>ዛሬ ነው ቀኑ።</u> (2)

አይዞሽ ሙሽሪት <u>አይበልሽ ከፋ፣</u> (2)

ሁሉም ያገባል <u>በየወረፋ።</u>(2)

እቴ ያገር ልጅ <u>ስሪ ጉልቻ፣</u> (2)

ከእንግዲህ ቀረ <u>የእናት እንጎቻ</u>። (2)

ዘመናይ ማርዬ ዘመናይ ማርዬ፣

ስም አወጣሁልሽ <u>አትጠገብ ብዬ</u>። (2)

ዘመናይ ናት እሷ ዘመናይ ናት እሷ፣

ጫማዋ ጥልፍልፍ <u>ሀር ነው ቀሚሷ</u>። (2)

<u>ችቦ አይሞላም ወገቧ፣</u> (2)

ማር እሸት ነው ቀለቧ።

ኧረ ያገሬ ልጅ ምንድን ነው ቀለቧ፣

ከፈረሱ ጭራ ይቀጥናል ወገቧ።

እጥፍ ዘርጋ ስትይ አወይ የወረብሽ፣

እህል ቀምሶ ያደረ አይመስልም ወገብሽ።

ባቷ ተረከዟ ስጋው ተነባብሮ፣

ወገቧ ቀጭን ነው አልበላም ወይ አብሮ።

የሙሽሪት እናት ውጪ ተከሰሻል፣

ይቺን መሳይ ቆንጆ ማን ውለጅ ብሎሻል፤

የሙሽሪት አባት ውጣ ተከሰሀል፣

ይቺን መሳይ ቆንጆ ማን ውለድ ብሎሀል።

ዓይኗን ወዲያ ወዲህ እያዋለለችው፣

ልቤን እንደ በሬ ሆብላ ነዳችው።

ዓይናማ ጥርሷማ መች ይበልጣል ከሰው፣

አንገቷ ነው እንጂ ሐረግ የሚመስለው።

እንሶስላ ሞቃ ወይባ ጨብጣለች፣

ራሷን ተሰርታ ወለባ አድርጋለች፣

እህቶች ተነሱ ታጠቁ ትላለች፣

ይህች ወይዘሮ ወዴት አስባለች።

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር 1

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. "ችቦ አይሞላም ወገቧ፣ ማርሽት ነው ቀለቧ" የሚለው ስንኝ ማንን የሚያመለክት ይመስላችኋል? እንዴት ይታወቃል?

ለ. "እቴ ያገር ልጅ ስሪ ጉልቻ" የሚለው ስንኝ መልዕክቱ ምንድን ነው?

ሐ. ሙሽራዋ በማግባቷ የሚቀርባት ምንድን ነው? እንዴት ይታወቃል?

መ. የሙሽራዋ አባትና እናት "ውጡ ተከሳችኋል" የተባሉ ለምን ይመስላችኋል?

ሠ. "ሐረግ ይመስላል" ተብሎ የተገለጸው የሙሽራዋ የአካል ክፍል የትኛው ነው?

ረ. በእናንተ አካባቢ ለወንድ ሙሽራ ምን ዓይነት ግጥሞች ይገጠማሉ?

### ተግባር 2

"ዘመናይ ማርዬ" የሚለውን ምንባብ መሠረት በማድረግ የሠርግ ክዋኔዎችን መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት በክፍል ውስጥ ከውኑ።

## 2ኛ ቀን

## ቃላት

### ቃላትን በማቃረን ማዛመድ

### ተግባር

በ "ሀ" ክፍል ለቀረቡት ቃላት ተቃራኒያቸውን ከ"ለ" ክፍል በመምረጥ አዛምዱ።

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. መደሰት | ሀ. መቀመጥ |
| 2. መቅረት | ለ. መታጠፍ |
| 3. መጨበጥ | ሐ. መልቀቅ |
| 4. መቅጠን | መ. መምጣት |
| 5. መብለጥ | ሠ. መከፋት |
| 6. መጥገብ | ረ. መራብ |
| 7. መነሳት | ሰ. መርጋት |
| 8. መዋለል | ሸ. መወፈር |
| 9. መውጣት | ቀ. ማነስ |
| 10. መዘርጋት | በ. መውረድ |
| | ተ. መንቀሳቀስ |

## መጻፍ

### የአጻጻፍ ሥርዓት

### የግጥም ሐረጋትን አስተካክሎ መጻፍ

#### ተግባር

የሚከተሉትን የግጥም ሐረጋት በትክክለኛ አሰዳደር በማደራጀት ግጥሙን አስተካክላችሁ ጻፉ።

ምሳሌ

| የተፋለሰ | የተደራጀ |
|---|---|
| ምንድን ነው ቀለቧ/ ኧረ ያገሬ ልጅ፣<br>ይቀጥናል ወገቧ/ከፈረሱ ጭራ። | ኧረ ያገሬ ልጅ/ ምንድነው ቀለቧ፣<br>ከፈረሱ ጭራ/ ይቀጥናል ወገቧ። |

ሀ. ስሪ ጉልቻ/እቴ ያገር ልጅ፣
የናት እንጎቻ/ከእንግዲህ ቀረ።

ለ. ወገቧ/ችቦ አይሞላም፣
ቀለቧ/ማር እሸት ነው።

ሐ. ተው ምታ ምታ/ ሚዜው በሙሉ
ይታዘባሉ/እናት አባቷ።

መ. ወይን አላት ወይን/ያውና በእጇ
    ሞልቷል ከደጇ/ከናት አባቷ ቤት።

ግጥም መጻፍ

## የተጓደሉ ሐረጋትን አሟልቶ ስንኝ መጻፍ

### ተግባር

የሚከተሉትን የግጥም ስንኞች በሳጥኑ ውስጥ ከተሰጡት ሐረጋት በመምረጥ አሟልታችሁ ጻፉ።

| | | |
|---|---|---|
| ዘርዛራ ወንፊት፣ | ታጅቦ በልልታ፣ | እስከለተሞቴ፣ |
| አፈር ባይነካሽ፣ | ስንቱን ጋራ ዘልቆ፣ | ባንቺ ተለክፌ፣ |

ምሳሌ

እንዳልበላ ጾሜ እንዳልጾም ገድፌ፣
እንዲህ ሆኜ ቀረሁ________________።
ተስተካክሎ ሲጻፍ፡-
እንዳልበላ ጾሜ/እንዳልጾም ገድፌ፣
እንዲህ ሆኜ ቀረሁ/ባንቺ ተለክፌ።

ሀ. አልጋሽ የዝሆን ጥርስ/መከዳሽ ሽንበቆ፣
    ትዝታሽ ይመጣል/ ______________።

ለ. ሌላሰው አልሻም/በሥጋ ህይወቴ፣
    ካንቺ እስከሚለየኝ/ ______________።

ሐ. ከውበትሽ ጋር/ ስምሽ ይሞካሽ፣
    ምንኛ ደግ ነው/ ________________።

መ. አታሞው ሲደለቅ/ ከበሮው ሲመታ፣
    ትከሻሽ ሲረግፍ/ ________________።

ሠ. የሙሽራው ማማር/ የሚዜው ውበት፣
    ልቤን አደረገው/ ________________።

3ኛ ቀን

# አቀላጥፎ ማንበብ

## ዘመናይ ማርዬ

### ቅድመንባብ

**ተግባር**

የሚከተሉትን የግጥም የአነባበብ ስልቶች በመጠቀም እንዴት እንደሚነበብ ከጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩ።

ማስታወሻ

ግጥም የሚዋቀረው ሐረግ በሐረግ ነው። ሐረጎች ደግሞ ስንኝን ይመሠርታሉ። ሐረግ በግጥም ውስጥ በአንድ ትንፋሽ የሚነበብ ሲሆን ስንኝ ደግሞ አንድ የግጥም መስመር ነው።

አንድን ግጥም አቀላጥፎ ለማንበብ የሚረዱ መመሪያዎች:-

- በሐረጎችና በስንኞች መጨረሻ የተወሰነ የጊዜ ቆይታ ማድረግ
- ግጥሙን በተገቢ ዜማዊ ቃና ማንበብ።
- የተለያዩ የግጥም አነባበብ ስልቶችን ከመምህራን፣ ከሬዲዮ፣ ከቴሌቪዥን፣ ከሥነጽሁፋዊ መድረኮች ወዘተ ማዳመጥ
- ግጥሙ የቅስቀሳ፣ የሀዘን፣ የግርምት፣ የትዝብት፣ የውዳሴ፣... መሆኑን በማጤን የአነባበብ ለዛውን እንደየግጥሙ ዓይነት እየቀያየሩ ለማንበብ መሞከር

### ማንበብ

**ተግባር**

መምህራችሁ ባሳዩአችሁ የግጥም አነባበብ ስልት መሠረት "ዘመናይ ማርዬ" በሚል ርዕስ ከቀረበው ግጥም መካከል ስድስት ስድስት ስንኞችን ዜማዊ ቃናቸውን በመጠበቅ በየተራ አንብቡ።

# ማዳመጥ

## የሀዘን እንጉርጉሮ

### ቅድመማዳመጥ

### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

#### ተግባር

መምህራችሁ "የሀዘን እንጉርጉሮ" በሚል ርዕስ የቀረበውን የሙሾ ግጥም ያነቡላችኋል። ግጥሙን ከማዳመጣችሁ በፊት ለሚከተሉት ጥያቄዎች በቃላችሁ መልስ ስጡ።

ሀ. ሰዎች በሞት በተለዩ ጊዜ የሚደረደር የሀዘን እንጉርጉሮ ይዘት በምን በምን ላይ ያተኩራል?

ለ. የምታውቁትን የሀዘን እንጉርጉሮ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ግለጹ፤ ምን መልዕክት እንደሚያስተላልፍም ተናገሩ።

### የማዳመጥ ሂደት

#### ተግባር

"የሀዘን እንጉርጉሮ" በሚል ርዕስ የቀረበውን ቃላዊ ግጥም በትኩረት አዳምጡ፤ በማዳመጥ ሂደት ለምትጠየቁት ጥያቄም ትክክለኛ መልስ ስጡ።

### አዳምጦ መረዳት

#### ተግባር 1

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ቃላዊ ግጥም መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. "አሞራና ዶሮ አይ እኛና ሞት" ከሚለው ስንኝ ውስጥ  አጥፊና ጠፊዎቹን ለይታችሁ ተናገሩ?

ለ. ገጣሚው/ዋ ምድርን ተጠንቅቆ/ቃ ለመርገጥ የፈለገው/ችው ለምንድን ነው?

ሐ. ገጣሚው/ዋ የወገኖቹን/ቿን በተደጋጋሚ መሞት የገለጸው/ችው ከምን ጋር በማመሳሰል ነው?

መ. እንደግጥሙ አገላለጽ ሰዎች የማይጠቅሙት ወይም የማይጎዱት መቼ ነው?

ሠ. በግጥሙ መሠረት "እኛ ወደእናንተ ምን ቢሆን አንቀርም" የሚለው ስንኝ ዋና መልዕክት ምን ይመስላችኋል?

ረ. በግጥሙ ውስጥ "ማነው የቆረጠው የመንገዱን ሾላ…" የሚለው አባባል መልዕክት ምንድን ነው?

## ተግባር 2

ቤተሰቦቻችሁን በመጠየቅ 10 ስንኝ የሥርግ ግጥም ወይም የሀዘን እንጉርጉሮ ጽፋችሁ በክፍል ውስጥ አንብቡ።

# ሰዋስው

## ሐተታዊ (አዎንታዊና አሉታዊ) ዓረፍተነገሮችን መለየት

### ተግባር

የሚከተሉት ሐተታዊ ዓረፍተነገሮች “አዎንታዊ” ወይም “አሉታዊ” መሆናቸውን በምክንያት ግለጹ።

ሀ. የሙሽራዋ እናት ቆንጆ ልጅ ወልደዋል።

ለ. የሙሽራዋ ጫማ ጥልፍልፍ ነው።

ሐ. ሚዜዎቹ የሀር ቀሚስ አለበሱም።

መ. ጀማነሽ ዓይናን ከወዲያ ወዲህ አዋለለችው።

ሠ. የመንገዱ ሾላ አልተቆረጠም።

ረ. ልጅቷ እንሶስላ ሞቃለች።

ሰ. ሠርገኞቹ እስካሁን አልመጡም።

## ማንበብ

### በሰፊው ለማፈስ

### ቅድመንባብ

### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

#### ተግባር

"በሰፊው ለማፈስ" የሚለውን የሥራ ግጥም ከማንበባችሁ በፊት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. የሥራ ላይ ግጥሞች በሥራ ወቅት ምን ምን ጠቀሜታዎች አሏቸው?

ለ. ሰዎች ግጥም የሚያንጎራጉሩት ምን ምን ሥራዎችን ሲያከናውኑ ነው?

ሐ. ከምታውቋቸው የሥራ ግጥሞች ውስጥ ሁለት ሁለት ስንኞችን ዜማቸውን ጠብቃችሁ ተናገሩ።

መ. "በሰፊው ለማፈስ" የሚለውን ርዕስ ከሥዕሉ ጋር በማገናዘብ የተረዳችሁትን ግለጹ።

### የማንበብ ሂደት

#### ተግባር

"በሰፊው ለማፈስ" በሚል ርዕስ የቀረበውን የሥራ ላይ ግጥም ስንኝ በስንኝ እየተቀባበላችሁ ድምጽ በማሰማት አንብቡ።

### በሰፊው ለማፈስ

ማረስ ነው እንጂ እያሸረጡ፣

እንደእንቧሮ ግንድ ሳይለመጡ።

ሥራ እንደኮሶ እየመረረው፣

ጠቅልሎ መጉረስ ማን አስተማረው?



አርሶአደር በእርሻ ሥራ ላይ

ማረሻው ሀዲድ ሞፈሩ ወይራ፣
ሰርዶ አራጋፊ እንደጨኻራ።
አርሶ መሸመት ተኩሶ መሳት፣
ይለበልባል እንደእግር እሳት።
አረንዛ  ውጦኝ እስከጉልበቴ፣
ሽልም አወጣኝ የነፍስ አባቴ።
ያላረሰ ጎበዝ እርፍ ያልነቀነቀ፣
ስልቻውን ይዞ በቃርሚያ ዘለቀ።
ያረሰማ ጎበዝ እርፍ የነቀነቀ፣
ወፍጮው እንዳኻራ መስከረም ዘለቀ።

እንደምን ነሽ እርሻ እንዴት ነሽ ማረሻ፣
ትብለጨለጫለሽ ከጀግናው ትከሻ።
ታታሪ አርሶአደር ጥሩ ምርት ያለው፣
ጎልጉሎ ይዘራል ምንም ቢደክመው።
ዘር በእጁ ጨብጬ በማሳው ስዘራ፣
ወፍም እንዳትለቅሚው ጉንዳንም አደራ።
ንቀይው አረሙን ሰርዶውን ለይተሽ፣
ከርሞ ነጭ ስንዴ ትበይበታለሽ።
ንቀለው ንቀለው ንቀለው በለጋው፣
ቢያድግ አይደለም ወይ እሾህ የሚወጋው።
ወፍ እጠብቃለሁ ዋርዳና ነጎዴ፣
እሸት እየቆረጥኩ እየበላ ሆዴ።
ልንገራት እኔስ ለአልቢኔ መላ፣
እየቆረጠች  እንድታበላ።
የኔማ ማጭድ ሆዱን አሚታል፣
እየቆረጠ ያስቀምጣታል።
አድርገው ድቅቅ አርገው ገለባ፣
ቤታችን ሩቅ ነው በጊዜ እንድንገባ።
እንውቃ አዝመራችንን እንሸክፍ በወቅቱ፣
አቅማችን ሳይደክም ሳይበላብን ከብቱ።

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር 1

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በግጥሙ መሠረት ትክክል ከሆኑ "እውነት" ስህተት ከሆኑ ደግሞ "ሐሰት" በማለት ምክንያት እየሰጣችሁ በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. ስልቻውን ይዞ በቃርሚያ የሚዘልቀው ጎበዝ አርሶአር ነው።

ለ. ጠንካራ አርሶአደር ሥራ እንደኮሶ አይመረውም።

ሐ. ወፍጮው እንዳጓራ እስከመስከረም የሚዘልቀው በሰነፍ አርሶአደር ቤት ነው።

መ. ጎበዝ አርሶአደርና የእንቧጮ ግንድ ተመሳሳይ ናቸው።

ሠ. ዋርዳና ነገዴ አዝመራ የሚያጠፉ የወፍ ዓይነቶች ናቸው።

## ተግባር 2

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በግጥሙ መሠረት በጽሑፍ በትክክል መልሱ።

ሀ. እንደእግር እሳት የሚለበልበው ምንድን ነው?

ለ. ገጣሚው ዘር በእጁ ጨብጦ በማሳው በሚዘራበት ጊዜ አደራ ያለው ማንን ነው? ለምን?

ሐ. በግጥሙ መሠረት ጠንክሮ የማያርስ ሰው ምን የሚያጋጥመው ይመስላችኋል?

መ. "ንቀይው አረሙን ሰርዶውን ለይተሽ" የተባለችው ማን ናት?

ሠ. በግጥሙ መሠረት አርሶአደሩ ወፍ የሚጠብቀው ምን እያደረገ ነው?

ረ. ገጣሚው በግጥሙ ውስጥ የጠቀሳቸው የእርሻ መሳሪያዎች ምን ምን ናቸው?

ሰ. "ሽልም አወጣኝ የነፍስ አባቴ" የሚለው ስንኝ ምንን ይገልጻል?

ቀ. የግጥሙ ዋና መልዕክት ምንድን ነው?

## 5ኛ ቀን

## ቃላት

### ቃላትን በተመሳሳያቸው መተካት

## ተግባር

ለተሠመረባቸው ቃላትና ሐረጋት በፍቺ የሚመሳሰሏቸውን ቃላት ከግጥሙ ውስጥ በመፈለግ ተክታችሁ ጻፉ።

ሀ. ሥራው <u>እንደሬት</u> መሮታል። (ከስንኝ 2-4)

ለ. ማረሻው <u>ጠንካራ</u> በመሆኑ አይሰበርም። (ከስንኝ 5-7)

ሐ. <u>ረግረግ</u> የሆነ መሬት ለእርሻ አይመችም። (ከስንኝ 7-10)

መ. ከፍየል ቆዳ የሚዘጋጅ <u>አቁማዳ</u> ለእህል መያዣ ያገለግላል። (ከስንኝ10-13)

ሠ. አርሶአደሮች ሰብሉን አጭደው ካነሱ በኋላ <u>ልቅምቃሚውን</u> አሰሱ። (ስንኝ

10-14)

ረ. አርሶአደሩ በማረሻ የነቀለውን የአረም አፈር አራግፎ ዘሩን ዘራ።(ከስንኝ16-18)

ሰ. ዘሩን ጨብጦ በእርሻው ላይ በተነው።(ከስንኝ18-19)

ሸ. አረም በለጋው ካልተነቀለ ሲያድግ አሜከላ ይሆናል። (ከስንኝ 23-24)

ቀ. ሰብል ለማጨድ የሰላ ማጭድ ያስፈልጋል። (ከስንኝ25-27)

## መጻፍ

### ግጥም መጻፍ

### የተጓደሉ ሐረጋትን ማሟላት

### ተግባር 1

ክፍት ቦታውን በተገቢው ሐረግ በማሟላት ግጥሙን አስተካክላችሁ ጻፉ።

ምሳሌ፡-

አስተራረሱን ሀገር ያወቀው

ሰነፍ ሲተክዝ ____________።

መልስ፡- እሱ የሳቀው ወይም ችግር አያውቀው

ሀ. አርሶአደር ነህ አሉኝ መሬትን አራሽ፣

የህዝብ መጋቢ ወገንን ________።

ለ. ከስንዴ ከገብሱ ከወጡ ባቄላ፣

ጤፍ እንጀራ እናቅርብ ለወጡ ________።

ሐ. አገር ጥሎ መሄድ ምን ያደርግልሃል፣

ጠንክሮ መስራቱ ላንተም ________።

መ. ማረስ ያስከብራል ነፃነት ያኮራል፣

በየደረሱበት ከልብ ________።

ሠ. እነጣቱ ለምለም እነታፋው ለምለም፣

ታመው የተኙ ቀን የሚቀምሱት ________።

### ተግባር 2

በእርሻ ሥራ ላይ የሚዜሙ ባለ10 ስንኝ ግጥሞችን ሰው በመጠየቅ ወይም መጽሐፍ በማንበብ ጽፋችሁ በክፍል ውስጥ አቅርቡ።

## የአጻጻፍ ሥርዓት

## ግጥምን አስተካክሎ መጻፍ

### ተግባር

በቅንፍ ውስጥ ያሉትን ቃላት በትክክለኛ ቅርፃቸው በመጻፍ የግጥሙን ሀሳብ አሟሉ።

ምሳሌ

| ያልተደራጀ | የተደራጀ |
|---|---|
| ማረስ ነው እንጂ ሰኞ ገስግሶ፣<br>አንተ የእገሌ ልጅ ከማለት (ደረሰ)። | ማረስ ነው እንጂ ሰኞ ገስግሶ።<br>አንተ የእገሌ ልጅ ከማለት ደርሶ። |

ሀ. ማረስ ነው እንጂ እያፎጫጨጩ፣

አይበረክትም ፌጦ (ረጨ)።

ለ. ማረስ ነው እንጂ እጅ እስኪቆስል፣

ሥርቆት ምንድን ነው ውሻ (መሰለ)።

ሐ. በጥቋቁር በሬ ጠምደው ካላረሱ፣

አበዳሪ ቢገኝ ይቸግራል (መለስ)።

መ. ደረሰ መጋል ሊያቅበጠብጠው፣

ፈለግ እያየ ላም (ረገጠ)።

ሠ. ማረስ ደግ ነበር መነቃቀል ሰርዶ፣

ሰውነት ያከሳል መቀላወጥ (ማለደ)።

ረ. አቤት አስተራረስ ምድር አመታት፣

የሞፈሩ መርዘም የበሬው (ጸና)

# 6ኛ ቀን

## አቀላጥፎ ማንበብ

### በሰፊው ለማፊስ

### ቅድመንባብ

**ተግባር**

"በሰፊው ለማፊስ" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ከማንበባችሁ በፊት በ1ኛው ሳምንት በ3ኛው ቀን ያለውን ማስታወሻ አስታውሳችሁ ከመምህራችሁ ጋር ተወያዩ።

### ማንበብ

**ተግባር**

"በሰፊው ለማፊስ" በሚል ርዕስ የቀረበውን ቃላዊ ግጥም መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት አንብቡ።

## መናገር

### ሀሳብን በንግግር መግለጽ

**ተግባር**

መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት በሚከተሉት ሀሳቦች መነሻነት በክፍል ውስጥ ንግግር አቅርቡ።

ሀ. ከእርሻ ጀምሮ እስከውቂያ ድረስ ያለውን ሂደት በቅደምተከተል ተናገሩ።

ለ. የእርሻ መሣሪያዎችን በመዘርዘር የእያንዳንዱን ተግባር ተናገሩ።

ሐ. በአካባቢያችሁ በእርሻ፣ በአጨዳ፣ በውቂያ ላይ የሚገጠሙ ግጥሞችን ከጓደኞቻችሁ ጋር ተወያይታችሁ በክፍል ውስጥ በቃላችሁ አቅርቡ።

## ሰዋስው

### ሐተታዊ (አዎንታዊና አሉታዊ) ዓረፍተነገሮችን መለየት

**ተግባር 1**

የሚከተሉትን ሐተታዊ ዓረፍተነገሮች አሉታዊ ወይም አዎንታዊ በማለት በምክንያት ለዩ።

ሀ. ዘይነባ ተረት ማዳመጥ ታዘወትራለች።

ለ. አስቴር ነገ አትመጣም።

ሐ. ሰይድ ሩቅ መንገድ መሄድ አይወድም።

መ. ተማሪዎቹ ተሰልፈው መዝሙር ዘመሩ።

ሠ. ካሳ መምህሩን ጠይቆ ይረዳል።

ረ. አርሶአደሮቹ ሰብላቸውን ገና አልሰበሰቡም።

## ተግባር 2

የሚከተሉትን አዎንታዊ ዓረፍተነገሮች ወደአሉታዊ ዓረፍተነገሮች ለውጣችሁ ጻፉ።

ሀ. መልዕክትን በቃል ማስተላለፍ ይቻላል።

ለ. የሰው ልጆች ማንነት በግጥም ይገለጻል።

ሐ. እንስሳት ሁሉ ጠቃሚዎች ናቸው።

መ. ወፎች ሰብልን ያጠፋሉ።

ሠ. ቤታችን ሩቅ ነው።

ረ. አርሶአደሮች ጎልጉለው ይዘራሉ።

## የቃላት ጥናት

### መነጠልና ማጣመር

#### ተግባር

1. የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት ነጣጥላችሁና አጣምራችሁ አንብቡ።

| | ነጣጥሎ ማንበብ | አጣምሮ ማንበብ |
|---|---|---|
| ሀ | አስ-ተማሪ-ነት-ኣቸው | አስተማሪነታቸው |
| ለ | ገጣሚ-ዎች-ም | ገጣሚዎችም |
| ሐ | ሀብት-ኦች-ኣችን | ሀብቶቻችን |
| መ | ይደረግ-ብ-ኣችሁ-ኣል | ይደረግባችኋል |
| ሠ | የ-ተ-መጠኑ-ት | የተመጠኑት |
| ረ | የ-አስ-ቆጠሩ | ያስቆጠሩ |
| ሰ | የ-ዐውድ-ዓመት | ያውዳመት |
| ሸ | የ-አኗኗር | ያኗኗር |

## ማንበብ

### ቃላዊ ግጥሞች

### ቅድመንባብ

### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

#### ተግባር

"ቃላዊ ግጥሞች" የሚለውን ምንባብ ከማንበባችሁ በፊት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. የምታውቋቸውን ቃላዊ ግጥሞች በማዜም ወይም በማንበብ አቅርቡ።

ለ. በቃላዊ ግጥሞች ውስጥ የሚካተቱት የቃላዊ ግጥም ዓይነቶች ምን ምን ናቸው?

## የማንበብ ሂደት

### ተግባር

የሚከተለውን ምንባብ ዋናና መዘርዝር ሀሳቦችን እየለያችሁ በለሆሳስ አንብቡ።

### ቃላዊ ግጥሞች

የሰው ልጆች ሀሳባቸውን በጽሑፍ መግለጽ ከመጀመራቸው በፊት ግጥምን ይጠቀሙ ነበር። ግጥም ቃላዊ በሆነ መንገድ ሰፊ አገልግሎት ሲሰጥ ቆይቷል። መልዕክትን በቃል ስለሚያስተላልፍ ቃላዊ ግጥም እየተባለ ይጠራል።

የቃላዊ ግጥም ዓይነቶች ብዙ ናቸው። ያውዳመት፣ የፉከራ፣ የልመና፣ የሙሾ፣ የሥራ ግጥሞች... ሁሉ የቃላዊ ግጥም ዓይነቶች ናቸው። ቃላዊ ግጥሞች እንደየሁኔታው ሊዜሙ ወይም በእንጉርጉሮ ሊቀርቡ ይችላሉ። ቃላዊ በመሆናቸው በአብዛኛው አጫጭር ናቸው። እነዚህ ቃላዊ ግጥሞች ምጣኔ፣ ምትና ዜማ አላቸው። ግጥሞቹ በአብዛኛው በእኩል ጊዜ እንዲያልቁ ሆነው የተመጠኑ ሐረጋት ይይዛሉ። የተመጠኑት ሐረጋት በተወሰነ ጊዜ ሲደጋገሙ ደግሞ ምት ይፈጥራሉ። ሲነበቡም ዜማ አላቸው። ግጥሙ እንደሚገልጸው ስሜት ዜማው ይለያያል።

ቃላዊ ግጥሞች ደራሲያቸው አይታወቅም፤ የኔ ባይ ባለቤት ስለሌላቸው ህዝባዊ ሀብት ናቸው። በዚህ ምክንያት ከሁኔታዎች ጋር ለማስማማት ሲባል በየጊዜው ማሻሻያዎችና ለውጦች ይደረጉባቸዋል። የበርካታ ሰዎች አሻራም ያርፍባቸዋል።

ቃላዊ ግጥሞች በርካታ ጠቀሜታዎች አሏቸው። በቃል እየተላለፉ ረዥም እድሜ ያስቆጠሩ በመሆናቸው የሰው ልጆችን ታሪክ ማጥናት ሲፈለግ እንደመረጃ ምንጭ ያገለግላሉ። የቋንቋ አጠቃቀማቸው የተመረጠና ቁጥብ ስለሆነ ሲዜሙ አድማጭን ያዝናናሉ፤ ያመራምራሉ፤ እርካታም ይፈጥራሉ። ከሁኔታዎች ጋር አስማምቶ መጠቀምን ስለሚፈቅዱ የፈጠራ ችሎታን ያጎለብታሉ። የተለያዩ ጉዳዮችን በተመለከተ በርካታ ቁምነገሮች ስለያዙ አስተማሪነታቸው ከፍተኛ ነው። መልካም ስነምግባሮች ተጠብቀው እንዲዘልቁ ለማድረግ ያስችላሉ። ለዘመናዊ ገጣሚዎችም ቢሆን መነሻ ሆነው ያገለግላሉ። በመሆኑም በብዙ ዘመናዊ ግጥሞች ውስጥ ቃላዊ ግጥሞችን በዓይነትና በብዛት ማግኘት የተለመደ ነው።

የአንድ ማህበረሰብ ባህል በቃላዊ ግጥሞች አማካይነት ጎልቶ ይወጣል። የማህበረሰቡ የአኗኗር፣ የአመጋገብ፣ የአለባበስ፣ ወዘተ ልማድ በግጥሞቹ ይተላለፋል። ሰዎች በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ያላቸው አመለካከት፣ እምነትና ፍልስፍና ሁሉ በቃላዊ ግጥሞች ይንፀባረቃል። በጥቅሉ የሰው ልጆች ማንነት በራሳቸው ቃላዊ ግጥሞች ይገለጻል። ስለሆነም እንደሌሎች ቅርሶች ሁሉ እነዚህን ጠቃሚ ሀብቶቻችንን ልንጠብቃቸው ይገባል።

(አንተነህ። 2001። *የአማርኛ ሥነቃል* አጭር ቅኝት እና ዘሪሁን። 1992። *የሥነጽሑፍ መሠረታውያን*። መጠነኛ ለውጥ ተደርጎ የተወሰደ)

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር 1

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. "ቃላዊ ግጥሞች ባለቤታቸው ህዝብ ነው" የተባለው ለምን ይመስላችኋል?

ለ. ቃላዊ ግጥሞች በቋንቋ አጠቃቀማቸው ልዩ የሚያደርጋቸው ምንድን ነው?

ሐ. ቃላዊ ግጥሞችን እንደቅርስ ጠብቆ ማቆየት የሚቻለው እንዴት ነው?

መ. ሰዎች ቃላዊ ግጥሞችን ከትውልድ ወደትውልድ የሚያስተላልፉበት ምክንያት ምን ይመስላችኋል?

ሠ. በቃላዊ ግጥሞች ላይ የበርካታ ሰዎች አሻራ የሚያርፈው ለምንድን ነው?

ረ. የምንባቡን ዋና መልዕክት በአንድ ዓረፍተነገር ተናገሩ።

### ተግባር 2

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት ተስማሚውን መልስ በመምረጥ መልሱ።

1. በቃላዊ ግጥሞች ውስጥ <u>የማይካተተው</u> የትኛው ነው?

   ሀ. ፉከራ　　ለ. ተረት　　ሐ. ቀረርቶ　　መ. ሙሾ

2. ስለቃላዊ ግጥሞች ትክክል <u>ያልሆነው</u> የቱ ነው?

   ሀ. ሐረጋቱን ሲደጋገሙ ምት ይፈጥራሉ።

   ለ. ሐረጋቱ ሲነበቡ ዜማ አላቸው።

   ሐ. ስንኞቹ የተመጠኑ ሐረጋትን ይይዛሉ።

   መ. በአብዛኛው ሐረጋቱ ረጃጅም ናቸው።

3. ቃላዊ ግጥሞችን በሚመለከት ትክክል የሆነው የቱ ነው?

   ሀ. መልካም ሥነምግባር ተጠብቆ እንዲቆይ ያደርጋሉ።

   ለ. የፈጠራ ችሎታን አያበረታቱም።

   ሐ. ሲዜሙ ወይም ሲነገሩ አድማጭን አያዝናኑም።

   መ. ታሪክን ለማጥናት እንደመረጃ ምንጭ አያገለግሉም።

4. የቃላዊ ግጥሞች ደራሲ <u>የማይታወቀው</u> ለምንድን ነው?

   ሀ. ደራሲ ስለሌላቸው

   ለ. የፈጠራቸውን ደራሲ በትክክል ማወቅ ስለማይቻል

   ሐ. ህዝቦች አንድ ላይ ተሰብስበው ስለሚፈጥሯቸው

   መ. የበርካታ ሰዎች አሻራ ስለሚያርፉባቸው

# 8ኛ ቀን

## ቃላት

### ቃላት ከምንባብ ውጪ ያላቸውን ፍቺ ማሳየት

#### ተግባር

የሚከተሉት ቃላት ከምንባቡ ውጪ ያላቸውን ፍቺ የሚያሳዩ ዓረፍተነገሮችን ሥሩና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡ።

ምሳሌ፡- "ጠቀመ" በምንባቡ ውስጥ የያዘው ፍቺ "ፈየደ፤ አገዘ፣ ረዳ፣ የሚል ነው።" ከምንባቡ ውጪ ያለው ፍቺ ደግሞ በሚከተለው ዓረፍተነገር ተመልከቱ።

አዛውንቱ የተቀደደ ልብሳቸውን በመርፌ <u>ጠቀሙ</u>። ዐውዳዊ ፍቹ ሰፉ፣ አያያዙ ይሆናል። ምክንያቱም ልብስ ይጠቀማል፤ ስለሚባል ልብስንና መርፌን አገናኝቶ የቃሉን ፍቺ ከዐውዱ መረዳት ይቻላል።

| | | |
|---|---|---|
| ሀ. ሐረግ | ሐ. መድረስ | ሠ. ማንፀባረቅ |
| ለ. መንገድ | መ. አሻራ | ረ. መጠበቅ |

## መጻፍ

### ግጥም መጻፍ

### በግጥም ውስጥ የተጓደሉ ሐረጋትን ማሟላት

#### ተግባር 1

የሚከተሉት ግጥሞች የሁለተኛ ስንኝ ሐረግ የጎደላቸው ናቸው። ከመጀመሪያው ስንኝ ሀሳብ ጋር ተስማሚ የሆነ ሐረግ በመጻፍ አሟሉ።

ሀ. እርሻውን እረሰው ግፋ በል አርሶአደር፣
ሀገር እንድትለማ________________

ለ. በጎምላላ በሬ ግፋ ሲል ግፋ ሲል፣
ቆርቆሮ ቤት ሠራ________________

ሐ. በሬና አርሶአደር ተስማምተው ከዋሉ፣
እርሻም ይታረሳል________________

መ. ተው ጎልጉል አርሶአደር ተው ወጥረህ ሥራ፣
ካልተጎለጎለ________________

## ተግባር 2

በአጨዳ ጊዜ የሚገጠሙ ቃላዊ ግጥሞችን ሰው በመጠየቅ ወይም መጽሐፍ በማንበብ ጽፉችሁ በክፍል ውስጥ አቅርቡ።

## የአጻጻፍ ሥርዓት

## ግጥምን አስተካክሎ መጻፍ

## ተግባር

በቅንፍ ውስጥ ያሉትን ቃላት ቅርጽ በመለወጥ ግጥሞቹን አስተካክላችሁ ጻፉ።

ምሳሌ፡- በጎምላላ በሬ ጠምደው ካላረሱት፣

አይሞላም ጎተራ አጎንብሰው (አየ)፣

መልስ፡- በጎምላላ በሬ ጠምደው ካላረሱት፣

አይሞላም ጎተራ አጎንብሰው ቢያዩት።

ሀ. በጥቋቁር በሬ ዲብ ካላፈረሱ፣

አይገኝም ገንዘብ ኪስን (ዳበስ)።

ለ. ሂድና ትለመው ተሻግረህ ገደሉን፣

ችግር እንደአውሬ ነው አይረሳም (በደለ)።

ሐ. ያርሳል በጠራራ ያርማል በጤዛ፣

ችግር ቤት ይፈታል መቀመጥ (በዛ)።

መ. ማልዶ በሬ ጠማጅ ሞፈር አስጨናቂ፣

ካንድ አውድማ ብቻ መቶ መቶ (ወቃ)።

ሠ. አሁን አያችሁ ወይ የማረሻው ለዛ፣

ወገንን አጥግቦ ከንፈርን (ወዝ።)

# አቀላጥፎ ማንበብ

## ቃላዊ ግጥሞች

### ቅድመንባብ

**ተግባር**

"ቃላዊ ግጥሞች" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ከማንበባችሁ በፊት የምንባቡን ዋና ሀሳብ በማስታወስ ተናገሩ።

### ማንበብ

**ተግባር**

"ቃላዊ ግጥሞች" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት ሁለት ሁለት አንቀጽ በአንድ ደቂቃ ውስጥ በየተራ ድምጽ በማሰማት አንብቡ።

# መናገር

### ውይይት ማካሄድ

**ተግባር**

በአካባቢያችሁ የሚከወኑ የሠርግ ሥርዓቶች ተገቢ ናቸው ወይስ አይደሉም? በቡድን በመወያየት ሀሳባችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።

# ሰዋስው

### ሐተታዊ (አዎንታዊና አሉታዊ) ዓረፍተነገሮችን መለየት

**ተግባር 1**

የሚከተሉትን አዎንታዊ ዓረፍተነገሮች ወደአሉታዊ ዓረፍተነገሮች በመለወጥ ጻፉ።

ሀ. አልማዝ ቤቷን አፀዳች።

ለ. ሀያት የሬዲዮ ትረካ ትወዳለች።

ሐ. ዓለሙ ለእናቱ ውኃ ቀዳ።

መ. ካሳ ዋና ይችላል።

ሠ. ሰለሞን ወደጎንደር ሔደ።

## ተግባር 2

ቀጥሎ የቀረቡትን አሉታዊ ዓረፍተነገሮች ወደአዎንታዊ ዓረፍተነገሮች ለውጡ።

ሀ. ጣይቱ ሽንኩርቱን አልተከለችውም።

ለ. አብዱ በዕረፍት ሰዓት ወደቤቱ አልሔደም።

ሐ. ሳምሶን ከዛፍ ላይ መውጣት አይችልም።

መ. አገሪቱ ቁርሷን አልበላችም።

ሠ. ነጃት መስኮቱን አልከፈተችውም።

## ተግባር 3

ሦስት አዎንታዊና ሦስት አሉታዊ ዓረፍተነገሮችን በደብተራችሁ ጻፉ።



# ልጅነት

ምዕራፍ 4

## የልጅነት ጨዋታዎች

1ኛ ሳምንት 1ኛ ቀን

## የቃላት ጥናት

### መነጠልና ማጣመር

**ተግባር**

የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት በመነጠልና በማጣመር አንብቡ።

| | ነጣጥሎ ማንበብ | አጣምሮ ማንበብ |
|---|---|---|
| ሀ | ይጫወቱ-አቸው-ኣል | ይጫወቷቸዋል |
| ለ | ይ-አዜሙ-አቸው-ኣል | ያዜሟቸዋል |
| ሐ | ይዝናኑ-ብ-አቸው-ኣል | ይዝናኑባቸዋል |
| መ | ይ-መቱ-አቸው-ኣል | ይመቷቸዋል |
| ሠ | ይ-መልሱ-አቸው-ኣል | ይመልሷቸዋል |
| ረ | ይ-አስቀምጡ-አቸው-ኣል | ያስቀምጧቸዋል |
| ሰ | ይ-አዩ-አቸው-ኣል | ያዩኣቸዋል |
| ሸ | ከ-እንቅስቃሴ-አቸው | ከእንቅስቃሴያቸው |
| ቀ | አጫዋቾ-ዋ-ን | አጫዋቿን |

## ማንበብ

### መሀረቤን ያያችሁ

**ቅድመንባብ**

**የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ**

**ተግባር**

ምንባቡን ከማንበባችሁ በፊት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. በሥዕሉ ላይ የሚታዩት ልጆች ምን ዓይነት ጨዋታ የሚጫወቱ ይመስላችኋል?

ለ. ልጆች ከሚጫወቷቸው ጨዋታዎች መካከል ሁለቱን ጥቀሱና የአጨዋወቱን ቅደምተከተል ግለጹ።

## የማንበብ ሂደት

### ተግባር

የሚከተለውን መመሪያ ሰጪ ምንባብ የድርጊት ቅደምተከተሎችን እየለያችሁ በለሆሳስ አንብቡ።

## መሀረቤን ያያችሁ



ልጆች በቤታቸው፣ በሰፈራቸውና በትምህርትቤታቸው ይሰባሰባሉ። ብዙ ዓይነት ጨዋታዎችን በመጫወትም ይዝናናሉ። በርካታዎቹ ጨዋታዎች በግጥምና በዜማ ይቀርባሉ። የየራሳቸው ደንብና ሥርዓትም አላቸው።

የልጆች ጨዋታ በአብዛኛው በአካል እንቅስቃሴ ይታጀባል። በመዝለል፣ በመሮጥ፣ በመቀመጥ፣ በመነሳት፣ ዓይንን በመጨፈን ይቀርባል። በተጨማሪም እጅ ለእጅ በመያያዝ፣ ክብ ሰርቶ በመቀመጥ ወይም በመቆምና በመስመር በመደርደር ወዘተ... ይከናወናል።

ልጆች በጨዋታ ጊዜ የሚያዜሟቸው ዜማዎች ከእንቅስቃሴያቸው ጋር ህብረት ይፈጥራሉ። አብዛኞቹ ግጥሞችም አጠር አጠር ያሉና ፍጥነት የሚታይባቸው ናቸው። ከልጆች ጨዋታዎች መካከል አንዱ መሀረቤን ያያችሁ የሚለው ነው።

ጨዋታው የራሱ የአጨዋወት ደንቦች አሉት። ጨዋታውን ለመጫወት የሚፈልጉ ልጆች በመጀመሪያ ክብ ይሥሩ። ፊታቸውን ወደክቡ ውስጥ አዙረው ይቀመጡ። ለጨዋታው የሚያገለግል መሀረብ ወይም ሌላ ጨርቅ ይዘጋጅ። ከዚያም ጨዋታውን የምታስጀምረው ተረኛ ልጅ መሀረቧን በሽሚዟ ሥር ደብቃ ትያዝ፤ በተቀመጡት ልጆች ዙሪያም እየሮጠች "መሀረቤን ያያችሁ እባካችሁ" በማለት ትዞር። ሌሎቹም "አላየንም እባካችሁ" እያሉ በህብረት ዜማ ይመልሱላት።እንዲህ እያለች በልጆቹ ዙሪያ ትሩጥ። ልጆቹ በተመሳሳይ ይመልሱላት። ከልጆቹ መካከል ፈዘዝ ብለው ከምታያቸው ልጆች አንዳቸውን መርጣ በስተጀርባ መሃረቡን በጥንቃቄ ታስቀምጥ፤ ከዚያም እንደበፊቱ በልጆቹ ዙሪያ እያዜመች ትሩጥ። በዚህ ጊዜ ክብ የሠሩት ልጆች ፊታቸውን ወደኋላ ሳይመልሱ በእጃቸው መሀረቡን ይፈልጉ።

መሀረቡን ዳስሰው ካገኙት ፈጥነው በመነሳት አጫዋቿን ልጅ በመሀረቡ ይምቷት። ልጅቷ በሩጫ ፈጣን ከሆነች ሳትመታ ዙሩን ልታጠናቅቅና በልጁ ቦታ ልትቀመጥ ትችላለች። በዚህ መልኩ አጫዋቿ ሳትመታ ካጠናቀቀች መሀረቡን ይዞ የተከተላት ልጅ ስለተሸነፈ ከክቡ መሀል ገብቶ ይቀመጥ። ፈጥኖ በመድረስ አጫዋቿን በመሀረቡ ከመታት ግን የአጫዋችነቱን ተራ ራሱ ይያዝ። አጫዋች የነበረችውም ልጅ ስለተሸነፈች ከክቡ ውስጥ ትቀመጥ። ነገርግን መሀረቡ የተቀመጠበት ልጅ በንቃት ካልተከታተለ አጫዋቿ ክቡን ዞራ መጥታ በመሀረቡ ትምታው። በክቡ ውስጥ ከተቀመጡ ልጆች ጋር እንዲቀመጥም ታድርገው። በዚህ መንገድ ጨዋታው ይቀጥል። ከጨዋታ ውጪ ላለመሆንና መሀል ላለመቀመጥ በንቃት ተጫወቱ።

(ዘሪሁን። 1992። *የሥነጽሑፍ መሠረታውያን።* ገጽ 56 ማሻሻያ ተደርጎበት የተወሰደ)

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር 1

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት ትክክል ከሆኑ "እውነት" ስህተት ከሆኑ ደግሞ "ሐሰት" በማለት መልሳችሁን በምክንያት ግለጹ።

ሀ. በክቡ ውስጥ ገብተው የሚቀመጡት አሸናፊዎቹ ልጆች ናቸው።

ለ. ጨዋታውን የምታስጀምረው ልጅ መሀረቡን የምታስቀምጠው ፈዘዝ ብለው ከሚታዩት ልጆች በስተጀርባ ነው።

ሐ. በመሀረቤን ያያችሁ ጨዋታ ፈጣንና ንቁ ተጫዋቾች የማሸነፍ ዕድላቸው ሰፊ ነው።

መ. የልጆች ጨዋታ በአብዛኛው በአካል እንቅስቃሴ አይታጀብም።

ሠ. በጨዋታው መካከል ልጆቹ የአጨዋችነቱን ተራ የሚያገኙት አጨዋች

የነበሩትን ልጆች በመሀረቡ ሲመቱ ነው።

## ተግባር 2

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. ተረኛዋ ልጅ መሀረቧን በሽሚዝ ሥር ደብቃ የምትይዘው ለምንድን ነው?

ለ. በመሀረቤን ያያችሁ ጨዋታ ጊዜ ተጫዋቾች የሚሸነፉት ምን ሲሆኑ ነው?

ሐ. አጫዋቿ በምትዞርበት ጊዜ መሀረቡን የምታስቀምጠው እንዴት ነው?

መ. የተለያዩ የልጆች ጨዋታዎችን መጫወት ለልጆች የሚሰጠው ጥቅም ምንድን ነው?

ረ. ልጆች የተለያዩ ጨዋታዎችን ሲጫወቱ ምን ዓይነት ጥንቃቄዎችን ማድረግ ይጠበቅባቸዋል?

# 2ኛ ቀን

## ቃላት

### ቃላትንና ሐረጋትን መዘርዘር፣ የድርጊት ቅደምተከተል አያያዦችን መጠቀም

## ተግባር 1

የጨዋታ ዓይነቶችን የሚገልጹ ቃላትንና ሐረጋትን በደብተራችሁ ውስጥ ዘርዝራችሁ ጻፉ።




## ተግባር 2

የሚከተሉትን አያያዦች በመጠቀም ስለ"ሰኞ ማክሰኞ" የልጆች ጨዋታ አጨዋወት ሂደት በቅደምተከተል ጻፉ።

ሀ. በመጀመሪያ ሐ. በመቀጠል

ለ. ከዚያም መ. በመጨረሻ

## መጻፍ

### ድርሰት መጻፍ

### የድርጊት ቅደምተከተልን በቢጋር ሠንጠረዥ መግለጽ

**ተግባር**

"መሀረቤን ያያችሁ" የሚለውን ጨዋታ የድርጊት ቅደምተከተል በቢጋር ሠንጠረዥ ውስጥ ግለጹ።

ድርጊት 1 → ክብ ሠርቶ መቀመጥ

ድርጊት 2 →

ድርጊት 3 →

ድርጊት 4 →

ድርጊት 5 →

### የአጻጻፍ ሥርዓት

### ዓረፍተነገርን አዳምጦ መጻፍ

**ተግባር**

መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን ዓረፍተነገሮች አዳምጣችሁ በትክክል ጻፉ።

## 3ኛ ቀን

## አቀላጥፎ ማንበብ

### መሀረቤን ያያችሁ

## ቅድመንባብ

### ተግባር

"መሀረቤን ያያችሁ" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ በማስታወስ የአጨዋወት ሂደቱን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።

## ማንበብ

### ተግባር

"መሀረቤን ያያችሁ" የሚለውን ምንባብ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት በተሰጣችሁ ደቂቃ አቀላጥፋችሁ አንብቡ።

## ማዳመጥ

### ገበጣና ዲሞ እንጫወት



## ቅድመማዳመጥ

### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

### ተግባር

ምንባቡን ከማዳመጣችሁ በፊት በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ።

ሀ. በሥዕሉ ላይ የምታዩአቸው ልጆች ምን ዓይነት ጨዋታዎች የሚጫወቱ ይመስላችኋል?

ለ. ገበጣ ምን ዓይነት ጨዋታ ነው?

ሐ. ዲሞ ተጫውታችሁ ወይም ሲጫወቱ አይታችሁ ታውቃላችሁ? የአጨዋወቱን ሂደት ለመምህራችሁ ተናገሩ።

## የማዳመጥ ሂደት

### ተግባር

መምህራችሁ "ገበጣና ዲሞ እንጫወት" በሚል ርዕስ የተጻፈ ምንባብ ያነቡላችኋል። የጨዋታዎቹን ቅደምተከተል እየለያችሁ በትክክል አዳምጡ።

## አዳምጦ መረዳት

### ተግባር

ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት ለሚከተሉት ጥያቄዎች በቃላችሁ መልስ ስጡ።

ሀ. የገበጣ ጉድጓዶች ቁጥር ጎደሎ መሆን የሚችል ይመስላችኋል? ለምን?

ለ. የገበጣ ተጫዋቾች ጠጠራቸውን በባዶ ጉድጓድ ጥለው ከጨረሱ በኋላ ምን ያደርጋሉ?

ሐ. ተጨዋቾች ጠጠሮቹን ከጉድጓድ ወስደው የሚያስቀምጧቸው ስንት ጠጠሮች ሲሆኑ ነው?

መ. የገበጣ ተጫዋቾች ጠጠራቸውን የት ጉድጓድ ጥለው ሊጨርሱ እንደሚችሉ ቀድመው ማስላት የሚችሉ ይመስላችኋል? እንዴት?

ሠ. በ"ዲሞ" ጨዋታ ጊዜ ልጆች ከጨዋታ ውጪ የሚሆኑት በምን ምክንያት ነው?

ረ. በገበጣና በዲሞ ጨዋታ መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

ሰ. ገበጣና ዲሞ መጫወት ምን ጠቀሜታ ይሰጣል?

ሸ. ልጆች በዲሞ ጨዋታ ጊዜ ጨዋታውን በጥንቃቄ ካልተጫወቱ ምን ምን አካላዊ ጉዳቶች ይደርሱባቸዋል?

# ሰዋስው

## ቅጽልን መለየት

### ተግባር 1

በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ውስጥ በምሳሌው መሠረት ቅጽል የሆኑትን ቃላት ከሥር አስምሩባቸው።

ምሳሌ:-

1. <u>ክብ</u> ጨዋታ መጫወት እወዳለሁ።
2. ወጣቶች በበዓላት ጊዜ <u>አዳዲስ</u> ልብሶችን ይለብሳሉ።

ሀ. እናቴ ነጭ በግ ገዛች።

ለ. ለገበጣ ጨዋታ ትንንሽ ጠጠሮች ያስፈልጋሉ።

ሐ. ህይወት አጭር ብርድልብስ አነጠፈች።

መ. እነአበበ ሰፊ ሜዳ ላይ ይጫወታሉ።

ሠ. ነጩ ፈረስ ደንብሮ ገደል ገባ።

## ተግባር 2

የሚከተሉትን ቅጽሎች በመጠቀም አምስት ዓረፍተነገሮች ሥሩ።

ሀ. ሰማያዊ

ለ. ቀጭን

ሐ. ብልህ

መ. ደግ

ሠ. ሩህሩህ

## ማንበብ

### የጠወለገ ልጅነት ሲያብብ

### ቅድመንባብ

### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

#### ተግባር

ምንባቡን ከማንበባችሁ በፊት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. ሕፃናት ከአቅማቸው በላይ ለሆነ የሥራ ጫና የሚዳረጉት መቼ ነው?

ለ. የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ በምን በምን ይገለጻል?

ሐ. በምንባቡ ውስጥ በቀለም ተለይቶ የቀረበው ጽሑፍ መልዕክት ምን ይመስላችኋል?

### የማንበብ ሂደት

#### ተግባር

የሚከተለውን ተራኪ ምንባብ የድርጊቶችን ቅደምተከተል እየለያችሁ በለሆሳስ አንብቡ።

### የጠወለገ ልጅነት ሲያብብ

ለምለምና ዘላለም በጣም የሚዋደዱ እህትና ወንድም ናቸው። ከቤተሰቦቻቸው ተለይተው ወደአዲስአበባ የሄዱት ከስምንት ዓመታት በፊት ነበር። እስኮብልለው በወሰዷቸው ሰዎች ቤት ለአምስት ዓመታት ኖረዋል።

በቆይታቸው እጅግ አስከፊ የኑሮ ፈተና ገጥሟቸዋል። ለምለም በቤት ውስጥ ከአቅሟ በላይ የሆነ ከባድ ሥራ እንድትሠራ ትገደድ ነበር። አሰሪዎቿ ምግብቤት ስለነበራቸው ሌሊት እንጀራ ስትጋግር ታድራለች። እንቅልፍና ድካም ቢሰማትም ሲነጋ የጋገረችውን እንጀራ ተሸክማ ወደምግብቤቱ ታመላልሳለች። እንደጨረሰች ደግሞ መኖሪያቤቱን ታፀዳና ቁርስ ማዘጋጀት ትጀምራለች። የአሰሪዎቿን ልብስ በሳምንት ሦስት ቀን ታጥባለች። የምግብ ቤቱ ሠራተኞች ሥራ በበዛባቸው ቀናት የመመገቢያ ሳህኖችንና መጠጫ ብርጭቆዎችን ለማጠብ እጆቿ ውኃ ውስጥ ተዘፍዝፈው ይውላሉ። ከአሰሪዎቿ ጋር ወደገበያ በመሄድ እህል በጀርባዋ ተሸክማ ሽንኩርት የያዘ ዘንቢል በእጇ አንጠልጥላ ወደቤቷ ትመለሳለች። ይህን መሠል

ሥራ ካጠናቀቀች በኋላ የአሰሪዎቿን የሁለት ዓመት ሕፃን ታዝላለች። ሕፃኑን ባዘለች ጊዜ ስለሚከብዳት ትከሻዋን ይደነዝዛት ነበር። ሕፃኑ እንቅልፍ ወስዶት እንኳ ከጀርባዋ እንድታወርደው አይፈቀድላትም።

ለምለም ከዚህ ሁሉ ስቃይዋ ይበልጥ የሚያሳስባት ግን የወንድሟ እንግልት ነበር። ዘላለም የ11 ዓመት ሕፃን ቢሆንም ዘወትር በጧት ተነስቶ የአሰሪዎቹን መኪና ያጥባል። የመኖሪያቤቱን ቅጥር ግቢ ያፀዳል። ወደምግብቤት የሚላኩ ዕቃዎችን ከእህቱ ጋር ሆኖ ያመላልሳል። ወደሱቅ፣ ወደገበያና ወደምግብቤት ይላላካል። ቀኑን ሙሉ ሲላላክ ድካም ስለሚሰማው ማረፍ ይፈልጋል፤ ሆኖም አይፈቀድለትም። የምሽት እንቅልፍ እያንጎላጀው እንኳ አንዴ እጅ ሲያስታጥብ፣ ሌላ ጊዜ ሳህን ሲያጥብ ያመሻል። ለምለም ወንድሟ በዚህ ዓይነት ስቃይ ላይ ሆኖ ስታየው ታነባ ነበር። ወንድሟን ይዛ ወደቤተሰቦቻቸው ለመመለስ ብትመኝም የትውልድ ቦታቸው ሩቅ ስለነበር ሳይሳካላት ቀረ።

ያለዕድሜያቸው እንዲሠሩ የተደረጉት ሁለቱ ሕፃናት በኑሯቸው ደስተኛ አልነበሩም። ከአሰሪዎቻቸው ተገቢ ፍቅር አላገኙም። መሠረታዊ ፍላጎቶቻቸው አልተሟሉላቸውም። በሰዓቱ አልበሉም፤ በቂ ምግብም አልተሰጡም። የአሰሪዎቻቸው ልጆች ለብሰው የጣሏቸው አሮጌ ልብሶች አላስደሰቷቸውም፤ አልሞቋቸውም። ከእኩዮቻቸው ጋር መቦረቅ አልቻሉም፤ እረፍትም አላገኙም። በአጠቃላይ አምስት ዓመታትን በዚህ አስከፊ ሁኔታ አሳለፉ። በመጨረሻም ከአሰሪዎቻቸው ቤት ጠፍተው ወደጎዳና ወጡ።

ከወላጆቻቸው አስኮብልለው ያመጧቸው ሰዎች የፈፀሙባቸው የጉልበት ብዝበዛ ለበርካታ ችግሮች ዳርጓቸዋል። በአዕምሯዊና በአካላዊ ዕድገታቸው ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድሮባቸዋል። እንደዕድሜ እኩዮቻቸው ማሰብና ማመዛዘን እንዳይችሉ አድርጓቸዋል። ለከባድ የጀርባ ሕመም ዳርጓቸዋል። ራሳቸውን የመምራትና የማስተዳደር ኃላፊነትም እንዳይሸከሙ አድርጓቸዋል። ጥንካሬ አሳጥቷቸዋል። በለጋ ዕድሜያቸው ቤተሰባዊ ፍቅርም ሆነ ተገቢ ትምህርት ስላላገኙ ለሰው ልጆች ጥላቻ አድሮባቸዋል። ለተለያዩ ሱሶችም ተጋልጠዋል። በአጠቃላይ ተስፋ ቢስ ሆነው አፍላ የወጣትነት ጊዜያቸውን በጎዳና ላይ ሲያሳልፉ ቆይተዋል።

> **ከወላጆቻቸው አስኮብልለው ያመጧቸው ሰዎች የፈጸሙባቸው የጉልበት ብዝበዛ ለበርካታ ችግሮች ዳርጓቸዋል።**

አሁን ለምለም የ22፣ ዘላለም ደግሞ የ19ዓመት ወጣቶች ሆነዋል። በስነልቦና ባለሙያ ምክር ከነበሩበት የጎዳና ህይወት የተላቀቁት በቅርብ ነው። ከሌሎች ወጣቶች ጋር በጥቃቅንና አነስተኛ ማህበር ተደራጅተው እየሰሩ ጥሩ ገቢ ያገኛሉ። ጤንነታቸው ተስተካክሏል፤ ሱስና መጥፎ ባህርያትን ሁሉ አስወግደዋል። ትምህርታቸውንም

በአግባቡ እየተከታተሉ ነው።

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር 1

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. ለምለምና ዘላለም ወደአዲስ አበባ የሔዱት እንዴት ነው?

ለ. "በአዕምሯዊና በአካላዊ ዕድገታቸው ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ፈጥሮባቸዋል" ሲል ምን ማለቱ ነው?

ሐ. ለምለምና ዘላለም ለሰው ልጆች ጥላቻ ያደረባቸው በምን ምክንያት ነው?

መ. ለምለምና ዘላለም ለጎዳና ህይወት የተዳረጉት በምን ምክንያት ነው?

ሠ. ሕፃኑ እንቅልፍ ወስዶት ለምለም ከጀርባዋ እንድታወርደው የማይፈቀድላት ለምን ይመስላችኋል?

ረ. አሁን ለምለምና ዘላለም በምን ዓይነት ደረጃ ላይ ይገኛሉ?

ሰ. እናንተ ለምለምንና ዘላለምን ብትሆኑ ኖሮ ምን ታደርጉ ነበር?

ሸ. በርዕሱና በምንባቡ ሀሳብ መካከል ያለው ተዛምዶ ምንድን ነው?

### ተግባር 2

ቀጥሎ ከተዘረዘሩት ተግባራት መካከል በምንባቡ መሠረት የዘላለምና የለምለም የሆኑትን ለይታችሁ በሠንጠረዡ ውስጥ ጻፉ።

ሀ. እንጀራ መጋገር

ለ. ቤት ማጽዳት

ሐ. ወደሱቅና ወደገበያ መላላክ

መ. ቁርስ ማዘጋጀት

ሠ. ሳህኖችንና ብርጭቆዎችን ማጠብ

ረ. መኪና ማጠብ

ሰ. እጅ ማስታጠብ

ሸ. ልብስ ማጠብ

ቀ. እህልና ሸንኩርት መሸከም

በ. ዕቃ ወደምግብ ቤት መውሰድ

ተ. ሕፃን ልጅ ማዘል

ቸ. ቅጥር ግቢ ማጽዳት

| የለምለም ተግባራት | የዘላለም ተግባራት |
|---|---|
| • | • |
| • | • |
| • | • |
| • | • |

## ቃላት

### ለቃላት ዐውዳዊ ፍቺ መስጠት

#### ተግባር

በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ለተሠመረባቸው ቃላትና ሐረጋት ዐውዳዊ ፍቺ በጽሑፍ ስጡ።

ምሳሌ፡-

የምሽት እንቅልፍ እያንጎላጀው ብዙ ሥራ ይሠራል። የተሠመረበት ቃል ፍቺ እያንገላታው፣ እያስቸገረው ማለት ነው።

ሀ. እጅግ አስከፊ የኑሮ ፈተና ገጥሟቸዋል።

ለ. ከቤተሰቦቻቸው ቤት አስኮብልለው ወደአዲስአበባ ወሰዷቸው።

ሐ. ወንድሟን ይዛ ወደቤተሰቦቻቸው ለመመለስ ብትመኝም ሳይሳካላት ቀረ።

መ. በለጋ ዕድሜያቸው የጉልበት ብዝበዛ ተፈጽሞባቸዋል።

ሠ. አፍላ የወጣትነት ጊዜያቸውን በጎዳና ላይ አሳለፉ።

ረ. ከእኩዮቻቸው ጋር መቦረቅ አልቻሉም።

ሰ. ለምለምና ዘላለም ተስፋቢስ ሆነው አልቀሩም።

ሸ. የሥነልቦና ባለሙያ ምክር ተቀብለዋል።

ቀ. ከነበሩበት የጎዳና ህይወት ተላቀቁ።

በ. ይበልጥ ያሳሰባት የወንድሟ እንግልት ነበር።

## መጻፍ

### ድርሰት መጻፍ

### የድርጊት ቅደምተከተሎችን አስተካክሎ መጻፍ

#### ተግባር1

የሚከተሉት ድርጊቶች ቅደምተከተላቸው የተፋለሰ ነው። በታሪኩ የድርጊት ቅደምተከተል መሠረት አስተካክላችሁ ጻፏቸው።

ሀ. ለምለምና ዘላለም ከቤተሰቦቻቸው ቤት ኮበለሉ።

ለ. ካስኮበለሏቸው ሰዎች መኖሪያቤት ጠፉ።

ሐ. የሥነልቦና ባለሙያ ምክር አገኙ።

መ. ከባድ የሥራ ሸክም ተጫነባቸው።

ሠ. ጥሩ ገቢ እያገኙ ትምህርታቸውን መከታተል ጀመሩ።

ረ. የሥነ ልቦናና የአካል ጉዳት ደረሰባቸው ።

ሰ. ከሌሎች ወጣቶች ጋር በጥቃቅንና አነስተኛ ማህበር ተደራጁ።

ሸ. ለጎዳና ህይወት ተዳረጉ።

ቀ. ከሰዎች ጋር ወደአዲስ አበባ ሔዱ።

### ተግባር 2

የሕፃናት መብቶችና ግዴታዎች ምን ምን እንደሆኑ ከሥነዜጋና ሥነምግባር መምህራችሁ በመጠየቅ ወይም መጽሐፍ በማንበብ አንድ አንቀጽ ከጻፋችሁ በኋላ በክፍል ውስጥ አንብቡ።

## የአጻጻፍ ሥርዓት

### የተጓደሉ ፊደላትን ማሟላት

### ተግባር

በተሰመረባቸው ቃላት ውስጥ የተጓደሉ ፊደላትን በማሟላት ወይም የቃላትን ቅርፅ በማስተካከል አንቀጹን በደብተራችሁ ጽፋችሁ በክፍል ውስጥ አንብቡ።

<u>ወላጆች</u> መጣላት <u>ቤተሰብ</u> መፍረስ ምክንያት ይሆናል። የቤተሰብ መፍረስ ደግሞ ልጆች እንደ<u>በተኑና ጎዳና</u> ህይወት እንደ<u>መሩ</u> ያደርጋል። እንዲሁም ተስፋ <u>ሚቆርጡ</u> <u>ውሸት፣</u> ለሥርቆት፣ ለሱስና ለሌሎች መጥፎ ሥነምግባሮች ይጋለጣሉ። ይህ ደግሞ <u>አንድ</u> ሀገር ዕድገት ትልቅ እንቅፋት ይፈጥራል።

6ኛ ቀን

# አቀላጥፎ ማንበብ

## የጠወለገ ልጅነት ሲያብብ

### ቅደመንባብ

### ተግባር

"የጠወለገ ልጅነት ሲያብብ" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ከማንበባችሁ በፊት በሬዲዮና በቴሌቪዥን በሚተላለፉ ዜናዎች የአነባበብ ስልት ላይ ተወያዩ።

## ማንበብ

### ተግባር

“የጠወለገ ልጅነት ሲያብብ” የሚለውን ምንባብ የጋዜጠኞችን አነባበብ በማስመሰል በፍጥነት አንብቡ።

## መናገር

### የድርጊት ቅደምተከተልን ጠብቆ ንግግር ማድረግ

### ተግባር

ከገበጣ፣ ከዳሞና ከመሀረቤን ያያችሁ ጨዋታዎች ውጪ የምታውቁትን የጨዋታ ዓይነት መርጣችሁ የጨዋታውን የአጨዋወት ቅደምተከተል በክፍል ውስጥ በንግግር ግለጹ።

## ሰዋስው

### መጣኝና ደረጃ አመልካች መስተኣምርን መለየት

### ተግባር

በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ውስጥ መስተኣምር የሆኑትን ቃላት ከሥራቸው አስምሩ፤ መጣኝና ደረጃ አመልካች መሆናቸውንም ግለጹ።

ሀ. ዘገየ አንድ ጥቁር ኮት ገዛ።

ለ. እኔ ለቤተሰቦቼ ሦስተኛ ልጅ ነኝ።

ሐ. ዘምዘም ሁለት ዶሮዎች ሸጠች ።

መ. ተማሪዎቹ ወደሰባተኛ ክፍል ተዛወሩ።

ሠ. አንዲት ልጅ ወደቤቷ ስትሮጥ አየሁ።

ረ. ሁለቱ ሕፃናት በኑሯቸው ደስተኛ አይደሉም።

ሰ. ሄና ከክፍሏ ተማሪዎች አንደኛ ወጣች።

## የቃላት ጥናት

### ማጣመርና መነጠል

**ተግባር**

የሚከተሉትን ከምንባቡ የወጡ ቃላት/ሐረግ በመነጠልና በማጣመር አንብቡ።

| | ነጣጥሎ ማንበብ | አጣምሮ ማንበብ |
|---|---|---|
| ሀ | አል-ተፈጸመ-ኡ-ብ-ኣት-ም | አልተፈጸሙባትም፡ |
| ለ | አል-ተገረዘ-ች-ም | አልተገረዘችም |
| ሐ | አል-ተፈለፈለ-ም | አልተፈለፈለም |
| መ | አል-ተመለከተ-ች-ም | አልተመለከተችም |
| ሠ | አል-ሰማ-ች-ም | አልሰማችም |
| ረ | አል-ታዘለ-ች-ም | አልታዘለችም |
| ሰ | አል-ገጠመ-ኣት-ም | አልገጠማትም |
| ሸ | ማበረታቻ-ዎች-ን | ማበረታቻዎችን |
| ቀ | የሚያስፈልግ-ኣት-ን | የሚያስፈልጓትን |

## ማንበብ

### በአግባቡ የታነፀ ልጅነት

### ቅድመንባብ

### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

**ተግባር**

የሚከተሉትን ጥያቄዎች የቀደመ ዕውቀታችሁን በመጠቀም በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. በሥዕሉ ላይ የምትታየው ልጅ ወዴት የምትሄድ ይመስላችኋል? እንዴት አወቃችሁ?

ለ. ሕፃናት በእንክብካቤ ለማደግ ምን ምን ነገሮች ያስፈልጓቸዋል?

ሐ. መምህሮቻችሁ በትምህርታችሁ እንድትጎብዙ ምን ዓይነት ድጋፍ ያደርጉላችኋል?

## የማንበብ ሂደት

### ተግባር

“በአግባቡ የታነፀ ልጅነት” በሚል ርዕስ የቀረበውን ተራኪ ምንባብ ጥንድ ጥንድ በመሆን ዋናና መዘርዝር ሀሳቦችን እየለያችሁ ድምፅ በማሰማት አንብቡ።

## በአግባቡ የታነፀ ልጅነት




አቶ ንጋቱና ወይዘሮ ሸዋነሽ ባልና ሚስት ናቸው። የሚተዳደሩትም በንግድ ሥራ ነው። ህይወት የምትባል ሴት ልጅ አለቻቸው። ህይወት 12 ዓመቷ ሲሆን የስድስተኛ ክፍል ተማሪ ናት።

ህይወት ለሁለት ዓመታት የእናቷን ጡት ጠብታለች። ከስድስት ወሯ ጀምሮ የተመጣጠነ ምግብ አግኝታለች። ሁሉንም የሕፃናት ክትባቶች በትክክለኛ ጊዜያቸው ተከትባለች። ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች አልተፈጸሙባትም። አልተገረዘችም፤ እንጥሏ አልተቆረጠም፤ ግጓም አልተፈለፈለም፤ አካላዊ ቅጣት አልተፈፀመባትም። በአጠቃላይ ጤንነቷንና መንፈሷን የሚያውክ ነገር እንዳይገጥማት ወላጆቿ ይንከባከቧታል። በመሆኑም ህይወት በሙሉ ጤንነት ላይ ትገኛለች።

ህይወት በራሷ የምትተማመንና ደስተኛ ልጅ ናት። ለዚህም የቤተሰቦቿ አስተዋጽኦ

ከፍተኛ ነው። ወላጆቿ በጣም ይወዷታል፤ ተገቢ ፍቅርም ይሰጧታል። በቤተሰባዊ ጉዳዮች ላይ በሚደረጉ ውይይቶች ሀሳብ ታቀርባለች። ወላጆቿ ሀሳቧን ያከብሩላታል። በየዕለቱ በቂ የመዝናኛ ሰዓት መድባ ከዕድሜ አቻዎቿ ጋር ትዝናናለች፤ ትጫወታለች። እቅድ አውጥታ ታጠናለች። ወላጆቿም ሁሌም ደስተኛ እንድትሆን የቻሉትን ሁሉ ያደርጉላታል። ዓላማ ያላትና ስኬታማ ልጅ እንድትሆንም ይመክሯታል።

ህይወት በወላጆቿና በመምህሮቿ ክትትልና ድጋፍ ስለሚደረግላት ጎበዝ ተማሪ ሆናለች። ከአራት ዓመቷ ጀምራ ቅድመመደበኛ ትምህርት ተከታትላለች። ወላጆቿም በቤት ውስጥ ማንበብና ማስላት አስተምረዋታል። ልዩ ልዩ ተረቶችን ይነግሯታል፤ መልሳ እንድትነግራቸውም ያደፋፍሯታል። መደበኛ ትምህርቷን ስትጀምር ጥሩ መሠረት ስለነበራት ከፍተኛ ውጤት ማስመዘገብ ጀመረች። በየክፍል ደረጃው ሁሉ አንደኛ እየሆነች ከሽልማት ጋር ከክፍል ወደክፍል ትዛወራለች። ወላጆቿም በጥረቷና በስኬቷ ስለተደሰቱ የተለያዩ ማበረታቻዎችን ይሰጧት ነበር። ለየክፍል ደረጃው የቀረበውን ትምህርት በሚገባ እንድትገነዘብ ዕቅድ አውጥተው ያስጠኗታል። የተሰጡትን የቤት ሥራዎች መስራቷንም በየዕለቱ ይከታተላሉ። የሚያስፈልጓትን የጽሕፈት መሳሪያዎች በየጊዜው ያሟሉላታል። ይህም በትምህርቷ ደስተኛ አድርጓታል። በደስታ መማሯ ደግሞ ለከፍተኛ ውጤት አብቅቷታል። መምህሮቿም ቢሆኑ ህይወት ያስቸገራትን ጉዳይ እንድትጠይቅና ስትጠየቅም ምላሽ እንድትሰጥ ያበረታቷታል። በትርፍ ጊዜያቸውም ከሌሎች ሕፃናት ጋር የማጠናከሪያ ትምህርት ይሰጧታል። በክፍል ውስጥም ንግግር ስታቀርብ እንዳታፍር ያደፋፍሯታል። በመሆኑም  በክፍል ጓደኞቿ ፊት ብዙ ተረቶችን አቅርባለች። በአጠቃላይ ለህይወት ጉብዝና የመምህሮቿና የወላጆቿ ሚና ከፍተኛ ነበር።

ወላጆቿ ርስበርስ ሲወያዩ እንጅ ሲጨቃጨቁ አይታ አታውቅም። ለየትኛውም ዓይነት ሱስ ተገዢ ሲሆኑ አልተመለከተችም። ሲጋራ ሲያጨሱም ሆነ ጠጥተው ሲሰክሩ አላየችም። ሲዋሹ አልሰማችም። ለሰዎች በጎ ሲያስቡ እንጂ ክፉ ሲመኙ አልታዘበችም። መምህሮቿም ለህይወት መልካም አርዓያ ሆነዋታል። ጥሩ ሥነምግባር እንዳላቸው ተረድታለች። ሙያቸውንና ተማሪዎቻቸውን እንደሚወዱ ተገንዝባለች። በትምህርትቤት ውስጥ እንደአንድ ቤተሰብ እንደሚተሳሰቡና እንደሚዋደዱ አውቃለች። ስለሆነም እንደመምህሮቿ ጥሩ ሥነምግባር እንዲኖራት ትመኝ ነበር። የሰፈሯ ሰዎች በችግርም ሆነ በደስታ እንደሚተባበሩ አይታለች። ስለልጆቻቸው አስተዳደግ በጋራ ሲመክሩ ሰምታለች። ለልጆቻቸው ጥሩ አርዓያ ለመሆን እንደተስማሙም አውቃለች። ራሳቸውን ከመጥፎ ባህርይ እንደሚጠብቁም ስለተረዳች የእነሱን መንገድ ለመከተል ችላለች። በትምህርትቤትም ሆነ በመኖሪያ አካባቢዋ ያሉት መልካም ነገሮች ሁሉ ህይወትን በስነምግባሯ ተወዳጅና በትምህርቷ ስኬታማ እንድትሆን አድርገዋታል።

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር 1

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ምን ምን ናቸው?

ለ. ህይወት ከክፍል ክፍል የምትዛወረው ስንተኛ ደረጃ በመውጣት ነው?

ሐ. ህይወት በትምህርቷ ደስተኛ የሆነችው ለምንድን ነው?

መ. ለሕፃናት ተረት መንገር ምን ጥቅም ይሰጣል?

ሠ. የህይወት የዕለትተዕለት ዕቅዶች ምን ምን ናቸው?

ረ. ህይወት ከመምህሮቿ የተማረቻቸው ጥሩ ሥነምግባሮች ምን ምን ናቸው?

ሰ. እናንተስ እንደህይወት በዕቅድ ትመራላችሁ? በዕቅድ የምትመሩ ከሆነ የየዕለት ዕቅዶቻችሁን ለመምህራችሁ ተናገሩ።

ሸ. ከዚህ ምንባብ ምን ምን ተረዳችሁ?

### ተግባር 2

በምንባቡ መሠረት በአግባቡ ለታነፀ ልጅነት የመምህራን፣ የወላጆችና የማህበረሰቡ ድርሻ ምንድን ነው? ዘርዝራችሁ ግለጹ።



## 8ኛ ቀን

## ቃላት

### ጥቅል መግለጫዎችን ከዝርዝር ቃላት ጋር ማዛመድ

### ተግባር

የሚከተሉትን ጥቅል መግለጫዎች በሠንጠረዡ ውስጥ ያሉትን ፊደላት በተለያየ አቅጣጫ በማንበብ ተመሳሳይ ፍቺ ከሚሰጡ ቃላት ጋር አዛምዱ።

ምሳሌ፡- ጥሩ ደረጃ ላይ መድረስ = ስኬት

ሀ. የጽሕፈት መሳሪያ

ለ. መጥፎ ሥነምግባር

ሐ. እናት ወይም አባት

መ. ለሕፃናት የሚነገር የሥነቃል ዓይነት

ሠ. አርዓያ መሆን

ረ. ወደአንድ ግብ ለመድረስ የተያዘ ዕቅድ

ሰ. የሥራ ድርሻ ወይም አስተዋጽዖ

ሸ. ሳንባን የሚጎዳና ለሱስ የሚያጋልጥ

ቀ. በሴት ልጅ ላይ የሚደርስ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊት

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ዳ | ና | | ዷ | መ | |
| | | ብ | ገ | ወ | ዓ |
| | ተ | ረ | ት | ላ | |
| ር | ዝ | ም | ማ | ጅ | ሚ |
| ሲ | | | ሳ | | ና |
| ጋ | | ሱ | | ሌ | ሜ |
| ራ | | | ስ | ኬ | ት |

## መጻፍ

### ድርሰት መጻፍ

### አሳጥሮ መጻፍ

ማስታወሻ

አንድን ጽሑፍ አሳጥሮ ለመጻፍ የሚከተሉትን ነጥቦች ተግባራዊ አድርጉ።

- ጽሑፉን ደጋግሞ ማንበብ
- የጽሑፉን ዋና ሀሳብ መረዳት
- ዋናና ዝርዝር ነጥቦችን መለየት

- የጸሐፊውን/ዋን ሀሳብ አለመልቀቅ
- የተደጋገሙ ሀሳቦችን ማስወገድ
- የሀሳቡን ቅደምተከተል መጠበቅ

## ተግባር

"በአግባቡ የታነፀ ልጅነት" በሚል ርዕስ ከቀረበው ምንባብ ውስጥ አራተኛውን አንቀጽ በስድስት ዓረፍተነገሮች አሳጥራችሁ ጻፉ።

## የአጻጻፍ ሥርዓት

## ሥርዓተነጥቦችን መጠቀም

ማስታወሻ

- ትእምርተአንክሮ (!)፡- ማጋነንን፣ መገረምን፣ መደንገጥን፣ መደነቅን፣ ቁጭትን፣ መደሰትን፣ ማዘንን የመሳሰሉትን ውስጣዊ ስሜቶች ለማመልከት የሚያገለግል የሥርዓተነጥብ ዓይነት ነው።

ምሳሌ፡-

ሀ. ወይኔ አምባቸው! (ቁጭትን ወይም ንዴትን ለመግለጽ)

ለ. እሰይ! ወንድሜ መጣ! (መደሰትን ለመግለጽ)

- እዝባር (/)፡- አሕጽሮተቃላት ለመመስረት ይረዳል። አሕጽሮተቃላት ለመመስረት እንደአንድ ነጥብ (ይዘት) ሆኖ ያገለግላል።

ምሳሌ፡-

ትምህርትቤት - ት/ቤት ወይም ት.ቤት

ቀን፣ ወርንና ዓመተምሕረትን ለመለየት፡- እዝባር በቁጥር የሚገለጽን የጊዜ አቆጣጠር ያለምንም ማብራሪያ በቅደምተከተል ለይቶ ለማመልከት ይረዳል።

ምሳሌ፡-

29/12/2006 ዓ.ም.

የመስሪያቤት ደብዳቤዎችን የፕሮቶኮል መዝገብ ቁጥር ለያይቶ ለማመልከት

ምሳሌ፡-

ቁጥር 1/3055/203/83

### ተግባር 1

ትእምርተአንክሮን በመጠቀም በሚከተሉት ቃላት ዓረፍተነገር ሥሩ።

ሀ. እኮ ለ. ውይ ሐ. አቤት መ. እንዴ ሠ. ጉድ

### ተግባር 2

የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት በእዝባር ወይም በይዘት አሳጥራችሁ ጻፏቸው።

ሀ. የ2ኛ ደረጃ ትምህርትቤት

ለ. የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ

ሐ. ፍርድቤት

መ. መስሪያቤት

ሠ. አማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

### ተግባር 3

መጽሐፍ በማንበብ ወይም ሰው በመጠየቅ በአሕጽሮት የተጻፉ ቃላትን ወይም ሐረጋትን ጽፋችሁ በክፍል ውስጥ አንብቡ።

## 9ኛ ቀን

## አቀላጥፎ ማንበብ

### በአግባቡ የታነፀ ልጅነት

### ቅድመንባብ

#### ተግባር

"በአግባቡ የታነፀ ልጅነት" የሚለውን ምንባብ ሀሳብ አስታውሳችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ግለጹ።

### ማንበብ

#### ተግባር

"በአግባቡ የታነፀ ልጅነት" የሚለውን ምንባብ ጥንድ ጥንድ በመሆን አንዳችሁ አንባቢ አንዳችሁ አድማጭ እየሆናችሁ አንድ አንድ አንቀጽ በትክክል አንብቡ።

## መናገር

### ውይይት ማካሄድ

#### ተግባር

በትምህርትቤታችሁ ካሉ ክበቦች አንዱን በመምረጥ ስለሥራ እንቅስቃሴው በቡድን

ተወያይታችሁ በክፍል ውስጥ ተናገሩ።

## ሰዋስው

### ቅጽልንና መስተኣምርን መለየት

#### ተግባር

የሚከተሉትን ቃላት ቅጽል ወይም መስተኣምር በማለት በሠንጠረዡ ውስጥ ለይታችሁ አመልክቱ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሀ. ደካማ | መ. ሩህሩህ | ሰ. አንዷት | በ. ታታሪ |
| ለ. ጥቁር | ሠ. ሰፊ | ሸ. አጭር | ተ. አንደኛ |
| ሐ. ሁለት | ረ. ጨካኝ | ቀ. አራት | ቸ. ሰባተኛ |

| ቅጽል | መስተኣምር |
|---|---|
| | |
| | |
| | |

#### ተግባር 2

ቅጽል የያዙ ሦስት ዓረፍተነገሮች ጻፉ።

#### ተግባር 3

ሦስት መጣኝና ሦስት ደረጃ አመልካች መስተዓምሮችን የያዙ ዓረፍተነገሮች ጻፉ።



# ቱሪዝም

ምዕራፍ 5

## አካባቢያዊ የቱሪስት መስህቦች

1ኛ ሳምንት 1ኛ ቀን

## የቃላት ጥናት

### መነጠልና ማጣመር

#### ተግባር

የሚከተሉትን ውስብስብ ቃላትና ሐረጋት በመነጠልና በማጣመር አንብቡ።

| | ነጣጥሎ ማንበብ | አጣምሮ ማንበብ |
|---|---|---|
| ሀ | ሎጂ-ዎች-ም | ሎጂዎችም |
| ለ | ተመሳስሎ-ዎች | ተመሳስሎዎች |
| ሐ | የሚ-መሳሰሉ-ብ-አቸው | የሚመሳሰሉባቸው |
| መ | መልክዐ-ምድር-አዊ | መልክዐምድራዊ |
| ሠ | መዳረሻ-ነት-አቸው-ን | መዳረሻነታቸውን |
| ረ | መስህብ-ኦች-አቸው | መስህቦቻቸው |
| ሰ | ጥንት-አዊ-ነት-አቸው | ጥንታዊነታቸው |

## ማንበብ

### ሎጎና ጥርባ ሀይቆች

#### ቅድመንባብ

#### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

#### ተግባር

የሚከተሉትን የቅድመንባብ ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. የምታውቋቸውን የቱሪስት መስህቦች ተናገሩ።

ለ. የቱሪስት መስህብ ጥቅሞችን ግለጹ።

ሐ. ከምንባቡ ርዕስ ሥር በሚገኙት ሁለት ሀይቆች መካከል ያለው ልዩነት ምን ይመስላችኋል?

## የማንበብ ሂደት

### ተግባር

"ሎጎና ጥርባ ሀይቆች" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ እያወዳደራችሁና እያነጻጸራችሁ በለሆሳስ አንብቡ።

## ሎጎና ጥርባ ሀይቆች



ሎጎ ሀይቅ



ጥርባ ሀይቅ

በኢትዮጵያ ውስጥ ብዙ ሀይቆች ይገኛሉ። ከእነዚህም መካከል ሎጎና ጥርባ ተጠቃሾች ናቸው። በሁለቱ ሀይቆች መካከል ተመሳሳይነቶችና ልዩነቶች አሉ። ለዚህም ተፈጥሯዊና ሰውሠራሽ ምክንያቶችን ማንሳት ይቻላል።

ሎጎና ጥርባ ሀይቆች የሚመሳሰሉባቸው ባህርያት አሏቸው። ሁለቱም ሀይቆች በአማራ ክልል ውስጥ ይገኛሉ። በሀይቆቹ ላይ የተለያየ ዝርያ ያላቸው አዕዋፍ

ይገኛሉ። ሀይቆቹና በዙሪያቸው ያለው መልክዐምድራዊ አቀማመጥ ማራኪነት አላቸው። በተጨማሪም በሁለቱም ሀይቆች ዙሪያ ደኖች፣ የዱር እንስሳት፣ አብያተክርስቲያናትና ጥንታዊ ቅርሶች ይገኛሉ። ሁለቱም ሀይቆች ተፈጥሯዊ እንጂ ሰውሠራሽ አይደሉም። የቱሪስት መዳረሻነታቸውን ለማጠናከር በሁለቱም ሀይቆች ዙሪያ ምቹ ሁኔታዎች አሉ፤ ሀይቆቹ ለዋና የመኪና መንገድ ቅርብ ስለሆኑ በቀላሉ መድረስ ይቻላል።

በሌላም በኩል በሎጎና በጥርባ ሀይቆች መካከል ብዙ ልዩነቶችን መጥቀስ ይቻላል። የመገኛ ቦታቸው መለያየትና መራራቅ አንዱ የልዩነታቸው መነሻ ነው። የጥርባ ሀይቅ በአብክመ በአዊ ብሄረሰብ ዞን በአንከሻ ጓጉሳ ወረዳ ውስጥ ይገኛል። ሀይቁ ከአገው ግምጃቤት ማርያም ስድስት ኪሎሜትር ርቀት ላይ ይገኛል። የሀይቁ ጥልቀት 155 ሜትር ይደርሳል። መጠኑ አነስተኛ ስለሆነ በውስጡ ደሴት የለውም። በአቅራቢያው ከሃያ ያላነሱ አስገራሚ የተፈጥሮ ዋሻዎች ይገኛሉ። የሀይቁ ውኃ ሲታይ አረንጓዴ መልክ አለው። የሎጎ ሀይቅ ግን በደቡብ ወሎ ዞን በሀይቅ ከተማ አቅራቢያ ይገኛል። ከከተማዋ ሦስት ኪሎ ሜትር ያህል ርቆ ይታያል። የሀይቁ ጥልቀት 23 ሜትር ይደርሳል። መጠኑም ቢሆን ሰፊ ነው። ሀይቁ በሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ ትልቅ ደሴት ነበረው። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ውኃው እየሸሸ በመሄዱ ደሴቱ በአንድ በኩል ከየብሱ ጋር የተገናኘ ወሽመጥ ፈጥሯል። በሀይቁ ውስጥ ቀረሶ፣ አምባዛና ዱቤ የተሰኙ ሦስት የአሳ ዝርያዎች ይገኛሉ። የሀይቁ መልክ ከተለመደው የውኃ መልክ የተለየ አይደለም።

ተፈጥሯዊ ከሆኑት ልዩነቶች በተጨማሪ ሰውሠራሽ ልዩነቶችም አሏቸው። በሎጎ ሀይቅ ደሴት ላይ የሀይቅ እስጢፋኖስ ገዳም ይገኛል። በገዳሙ ውስጥ የሚኖሩ መነኮሳትም አትክልትና ፍራፍሬ በማልማት ይተዳደራሉ። በተጨማሪም ከብት ያደልባሉ፤ ዶሮ ያረባሉ፤ የእጅ ሥራ ማዕከሎችም አሏቸው። ወደገዳሙ የሚመጡ እንግዶችን በትንንሽ ጀልባዎች በማመላለስም አገልግሎት ይሰጣሉ። እንግዶችን በሞተር ጀልባ የማመላለሱን ሥራ የአካባቢው ኗሪዎችም ያከናውኑታል። ሀይቁ በበርካታ የአገር ውስጥና የውጪ ቱሪስቶች ይጎበኛል። በሀይቁ ዙሪያ ሁለት ሎጂዎችም ተሰርተዋል። “ሀይቅ ሎጂ”ና “እሪኩም ሎጂ” ይባላሉ። የጥርባ ሀይቅ ግን የማስተዋወቅ ሥራ በስፋት የተሠራለት አይመስልም፤ በመሆኑም በበርካታ ቱሪስቶች እየተጎበኘ አይደለም። በሀይቁ ውስጥ አገልግሎት የሚሰጡ ተመላላሽ የሞተር ጀልባዎችም በብዛት አይገኙበትም። ለእንግዶች ማረፊያና መዝናኛ የሚያገለግሉ ሎጂዎችም አልተሰሩለትም። በአጠቃላይ ሁለቱ ሀይቆች ተመሳስሎ እንዳላቸው ሁሉ ልዩነታቸውም የጎላ ነው።

(አብክመ ባቱማ ቢሮ። 1991። *የአማራ ክልል የቱሪስት መስህብ ሀብቶች።* ገጽ 31-38፤ 57-58።መጠነኛ ለውጥ ተደርጎ የተወሰደ።)

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. የጥርባ ሀይቅ የቱሪስት መዳረሻ እንዲሆን ምን ምን ቅድመሁኔታዎች ሊሟሉ ይገባል?

ለ. የሎጎና የጥርባ ሀይቆችን ሰውሠራሽና ተፈጥሯዊ ልዩነቶች በዝርዝር ጻፉ።

ሐ. ሁለቱ ሀይቆች በምን በምን ይመሳሰላሉ?

መ. የሎጎ ሀይቅ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየሸሸ የሔደው ለምን ይመስላችኋል?

## 2ኛ ቀን

## ቃላት

### ቃላትን በማቃረን ማዛመድ

### ተግባር

በ"ሀ" ረድፍ ለተዘረዘሩ ቃላት ተቃራኒያቸውን ከ"ለ" ረድፍ በመምረጥ አዛምዱ።

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 1. የብስ | ሀ. አስቀያሚ |
| 2. ከተማ | ለ. ቅርበት |
| 3. ማራኪ | ሐ. ተመሳሳይነት |
| 4. ልዩነት | መ. ሰውሠራሽ |
| 5. እንግዳ | ሠ. ቤተኛ |
| 6. ጥንታዊ | ረ. ዘመናዊ |
| 7. ተፈጥሯዊ | ሰ. ውኃማ አካል |
| 8. ጥልቀት | ሸ. ገጠር |

## መጻፍ

### ድርሰት መጻፍ

### በማወዳደርና በማነጻጸር ስልት ድርሰት መጻፍ

#### ተግባር

የሚከተሉትን ሀሳቦች በመጠቀም “ሁለቱ ፏፏቴዎች” በሚል ርዕስ በማወዳደርና በማነጻጸር ስልት ባለሦስት አንቀጽ ድርሰት ጻፉ።

| ትስኪ ፏፏቴ | ጢስ አባይ ፏፏቴ |
|---|---|
| ✓ በአማራ ክልል በአዊ ዞን ይገኛል<br>✓ ከአዊሲና ከግዛኒ ወንዞች የተፈጠረ | ✓ በአማራ ክልል ባህር ዳር ዙሪያ ይገኛል።<br>✓ ርዝመት ከ40-50 ሜትር |
| ✓ ርዝመት 180 ሜትር<br>✓ በተፈጥሮ ደን ያጌጠ<br>✓ ሰስ፣ የምኒልክ ድኩላ፣ ጥቁር ጦጣ፣ ጉሬዛ፣ ዝንጀሮ፣ ጥርኝ፣ ቀይቀበሮ የሚገኙበት<br>✓ ከ75 ሜጋዋት ያላነሰ የኃይድሮ ኤሌክትሪክ ኃይል ሊያመነጭ የሚችል | ✓ የፏፏቴው የውኃ ፍንጣሪ አካባቢውን በጉም የሚሸፍንና መግነጢሳዊ ኃይል ያለው፣<br>✓ ነጎድጎዳማ ድምፅ ያለው<br>✓ በአካባቢው ጥንታዊ እንደሆነ የሚነገርለት የአለታ ድልድይ የሚገኝበት<br>✓ የቀስተዳመና መኖር |

### የአጻጻፍ ሥርዓት

### ሥርዓተነጥቦችን መጠቀም

#### ተግባር 1

የሚከተሉትን ዓረፍተነገሮች ሥርዓተነጥቦችን በተገቢ ቦታ በማስገባት እንደገና ጻፏቸው።

ሀ. የአማራ ክልል በማዕድን ውኃ በኖራ ድንጋይ  በድንጋይ ከሰልና በጨው በመሳሰሉት የከበረ ነው

ለ. በሎጎ ሀይቅ እስጢፋኖስ ገዳም መነኮሳቱ አትክልትና ፍራፍሬ ያለማሉ ከብት ያደልባሉ ዶሮ ያረባሉ

ሐ. የሀይቅ ውኃ ለምን አረንጓዴ መልክ ይኖረዋል

መ. የፏፏቴው ነጎድጓዳማ ድምፅ የተነደፈ ጥጥ የመሰለው ጉም አቤት እንዴት ልብን ይሰርቃል

### ተግባር 2

የሚከተሉትን ሐረጎች በአሕጽሮተቃል ጻፉ።

ሀ. አማራ ብዙኃን መገናኛ ድርጅት

ለ. የአማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም

ሐ. የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር

መ. የተባበሩት መንግስታት ድርጅት

ሠ. የትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት

## 3ኛ ቀን

## አቀላጥፎ ማንበብ

### ሎጎና ጥርባ ሀይቆች

### ቅድመንባብ

### ተግባር

"ሎጎና ጥርባ ሀይቆች" በሚል ርዕስ ያነበባችሁትን ምንባብ አስታውሳችሁ የሁለቱን ሀይቆች ልዩነት ግለጹ።

### ማንበብ

### ተግባር

"ሎጎና ጥርባ ሀይቆች" በሚል ርዕስ ከቀረበው ምንባብ ውስጥ ሦስተኛውንና አራተኛውን አንቀጽ በአንድ ደቂቃ ውስጥ በጥንድ በጥንድ በመሆን በየተራ በፍጥነት አንብቡ። በምታነቡበት ጊዜ የፊደላት ግድፈት፣ የቃላት መደጋገም፣ የመዘግየት የመሳሰሉትን ሁኔታዎች ማስወገድ ይኖርባችኋል።

## ማዳመጥ

### ጋምቤላና ነጭ ሳር ብሔራዊ ፓርኮች

### 6ሀ. ቅድመማዳመጥ

### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

### ተግባር

በሚከተሉት የቅድመንባብ ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ።

ሀ. የምታውቁትን ፓርክ በመጥቀስ የት እንደሚገኝ ለጓደኞቻችሁ ግለጹ።

ለ. ፓርክ ማለት ምን ማለት ነው? በውስጡስ ምን ምን ነገሮችን ይይዛል?

## የማዳመጥ ሂደት

### ተግባር

"ጋምቤላና ነጭ ሳር ፓርኮች" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ መምህራችሁ ሲያነቡላችሁ የጋምቤላና የነጭ ሳር ብሔራዊ ፓርኮችን እያወዳደራችሁና እያነጻጸራችሁ በትኩረት አዳምጡ።

## አዳምጦ መረዳት

### ተግባር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. ከጋምቤላና ከነጭ ሳር ብሔራዊ ፓርኮች ለአዲስ አበባ ቅርብ የሆነው የትኛው ነው?

ለ. ከጋምቤላና ከነጭ ሳር ብሔራዊ ፓርኮች ሰፊ ሄክታር የሚሸፍነው የትኛው ነው?

ሐ. የነጭ ሳር ብሔራዊ ፓርክ የት አካባቢ ይገኛል?

መ. ከሁለቱ ፓርኮች መሰረተልማቶች የተሟሉለት የትኛው ነው?

ሠ. በነጭ ሳር ብሔራዊ ፓርክ ውስጥ ያሉ የቱሪስት መስህቦች ምን ምን ናቸው?

ረ. የተለያዩ የቱሪስት መስህቦች ለአንድ ሀገር ምን ምን ጠቀሜታ ይሰጣሉ?

ሰ. አንድን ፓርክ የመጎብኘት እድል ቢያጋጥማችሁ ምን ዓይነት ቅድመዝግጅት የምታደርጉ ይመስላችኋል? ለምን?

## ሰዋስው

## የስምን ሙያ መለየት

### ተግባር 1

ከሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ውስጥ ሰዋስዋዊ ባለቤት የሆኑትን ስሞች ከሥራቸው በማሥመር ለዩ።

ምሳሌ፡- <u>ሀና</u> ደብዳቤ ጻፈች።

ሀ. ትዕግስት ፈጣን ልጅ ናት።

ለ. እናንተ ኳስ ተጫወቱ።

ሐ. ሐይቁ በጣም ሰፊ ነው።

መ. ሰውዬው መጽሐፍ ያነባል።

ሠ. ሽምስያ ለእናቷ አዲስ ቀሚስ ገዛች።

ረ. እባብ ይናደፋል።

ሰ. ደሴት በውኃማ አካል የተከበበ የብስ ነው።

## ተግባር 2

መምህራችሁ የሚጽፉላችሁን ዓረፍተነገሮች በደብተራችሁ በመጻፍ ሰዋስዋዊ ባለቤታቸውን ለይታችሁ አመልክቱ።

## ማንበብ

### ቱሪዝም በኢትዮጵያ

### ቅድመንባብ

### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

**ተግባር**

በሚከተሉት የቅድመንባብ ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ።

ሀ. “ጢስ አልባ ኢንዱስትሪ” የሚባለው ምንድን ነው? ስያሜው ለምን የተሰጠ ይመስላችኋል?

ለ. በኢትዮጵያ የቱሪዝም መስክ እንዲያድግ ምን መደረግ አለበት ትላላችሁ?

### የማንበብ ሂደት

**ተግባር**

“ቱሪዝም በኢትዮጵያ” የሚለውን መረጃ ሰጪ ምንባብ ጥንድ ጥንድ እየሆናችሁ ድምጽ በማሰማት አንብቡ። በምታነቡበት ጊዜ ወደፊት ምን ሊመጣ እንደሚችል እየገመታችሁ አንብቡ።

### ቱሪዝም በኢትዮጵያ

ኢትዮጵያ የበርካታ ተፈጥሯዊና ሰውሠራሽ ቅርሶች ባለቤት ናት። ከእነዚህ መካከል አሥሩ በዓለም ቅርስነት የተመዘገቡ የማይንቀሳቀሱ ቅርሶች ናቸው። ኢትዮጵያ፣ ከማይንቀሳቀሱ ቅርሶች በተጨማሪ በዓለም ቅርስነት የተመዘገቡ 12 የስነጽሑፍና የመዛግብት ቅርሶችም ባለቤት ናት። እንዲሁም ታሪካቸውና አጠቃላይ ይዘታቸው ተጠንቶ በዓለም ቅርስነት እንዲመዘገቡ ለተባበሩት መንግስታት የትምህርት፣ የሳይንስና የባህል ድርጅት (ዩኔስኮ) ጥያቄ የቀረበባቸው ቅርሶችም አሏት።

ኢትዮጵያ ያሏትን ተፈጥሯዊና ሰውሠራሽ መስህቦች በማስተዋወቅ ከዘርፉ የሚገኘውን ገቢ ለማሳደግ ፈርጀብዙ ስራዎችን እያከናወነች ነው። በዚህም የሀገራችን የቱሪዝም ኢንዱስትሪ በፈጣን ሁኔታ እያደገ መጥቷል። ባለፉት አምስት ዓመታት የቱሪስት ፍሰቱ 12.8 በመቶ ዕድገት አሳይቷል። ለምሳሌ በ2005 ዓ.ም. ከ629 ሺህ በላይ የውጪ ሀገር ቱሪስቶች ለጉብኝት ወደሀገራችን መጥተዋል። በዚህም ከ633.7 ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ ተገኝቷል። ይህም ከ2004 ዓ.ም. ጋር ሲነጻጸር

የ37 በመቶ ብልጫ አለው።

ለኢትዮጵያ የቱሪዝም ኢንዱስትሪ ዕድገት፣ የግል ባለሃብቶችና የአስጎብኚ ድርጅቶች ሚና ከፍተኛ ነው። በመስኩ የሚሳተፉት ባለሃብቶችና የአስጎብኚ ድርጅቶች ቁጥር እየጨመረ መጥቷል። በአሁኑ ወቅት በባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር እውቅና የተሰጣቸው ከ310 በላይ የግል አስጎብኚ ድርጅቶች አሉ። እነዚህ ድርጅቶች ቱሪስቶችን ለመሳብ በትጋት እየሰሩ ይገኛሉ። ለቱሪስቶች አገልግሎት የሚሰጡ ደረጃቸውን የጠበቁ ሆቴሎች፣ ሎጂዎችና ሪዞርቶች ቁጥርም እያደገ ነው። በ1999 ዓ.ም. በኢትዮጵያ የነበረው የሆቴሎች፣ የሎጂዎችና የሪዞርቶች ቁጥር 157 ብቻ ነበር። በ2006 ዓ.ም. ግን ይህ አሀዝ ወደ800 አድጓል።

ኢትዮጵያ እምቅ የቱሪስት መስህብ ሀብት ያላት ሀገር ናት። ሆኖም ከቱሪዝም ሀብቷ የሚጠበቀውን ያህል ገቢ እያገኘች አይደለም። ከዚህ በተሻለ ከዘርፉ ተጠቃሚ ለመሆን የሚከተሉትን ተግባራት ማከናወን ይጠበቃል። በተለያዩ መንገዶች መስህቦችን የማስተዋወቅ ሥራ ማከናወን ይገባል። መስህቦቹን በአግባቡ መጠበቅና መንከባከብ ያሻል። በተጨማሪም ለቱሪስቶች አገልግሎት የሚሰጡ ደረጃቸውን የጠበቁ ሆቴሎችን ማስፋፋት ያስፈልጋል። ወደቱሪስት መስህብ ቦታዎች የሚያደርሱ መንገዶች በጥራት መሰራት ይኖርባቸዋል። በቱሪዝም ዘርፍ የተሰማራውን የሰው ሃይል ማሰልጠንም ያስፈልጋል። ሕዝቡም ለቱሪዝም ዕድገት የበኩሉን አስተዋጽኦ እንዲያበረክት ማስተማር ያሻል። ለምሳሌ የመስኩን ባለሙያዎች ለማብቃት የትምህርት ማዕከላት፣ የኅብረተሰቡን ግንዛቤ ለማሳደግ የመገናኛ ብዙኀን የበኩላቸውን ድርሻ መወጣት አለባቸው። ይህ ግን በአንድ ጀንበር የሚፈፀም ሳይሆን ሒደታዊና ርብርብ የሚጠይቅ ተግባር ነው።

በአጠቃላይ ከቱሪዝም ዘርፍ በቂ ገቢ ለመሰብሰብ የተጀመሩ ተግባራት ተጠናክረው ሊቀጥሉ ይገባል። የቱሪስት መስህቦችን በሬዲዮ፣ በቴሌቪዥን፣ በኢንተርኔት፣ በጋዜጣ፣ በመጽሔት ወዘተ በስፋት ማስተዋወቅ ያስፈልጋል። ለቱሪስቶቹ ምቹ የማረፊያና የመዝናኛ አካባቢዎችን ማስፋፋት ይገባል። የውጪ ቱሪስቶችን በአግባቡ ማስተናገድና ደህንነታቸውንም መጠበቅ ያስፈልጋል። በዚህም በሀገር ውስጥ የቆይታ ጊዜያቸውን እንዲያራዝሙ በማድረግ የውጪ ምንዛሬን ማሳደግ ይቻላል።

(ከኤርታ ጎብ ድረገጽ። 2006። ለውጥ ተደርጎ የተወሰደ።)

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. ኢትዮጵያ በዩኔስኮ ካስመዘገበቻቸው ቅርሶች ሦስቱን ጥቀሱ።

ለ. ለኢትዮጵያ የቱሪዝም ኢንዱስትሪ ዕድገት የግል ባለሀብቶች ሚና ምን ምን

ይመስሏችኋል?

ሐ. የሆቴሎች፣ የሎጂዎችና የሪዞርቶች መገንባት ለቱሪዝም ዕድገት ምን ጥቅም ይሰጣል?

መ. ኢትዮጵያ ከቱሪዝም ዘርፍ የሚፈለገውን ያህል ገቢ እንዳታገኝ ያገዳት ምን ይመስላችኋል?

ሠ. መገናኛ ብዙኀን ቱሪዝምን ለማሳደግ የሚጫወቱት ሚና ምንድን ነው?

ረ. ከቱሪዝም ውጪ የውጪ ምንዛሬን ማሳደግ የሚቻለው እንዴት ነው?

## 5ኛ ቀን

### ቃላት

#### ለቃላት ዐውዳዊ ፍቺ መስጠት

**ተግባር**

በሚከተሉት ቃላት ዓረፍተነገር በመሥራት ዐውዳዊ ፍቻቸውን አሳዩ።

**ምሳሌ፡-** ታሪካችንንና ባህላችንን ጠብቆ ለማቆየት የሁላችንም ድርሻ ወሳኝ ነው።

በዚህ ዓረፍተነገር ውስጥ "ድርሻ" የሚለው ቃል ዐውዳዊ ፍቺ "ሚና፣ ተግባር፣ ሥራ ወዘተ" ይሆናል።

ሀ. ትጋት

ለ. እምቅ

ሐ. መዛግብት

መ. መስክ

ሠ. ተርታ

ረ. ምንዛሬ

ሰ. አስተዋፅዖ

### መጻፍ

#### ድርሰት መጻፍ

#### በመረጃ ሰጪ የአጻጻፍ ስልት ድርሰት መጻፍ

**ተግባር**

የሚከተለውን የቢጋር ሠንጠረዥ በመጠቀም "የቱሪዝም ጥቅም" በሚል ርዕስ ሦስት አንቀጽ ያለው መረጃ ሰጪ ድርሰት ጻፉ።

- የቱሪዝም ጥቅም
  - ለጎብኚዎች
  - ለግል ባለሀብቶች
  - ለአካባቢው ማህበረሰብ
  - ለመንግስት

## የአጻጻፍ ሥርዓት

### አዳምጦ መጻፍና የሰላምታ ደብዳቤ

**ተግባር 1**

መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን ሐረጋት አዳምጣችሁ በትክክል ጻፉ።

**ተግባር 2**

ለአንድ/ዷ ጓደኛችሁ ወይም ዘመዳችሁ የሰላምታ ደብዳቤ ጽፉችሁ በፖስታ በማሸግ ለመምህራችሁ አቅርቡ።

# 6ኛ ቀን

## አቀላጥፎ ማንበብ

### ቱሪዝም በኢትዮጵያ

### ቅድመንባብ

**ተግባር**

በመናገርና በማንበብ መካከል ባለው ልዩነት ላይ ተወያዩ።

### ማንበብ

**ተግባር**

"ቱሪዝም በኢትዮጵያ" ከሚለው ምንባብ አንድ አንድ አንቀጽ ጥንድ ጥንድ እየሆናችሁ ቀስቃሽ በሆነ የአነባበብ ስልት አቀላጥፋችሁ አንብቡ።

## መናገር

### ውይይት ማካሄድ

#### ተግባር

ከሚከተሉት ሀሳቦች አንዱን በመምረጥ በክፍል ውስጥ ውይይት አድርጉ።

ሀ. ከቱሪዝም ዘርፉ ገቢ ቢገኝም በቅርሶች ላይ ጉዳት ሊደርስ ይችላል ብላችሁ ታስባላችሁ? እንዴት?

ለ. ኢትዮጵያውያን የቱሪስት መስህቦችን መጎብኘታቸው ምን ምን ጠቀሜታዎች የሚያስገኙ ይመስሏችኋል?

## ሰዋስው

### የስም ሙያዎችን (ባለቤትና ተሳቢን) እና ግስን መለየት

#### ተግባር 1

በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ባለቤት፣ ተሳቢና ግስ የሆኑትን ቃላት ለይታችሁ ጻፉ።

ምሳሌ፡-

1. ሰለሞን ሐውልቱን ጎበኘ።
2. ጀማነሽ ውኃ ቀዳች።

| ባለቤት | | ተሳቢ | ግስ |
|---|---|---|---|
| 1 | ሰለሞን | ሐውልቱን | ጎበኘ |
| 2 | ጀማነሽ | ውኃ | ቀዳች |

ሀ. ከበደ አልጋውን አነጠፈ።

ለ. አህያዋ የተከለለውን ሳር ጋጠች።

ሐ. ፍቅርተ ጓደኛዋ ያቀበለቻትን ኳስ መታች።

መ. ሀሚድ በጧት ቡና አፈላ።

ሠ. ነኢማ ከትምህርትቤት እህቷን ጠራች።

ረ. ኢትዮጵያውያን ምርታቸውን ወደገበያ ወስደው ሸጡ።

#### ተግባር 2

በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች የተሠመረባቸውን ቃላት ሰዋስዋዊ ተግባር ጻፉ።

ሀ. ሥርጉት የገዛችው <u>ቤት</u> በጣም ያምራል።

ለ. <u>ሶፊያ</u> ባለፈው ወር ሶፋ አሰራች።

ሐ. አሊ በቢላዋ ሽንኩርት ከተፈ።

መ. ካሳ ለድርቆሽ ሳር አጨደ።

ሠ. ሐመልማል ወርቅ ገዛች።

ረ. ንቦቹ አበባ ቀሰሙ።

## የቃላት ጥናት

### መነጠልና ማጣመር

**ተግባር**

የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት በመነጠልና በማጣመር ደጋግማችሁ አንብቡ።

| | ነጣጥሎ ማንበብ | አጣምሮ ማንበብ |
|---|---|---|
| ሀ | ቱ-ሪ-ዝ-ም | ቱሪዝም |
| ለ | መንገላታት-ኣችን | መንገላታታችን |
| ሐ | በ-አስ-ጎብ'ኚ-ነት | በአስጎብ'ኚነት |
| መ | አብራ-ራ-ን-ል-ኣቸው | አብራራንላቸው |
| ሠ | እየ-ተ-ቋደስን | እየተቋደስን |
| ረ | አግባባ-ን-ኣቸው | አግባባናቸው |
| ሰ | እየ-ተ-ወነጀለ | እየተወነጀለ |
| ሸ | መዋለል-ኣቸው | መዋለላቸው |
| ቀ | መጎብ'ኘት-ኣቸው | መጎብ'ኘታቸው |
| በ | የ-ኤ-ሌ-ክ-ት-ሪ-ክ | የኤሌክትሪክ |

## ማንበብ

### ቱሪዝምና ቀበሌያችን

### ቅድመንባብ

### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

**ተግባር**

የሚከተሉትን የቅድመንባብ ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. በአካባቢያችሁ ለማህበረሰቡ አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማትን ዘርዝሩ።

ለ. መሠረተልማቶቹ ለአካባቢው ማህበረሰብ ምን ምን ጠቀሜታዎች አሏቸው?

ሐ. በአካባቢያችሁ የሚገኙ ወጣቶች በብዛት የተሠማሩባቸው የሙያ ዘርፎች ምን ምን ናቸው?

## የማንበብ ሂደት

### ተግባር

“ቱሪዝምና ቀበሌያችን” በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ቀጥሎ የሚመጣውን ሀሳብ እየገመታችሁ በለሆሳስ አንብቡ።

### ቱሪዝምና ቀበሌያችን

እኔና ገረመው ጓደኛሞች ነን። የምንኖረው በአንድ የገጠር ቀበሌ ነው። በቀበሌያችን አንድ ጥንታዊ የቱሪስት መስህብ ይገኛል። የወረዳው ባህልና ቱሪዝም ጽሕፈትቤት በተለያየ መንገድ ታሪካዊ ቦታውን የማስተዋወቅ ሥራ ሰርቷል። በመሆኑም ከአምስት ዓመታት ወዲህ በርካታ ቱሪስቶች ወደቀበሌያችን እየመጡ ነው።

ቱሪስቶቹ ወደቀበሌያችን በመምጣታቸው ተጠቃሚዎች ሆነናል። ሰፊ የሥራ ዕድል ተፈጥሮልናል። እኔና ገረመው በአስጎብኝነት ማገልገል ከጀመርን ሁለት ዓመታትን አስቆጥረናል። ገረመው አንድ ዓይኑ በልጅነቱ ቢጠፋበትም በሥራው ላይ ምንም ዓይነት ተጽዕኖ አልፈጠረበትም። በምንሠራው ሥራ በቂ ገንዘብ ማግኘት ችለናል። ስለሆነም በሥራችንና በኑሯችን ደስተኞች ሆነናል። የሀገራችንን ታሪክ ጠንቅቀን ስለምናውቅና በቂ ስልጠና ስላገኘን የማስጎብኘቱን ሥራ በአግባቡ በማከናወን ላይ እንገኛለን።

ከቱሪስቶች በተገኘው ገቢ በፍትሐዊ የሀብት ክፍፍል መሠረት በቀበሌያችን ውስጥ አንድ አንድ መሠረተ ልማቶች በመንግሥት ስለተሟሉልን ደስተኞች ሆንን። ለብዙ ዘመናት ስንመኘው የነበረው የመኪና መንገድ ከአራት ዓመት በፊት ተሠራልን። በመንገዱ መሠራት የተሰማንን ደስታ በማጣጣም ላይ ሳለን ደግሞ የኤሌክትሪክ መብራት ገባልን። ወዲያውኑ የቧንቧ ውኃ ተጠቃሚ መሆን ቻልን። በቀበሌያችን የነበረው ጤና ኬላ ወደጤናጣቢያ አደገልን። በዚህ የተነሳ በሽተኞችን በቃሬዛ ተሸክመን ሩቅ ቦታ በመጓዝ መንገላታታችን ቀርቷል። ብዙ ሳይቆይ ደግሞ ዕውቀት ለሚሹ ሕፃናት በቅርብ ርቀት ትምህርትቤት ተሠራላቸው። ህጻናቱም በደስታ መማር ጀመሩ። ከዚህ ጎን ለጎን የስልክ ተጠቃሚ መሆን ቻልን። ይህን ምቹ ሁኔታ የተመለከቱ ባለሀብቶችም የእንግዳ ማረፊያ ሆቴሎችን ገነቡልን። በዚህም በርካታ ኗሪዎች  በጉልበት ሥራ፣ በአስተዳደርና በጸጥታ ዘርፍ ገቢ ማግኘት ቻሉ፤ የኑሮ ደረጃቸውም ተሻሻለ።

ይሁን እንጂ ከቱሪስቶቹ መምጣት ጋር ተያይዞ አልፎ አልፎ ችግሮች መከሰት ጀመሩ። ለምሳሌ አንዳንድ ወጣቶች በዘመናዊነት ሰበብ የቱሪስቶችን አለባበስ፣ የፀጉር አቆራረጥ፣ አረማመድና አነጋገር መኮረጅ ጀመሩ። በዚህ የተነሳ በቀበሌያችን ያልነበረ ሁኔታ ተፈጠረ። በተወሰኑ ወጣቶች ዘንድ ነባሩ ባህላችን እየተረሳ መጤው ባህል እየተለመደ መጣ። አደንዛዥ ዕጽ የሚጠቀሙ ወጣቶች ተበራከቱ። ትምህርታቸውንና ብሩህ ተስፋቸውን በመተው ባልተጨበጠ ምኞት ውስጥ መዋለል ጀመሩ። ህገወጥ የንግድ እንቅስቃሴና የመድሃኒት ዝውውር የሚፈጽሙ

ወንጀለኞች ተበራከቱ። ቱሪስቶችን እየተከተሉ ሳንቲም የሚለምኑ ታዳጊ ወጣቶች በዙ። ልመናም በየጎደናው ተስፋፋ።

ከቱሪዝም መስፋፋት ጋር የሚፈጠሩ ጥቂት አሉታዊ ገጽታዎች መኖራቸውን እኔና ገረመው ተገነዘብን። ከዚያም ችግሩን ለመቅረፍ ብዙ ጥረት አደረግን። በመጀመሪያ ቱሪስቶቹ ራሳቸው ባህላችንን እንዲያከብሩ ገለጽንላቸው። ለማኅበረሰቡ በሚጠቅሙ ተግባራት ላይ እንዲሳተፉ አግባባናቸው። ህገወጥ በሆኑ ሥራዎች ላይ እንዳይሳተፉ አሳመናቸው። ከዚያም ከባህልና ቱሪዝም ጽሕፈትቤት ባለሙያዎች ጋር ሆነን የአካባቢውን ማኅበረሰብ አወያየን። በውይይታችንም የራሳችንን ባህል ልንኮራበትና ልንጠብቀው እንደሚገባ ተግባባን። ልመናን ጨምሮ ባህላችንን የሚበርዙ ሌሎች መጥፎ ተግባራትን ሁሉ እንዲያወግዙ አብራራንላቸው። ህጋዊ ባልሆነ መንገድ የሚንቀሳቀሱ ሰዎችን ለማጋለጥና ለማስተማር የጋራ ስምምነት ላይ ደረስን። ከዚያ ጊዜ ወዲህ በቀበሌያችን ውስጥ ችግሮቹ እየቀነሱ መጡ። ከቱሪዝም ጋር ብቅብቅ ያሉ ችግሮችን በማስወገዳችን የቱሪዝምን በረከት እየተቋደስን እንገኛለን።

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር 1

ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል መርጣችሁ በመጻፍ መልሱ።

1. በእነገረመው ቀበሌ ከተዘረጉት መሠረተልማቶች መካከል የሚመደበው የቱ ነው?

   ሀ. የኤሌክትሪክ መብራት　　　ሐ. የአውሮፕላን ማረፊያ

   ለ. ዘመናዊ ስታዲየም　　　መ. የገበያ ማዕከል

2. ከቱሪስቶች መምጣት ጋር ተያይዞ ከሚከሰቱ ችግሮች **የማይካተተው** የትኛው ነው?

   ሀ. መጤ ባህል ብቅ ብቅ ማለት

   ለ. የቱሪስቶችን አለባበስና አረማመድ መኮረጅ

   ሐ. ወጣቶች ነባሩን ባህል መጠበቃቸው

   መ. ህገወጥ የንግድ እንቅስቃሴ መኖር

3. ለቱሪዝም ዕድገት **የማይጠቅመው** የቱ ነው?

   ሀ. የራሳችንን ባህል መጠበቅ

   ለ. ህጋዊ ባልሆነ መንገድ መንቀሳቀስ

   ሐ. ቱሪስቶች ባህላችንን እንዲያከብሩ ማድረግ

   መ. ህብረተሰቡን ስለቱሪዝም ጥቅም ማስተማር

4. ዕውቀት ለሚሹ ሕፃናት የተሰራላቸው ምንድን ነው?

ሀ. የእንግዳ ማረፊያ ሆቴል　　ሐ. የስልክ መስመር

ለ. የመኪና መንገድ　　መ. ትምህርትቤት

5. ባልተጨበጠ ምኞት መዋለልን የሚያመለክተው የትኛው ነው?

ሀ. ሳይሰሩ ለመክበር መፈለግ　　ሐ. ዕቅድን ወደተግባር መለወጥ

ለ. ዓላማን ተከትሎ መሥራት　　መ. በሥራ ለመለወጥ መጣር

6. በዘመናዊነት ሰበብ ከሚመጡ አሉታዊ የባህል ተፅዕኖዎች መካከል የማይካተተው የቱ ነው?

ሀ. የጠጉር አቆራረጥ　　ሐ. የቴክኖሎጂ አጠቃቀም

ለ. አለባበስ　　መ. የቋንቋ አጠቃቀም

### ተግባር 2

የሚከተሉት ዋናዋና ሀሳቦች ከምንባቡ የተወሰዱ ናቸው። ሀሳቦቹ የተወሰዱባቸውን አንቀጾች ለይታችሁ አመልክቱ።

ሀ. ባህልን የሚበርዙ በርካታ ተጽዕኖዎች መታየት ጀመሩ።

ለ. በአካባቢ ያሉ ታሪካዊ ቦታዎችን በማስተዋወቅ ጎብኚዎችን መሳብ ተችሏል።

ሐ. ችግሮቹን ለማስወገድ ከባለድርሻ አካላት ጋር ምክክር ተደረገ።

መ. በቀበሌው በርካታ መሠረተልማቶች ስለተሟሉ ማህበረሰቡ ተጠቃሚ ሆነ።

ሠ. በአካባቢው ለሚገኙ ወጣቶች ሰፊ የሥራ ዕድል ተፈጠረላቸው።

## 8ኛ ቀን

## ቃላት

### ለቃላት ዐውዳዊ ፍቺ መስጠት

### ተግባር

ለሚከተሉት ቃላት ዐወዳዊ ፍቻቸውን በጽሑፍ ስጡ።

ምሳሌ፡-

መለመን ⟶ መመፅወት (ምፅዋት መቀበል)

ሀ. ቃሬዛ (አንቀጽ 3)　　ሐ. መኮረጅ (አንቀጽ 4)

ለ. መጤ (አንቀጽ 4)　　መ. መዋለል (አንቀጽ 4)

ሠ. ምኞት (አንቀጽ 4)

ረ. ማሳመን (አንቀጽ 5)

ሰ. መቋደስ (አንቀጽ 5)

ሸ. መበረዝ (አንቀጽ 5)

## መጻፍ

### ድርሰት መጻፍ

### በመረጃ ሰጪ የአጻጻፍ ስልት ድርሰት መጻፍ

#### ተግባር 1

የሚከተለውን ዓረፍተነገር መነሻ በማድረግ በመረጃ ሰጪ የአጻጻፍ ስልት ባለሦስት አንቀጽ ድርሰት ጻፉ።

- ወጣቶች የውጪ ሀገር ባህሎችን መከተል የለባቸውም።

#### ተግባር 2

በመረጃ ሰጪ የአጻጻፍ ስልት የጻፋችሁትን ድርሰት መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት እንደገና አስተካክላችሁ ጻፉ።

### የአጻጻፍ ሥርዓት

### የቃላትን መዋቅር በማስተካከል አንቀጽ መጻፍ

#### ተግባር

በሚከተለው ጽሑፍ ውስጥ የተሠመረባቸውን ቃላት/ሐረጋት አስተካክላችሁ ከጻፋችሁ በኋላ አንብቡ።

ድህነት የተማላ ሀብት ወይም ገቢ መኖር ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። ነገርግን ድህነት መሠረታዊ ፍላጎት ጥረት ወይም ማማላት (በቂ ምግብ፣ ልብስ፣ መጠለያ፣ ንፁህ ውኃና የጤና አገልገሎት ማግኘትን) ያጠቃልላል።

## 9ኛ ቀን

## አቀላጥፎ ማንበብ

### ቱሪዝምና ቀበሌያችን

### ቅድመንባብ

#### ተግባር

"ቱሪዝምና ቀበሌያችን" በሚል ርዕስ ከቀረበው ምንባብ የምታስታውሱትን ተናገሩ።

## ማንበብ

### ተግባር

"ቱሪዝምና ቀበሌያችን" በሚል ርዕስ ከቀረበው ምንባብ የመጨረሻውን አንቀጽ ያለምንም የፊደል ግድፈት በአንድ ደቂቃ ውስጥ አንብቡ።

# መናገር

## ክርክር ማድረግ

### ተግባር

የሚከተለውን ጥያቄ ሀሳብ በመደገፍ ወይም በመቃወም ተናገሩ።

- የሌላውን ማህበረሰብ ባህል መቀበልና የራስ ማድረግ ጠቃሚ ነው ወይስ ጎጂ?

# ሰዋስው

## በዓረፍተነገር ውስጥ ባለቤትን፣ ተሳቢንና ግሥን መለየት

### ተግባር 1

በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ባለቤት፣ ተሳቢና ግሥ የሆኑትን ቃላት ለይታችሁ ጻፉ።

ሀ. ዝናሽ ለባለቤቱ ያነበበችውን መጽሐፍ መለሰች።

ለ. ተማሪዎች ጥያቄውን መለሱ።

ሐ. እኛ በመወልወያ ትልቁን ቤት አጸዳን።

ሠ. ዘይነባ የተሰበረውን መስኮት ቀስ ብላ ከፈተች።

ረ. ቱሪስቶች ታሪካዊ ቦታዎችን ጎበኙ።

### ተግባር 2

የሚከተሉትን ቃላት በመጠቀም ባለቤትና ተሳቢ ያላቸው ዓረፍተነገሮች መሥርቱ።

ሀ. ለገሰ

ለ. ሠራች

ሐ. ለቀመ

መ. ለበሰ

ሠ. ያዘች

ረ. አስተዋወቀች



# ተወዳጅ ታሪኮች

ምዕራፍ 6

## ሁለት ታሪኮችን ማወዳደርና ማነጻጸር

1ኛ ሳምንት 1ኛ ቀን

## የቃላት ጥናት

### መነጠልና ማጣመር

#### ተግባር

የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት በመነጠልና በማጣመር አንብቡ።

| | ነጣጥሎ ማንበብ | አጣምሮ ማንበብ |
|---|---|---|
| ሀ | የ- አስቀመጠ-ል-ኣቸው-ን | ያስቀመጠላቸውን |
| ለ | እንዳ ይባክን-ብ-ኣችሁ-ም | እንዳይባክንባችሁም |
| ሐ | አቆይ-ቼ-ል-ኣችሁ-ኣል-ኧሁ | አቆይቼላችኋለሁ |
| መ | አሳምን-ኣችሁ-አለ-ሁ | አሳምናችኋለሁ |
| ሠ | እንዲጠቀሙ-በ-ት | እንዲጠቀሙበት |
| ረ | አሰናበቱ-ኣቸው | አሰናበቷቸው |
| ሰ | ይ-ቀኑ-ብ-ኣቸው-ኣል | ይቀኑባቸዋል |
| ሸ | ከ-አስቀመጡ-ል-ኣቸው | ካስቀመጡላቸው |

## ማንበብ

### ቤተሰባዊ ገጽታ

#### ቅድመንባብ

ከርዕስና ከሥዕል የምንባብን ሀሳብ መገመትና ለቃላት ፍቺ መስጠት

#### ተግባር

ምንባቡን ከማንበባችሁ በፊት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. በምንባቡ ርዕስና በሥዕሉ መካከል ምን ዓይነት ዝምድና ያለ ይመስላችኋል?

ለ. የሚከተሉትን ቃላት ፍቺ ተናገሩ።

| ገጽታ | ኀተራ | ውርስ |
|---|---|---|

## የማንበብ ሂደት

## ታሪኮችን በማወዳደርና በማነጻጸር ማንበብ

### ተግባር

በሚከተለው ምንባብ ውስጥ ያሉ ታሪኮችን እያወዳደራችሁና እያነጻጸራችሁ በለሆሳስ አንብቡ።

## ቤተሰባዊ ገጽታ

### ወንድማማቾቹ



በአንድ አካባቢ የሚኖሩ የአንድ ባለፀጋ ልጆች ነበሩ። አንደኛው ባለትዳር ሲሆን ሌላው ደግሞ ወንደላጤ ነበር። ሁለቱም ወንድማማቾች የሚተዳደሩት በወረሱት የእርሻ መሬት ነው። ወላጆቻቸው ያወረሷቸውን መሬት በጋራ እያረሱ ምርቱን እኩል ይካፈላሉ። በሥራና በኑሮ ባላቸው መተጋገዝ የአካባቢው ሰዎች እጅግ ይቀኑባቸዋል። አንዱ ለሌላው የሚያስበውን ያህል ለግላቸው አይጨነቁም ነበር።

አንድ ቀን ላጤው "ወንድሜ ቤተሰብ አለው። ልጆቹን፣ የባለቤቱን ወላጆችና የቤት ሠራተኞቹን መመገብ አለበት። ስለዚህ ምርቱን ከእኔ ጋር እኩል መካፈል የለበትም። እሱ ከእኔ የሚበልጥ ምርት ማግኘት አለበት። ነገርግን አሁን ከእኔ የበለጠ ውሰድ ብለው አይቀበለኝም። ስለዚህ በሌላ መንገድ መርዳት አለብኝ" ሲል አሰበ።

ብዙ ካሰበ በኋላ በጎተራ ካለው እህሉ ማታ ማታ ተደብቆ እየወሰደ በወንድሙ ጎተራ ውስጥ ለማስቀመጥ ወሰነ። ማታ ማታ ተደብቆ በመውጣት ከራሱ ጎተራ ወደወንድሙ ጎተራ እህል ይገለብጥ ነበር። ነገርግን ጧት ጎተራውን ሲያየው እንኳንስ ሊጎድል ካለፈው የበለጠ ሞልቶ ያገኘው ነበር። ይህም እጅግ ይገርመው ነበር። "በጎ ሥራዬን አይቶ እየባረከልኝ ነው" ብሎም ፈጣሪውን አመሰገነ።

ባለትዳሩም እንዲሁ ለብቻው "ወንድሜ እንደእኔ አላገባም። ለወደፊትም ከባድ ኃላፊነት ይጠብቀዋል። ትዳር መመስረት አለበት፤ ልጆች ማፍራት አለበት። ለዚህ ደግሞ አሁን የሚያገኘው ምርት በቂው አይደለም። እኔ የራሴን ኑሮ አደላድያለሁ። እሱ ግን ገና አዳጊ ነው። አሁን የሚበልጠውን ምርት ውሰድ ብለው አይቀበለኝም። ስለዚህ በድብቅ ልረዳው ይገባኛል" ብሎ አሰበ።

ባለትዳር ወንድሙም ሊነጋጋ ሲል እየተነሳ ከራሱ ጎተራ ወደወንድሙ ጎተራ እህል ይጨምር ነበር። ጧት ሲነሳ ግን ጎተራው ሳይጎድል ያገኘዋል። ይህም ሁልጊዜ ይገርመዋል። "መስጠቴን ተመልክቶ ነው የሞላልኝ" እያለም ፈጣሪውን ያመሰግን ነበር።

እንዲህ እያደረጉ ለብዙ ጊዜ ኖሩ። በአንድ ሌሊት ግን ሁለቱም እህል ተሸክመው ወደየጎተራው ሊከቱ ሲሄዱ በድንገት መንገድ ላይ ተገናኙ። ሁለቱም በነገሩ ተገርመው ተቃቅፈው እየተላቀሱ የሆነውን ሁሉ ተነጋገሩ። ከበፊቱ የበለጠም ፍቅራቸው እጅግ ጸና።

(ከዳንኤል ክብረት ድረገጽ፣ ግንቦት 15። 2014። ለውጥ ተደርጎ የተወሰደ።)

## ወራሾቹ



በአንድ አካባቢ አንድ ወንድና አንዷት ሴት የባለፀጋ ልጆች ነበሩ። ከወላጆቻቸው በርካታ ንብረቶችን በውርስ ስላገኙ ሥራ አይወዱም ነበር። ከዕለታት አንድ ቀን አባታቸው በሳጥን ቆልፎ ከጎረቤት ያስቀመጠላቸውን ዕቃ መከፋፈል ፈለጉ። ወንዱ "እኔ ታላቅ ስለሆንኩ ካንቺ የሚበልጠውን መውሰድ አለብኝ እንጂ፣ እኩል መካፈል የለብኝም" ሲል ሴቷ ደግሞ "አባቴ እጅግ ይወደኝ እንደነበር ታውቃለህ፤ ስለዚህ አብዛኛውን መውሰድ ያለብኝ እኔ ነኝ" በማለት መጨቃጨቅ ጀመሩ። መስማማትም ስላልቻሉ ሳጥኑን በአደራ ካስቀመጡላቸው ሽማግሌ ቤት ሄዱ።

ሁለቱም ሀሳባቸውን ለሽማግሌው በየተራ ገለፁ። ሽማግሌውም በልጆቹ ሀሳብ በጣም ተገረሙ። "ልጆቼ አባታችሁ ደግ ሰው ነበር። ለሰዎች የሚያዝን ለእኔ ከማለት ይልቅ ለእናንተ የሚል ቸር ነበር። ለዚያ ደግነቱ ወሮታ የመለስኩ ስለመሰለኝ የአባታችሁን አደራ ለአምስት ዓመታት ጠብቄ አቆይቼላችኋለሁ። እንዳይባክንባችሁም በማሰብ እስካሁን ሳልነግራችሁ ቆይቻለሁ። አሁንም በውስጡ ያለውን ሀብት ባላውቅም ተስማምታችሁ እንድትከፋፈሉ እለምናችኋለሁ። አንተም ታላቅ በመሆንህ አንቺም ታናሽና ተወዳጅ በመሆንሽ የበለጠውን መውሰድ አለብኝ አትበሉ። ሁላችሁም እኩል ልትካፈሉ ይገባል" በማለት አግባቧቸው።

ሁለቱ ወራሾችም ሽማግሌው ባሉት መሠረት እኩል ሊከፋፈሉ ተስማሙ። ሽማግሌውም በአደራ ያስቀመጡትን ሳጥን ከልጆቹ ፊት አቀረቡ። ልጆቹም ሳጥኑ በአባታቸው ፊርማ መታሸጉን አረጋገጡ። ከዚያም በሽማግሌው እጅ ሳጥኑ እንዲከፈት ተስማሙ። ሽማግሌውም ሳጥኑን ከፈቱት፤ በውስጡ ግን ልጆቹ እንዳሰቡት ወርቅ ሳይሆን ምክር የያዘ መጽሐፍ ሆኖ ተገኘ። ሽማግሌውም በልጆቹ አባት ብልህነት በጣም ተደነቁ። የማያልቅ የሀብት ምንጭ የሆነውን መጽሐፍ በመዋዋስ እንዲያነቡትና እንዲጠቀሙበት አሳስበው አሰናበቷቸው።

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር 1

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. የአካባቢው ሰዎች በወንድማማቾቹ የሚቀኑባቸው ለምንድን ነው?

ለ. ሁለቱ ወንድማማቾች በግልጽ አለመወያየታቸው ትክክል ነው ወይስ አይደለም? ለምን?

ሐ. የልጆቹ አባት መጽሐፍ ያወረሷቸው ለምን ይመስላችኋል?

መ. “ወራሾቹ” በሚለው ምንባብ ውስጥ ሁለቱ የባለፀጋ ልጆች በውርስ ያገኙትን ንብረት መካፈል የፈለጉት ለምንድን ነው?

ሠ. “ወራሾቹ” በሚለው ምንባብ ውስጥ ሽማግሌው በልጆቹ ሀሳብ የተገረሙት ለምን ይመስላችኋል?

ረ. እናንተ ወንደላጤውን ብትሆኑ ምን ታደርጉ ነበር? ለምን?

ሰ. “ወንድማቾቹ” ከሚለው ምንባብና “ወራሾቹ” ከሚለው ምንባብ የትኛውን ወደዳችሁት? ለምን?

### ተግባር 2

በቢጋር ሠንጠረዦቹ ውስጥ ያሉትን ሀሳቦች በቡድን ተከፋፍላችሁ በመወያየት የየግል አስተያየታችሁን በክፍል ውስጥ አቅርቡ።







## 2ኛ ቀን

## ቃላት

### ለቃላት ዐውዳዊ ፍቺ መስጠት

**ተግባር**

ለሚከተሉት ቃላት በምንባቡ መሠረት ዐውዳዊ ፍቻቸውን ጻፉ።

ሀ. ባለፀጋ (አንቀጽ 1)
ለ. ወንደላጤ (አንቀጽ 1)
ሐ. እየባረከልኝ (አንቀጽ 3)
መ. ማፍራት (አንቀጽ 4)
ሠ. አደላድያለሁ (አንቀጽ 4)
ረ. እንዳይባክንባችሁ(አንቀጽ8)
ሸ. ወሮታ (አንቀጽ 8)
ሰ. አደራ (አንቀጽ 8)

## መጻፍ

### 4ሀ. ድርሰት መጻፍ

### በማወዳደርና በማነጻጸር ስልት ድርሰት መጻፍ

**ተግባር**

የቢጋር ሠንጠረዡን በመጠቀም በማወዳደርና በማነጻጸር ስልት አንድ አንቀጽ ጻፉ።




## የአጻጻፍ ሥርዓት

### ምንባብን አዳምጦ ሥርዓተነጥቦችን በተገቢ ቦታ በመጠቀም መጻፍ

### ተግባር 1

መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን አንቀጽ እያዳመጣችሁ ትክክለኛ ሥርዓተነጥቦችን በተገቢ ቦታ በመጠቀም በደብተራችሁ ላይ ጻፉ።

### ተግባር 2

የነጠላሰረዝን፣ የድርብሰረዝን፣ የጥያቄ ምልክትን አጠቃቀም የሚያሳዩ ከ6-8 የሚደርሱ ዓረፍተነገሮችን ጻፉ።

## 3ኛ ቀን

## አቀላጥፎ ማንበብ

### ቤተሰባዊ ገጽታ

### ቅድመንባብ

### ተግባር

"ቤተሰባዊ ገጽታ" በሚል ርዕስ ሥር ከቀረቡት ምንባቦች ውስጥ የምታስታውሷቸውን ሁለት ዋናዋና ሀሳቦችን ተናገሩ።

## ማንበብ

### ተግባር

"ቤተሰባዊ ገጽታ" ከሚለው ምንባብ "ወራሾቹ" በሚል ንዑስ ርዕስ የቀረበውን ምንባብ በ2 ደቂቃ ውስጥ ድምጽ በማሰማት አቀላጥፋችሁ አንብቡ።

### ማዳመጥ

## የእናት ምክር



የመልካም ሥራ ዋጋ



ብልሀተኛዋ ሴት

## ቅድመማዳመጥ

## የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

### ተግባር

መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን ምንባብ ከማዳመጣችሁ በፊት የሚከተሉትን የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. ከምንባቡ ርዕስ ሥር ያሉትን ሥዕሎች ተመልክታችሁ የተረዳችሁትን በቃላችሁ ግለጹ።

ለ. በዕለት ተዕለት ኑሯችሁ ቤተሰቦቻችሁ የሚመክሯችሁ ለምን ይመስላችኋል?

## የማዳመጥ ሂደት

### ተግባር

የሚከተለውን ሠንጠረዥ በደብተራችሁ ላይ አዘጋጁና "የመልካም ሥራ ዋጋ" በሚል ንዑስ ርዕስ ምንባብ እያዳመጣችሁ መረጃዎቹን ሙሉ።

| ድርጊት ፈጻሚዎች | የተፈጸሙ ድርጊቶች |
| --- | --- |
| | |

## አዳምጦ መረዳት

### ተግባር 1

በማዳመጥ ሂደት በሠንጠረዥ ውስጥ የጻፋችኋቸውን ድርጊት ፈጻሚዎችንና የተፈጸሙ ድርጊቶችን በክፍል ውስጥ አንብቡ።

### ተግባር 2

"ብልሀተኛዋ ሴት" በሚል ንዑስ ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ባዳመጣችሁት መሠረት የሚከተሉትን ሀሳቦች በቅደምተከተል በማስተካከል እንደገና ጻፉ።

ሀ. እናታቸው መሬታቸውን በመደዳ እንዲቆፍሩ አዘዟቸው።

ለ. ያመረቱትን በመሸጥ ወርቅ ሰበሰቡ።

ሐ. ልጆቻቸውን ጠሩ።

መ. እናታቸው የመሞቻ ጊዜያቸው ተቃረበ።

ሠ. መሬታቸውን ከዳር እስከዳር ቆፈሩት።

ረ. እናታቸው መሬት ውስጥ የተቀበረ ወርቅ እንዳለ ነገሯቸው።

ሰ. በቆፈሩት መሬታቸው ላይ ስንዴና ገብስ ዘሩ።

ሸ. ልጆቹ የተቀበረ ወርቅ ባለማግኘታቸው በጣም ተናደዱ።

ቀ. ከዘሩት ስንዴና ገብስ ብዙ ምርት አመረቱ።

## ሰዋስው

### ምድብ ተውላጠስምን፣ አገናዛቢ ተውላጠስምንና ዘርፍን መለየት

#### ተግባር 1

በምሳሌው መሠረት በቅንፍ ውስጥ ያሉትን ተውላጠስሞች በመምረጥ ዓረፍተነገሩን አሟሉ።

ምሳሌ፡- ———ንቁ ተማሪ ናት። (እሷ፣አንቺ)

<u>እሷ</u> ንቁ ተማሪ ናት።

ሀ.——— ወደትምህርትቤት ሄድን። (እነሱ፣ እኛ)

ለ.——— ገንዘብ እንዳስቀምጥለት ሰጠኝ። (እኔ፣ እሱ)

ሐ.——— አርሶአደር ናት። (እሷ፣ አንቺ)

መ.——— መሬታቸውን ዳር እስከዳር ቆፈሩት። (እናንተ፣ እነሱ)

ሠ.——— በርትተሽ ከሠራሽ ስኬታማ ትሆኛለሽ (አንቺ፣ እሷ)

ረ. ——— የሚመክሩንና የሚገስጹን አባታችን ነዎት። (እርስዎ፣ እሳቸው)

#### ተግባር 2

ከሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ውስጥ ባለንብረትነትን የሚያመለክቱ አገናዛቢ ተውላጠ ስሞችን (ዘርፎችን) አሥምሩባቸው።

ምሳሌ፡-

<u>የእኔ</u> ወንድም ነገ ይመጣል። *(የተሠመረበት "የእኔ" የሚለው አገናዛቢ ተውላጠስም ሲሆን ባለንብረትነትን ያመለክታል።)*

<u>ወንድሜ</u> ነገ ይመጣል። *(የተሠመረበት "ወንድሜ" የሚለው ዘርፍ ሲሆን ባለንብረትነትን ያመለክታል።)*

ሀ. ልጄ ጎበዝ ተማሪ ናት።

ለ. የእሱ መጽሐፍ አዲስ ነው።

ሐ. ቤታችን ቀለም ተቀባ።

መ. አትክልታቸው ጸደቀ።

ሠ. የአንቺ ጽሑፍ ያምራል።

ረ. ልብሳችሁ ንጹህ ነው።

ሰ. አጎትሽ ወደትምህርትቤት ወሰደን።

## ተግባር 3

የተሠመረባቸውን ቃላት በተውላጠስሞች በመተካት ዓረፍተነገሮችን እንደገና ጻፉ።

ሀ. <u>አስናቀችና ዘሪቱ</u> እህትማማቾች ናቸው።

ለ. <u>አክስቴ</u> በመምህርነት ሙያ ተመረቀች።

ሐ. <u>ሐዲስ ዓለማየሁ</u> የፍቅር እስከመቃብር ደራሲ ናቸው።

መ. <u>ፍቅርተ</u> ሂጅና ሽልማትሽን ተቀበይ።

ሠ. <u>እኔና ጓደኞቼ</u> ለሽርሽር ሶደሬ ሄድን።

ረ. <u>አዛናው</u> በደንብ ስለሚያጠና ፈተናውን ያልፋል።

## ማንበብ

### ጓደኞቼ

8ሀ. ቅድመንባብ

### ከርዕስና ከሥዕል የምንባብን ሀሳብ መገመት

**ተግባር**

"ጓደኞቼ" የሚለውን ምንባብ ከማንበባችሁ በፊት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. "ለፍሬ መብቃት" ማለት ምን ማለት ይመስላችኋል? በምሳሌ አስደግፋችሁ ግለጹ።

ለ. "ለፍሬ መብቃት" የሚለውን ንዑስ ርዕስና ሥዕሉን በማዛመድ የተረዳችሁትን ተናገሩ።

ሐ. "መና የቀረ ምክር" የሚለው ንዑስ ርዕስ ምን የሚገልጽ ይመስላችኋል? በምሳሌ አስደግፋችሁ ግለጹ።

መ. "መና የቀረ ምክር" በሚለው ርዕስና በሥዕሉ መካከል ምን ዓይነት ግንኙነት ያለ ይመስላችኋል?

### የማንበብ ሂደት

**ተግባር**

"ጓደኞቼ" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ጥንድ ጥንድ በመሆን አንብቡ። ግልጽ ያልሆነላችሁ ሀሳብ ሲኖር ማንበባችሁን ቆም አድርጉና በማሰላሰል ሀሳቡን ለመረዳት ሞክሩ።

# ጓደኞቼ

## ለፍሬ መብቃት





በምኖርበት ከተማ በተደጋጋሚ ለሥልጠና መጥቷል። ብዙ ጊዜ የሚያርፈው ከእኔ ቤት ነው፡ ዛሬም የሚገኘው ከእኔ ጋር ነው፤ አህመድ ይባላል። ያደግነው በአንድ ሰፈር ውስጥ ነው። በጣም እንዋደዳለን። በዕድሜ ብዙ አይበልጠኝም። ታላቅ የምመስለው ወፍራም ስለነበርኩ ነው። የእሱ ቅጥነት ደግሞ የበለጠ ታላቅ ያስመስለኛል። ትምህርትቤት የገባነው በተመሳሳይ ጊዜ ነበር። ሁለታችንም ትምህርት እንወድ ነበር። ስለሆነም በጋራ እናጠናለን። እኔም ሆንኩ አህመድ ብዙ ጊዜ ለጨዋታ ግድ አልነበረንም። አንዳንዶቹን ጨዋታዎች እስካሁን ድረስ አናውቃቸውም። ጎበዝ ተማሪዎች ስለነበርን በሁሉም የክፍል ደረጃዎች ሽልማት ያላገኘንበት ጊዜ አልነበረም። አህመድ ከልጅነቱ ጀምሮ ለሕክምና ሙያ የተለየ ፍቅር ነበረው። እኔ ደግሞ የመምህርነትን ሙያ በጣም እወድ ነበር።

የልጅነት ምኞታችን ሰምሮልን እኔ መምህር ስሆን እሱ ደግሞ ነርስ ሆኗል። አሁን የምንኖረው ካደግንበት እስቴ ወረዳ ራቅ ብለን ነው። እኔ በወልድያ ከተማ መኖር ከጀመርኩ አራት ዓመት ሆኖኛል። አህመድ ደግሞ ከሦስት ዓመት ወዲህ ደሴ ከተማ ውስጥ ይኖራል። ሁለታችንም ትዳር አልመሠረትንም። ይሁን እንጂ አህመድ ለማግባት በዝግጅት ላይ ነው። እኔ ግን ገና የኑሮ አጋሬን እየፈለኩ ነው። ሁለታችንም በየመሥሪያቤታችን ኮከብ ሠራተኞች ተብለን በተደጋጋሚ በመሸለም ተመስግነናል። አሁንም ለሁለተኛ ዲግሪ የትምህርት ዕድል አግኝተናል። በቅርቡ ወደተመደብንበት ዩኒቨርሲቲ ለመሄድ በዝግጅት ላይ ነን።

# መና የቀረ ምክር



ከትምህርትቤት የወጣሁት ሠላሳ ደቂቃ ያህል ዘግይቼ ነበር። አቅጣጫዬን ወደመኖሪያቤቴ አድርጌ በቀስታ እጓዛለሁ። በተቃራኒ አቅጣጫ ደግሞ የልጅነት የክፍል ጓደኛዬን ሲመጣ አየሁት፤ ከተገዛች ወልቃ የማታውቅ የምትመስል ስስ ሹራብ ለብሷል። ከመቆሸሿ የተነሳ መልኳን ለመለየት ያስቸግራል።ብዙ ቦታ ላይ ተበሳስታ ሰውነቱን አጋልጣዋለች። ያለቀበቶ የለበሰው ጂንስ ሱሪ ጉልበቱ አካባቢ በመስመር በመስመር ተቀዳዷል። የሱሪውን ጫፍ ባደረገው <u>ነጠላ</u> ጫማ ስለሚረግጠው በጭቃ ተለውሷል። የኪሶቹ አካባቢም ወዝ ጠግቧል። እየተጠጋኝ ሲመጣ ራሴን ለሰላምታ አዘጋጀሁ። በአፉ ጫት፣ በእጁ ደግሞ ሲጋራ ይዟል። ትንሽ ፍርሃት ቢጤ አደረብኝ። እንደምንም ራሴን አደፋፍሬ ሰላምታ አቀረብኩለት። እሱ ግን አፀፋውን ሳይመልስልኝ ጉዞውን ቀጠለ። እንደረሳኝ ገብቶኛል።እኔም በነርሱ ጓደኛዬ ብደሰትም በዚህኛው ጓደኛዬ ሁኔታ በጣም አዘንኩ።

የምንተዋወቀው የስድስተኛ ክፍል ተማሪዎች ሳለን ነበር። ያኔ ታዲያ ጨዋታ እንጂ ትምህርት አይወድም ነበር። ብዙ ጊዜ ወደትምህርትቤት ሄድኩ እያለ መንገድ ላይ ሲጫወት ይውል ነበር። እናቱ እንዳያውቁበትም ይጠነቀቅ ነበር። አንድ ቀን እንደለመደው ሲጫወት የጎረቤት ልጅ አየውና ለእናቱ ተናገረበት። እናቱም ትምህርቱን መከታተል እንዳለበትና ለወደፊቱም ይጠረኛል የሚሉት ተስፋቸው

እንደሆነ ገለፁለት። እያለቀሱም ተማፀኑት። መምህራችንም ደጋግመው መከሩት። የሚያጠናበትንና የሚጫወትበትን የጊዜ ዕቅድ ቢያዘጋጁለትም ሊጠቀምበት ግን አልፈለገም። በመጨረሻም ትምህርቱን ሙሉ በሙሉ አቋረጠው፤ ወዲያው ጫት መቃምና አልኮል መጠጣት ጀመረ። በልጅነቱ እንደዋዛ የጀመረው ሱስ ዛሬ የእናቱ ጥገኛ ሆኖ ያለሥራ እንዲውል አድርጎታል።

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር 1

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. በጋራ ማጥናት ጠቀሜታው ምንድን ነው?

ለ. ተራኪው የዱሮ ጓደኛውን ሲያገኘው ፍርሀት ያደረበት ለምን ይመስላችኋል?

ሐ. የነርሱና የአጫሹ የትምህርትቤት ህይወት ምን ይመስል ነበር?

መ. ወደፊት በምን ሙያ ላይ መሰማራት ትፈልጋላችሁ? ለምን?

### ተግባር 2

ከምንባቡ ሀሳብ በመረዳት ገፀባህርያቱ የሚኖሩበትን ቦታ፣ ሥራቸውን፣ ያሳለፉትን ህይወት፣ የገጠማቸውን ችግርና አሁን የደረሱበትን ደረጃ መሠረት በማድረግ የሚከተለውን ሠንጠረዥ ሙሉ።

| ገፀባህርያት | የሚኖሩበት ቦታ | ሥራቸው | የገጠማቸው ችግር | ያሳለፉት ህይወት | በመጨረሻ የደረሱበት ሁኔታ (ደረጃ) |
|---|---|---|---|---|---|
| እኔ (ተራኪው) | | | | | |
| ነርሱ ጓደኛዬ | | | | | |
| አጫሹ ጓደኛዬ | | | | | |

## 5ኛ ቀን

### ቃላት

**ለቃላት ዐውዳዊ ፍቺ መስጠት**

**ተግባር**

ለሚከተሉት ቃላት “ጓደኞቼ” በሚለው ምንባብ ውስጥ ያላቸውን ዐውዳዊ ፍቺ ከጻፋችሁ በኋላ በምንባቡ ካላቸው ፍቺ ውጪ ዓረፍተነገር ሥሩባቸው።

ሀ. የሚያርፌው (አንቀጽ 1)

ለ. ደረጃ (አንቀጽ 1)

ሐ. ኮኮብ (አንቀጽ 2)

መ. መሸለም (አንቀጽ 2)

ሠ. ነጠላ (አንቀጽ 3)

ረ. እንዲውል (አንቀጽ 4)

### መጻፍ

**ድርሰት መጻፍ**

**በማወዳደርና በማነጻጸር ስልት ድርሰት መጻፍ**

**ተግባር 1**

“ጓደኞቼ” በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ዋናዋና ደጋፊ ሀሳቦች በማውጣት የቢጋር ሠንጠረዡን አሟሉ።



## ተግባር 2

"ጓደኞቼ" በሚል ርዕስ ያዘጋጃችሁትን የቢጋር ሠንጠረዥ በመጠቀም በማወዳደርና በማነጻጸር ስልት ባለሦስት አንቀጽ ድርሰት ጻፉ።

## የአጻጻፍ ሥርዓት

### የዓረፍተነገር ቅደምተከተሎችን አስተካክሎ አንቀጽ መጻፍ

## ተግባር

ቅደምተከተላቸው የተፋለሱ ዓረፍተነገሮችን በማስተካከል አንድ አንቀጽ አድርጋችሁ ጻፉ።

ሀ. ነገር ግን ማንበብና ማዳመጥ የየራሳቸው ባህርያት አሏቸው።

ለ. ማንበብ አንድን የተጻፈ ጽሑፍ ለመረዳት የምናነብበት ሂደት ነው።

ሐ. ማንበብና ማዳመጥ መረጃን ከሌላ ምንጭ የምንቀበልባቸው ክሂሎች ናቸው።

መ. በማዳመጥ ሂደት ግን የምናዳምጠው ሀሳብ የተቀረፀ ካልሆነ በስተቀር እንደገና ሀሳቡን ለማዳመጥ አንችልም።

ሠ. በማንበብ ሂደት ሀሳቡ ካልገባን መልሰን መላልሰን ለማንበብ ዕድል ይኖረናል።

ረ. ማዳመጥ ግን ከሌላ አካል የሚነገርን ሀሳብ በጆሯችን የምናዳምጥበት ሂደት ነው።

## 6ኛ ቀን

# አቀላጥፎ ማንበብ

## ጓደኞቼ

### ቅድመንባብ

## ተግባር

"ጓደኞቼ" የሚለውን ምንባብ ከማንበባችሁ በፊት የሚከተለውን ጥያቄ በቃላችሁ መልሱ።

"ለፍሬ መብቃት" እና "መና የቀረ ምክር" በሚሉት ንዑሳን ርዕሶች የተጻፉትን ታሪኮች አስታውሳችሁ ገፀባህርያቱን እያወዳደራችሁና እያነጻጸራችሁ ተናገሩ።

### ማንበብ

#### ተግባር

"ጓደኞቼ" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት በፍጥነት አቀላጥፋችሁ አንብቡ።

## መናገር

### ውይይት

#### ተግባር

በሚከተሉት ሀሳቦች ላይ በቡድን በመወያየት የግል አስተያየቶቻችሁን ለቡድን አባሎቻችሁ ግለጹ።

ሀ. እናንተ የሱሰኛው የድሮ ጓደኛ ብትሆኑ ምን ታደርጉ ነበር? ለምን?

ለ. ሱሰኛው ልጅ የመምህሩን ምክር ያልተጠቀመበት ለምን ይመስላችኋል? እናንተ መምህሩን ብትሆኑ ምን ታደርጉ ነበር? ለምን?

## ሰዋስው

### ምድብ ተውላጠስምን፣ አገናዛቢ ተውላጠስምንና ዘርፍን መለየት

#### ተግባር 1

ተስማሚ ተውላጠስምን በክፍት ቦታው በማስገባት ዓረፍተነገሩን አሟሉ።

ሀ. ________ አኩሪ ተግባር የፈፀሙ ናቸው::

ለ. ________ የሀገር ፍቅር ስሜት ሊያድርብን ይገባል።

ሐ.________ ከመጫወት ማጥናት ሳይሻልህ አይቀርም።

መ.________ ውይይት በማድረግ ችግራቸውን ይፈታሉ።

ሠ.________ ጠንክራችሁ በማጥናት ለሽልማት መብቃት አለባችሁ።

#### ተግባር 2

የተሠመረባቸውን ሐረጋት በምሳሌው መሠረት ቀይራችሁ ዓረፍተነገሮችን እንደገና ጻፏቸው።

ምሳሌ፡- <u>የእሷ ቦርሳ</u> ያምራል።

<u>ቦርሳዋ</u> ያምራል።

ሀ. <u>የአንተ ኮት</u> ታጠበ።

ለ. <u>የእኔ እርሳስ</u> ጠፋ።

ሐ. <u>የእነሱ ቤት</u> ሩቅ ነው።

መ. <u>የእናንተን ግጥም</u> አሳተማችሁ።

ሠ. <u>የእኛ መምህሮች</u> ወደትምህርትቤት ሄዱ።

ረ. <u>የአንቺ እናት</u> በጣም ደግ ናቸው።

## ተግባር 3

የሚከተሉትን ሐረጋት በማንበብ አገናዛቢ ተውላጠ ስሙን ከንብረቱ ለይታችሁ ጻፉ።

ሀ. የእኔ ደብተር

ለ. የአንቺ ሀብት

ሐ. የአንተ እህት

መ. የእነሱ ወርቅ

ሠ. የእሷ መጽሐፍ

ረ. የእሱ ልጅ

## የቃላት ጥናት

### መነጠልና ማጣመር

**ተግባር**

የሚከተሉትን ቃላት ነጥላችሁና አጣምራችሁ አንብቡ።

| | ነጣጥሎ ማንበብ | አጣምሮ ማንበብ |
|---|---|---|
| ሀ | አልተሟሉ-ል-ኝ-ም | አልተሟሉልኝም |
| ለ | እኳት-ን-አለ-ሁ | እኳትናለሁ |
| ሐ | አልነግር-ኣችሁ-ም | አልነግራችሁም |
| መ | ከሚርመሰመስ-ኡ-ት | ከሚርመሰመሱት |
| ሠ | የሚሸፍን-ል-ኝ | የሚሸፍንልኝ |
| ረ | አካባቢ-ያዊ | አካባቢያዊ |

## ማንበብ

**ህይወት በየፈርጁ**

### ቅድመንባብ

### ከሥዕልና ከርዕስ የምንባብን ሀሳብ መገመት

**ተግባር**

የሚከተሉትን የቅድመንባብ ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. ከንዑስ ርዕሶቹ ሥር ያሉትን ሥዕሎች ተመልከቱና የተረዳችሁትን ግለጹ።

ለ. "አትርፍ ባይ..." ነጠብጣቦቹን ሊተካ የሚችል ሀሳብ ምን ይመስላችኋል? ምን መልዕክት ያስተላልፋል?

### የማንበብ ሂደት

### ምንባቦችን በማነጻጸርና በማወዳደር ማንበብ

**ተግባር**

ቀጥሎ "ህይወት በየፈርጁ" በሚል ዋና ርዕስ ሥር "የህይወት ውጣ ውረድ"እና

“አተርፍ ባይ…” በሚሉ ንዑሳን ርዕሶች የቀረቡትን ምንባቦች ርስበርስ በማነጻጸርና በማወዳደር አንብቡ።

## ሕይወት በየፈርጁ

### የህይወት ውጣውረድ



የገጠር ልጅ ነኝ። 15 ዓመት ሞልቶኛል። አውቶቡስ ተራ አካባቢ ሊስትሮ ሆኜ እሠራለሁ። ከተገኘ ደግሞ እንደአቅሜ ዕቃ እሸከማለሁ። የዕለት ጉርሴን ለማሟላት ሌት ተቀን እኳትናለሁ። ለምግብ የሚሆን ሳንቲም ሳገኝ ለመኝታ ክፍያ ይጎድልብኛል። መኝታዬ ሲመቻችልኝ ደግሞ ጦሜን ወዬ አድራለሁ። ዛሬ ግን ሁለቱም አልተሟሉልኝም። ቁርስም ሆነ ምሳ አልበላሁም። የመኝታዬም ነገር አስጨንቆኛል። ማደሪያ ወለል የሚያከራዩኝም ስለተማረሩ <u>በዱቤ</u> አያሳድሩኝም። የአውቶቡስ ማረፊያውን አጥር ተደግፌ ረሃቤን ማዳመጥ ጀመርኩ። ከተለያዩ አቅጣጫዎች መኪናዎች ይመጣሉ፤ እንደገና ይሄዳሉ። ይህን መሰል ዘወትራዊ ትርዒት ልብ ብዬ ባላውቅም ዛሬ ግን ትኩረቴን ስቦታል። አጎቴ “አዲስ አበባ ውስጥ የሰውና የመኪና ቊጥር እኩል ነው” ያለው ትክክል መሰለኝ። ሰው ሲርበው ነው እንዴ ተመልካችና አድማጭ የሚሆነው?

ከሚርመሰመሱት መኪናዎች መካከል አንዱ ከፊትለፊቴ ቆመ። ትልቅ ሻንጣ የያዘ አንድ ወጣት ከመኪናው ወረደ። ሻንጣውን እንድሸከምለት ጠራኝ፤ ሄድኩ። ለመኝታ ክፍያ የሚሸፍንልኝን ያክል ብቻ ጠየቅሁት፤ ተስማማን። ለመኝታዬ አንድ ብር በማግኘቴ ተደሰትኩ። እኔም ለመሸከም ተዘጋጀሁ። ሻንጣው ግን በእኔ

አቅም በቀላሉ የሚንቀሳቀስ አልነበረም። እንደምንም አሽከመኝና ወደአንድ ሆቴል አመራን። ትከሻዬ እየተንቋቋ ሻንጣውን ከሆቴሉ አደረስኩለት። ወጣቱም አንዱን ብር ይሰጠኛል ብዬ ስጠብቅ “ዝርዝር የለኝም” በሚል ሰበብ አምሳ ሳንቲም ብቻ ወርውሮ አሰናበተኝ። ታዲያ ራት መብላት ባልችልም በግማሽ ክፍያ እስከእኩለ ሌሊት ወለል የሚያከራየኝ አገኝ ይሆን? እስኪ ልፈልግ።

## “አተርፍ ባይ…”



ስሜን አልነግራችሁም። ዕድሜዬ ግን 55 ዓመት ነው። የኖርኩት በአንድ ትልቅ ከተማ ውስጥ ነበር። ከጥቂት ዓመታት በፊት ባለፀጋ ነበርኩ፤ያውም ሀገር ያወቀኝ <u>ፀሀይ የሞቀኝ</u>። ባገኘሁት ገቢ መጠን የሚጠበቅብኝን ያህል ግብር በወቅቱ እከፍል ነበር። በተለያዩ አካባቢያዊ ልማቶችም እሳተፍ ነበር። በዚህም ማህበረሰቡ አጥብቆ ይወደኝ ነበር። <u>ህጋዊ ነጋዴ</u> በመሆኔም ዝናዬ ከፍ ከፍ አለ። በሀብቴም በከተማዋ ውስጥ ካሉ ነጋዴዎች ተርታ መሰለፍ ቻልኩ።

ይሁን እንጂ ከአንድ ክፉ ሰው ጋር ተወዳጀሁ። አዲሱ ወዳጄ ግብር መክፈሌን እንደሞኝነት፣ በልማት መሳተፌን እንደቂልነት ቆጠረው። እኔም ሁሉም ነገር እኛን የሚጠቅም መሆኑን በማውሳት ተከራከርኩት። የንግድ አቅጣጫዬን ብቀይር በአጭር ጊዜ ልበለፅግ እንደምችልም ገለፀልኝ፤ የሚነግረኝን እንድፈፅምም

ወተወተኝ። ሥራው "የአየር ባየር ንግድ" መሆኑንም ገለጸልኝ። እኔም ተስማማሁ። ሥራውን ለመጀመር ብዙ ብር እንደሚያስፈልግ ነገረኝ። በመጋዘን ውስጥ ያሉኝን ዕቃዎች ሸጬ ቀሪውን ደግሞ ቤቴንና መጋዘኔን አስይዤ ከባንክ ተበደርኩ። ከእኔ የተሻለ ሀብት እንዳለው ስለገለፀልኝ ለቀብድ የሚያስፈልገውን ብር ያለደረሰኝ ሰጠሁት። ሦስት መኪናዎች እንደምንገዛና "አየር ባየር" በጥሩ ትርፍ ለሌላ ሰው እንደምንሸጣቸው ነገረኝ። የትርፉ መጠን ስላማለለኝ ቀሪ ገንዘቤን ሁሉ ለወዳጄ አስረከብኩት።

ገንዘቤ ከነትርፉ በቅርቡ እንደሚመለስ ስጠብቅ ወዳጄ የውኃ ሽታ ሆኖ ቀረ። በሕግ እንዳልይዘው ደረሰኝ የለኝም። በዚህ የተነሳ በፀና ታምሜ ሆስፒታል ገባሁ። ከአንድ ዓመት በላይም የአልጋ ቁራኛ ሆንኩ። በመካከል ለባንክ ብድር በዋስትና ያስያዝኩት መጋዘኔና መኖሪያ ቤቴ በባንኩ ተሸጠ። እንድለቅም ተገደድኩ። ከሕግ ውጪ ሆኜ ህጋዊ ሀብቴን አስወሰድኩት። ሀብትን ተጠንቅቀው ካልያዙት የጧት ጤዛ ነው። የሚያውቁኝ ሁሉ ጠሉኝ። ቤተሰቦቼም ተበተኑ። ጤናዬ ስላልተመለሰ ሥራ ለመሥራትም አልቻልኩም። የዕለት ጉርሴን መሸፈንም ተሳነኝ። እናም ወደማልታወቅበት ከተማ መጥቼ የጎዳና ተዳዳሪ ሆንኩ።

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር 1

በምንባቡ መሠረት ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልሶችን በጽሑፍ ግለጹ።

ሀ. "ህይወት በየፈርጁ" ከሚለው ምንባብ ተራኪው (የገጠሩ ልጅ) የሚተዳደረው በምን ዓይነት ሥራ ነው?

ለ. "ህይወት በየፈርጁ" ከሚለው ምንባብ ሊስትሮውንና ባለፀጋውን ነጋዴ የሚያመሳስላቸው ምንድን ነው? የሚያለያያቸውስ?

ሐ. "ህይወት በየፈርጁ" ከሚለው ምንባብ ባለፀጋው ነጋዴ በማህበረሰቡ ዘንድ የሚወደዱት በምን ምክንያት ነበር? ተወዳጅነታቸው እስከመጨረሻው የዘለቀ ነበር? ለምን?

መ. "ህይወት በየፈርጁ" ከሚለው ምንባብ "አተርፍ ባይ አጉዳይ" የሚለው ርዕስ ከምንባቡ ሀሳብ ጋር ምን ያህል ተዛማጅነት አለው? እንዴት ይታወቃል?

ሠ."ህይወት በየፈርጁ" ከሚለው ምንባብ ሊስትሮውና ባለፀጋው ነጋዴ ከችግራቸው ለመውጣት ምን ማድረግ ይጠበቅባቸዋል?

ረ. "ህይወት በየፈርጁ" ከሚለው ምንባብ ባለፀጋው ነጋዴ ገንዘባቸውን ለወዳጃቸው መስጠታቸው ተገቢ ነው ብላችሁ ታስባላችሁ?ለምን?

### ተግባር 2

የሚከተለውን የቢጋር ሠንጠረዥ በምንባቡ መሠረት በትክክል አሟሉ።




## 8ኛ ቀን

### ቃላት

**ለቃላትና ለሐረጋት ፍቺ መስጠት**

**ተግባር 1**

በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ለተሠመረባቸው ቃላትና ሐረጋት ዐውዳዊ ፍቻቸውን

በቃላችሁ ስጡ።

ሀ. የአየርባየር ንግድ ሀገርንና ወገንን ይጎዳል። (አንቀጽ 2)

ለ. የሚያከራዩኝም ስለተማረሩ በዱቤ አያሳድሩኝም። (አንቀጽ 1)

ሐ. ሀገር ያወቀኝ ፀሐይ የሞቀኝ ባለፀጋ ነበርኩ። (አንቀጽ 1)

መ. ህጋዊ ነጋዴ በመሆኔ ዝናዬ ከፍ ያለ ነው። (አንቀጽ 1)

ሠ. የጠበቅሁት ወዳጄ የውኃ ሽታ ሆኖ ቀረ። (አንቀጽ 3)

ረ. በዋስትና ለባንክ ያስያዝኩት መጋዘኔና መኖሪያ ቤቴ ተሸጠ። (አንቀጽ 3)

ሰ. ሀብትን ተጠንቅቀው ካልያዙት የጧት ጤዛ ነው። (አንቀጽ 3)

ሸ. ከአንድ ዓመት በላይ የአልጋ ቁራኛ ሆንኩ። (አንቀጽ 3)

### ተግባር 2

የሚከተሉትን ቃላት ፍቺ ከመዝገበ ቃላት በመፈለግ ጻፉ።

| | | |
|---|---|---|
| ሀ. ወለል | መ. መወዳጀት | ሰ. ማውሳት |
| ለ. ሰበብ | ሠ. መወትወት | ሸ. መኳተን |
| ሐ. ግብር | ረ. ቀብድ | ቀ. ጎዳና |

## መጻፍ

### ድርሰት መጻፍ

### ምንባብን አሳጥሮ መጻፍ

### ተግባር

"አትርፍ ባይ - - -" የሚለውን ምንባብ በአንድ አንቀጽ አሳጥራችሁ ጻፉ። በምትጽፉበት ጊዜ የሚከተሉትን መመሪያዎች ተግባራዊ አድርጉ።

- ምንባቡን ቢያንስ ለሁለት ጊዜ ያህል አንብቡ።
- ዋናና ዝርዝር ሀሳቦችን ለዩ።
- ኃይለቃሉ ላይ በማተኮር ለአንቀጹ የማጠቃለያ ሀሳብ ጻፉ።
- የምትጽፉት አንቀጽ የሀሳብ ቅደምተከተሉን የጠበቀ መሆኑን አረጋግጡ።

### የአጻጻፍ ሥርዓት

### ተግባር

ተገቢ ሥርዓተነጥቦችን በተገቢ ቦታ በመጠቀም አንቀጹን እንደገና ጻፉ።

*ስኬታማ ለመሆን መውጣት መውረድ ያስፈልጋል (1) በዕቅድ መመራት*

*(2) ሥራን ሳይታክቱ መሥራትና ከሰዎች ለመማር መጣር የስኬት ቁልፍ በሮች ናቸው (3) ቅናት (4) ምቀኝነትና ተንኮል ለስኬት እንቅፋት የሆኑ መጥፎ ሥነምግባሮች ናቸው (5) እንዲሁም የሚሠሩ ሰዎችን በአሉባልታና በወሬ ማደናቀፍም ሌላው የስኬት አሉታዊ ተጽዕኖ ነው (6) ስለዚህ እነዚህን እንቅፋቶችና ተጽዕኖዎች በማስወገድ ዓላማን ከግብ ለማድረስ መጣር ትልቅ ብልህነት ነው (7)*

## 9ኛ ቀን

## አቀላጥፎ ማንበብ

### ህይወት በየፈርጁ

### ቅድመንባብ

### የምንባብን ሀሳብ አስታውሶ መናገር

#### ተግባር

"ህይወት በየፈርጁ" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ በማስታወስ ሊተላለፍ የተፈለገውን መልዕክት ተናገሩ።

### ማንበብ

#### ተግባር

"ህይወት በየፈርጁ" በሚል ርዕስ ከቀረቡት ንዑሳን ርዕሶች ውስጥ "የህይወት ውጣ ውረድ" የሚለውን ምንባብ በ1 ደቂቃ ውስጥ አቀላጠፋችሁ አንብቡ።

## መናገር

#### ተግባር

"ህይወት በየፈርጁ" የሚለውን ምንባብ መሠረት በማድረግ በቡድን ሆናችሁ በቢጋር ሠንጠረዡ ውስጥ ከሰፈሩት ሀሳቦች አንዱን በመምረጥ በክፍል ውስጥ ንግግር አድርጉ።







## ሰዋስው

### ምድብ ተውላጠስምን መጠቀም፣ ዘርፍን መለየት

### ተግባር 1

የሚከተሉትን ተውላጠ ስሞች በመጠቀም ዓረፍተነገር ሥሩ።

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| እኛ | እነሱ | አንተ | እኔ | አንቺ | እናንተ | እሷ |

### ተግባር 2

በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ውስጥ ባለንብረትነት የሚያመለክቱትን ቃላት አስምሩ።

ሀ. መጽሐፋቸውን ስለሸፈኑ ተሸለሙ።

ለ. ዘርፌ ልጇን በደንብ ትንከባከባለች።

ሐ. እውቀታችሁ የማይሰረቅ ሀብታችሁ ነው።

መ. ትምህርትቤቴ የዕውቀት መሠረቴ ናት።

ሠ. ከትምህርትቤት ሲመለስ የደንብ ልብሱን ይቀይራል።

ረ. ጋቢያቸው ስለቆሸሸ አጠቡት።



# ኤች.አይ.ቪ./ኤድስ በኢትዮጵያ

ምዕራፍ 7

## የኤች አይ/ቪ ኤድስ መተላለፊያውና መከላከያው

1ኛ ሳምንት 1ኛ ቀን

## የቃላት ጥናት

### መነጠልና ማጣመር

**ተግባር**

የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት ነጣጥላችሁና አጣምራችሁ አንብቡ።

| ነጣጥሎ ማንበብ | | አጣምሮ ማንበብ |
|---|---|---|
| ሀ | ሆ-ስ-ፒ-ታ-ል | ሆስፒታል |
| ለ | ቫ-ይ-ረ-ስ | ቫይረስ |
| ሐ | የሚ-ጠቀም-ኡ-ብ-ኣቸው-ን | የሚጠቀሙባቸውን |
| መ | እየ-ተሰራጨ-ብ-ኣቸው | እየተሰራጨባቸው |
| ሠ | እንደሚ-ተላለፍ-ብ-ኣቸው | እንደሚተላለፍባቸው |
| ረ | ከ-ተገለገለ-ብ-ኣቸው | ከተገለገሉባቸው |

## ማንበብ

### ኤች.አይ.ቪ. እና መተላለፊያዎቹ

### ቅድመንባብ

### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

**ተግባር**

ምንባቡን ከማንበባችሁ በፊት የሚከተለውን ጥያቄ በጽሑፍ መልሱ።

የኤች.አይ.ቪ. ቫይረስ በደም ውስጥ ለመኖር ምክንያት የሆኑ ነገሮችን ዘርዝራችሁ ጻፉ።




## የማንበብ ሂደት

### የሀሳቦችን ምክንያትና ውጤት በማጤን ማንበብ

**ተግባር**

ቀጥሎ "ኤች.አይ.ቪ. እና መተላለፊያዎቹ" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ የሀሳቦቹን የምክንያትንና ውጤት ግንኙነት እያጤናችሁ በለሆሳስ አንብቡ።

## ኤች.አይ.ቪ. እና መተላለፊያዎቹ

ኤች.አይ.ቪ. የሰውነትን በሽታ የመከላከል አቅም በማዳከም ለሌሎች በሽታዎች የሚያጋልጥ ቫይረስ (ረቂቅ ተሃዋስ) ነው። ቫይረሱ በዓለም ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ የታወቀው ከ30 ዓመት በፊት ሲሆን፣ በኢትዮጵያ ደግሞ በ1977 ዓ.ም. ነው። በኢትዮጵያ የመጀመሪያው የኤድስ ሕመምተኛ የታወቀው ከሁለት ዓመታት በኋላ ነበር። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ በሽታው በከፍተኛ ፍጥነት እየተሰራጨ ይገኛል። በ2000 ዓ.ም. በኢትዮጵያ 1.2 ሚሊዮን ሰዎች ከኤች.አይ.ቪ. ጋር ይኖሩ እንደነበር በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ተገምቷል። ይህ አሃዝ ኢትዮጵያን በዓለም ላይ ቫይረሱ በከፍተኛ ፍጥነት እየተሰራጨባቸው ከሚገኙ ሀገሮች አንዷ አድርጓታል።

ቫይረሱ በተለያዩ መንገዶች ይተላለፋል። መተላለፊያ መንገዶችን ማወቅ ራስን ለመጠበቅና የበሽታውን ሥርጭት ለመቀነስ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው።

ቫይረሱ ከሚተላለፍባቸው መንገዶች አንዱ ልቅ የግብረሥጋ ግንኙነት ነው። ከቫይረሱ ጋር ከሚኖሩ ሰዎች ጋር በሚደረግ ጥንቃቄ የጎደለው የወሲብ ግንኙነት ቫይረሱ ወደጤነኞቹ ይተላለፋል። በዓለም ላይ ከ75 በመቶ በላይ የሚሆኑት የቫይረሱ ተጠቂዎች የተያዙት በዚሁ መንገድ እንደሆነ ይገመታል።

ቫይረሱ ከእናት ወደልጅም ይተላለፋል። በኤች.አይ.ቪ.ኤድስ ከተያዙ እናቶች የሚወለዱ ሕፃናት ቫይረሱ እንደሚተላለፍባቸው ተረጋግጧል። በእርግዝና ጊዜ ተገቢ የሕክምና ክትትል ካልተደረገ ቫይረሱ ከእናት ወደልጅ በሦስት መንገዶች ይተላለፋል። በእርግዝና ወቅት ከእናት ወደጽንስ ሊተላለፍ ይችላል፤ በወሊድ ጊዜ በሚኖር የደም ንክኪም ቫይረሱ ወደጨቅላው ሊዛመት ይችላል፤ ሕፃናት የእናት ጡት ወተት በሚመገቡበትም ጊዜ ቫይረሱ ሊተላለፍ ይችላል።

በተበከለ ደም ልገሳ አማካይነትም ቫይረሱ ይተላለፋል። በተለያዩ የሕክምና ተቋማት ውስጥ የሚታከሙ ሰዎች ተጨማሪ ደም ሊያስፈልጋቸው ይችላል። በዚህ ወቅት የሚሰጣቸው ደም በኤች.አይ.ቪ. የተበከለ ከሆነ ቫይረሱ ይተላለፍባቸዋል። ይህ እንዳይሆን ግን ሐኪሞች የለጋሾቹን ደም በመመርመር ከፍተኛ ጥንቃቄ ያደርጋሉ።

ቫይረሱ በደም ንክኪ ሊበከሉ በሚችሉ ሌሎች መሳሪያዎች አማካይነትም ይተላለፋል። ቫይረሱ ያለባቸው ሰዎች የተጠቀሙባቸውን መርፌ፣ ምላጭ፣ ወረንጦና የመሳሰሉ ስለታም ነገሮች ጤነኛ የሆኑ ሰዎች ከተገለገሉባቸው ቫይረሱ ሊተላለፍባቸው ይችላል። አደንዛዥ ዕፅ በመርፌ የሚወስዱ ሰዎች ቫይረሱ የሚተላለፍባቸው መርፌ ተጋርተው ስለሚጠቀሙ ነው። በተጨማሪም ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ለኤች.አይ.ቪ. መተላለፊያ መንገዶች ናቸው። ለምሳሌ በግርዛት፣ በንቅሳት፣ በእንጥል ማስቆረጥ፣ በግግ ማስፈልፈል ወ.ዘ.ተ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች አማካይነት በሚፈጠር የደም ንክኪ ቫይረሱ ሊተላለፍ ይችላል።

በአንጻሩ ደግሞ ቫይረሱ የማይተላለፍባቸውን መንገዶች ማወቁም ከአጉል ፍርሀትና ጭንቀት ይገላግላል። በመሆኑም ከቫይረሱ ጋር ከሚኖሩ ሰዎች ጋር እጅ ለእጅ በመጨባበጥ፣ ጉንጭ ለጉንጭ በመሳሳም፣ መታጠቢያቤት በጋራ በመጠቀም፣ አብሮ በመብላት፣ በአንድ ቤት ውስጥ አብሮ በመኖር አይተላለፍም። በትንፋሽ፣ በሳልና በንጥሻ መተላለፍ አይችልም። በትንኞችና በሌሎች ደም መጣጭ ነፍሳትም ቫይረሱ አይዛመትም። እርሳስ፣ እስክሪቢቶ፣ ደብተርና መጽሐፍ ወዘተ. በመዋዋስም ቫይረሱ ከሰው ወደሰው አይተላለፍም።

(ኢፌዴሪ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር። 2011። *ኤች.አይ.ቪ. ፕሪቬንሽን ፓኬጅ።* ገጽ 2-4፤ ሥትዝጥም ኢንስቲትዩት። 1995። *የኤች.አይ.ቪ./ ኤድስ ትምህርት።* ገጽ 1-30 መጠነኛ ለውጥ ተደርጎበት የተወሰደ።)

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር 1

በምንባቡ መሠረት ቫይረሱ የሚተላለፍባቸውንና የማይተላለፍባቸውን መንገዶች ለይታችሁ ቀጥሎ በደብተራችሁ ጻፉ።

| ኤች.አይ.ቪ. የሚተላለፍባቸው መንገዶች | ኤች.አይ.ቪ. የማይተላለፍባቸው መንገዶች |
|---|---|
| •<br>•<br>•<br>•<br>• | •<br>•<br>•<br>•<br>• |

### ተግባር 2

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. ኤች.አይ.ቪ. ከእናት ወደልጅ እንዴት ይተላለፋል?

ለ. በጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ኤች.አይ.ቪ. እንዴት ሊተላለፍ ይችላል?

ሐ. በዓለም ላይ ኤች.አይ.ቪ. በከፍተኛ ፍጥነት ከሚሰራጭባቸው ሀገራት መካከል ኢትዮጵያ የተመደበችበት ምክንያት ምንድን ነው?

መ. ኤች.አይ.ቪ. የማይተላለፍባቸውን መንገዶች ማወቁ ምን ጠቀሜታ አለው?

ሠ. ሰዎች ሁሉንም የ"መ" ሕጎች ቢጠብቁም በኤች አይ ቪ/ ኤድስ ሊያዙ ይችላሉ። ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል ብላችሁ ታስባላችሁ?

## 2ኛ ቀን

## ቃላት

### ቃላትንና ሐረጋትን በተመሳሳይ መተካት

### ተግባር

በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች የተሠመረባቸውን ቃላትና ሐረጋት በምንባቡ መሠረት በተመሳሳይ ቃላትና ሐረጋት ተክታችሁ ጻፉ።

ሀ. የኤች.አይ.ቪ./ኤድስ በሽተኞች <u>ቁጥር</u> በየዓመቱ እየጨመረ ነው።(አንቀጽ 1)

ለ. ኢትዮጵያ ኤች.አይ.ቪ./ኤድስ በፍጥነት <u>ከሚዛመትባቸው</u> ሀገራት እንዷናት። (አንቀጽ 3)

ሐ. ኤች.አይ.ቪ. ቫይረስ <u>አስተላላፊ</u> ከሆኑ ሰዎች ጋር ወሲባዊ ግንኙነት መፈፀም ለኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ያጋልጣል።(አንቀጽ 3)

መ. በርካታ ወጣቶች የአደንዛዥ <u>ተክል</u> ከተጠቀሙ ራሳቸውን መቆጣጠር

አይችሉም። (አንቀጽ 6)

ሠ. ከኤች.አይ.ቪ. ኤድስ ቫይረስ ጋር ከሚኖሩ እናቶች የሚወለዱ ሕፃናት ረቂቁ ተሃዋስ እንደሚተላለፍባቸው ተረጋግጧል።(አንቀጽ 4)

ረ. የሕክምና ማዕከላት ለኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ተጠቂዎች ተገቢ ክትትል ማድረግ አለባቸው። (አንቀጽ 5)

## መጻፍ

### ድርሰት መጻፍ

### በምክንያትና ውጤት ስልት ድርሰት መጻፍ

### ተግባር 1

በቢጋር ሠንጠረዡ በሠፈሩት ሀሳቦች መነሻነት በምክንያትና ውጤት ስልት “ኤች. አይ.ቪ. እና መዘዙ” በሚል ርዕስ ባለሦስት አንቀጽ ድርሰት ጻፉ።




### ተግባር 2

የሚከተሉትን ጉዳዮች በተመለከተ የትምህርትቤታችሁን ጤናና ፀረ ኤድስ ክበብ ተጠሪ መምህር ጠይቃችሁ ያገኛችሁትን ሀሳብ በጽሑፍ ግለጹ።

ሀ. የክበቡ የአባላት ብዛት

ለ. የክበቡ ዋናዋና ተግባራት

ሐ. የክበቡ ዓላማ

መ. የክበቡ የገቢ ምንጭ

ሠ. የክበቡ የወደፊት ዕቅድ

ረ. ያጋጠሙ ችግሮች

ሰ. መፍትሔዎች

## የአጻጻፍ ሥርዓት

### የቃላትን ቅደምተከተል እንደገና በማደራጀት ዓረፍተነገር መጻፍ

**ተግባር**

የቃላቱን ቅደምተከተል እንደገና በማደራጀት ዓረፍተነገሩን አስተካክላችሁ ጻፉ።

ሀ. ነው/ረቂቅ/ኤች.አይ.ቪ./ተሀዋስ።

ለ. ደም መጣጭ/ኤች.አይ.ቪ./ በሆኑ ነፍሳት/አይተላለፍም።

ሐ. የሚታከሙ/ተኝተው/ሰዎች/ይችላል/ሊያስፈልጋቸው/ደም።

መ. የተጠቀሙበትን/የተያዙ/በቫይረሱ/ሰዎች/መጠቀም/መርፌ/ለኤች.አይ.ቪ. ያጋልጣል።

## 3ኛ ቀን

## አቀላጥፎ ማንበብ

### ኤች.አይ.ቪ. እና መተላለፊያዎቹ

**ቅድመንባብ**

**ተግባር**

"ኤች.አይ.ቪ. እና መተላለፊያዎቹ" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ከማንበባችሁ በፊት የምንባቡን ዋናዋና ሀሳቦች በክፍል ውስጥ አቅርቡ።

**ማንበብ**

**ተግባር**

"ኤች.አይ.ቪ. እና መተላለፊያዎቹ" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ አንድ አንድ ዓረፍተነገር ርስበርስ እየተቀባበላችሁ ድምጽ በማሰማት በፍጥነት አንብቡ።

## ማዳመጥ

### ኤች.አይ.ቪ. እና መከላከያው

**ቅድመማዳመጥ**

**ተግባር**

"ኤች.አይ.ቪ. እና መከላከያው" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ከማዳመጣችሁ

በፊት የሚከተለውን የቢጋር ሠንጠረዥ አሟሉና ጻፉ።




## የማዳመጥ ሂደት

### ተግባር

"ኤች.አይ.ቪ. እና መከላከያው" በሚል ርዕስ መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን ምንባብ የሀሳቦችን ምክንያትና ውጤት ግንኙነት በማስተዋል አዳምጡ።

## አዳምጦ መረዳት

### ተግባር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. ኤች.አይ.ቪ. ቫይረስ በዋናነት የሚተላለፍባቸው መንገዶች ምን ምን ናቸው?

ለ. አንድ ወንድና አንዲት ሴት፣ አንድ ለአንድ ጸንተው የሚቆዩበት የ"መ" ሕግ ምን ይባላል?

ሐ. ራስን ማወቅ ከ"መ" ሕጎች የትኛውን ያመለክታል? ጠቀሜታውስ ምን ይመስላችኋል?

መ. ኤች.አይ.ቪ.ን ሊያስተላልፉ የሚችሉ ቁሳቁሶችን ዘርዝሩ።

ሠ. ተማሪዎች ስለኤች.አይ.ቪ. በቂ ዕውቀት የሚኖራቸው እንዴት ነው?

ረ. ሕፃናት በኤች.አይ.ቪ. ቫይረስ እንዳይያዙ እንዴት መከላከል የሚቻል ይመስላችኋል? አብራሩ።

ሰ. ማንኛውም ሰው ከኤች.አይ.ቪ. ነፃ ነኝ ማለት ይችላል? ለምን?

## ሰዋስው

### ተውሳከግስንና እምርነት አመልካች ቅጥያዎችን መለየት

### ተግባር 1

በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ተውሳከግስ የሆኑትን ቃላትና ሐረጋት ለይታችሁ ጻፉ።

ምሳሌ:-

1. ልጁ ከደረጃው ላይ ክፉኛ ወደቀ። በዚህ ዓረፍተነገር “ክፉኛ” የሚለው ቃል ተውሳከግስ ነው።
2. አስቴር በጊዜ ተኛች። በዚህ ዓረፍተነገር “በጊዜ” የሚለው ሐረግ ተውሳከግስ ነው።

ሀ. አሚሚቱ ምንኛ ያሳዝናል።

ለ. አለምነሽ በድንገት መጣች።

ሐ. አቤል ጥያቄውን በፍጥነት መለሰ።

መ. መርከቧ ወደወደቡ ገና አልደረሰችም።

ሠ. ዘሀራ ወደትምህርትቤት እየሮጠች ሄደች።

ረ. ዝናቡ ሳይመጣ ወደቤታችን ቶሎ እንሂድ።

### ተግባር 2

የሚከተሉትን ስሞች ከእምርነት አመልካች ቅጥያዎች ጋር በማጣመር ጻፉ።

ሀ. ፈረስ-ኡ

ለ. በሬ-ው

ሐ. ፍየል-ዋ

መ. ወንበር-ኡ

ሠ. በጊት-ዋ

ረ. ልጂት-ዋ

ሰ. አርሶአር-ዋ

## ማንበብ

### "በሽታውን የደበቀ..."

### ቅድመንባብ

### ከርዕስና ከሥዕል የምንባብ ሀሳብ መገመት

**ተግባር**

"በሽታውን የደበቀ..." በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ከማንበባችሁ በፊት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. "በሽታውን የደበቀ---" የሚለውን ጅምር ሀሳብ አሟልታችሁ የሚያስተላልፈውን መልዕክት ተናገሩ።

ለ. በመጀመሪያው ሥዕል የሚታየው ሰውዬ ምን የሆነ ይመስላችኋል? አብረው ያሉትስ አዛውንት ምን እያደርጉ ነው?

ሐ. በሁለተኛው ሥዕል የሚታዩት አዛውንት ምን የሆኑ ይመስላችኋል? ለምን?

### የማንበብ ሂደት

የምክንያትና ውጤት ግንኙነትን በማስተዋልማንበብ

**ተግባር**

"በሽታውን የደበቀ---" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ የሀሳቦችን የምክንያትና ውጤት ግንኙነት በማስተዋል አንብቡ።

# "በሽታውን የደበቀ..."



በአንድ ፋብሪካ ውስጥ በወዛደርነት ተቀጥሮ ይሠራል። የሚከፈለው በሠራው ሰዓት መጠን ነው። ስለሆነም በቀንና በሌሊት ፈረቃ ብዙ ሰዓት በመሥራት ጥሩ ገቢ ያገኛል። ዕድሜው 21 ዓመት ነው። ትዳር ግን አልመሰረተም። አባቱ በልጅነቱ ሞተዋል። አሁን የሚኖረው በዕድሜ ከገፉት እናቱ ጋር ነው። እናቱን በጣም ይወዳቸዋል። እንዳይከፉቸውም የቻለውን ሁሉ ያደርግላቸዋል፤ ይንከባከባቸዋል። እናቱም ለልጃቸው የተለየ ፍቅር አላቸው። በእርጅና የተነሳ ጉልበታቸው ተዳክሟል።ይህን ብቸኛ ልጅ ባይጥልላቸው ኖሮ ከባድ የኑሮ ፈተና እንደሚገጥማቸው ሲያስቡት ፈጣሪያቸውን ያመሰግናሉ።

በጥሩ ሥነምግባሩ የሚታወቀው ይህ ወጣት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን አዲስ ባህርይ አመጣ። አንድ ቀን ከሥራ ውሎ ሲመለስ "በሥራ የደከመ ሰውነታችንን እናፍታታው" በማለት ከሥራ ባልደረባው ጋር ወደአንድ መጠጥቤት ገቡ። የመጠጥ ልምድ ባይኖረውም አልፎ አልፎ ግን ይቀማምሳል። በዚያን ቀን በጓደኛው ግብዣ ሦስት መለኪያ አረቄ ጠጥቶ ወደቤቱ ሄደ። በዕለቱ የተመለከታት ቀደም ሲል በርካታ የወንድ ደንበኞች የነበሯት አስተናጋጅ ልቡን ነጠቀችው፤ ወደዳት። በውበቷም ስለተማረከ ከእሷ ተለይቶ መኖር እንደማይችል አመነ። እሷን ለማየት ሲል ወደመጠጥቤቱ መመላለስ አዘወተረ። ጥቂት ሰነባብቶ ከአስተናጋጇ ጋር የፍቅር ጓደኝነት መሠረተ። እሷ ሁሉ ነገሩ ሆነች። ወደሥራ ሲሄድም ሆነ ከሥራ ሲመለስ ሳያገኛት አያልፍም። አልፎ አልፎ የሌሊት ተረኛ መሆኑን ለእናቱ ይነግራቸውና ከልጅቷ ጋር ያድራል።

ከጥቂት ወራት በኋላ ግን ድካምና ሕመም ይሰማው ጀመር። ያ፣ ለወትሮው በየቀኑ ከአሥር ሰዓት በላይ ሠርቶ የማይደክመው ጀግና አሁን ሁለትና ሦስት ሰዓት እንደሠራ በላብ ይነከራል። አተነፋፈሱም ይለዋወጣል። አንድ ኩንታል ሲሸከም የወፍ ያህል የማይቆጥር የነበረው ትከሻ አሁን በአምሳ ኪሎ መንቋቋት ጀምሯል።

በአጭር ጊዜ ውስጥ ክብደቱ ክፉኛ ቀንሷል። ግራ ጎኑን ውጋት ያጣድፈዋል። በሳል ቁጥር ውጋቱን መቋቋም እያቃተው ያቃስታል። ህመሙ ያስጨነቃቸው እናቱና ጓደኞቹ እንዲታከም ደጋገመው መከሩት።

ህመሙ ሲበረታበት በቅርብ ወደሚገኝ ሆስፒታል ሄዶ ለመመርመር ወሰነ። ምልክቶቹን በሚገባ ያጤነችው የውስጥ ደዌ ሀኪም በማግባባት ካሳመነችው በኋላ የኤች.አይ.ቪ. ምርመራ እንዲደረግለት አዘዘች። ቫይረሱ በደሙ ውስጥ መኖሩ ተረጋገጠ። ሀኪሟ ብዙ ከመከረችውና ካረጋጋችው በኋላ ውጤቱን ገለፀችለት። በጣም ደነገጠ፤ ፈራ፤ ተንቀጠቀጠ። ለቫይረሱ ሊጋለጥ የቻለባቸው አጋጣሚዎች በዐይነህሊናው ታዩት። አዞረው፤ አቅለሸለሸው። ድንገት ከተቀመጠበት ተስፈንጥሮ በመነሳት ሆስፒታሉን ለቆ ወጣ። የሀኪሟን ምክር ችላ ብሎ ውጤቱን ለሌላ ሰው ላለመናገር ከራሱ ጋር ተማማለ። በኤች.አይ.ቪ. ቫይረስ በደም ውስጥ መኖሩን ሰዎች ከሚያውቁበትም ሞቱን መረጠ።

የኤች.አይ.ቪ. ቫይረስ በደሙ ውስጥ መኖሩን በመደበቁና ሕክምና ባለመጀመሩ ህመሙ እየፀናበት መጣ። ለሚጠይቁት ሁሉ ሳሉን በብርድ፣ ውጋቱን በንፋስ ማሳበብ ጀመረ። ይሁን እንጂ ከሥራ ቦታ የሚቆይበት ጊዜ እየቀነሰ፣ ተኝቶ የሚውልበት ጊዜ እየጨመረ መጣ። ከሁለት ወራት በኋላ ወደሥራ ቦታው መሄድ አቆመ። ህመሙ በረታበት፣ ክብደቱ ቀነሰ። ሰውነቱ ቆሰለ። ተኝቶ ካደረበት አልጋ ላይ ተኝቶ መዋል ጀመረ። ራሱን ችሎ መነሳትና ወደውጪ መውጣት አቃተው። የሰፈሩ ሰዎች ተወያይተው በቅርብ ወደሚገኝ የግል ክሊኒክ ወሰዱት። ህመሙ እየበረታ ሄዶ በአስረኛው ቀን ህይወቱ አለፈች።



በልጃቸው ሞት ከልብ ያዘኑት እናት ያለጧሪ በመቅረታቸው ስቃያቸው ጨመረ። ልጃቸው ጤነኛ በነበረበት ወቅት ያጠራቀሙትን ጥሪት ለሕክምና አውለውታል። አሁን በቤት ውስጥ የሚላስ የሚቀመስ ነገር የላቸውም። ከልጃቸው ሀዘን በተጨማሪ ርሀብ ቆርጥሞ ሊበላቸው ደርሷል። ሁሉንም ገመና ከታች በሆነው ቤታቸው ውስጥ መታገል ቢፈልጉም ሀዘንና ርሀብ ጎትተው ወደጎዳና አስወጧቸው። በየጎዳናው እያዘገሙ እድላቸውን በማማረር ማንባት የዘወትር ተግባራቸው ሆነ።

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. ባለታሪኩ ከጓደኛው ጋር ወደመጠጥቤት ባይገባ ኖሮ ለኤች.አይ.ቪ. የሚጋለጥ ይመስላችኋል? ለምን?

ለ. ችግርን መደበቅ ምን ጉዳት ያደርሳል?

ሐ. ባለታሪኩ የኤች.አይ.ቪ. ሕክምና ተከታትሎ ቢሆን ኖሮ የታሪኩ ፍጻሜ ምን ይሆን ነበር?

መ. የአምስተኛው አንቀጽ ዋና ሐሳብ ምንድን ነው?

ሠ. ባለታሪኩ የኤች.አይ.ቪ. ቫይረስ በደሙ ውስጥ እንዳለበት ሲረጋገጥ የወሰነው ውሳኔ ተገቢ ነበር ወይ? ለምን?

ረ. ከስድስተኛው አንቀጽ በመነሳት ኤች.አይ.ቪ. በማህበረሰቡ ላይ የሚያደርሰው ተጽዕኖ ምንድን ነው?

ሰ. በምንባቡ ሊተላለፍ የተፈለገው ዋና መልዕክት ምንድን ነው?

## 5ኛ ቀን

## ቃላት

## ዐውዳዊ የቃላት አጠቃቀም

### ተግባር

ከሚከተሉት ቃላትና ሐረጋት ተገቢ የሆኑትን መርጣችሁ ጽሑፉን አሟልታችሁ ጻፉ።

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ያማርራል | ማሳበብ | መቋቋም | በዓይነህሊናው | የሚቆረጣጥመውን |
| እያቅለሸለሸው | ገመናውን | ጥሪቱ | ሲመለስ | |

በወጣትነት ዘመኑ አርቆ አለማሰቡ ምንያህል እንደጎዳው በዓይነህሊናው ታየው። 2 ለመሸፈን በማይረቡ ምክንያቶች 3 ይወድ ነበር። ዕድሜው እየገፋ ሲሄድ ግን 4 ሁሉ ተሟጦ በማለቁ ኑሮውን 5 አልቻለም። በዚህ የተነሳ በየዕለቱ አምላኩን 6። ከችግሩ ለመደበቅም ማታማታ ጓደኞቹ የሚጋብዙትን የአልኮል መጠጥ ሲጋት ያድራል። ጧት ጧት ደግሞ 7 ሲያስመልሰው ያረፍዳል። ተስፋቢስ ህይወቱን ሲያስብ ቆየና ድንገት ከሀሳቡ 8 'ወይ ጉድ?' አለ ለራሱ፤ ከዚያም "በፊት ነበር እንጂ መጥኖ መደቆስ---" አለ ያገሬ ሰው በማለት 9 እግሩን እያፍታታ ከቤቱ ወጣ።

## መጻፍ

### ድርሰት መጻፍ

### በምክንያትና ውጤት ስልት ድርሰት መጻፍ

#### ተግባር

ከሚከተሉት ርዕሰጉዳዮች አንዱን በመምረጥ በምክንያትና ውጤት ስልት ባለሦስት አንቀጽ ድርሰት ጻፉ።

ሀ. የአልኮል መጠጥና መዘዙ

ለ. ከትምህርትቤት መቅረት የሚያስከትለው ችግር

ሐ. አዛውንቶችን ያለጧሪ የሚያስቀሩ ችግሮች

### የአጻጻፍ ሥርዓት

### የሥርዓተነጥብ አጠቃቀም

#### ተግባር

ተገቢ ሥርዓተነጥቦችን በተገቢ ቦታቸው በመጠቀም የሚከተለውን ጽሑፍ እንደገና ጻፉ።

በዕቅድ የሚመሩ ሰዎች ውጤታማ ናቸው 1 የዕለት ዕቅዳቸውን በ24 ሰዓት ከፋፍለው ያደራጃሉ 2 እቅዳቸውን ለመመገብ 3 ለመሥራት 4 ከቤተሰብ ጋር ለመወያየት 5 ለመተኛትና ለመሳሰሉት ይጠቀሙበታል 6 ሁልጊዜም ቢሆን ዕቅዳቸውን በተግባር ያሳያሉ 7 ይተረጉማሉ 8 እናንተስ በየዕለቱ ምን ምን ታደርጋላችሁ 9

# 6ኛ ቀን

## አቀላጥፎ ማንበብ

**"በሽታውን የደበቀ..."**

### ቅድመንባብ

### የምንባቡን ዋናዋና ሀሳቦች አስታውሶ መናገር

**ተግባር**

"በሽታውን የደበቀ---" በሚል ርዕስ በሁለተኛው ሳምንት በአራተኛው ቀን ያነበባችሁትን ምንባብ በማስታወስ ምክንያቶቹ የሚያስከትሉትን ውጤት ጻፉ።

| ምክንያት | | ውጤት |
|---|---|---|
| • ወዛደሩ ከጓደኛው ጋር ወደመጠጥቤት ሔደ። | → | |
| • ወዛደሩ አልፎ አልፎ ውጪ ያድር ጀመር። | → | |
| • ወዛደሩ ህመሙ እየበረታ ሔደ። | → | |

### ማንበብ

**ተግባር**

"በሽታውን የደበቀ---" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት ጥንድ ጥንድ እየሆናችሁ አንብቡ።

## መናገር

### የቢጋር ሠንጠረዥን በመጠቀም መናገር

**ተግባር**

የኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ሥርጭትን በመቀነስ ረገድ ከጤና ተቋማት፣ ከቤተሰብ፣ ከትምህርትቤትና ከማህበረሰብ ምን እንደሚጠበቅ በቢጋር ሠንጠረዡ መሠረት በመወያየት የተስማማችሁበትን ሀሳብ ተናገሩ።




## ሰዋስው

### ግስን በመደብ፣ በፆታና በቁጥር ማርባት

### ተግባር 1

በምሳሌው መሠረት ሌሎቹን ቃላት በሠንጠረዥ ውስጥ ጻፉ።

| ቃል | እኔ | እኛ | አንተ | አንቺ | እናንተ | እሱ | እሷ | እነሱ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| አጸዳ | አጸዳለሁ | እናጸዳለን | ታጸዳለህ | ታጸጃለሽ | ታጸዳላችሁ | ያጸዳል | ታጸዳለች | ያጸዳሉ |
| ቆጠረ | | | | | | | | |
| አጠበ | | | | | | | | |
| አገደ | | | | | | | | |
| ዘመረ | | | | | | | | |
| ቀባ | | | | | | | | |

## ተግባር 2

በምሳሌው መሠረት ሌሎቹን ቃላት በሠንጠረዡ ውስጥ አሟሉ።

| ቃል | እኔ | እኛ | አንተ | አንቺ | እናንተ | እሷ | እነሱ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ለበሰ | ለበስኩ | ለበስን | ለበስክ | ለበስሽ | ለበሳችሁ | ለበሰች | ለበሱ |
| መረጠ | | | | | | | |
| ቆፈረ | | | | | | | |
| ጻፍ | | | | | | | |
| ወደደ | | | | | | | |
| ሔደ | | | | | | | |
| ሰበረ | | | | | | | |

# ስለኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ግንዛቤ መፍጠር

## የቃላት ጥናት

### መነጠልና ማጣመር

#### ተግባር

የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት ነጣጥላችሁና አጣምራችሁ አንብቡ።

| ነጣጥሎ ማንበብ | | አጣምሮ ማንበብ |
|---|---|---|
| ሀ | ቡ-ር-ሽ-ዋ-ን | ቡርሿን |
| ለ | ጓደኛ-ነት-ኣቸው-ም | ጓደኛነታቸውም |
| ሐ | እ-ስ-ኪ-ዶ-ለ-ዱ-ም | እስኪዶለዱም |
| መ | ይንከባከቡ-ኣቸው-ኣል | ይንከባከቧቸዋል |
| ሠ | የ-ምህንድስና | የምህንድስና |
| ረ | እንደ-ኣይ-ጠቀሙ-ም | እንዳይጠቀሙም |
| ሰ | ሊ-ተላለፍ-ብ-ኣት | ሊተላለፍባት |
| ሸ | አስተዳደግ-ዋ-ም | አስተዳደጓም |
| ቀ | ሲ-ያጠናቅቅ-ኡ | ሲያጠናቅቁ |

## ማንበብ

### ህያትና ጓደኛዋ

#### ቅድመንባብ

#### የቅደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

#### ተግባር

"ህያትና ጓደኛዋ" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ከማንበባችሁ በፊት ለሚከተሉት ጥያቄዎች በቃላችሁ መልስ ስጡ።

ሀ. ሰዎች ስለኤች.አይ.ቪ. በግልጽ አለመወያየታቸው ምን ምን ጉዳቶችን ያስከትላል?

ለ. የኤች.አይ.ቪ. ቫይረስ በደማቸው ውስጥ ያለባቸው ጓደኞች ቢኖሯችሁ ምን ዓይነት እንክብካቤ ታደርጉላቸዋላችሁ?

## የማንበብ ሂደት

### ተግባር

ቀጥሎ "ሀያትና ጓደኛዋ" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ የሀሳቦችን ምክንያትና ውጤት ግንኙነት በማስተዋል በለሆሳስ አንብቡ።

## ሀያትና ጓደኛዋ

ሀያት ተወልዳ ያደገችው ደጀን ከተማ ውስጥ ነው። በልጅነቷም አሁንም ጎበዝ ተማሪ ነች። ስለኤች.አይ.ቪ./ኤድስ በቂ ግንዛቤ ያገኘችው ስድስተኛ ክፍል እያለች ነው። ከዚያን ጊዜ ጀምራ ራሷን ከበሽታው ለመጠበቅ ጥንቃቄዋ ወሰን አልነበረውም። ቫይረሱ በዋናነት በደም ንክኪና በግብረስጋ ግንኙነት እንደሚተላለፍ ስለተረዳች ባል ከማግባቷ በፊት በመታቀብ ተጠንቅቃ ኖራለች። ስለታም ነገሮችን ከጓደኞቿና ከቤተሰቦቿ ጋር ተጋርታ አትጠቀምም። የጥርስ ቡርሿንና የጥፍር መቁረጫዋን ለሌሎች ሰዎች አጋርታ አታውቅም።

ሀያት አስረኛ ክፍል ስትደርስ ቫይረሱ በደሟ ውስጥ ካለባት አንዲት ልጅ ጋር ተዋወቀች። ጎንለጎን በመቀመጥ፣ እጅ ለእጅ በመጨባበጥና፣ በትንፋሽ በሽታው እንደማይተላለፍ ስለተረዳች አብራ ለማጥናት ወሰነች። ጓደኝነታቸውም እየተጠናከረ መጣ። አዲሷ ጓደኛዋ ቫይረሱ በደሟ ውስጥ ቢኖርም ራዕይ ነበራት። ተምራ ትልቅ ደረጃ ላይ ለመድረስ ትጥር ነበር። በዚህ ጥረቷም ሀያት በጣም ትወዳት ነበር። የርስበርስ መተሳሰባቸውም ወሰን አልነበረውም።

ሀያትና ጓደኛዋ ከጥናት ሰዓታቸው ውጪ ስለኤች.አይ.ቪ./ኤድስ በግልጽ ይወያዩ ነበር። የሀያት ጓደኛ ስለአስተዳደጓም በዝርዝር ገልጻላታለች። የተወለደችውና ያደገችው በአንድ የወረዳ ከተማ ውስጥ ነው። ቫይረሱ እንዴት እንደተላለፈባቸው ለሀያት የነገረቻት በጥልቅ ሀዘን ውስጥ ሆና ነው። ስለቫይረሱ መጠነኛ ግንዛቤ ቢኖራትም ጥንቃቄዋ ግን ዝቅተኛ ነበር። በአደገችበት ሰፈር ውስጥ ከእሷ ጋር በዕድሜ አቻ የሆኑ በርካታ ልጆች ነበሩ። ሁሉም የአካባቢው ኗሪዎች እነዚህን ሕፃናት በሙሉ እንደራሳቸው ልጆች አድርገው ይንከባከቧቸዋል። በመሆኑም አንዲት እናት የልጃቸውን ፀጉር የሚላጩ ከሆነ ምላጩ እስኪዶለዱም ድረስ የሰፈሩን ልጆች እያተካከሉ ይላጫሉ። ምላጩ የመላጨት አቅሙ ካልቀነሰም ለሌላ ጊዜ እንዲያገለግል ይቀመጣል።

ሀያት በጓደኛዋ ላይ በተፈፀመው ስህተት በጣም አዘነች። በጎረቤታሞች መካከል ማህበራዊ ኑሮ፣ መተሳሰብና መፋቀር የሚፈለግ ቢሆንም ሞትን ሊወልድ በሚችል መልኩ መከናወኑ አበሳጫት። በምላጩ አማካይነት የቫይረሱን ሥርጭት ስታስበው ደግሞ ይበልጥ ከፋት። ታቅባ ያለች ጓደኛዋ በዚህ ሁኔታ በለጋ ዕድሜዋ በቫይረሱ መያዟ አስለቀሳት። ሆኖም መድሃኒት መጀመሯን ስታስታውስ ተፅናናች።

ሀያትና ጓደኛዋ ጥንቃቄ እያደረጉ አብረው ማጥናታቸውን ስለቀጠሉ ስኬታማ ሆኑ። በአስረኛና በአሥራሁለተኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተናዎች ከፍተኛ ውጤት በማስመዝገብ ወደዩኒቨርሲቲ ገቡ። ሀያት ምህንድስና፣ ጓደኛዋ ደግሞ ሕክምና

ለማጥናት ወሰኑ። ትምህርታቸውን ሲያጠናቅቁ ሀያት ደብረብርሃን ጓደኛዋ ደግሞ ደብረማርቆስ ተመደቡ። ዘወትር በስልክ ይጠያየቃሉ። አልፎአልፎም በአካል ይገናኛሉ።

ሁለቱ ጓደኛሞች ከመደበኛ ሥራቸው ጎንለጎን ስለኤች.አይ.ቪ./ኤድስ መተላለፊያና መከላከያ ዘዴዎች ያስተምራሉ። ሀያት በምትሰራበት ድርጅት ውስጥ የፀረ ኤድስ ክበብ አቋቁማ ለድርጅቱ ሠራተኞች ስለኤች.አይ.ቪ. ትምህርት ትሰጣለች። ጓደኛዋም የሕክምናን ሙያ የመረጠችው ሳያውቁ ለቫይረሱ የሚጋለጡ ለጋ ሕፃናትን አስተምራ ለመታደግ ነው። ስለሆነም <u>በመቆጠብ፣</u> <u>በመወሰን፣</u> በመጠቀምና በመመርመር ቫይረሱን መከላከል እንደሚቻል ያለመታከት ታስተምራለች። ስለታም ነገሮችን በጋራ እንዳይጠቀሙም አጥብቃ ትመክራለች። ቫይረሱ ያለባቸው ሰዎች ሕክምናውን እንዲጀምሩ ራሷን ምሳሌ በማድረግ ታስረዳለች። በቅርቡ ደግሞ "እኛ ለእኛ" የተባለ በጎ አድራጎት ድርጅት አቋቁማለች። በድርጅቱ አማካይነት በኤች.አይ.ቪ./ኤድስ የተጎዱ ወገኖቿን ትንከባከባለች፤ ለማህበረሰቡም ትምህርት በመስጠት ላይ ትገኛለች።

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር 1

ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል መርጣችሁ በመጻፍ መልሱ።

1. ሀያት ከጓደኛዋ ጋር አብራ ለማጥናት የወሰነችው ለምንድን ነው?

   ሀ. በትምህርቷ ደካማ ስለነበረች

   ለ. የአንድ ሰፈር ልጆች በመሆናቸው

   ሐ. የኤች.አይ.ቪ./ኤድስ መተላለፊያ መንገዶችን ስላወቀች

   መ. ጓደኛዋ በጣም ስለምትወዳት

2. የሀያት ጓደኛ የኤች.አይ.ቪ. ቫይረስ የተላለፈባት እንዴት ነበር?

   ሀ. አንድ ለአንድ ባለመወሰኗ

   ለ. ሌሎች በተጠቀሙበት ምላጭ በመላጨቷ

   ሐ. በዕድሜ አቻ ከሆኑ ልጆች ጋር አብራ በመኖሯ

   መ. እንዴት እንደተላለፈባት አይታወቅም

3. የሀያት ጓደኛ በምን የሙያ ዘርፍ ተመረቀች?

   ሀ. በምህንድስና  ሐ. በሕክምና

   ለ. በመምህርነት  መ. በግብርና

4. ሀያት በጓደኛዋ ላይ በተፈፀመው ስህተት ያዘነችው ለምንድን ነው?

ሀ. በማህበረሰቡ የግንዛቤ እጥረት ምክንያት ቫይረሱ ስለተላለፈባት

ለ. ጓደኛዋ እያወቀች ጥፋት በመፈፀሟ

ሐ. ጓደኛዋን ሌሎች ሰዎች በማግለላቸው

መ. ጓደኛዋ የኤች.አይ.ቪ./ኤድስ መድኀኒት ባለመጠቀሟ

5. የህያት ጓደኛ ተግባር **ያልሆነው** የትኛው ነው?

ሀ. ቫይረሱን መከላከል እንዲቻል ማስተማር

ለ. በቫይረሱ የተያዙ ሰዎች ሕክምና እንዲጀምሩ መወያየት

ሐ. እኛ ለእኛ የተባለ የንግድ ድርጅት ማቋቋም

መ. በቫይረሱ የተጎዱ ወገኖችን መንከባከብ

## ተግባር 2

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. የህያት ጓደኛ የሕክምናን ሙያ የመረጠችው ለምንድን ነው?

ለ. የህያትን ጓደኛ የሰፈር ሰዎች ምን ብላችሁ ትመክሯቸዋላችሁ?

ሐ. ሰዎች አንድ ጊዜ ብቻ የኤች.አይ.ቪ. ምርመራ ሲያደርጉ ቫይረሱ በደማቸው ውስጥ ባይገኝ ከኤች.አይ.ቪ. ነፃ ናቸው ማለት ይቻላል? ለምን?

መ. የኤች.አይ.ቪ. ቫይረስ በደማቸው ውስጥ ያለባቸው ሰዎች ህይወታቸውን በአግባቡ እንዳይመሩ የሚያደርጉ ተፅዕኖዎች ምን ምን ናቸው?

# 8ኛ ቀን

## ቃላት

### የቃላትን ፊደላት በማጥበቅና በማላላት የተለያየ ፍቺ መስጠት

## ተግባር

የሚከተሉትን ቃላት ፊደላቸውን በማጥበቅና በማላላት ሁለት ፍቺ እንዲሰጡ አድርጋችሁ ዓረፍተነገር ሥሩባቸው።

ምሳሌ:-

<u>ጥፍር</u> ካደገ ቆሻሻ ይይዛል።

መንገደኛዋ ወገቧን በመቀነቷ <u>ጥፍር</u> አድርጋ ስትጓዝ ዋለች።

ሀ. አብራ (አንቀጽ 2)

ለ. ሰፈሩ (አንቀጽ 3)

ሐ. ጥልቅ (አንቀጽ 3)

መ. ለጋ (አንቀጽ 4)

ሠ. መቆጠብ (አንቀጽ 6)

ረ. መወሰን (አንቀጽ 6)

## መጻፍ

### ድርሰት መጻፍ

### በምክንያትና ውጤት ስልት ድርሰት መጻፍ

#### ተግባር

ከሚከተሉት ርዕሰ ጉዳዮች አንዱን በመምረጥ በምክንያትና ውጤት ስልት ባለሦስት አንቀጽ ድርሰት ጻፉ።

ሀ. ለሱስ ተገዢ መሆን

ለ. የትራፊክ ሕግ አለማክበር

ሐ. ጠንክሮ አለማጥናት

### የአጻጻፍ ሥርዓት

### የቃላትንና የሐረጋትን ቅርጽ አስተካክሎ መጻፍ

#### ተግባር

በሚከተለው አንቀጽ የተሠመረባቸውን ቃላትና ሐረጋት ቅርጽ አስተካክላችሁ ጻፉ።

<u>በራስ መተማመን</u> ባህርይ ያላቸው <u>ወጣት</u> ስለራሳቸውም ሆነ <u>ሌላው</u> ሰው መልካም አመለካከት <u>አለው።</u> የማያምኑበትን ነገር ወይም ግፊት መቋቋም ይችላሉ። ማድረግ የማይፈልጉትን በግልጽ <u>ያሳውቃል።</u> በውሳኔያቸውም ይጸናሉ። ልል ባህርይ ያላቸው ወጣቶች ግን <u>ጓደኞቻቸው</u> ግፊት መቋቋም አይችሉም፤ በዚህም የተነሳ ችግር ውስጥ ይገባሉ።

# 9ኛ ቀን

## አቀላጥፎ ማንበብ

**ሀያትና ጓደኛዋ**

### ቅድመንባብ

**ተግባር**

በ3ኛው ሳምንት፣ በ7ኛው ቀን "ሀያትና ጓደኛዋ" በሚል ርዕስ ከቀረበው ምንባብ ዋናዋና ሀሳቦችን አስታውሳችሁ ተናገሩ።

### ማንበብ

**ተግባር**

"ሀያትና ጓደኛዋ" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ጥንድ ጥንድ እየሆናችሁ አንድ አንድ ዓረፍተነገር በየተራ እየተቀባበላችሁ በፍጥነት አንብቡ።

## መናገር

### ሀሳብን በንግግር መግለጽ

**ተግባር**

የሚከተሉት ሰብዓዊ ባህርያት ሰዎች በኤች.አይ.ቪ./ኤድስ እንዳይጠቁ በማድረግ ረገድ ያላቸውን ፋይዳ ተናገሩ።

ሀ. ደስተኛ ቤተሰብ

ለ. እውነተኛ ጓደኝነት

ሐ. ግልፀኝነት

መ. ታማኝነት

ሠ. ለሌላ ሰው እንደራስ ማሰብ

ረ. እምነትን ማክበር

## ሰዋስው

### ተውሳከግስን፣ እምርነት አመልካች ቅጥያንና መደብን መለየት

**ተግባር 1**

የሚከተሉትን ተውሳከግሶች በመጠቀም ዓረፍተነገር ሥሩ።

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ግምኛ | ቶሎ | ክፉኛ | ገና | እየሮጠ | በፍጥነት |

## ተግባር 2

የሚከተሉትን እምር አመልካች ቅጥያዎች ከስም ጋር በማጣመር ስሞችን እምር አድርጉ።

| | | |
|---|---|---|
| -ኡ | -ው | -ዋ |

## ተግባር 3

እምር የሆኑትንና ያልሆኑትን ስሞች ለይታችሁ ጻፉ።

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| በሬ | ውሻዉ | ልብስ | ሴትዮዋ | ልጇቱ | ድመቲት |
| በጉ | ዶሮዋ | ጥጃ | ሰው | ፍየሏ | |

## ተግባር 4

የሚከተሉትን ቃላት መደባቸውን በመለየት በሠንጠረዡ ውስጥ በትክክለኛ ቦታቸው ጻፉ።

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ቆረሱ | ቆረስህ | ቆረሰ | ቆረስኩ | ቆረሰች | ቆረስን | ቆረሳችሁ | ቆረስሽ |
| ቆፈርኩ | ቆፈራችሁ | ቆፈርክ | ቆፈሩ | ቆፈርን | ቆፈረ | ቆፈርሽ | ቆፈረች |

| 1ኛ መደብ | | 2ኛ መደብ | | | 3ኛ መደብ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ነጠላ | ብዙ | ነጠላ | | ብዙ | ነጠላ | | ብዙ |
| | | ተባዕታይ | አንስታይ | | ተባዕታይ | አንስታይ | |
| | | | | | | | |



# ባህላዊ ክንዋኔዎች

ምዕራፍ 8

## በዓላትና አከባበራቸው

1ኛ ሳምንት 1ኛ ቀን

## የቃላት ጥናት

### መነጠልና ማጣመር

**ተግባር**

የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት ነጣጥላችሁና አጣምራችሁ አንብቡ።

| ነጣጥሎ ማንበብ | አጣምሮ ማንበብ |
|---|---|
| ሀ. እ-ን-ግ-ጫ | እንግጫ |
| ለ. እንቁ-ጣጣሽ | እንቁጣጣሽ |
| ሐ. እየ-ጎነጎኑ | እየጎነጎኑ |
| መ. የ-ለገሱ-አቸው | የለገሷቸው |
| ሠ. የምትፈነጥቅ-ብ-ኧት | የምትፈነጥቅበት |
| ረ. የምታሸበርቅ-ብ-ኧት | የምታሸበርቅበት |
| ሰ. እንዲ-ቆዩ-ል-አቸው | እንዲቆዩላቸው |

## ማንበብ

### እንቁጣጣሽ

### ቅድመንባብ

የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

**ተግባር**

የሚከተሉትን የቅድመንባብ ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. "እንቁጣጣሽ" በሚል ርዕስ በቀረበው ምንባብ ጎን ጎላ ብለው በተለየ ቀለም የተጻፉትን በማንበብ የምንባቡን ሀሳብ ግለጹ።

ለ. "እንቁጣጣሽ" ከሚለው ርዕስ ሥር ያለውን ሥዕል ተመልከቱና የተረዳችሁትን ግለጹ።

ሐ. በእንቁጣጣሽ ዋዜማ አዲሱን በዓል ለመቀበል ምን ምን ድርጊቶች ይከናወናሉ?

## የማንበብ ሂደት

## ዋናና መዘርዝር ሀሳቦችን እየለዩ ማንበብ

### ተግባር

"እንቁጣጣሽ" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ጥንድ ጥንድ በመሆን ዜማውን ጠብቃችሁ አንብቡ።

## እንቁጣጣሽ



እንቁጣጣሽ በኢትዮጵያ በየዓመቱ መስከረም ሲጠባ የሚከበር የዘመን መለወጫ በዓል ነው። በዓሉ ፀሐይ የምትፈነጥቅበትና ምድር በአበባ የምታሸበርቅበት የአዲስ ዓመት ማብሰሪያ ዕለት ነው።

በዚህ ዐውዳመት በተለይ በአንዳንድ አካባቢዎች በዋዜማው ዕለት አመሻሽ ላይ ችቦ ይበራል። ችቦ አብሪዎች "የጎመን ዘመን አልፎ ፍሬ የምናይበት ዘመን መጥቷል" ለማለት ችቦውን ካቀጣጠሉ በኋላ ከቤት ሲወጡ መዝጊያውን ሶስቴ እያስነኩ፡-

**ልጆች አበባዎችን ከእንግጫ ጋር እየጎነጎኑ የመልካም ምኞት መግለጫ ስጦታ ያዘጋጃሉ።**

**"የብርሃን ዘመን መጥቷል፤ እንኳን ወደብርሃን ዘመን ተሸጋገራችሁ።"**

"የጎመን ምንቸት ውጣ!

የገንፎ ምንቸት ግባ!"

ይሉና ችቦውን እያበሩ ወደውጪ ይሄዳሉ።

ከውጪ ሆነው ችቦው በርቶ እስኪያልቅ ድረስ

"እ … ዮ … ሐ … አ … በ … ባ … ዬ!

መስከረም ጠባዬ

መስከረም ሲጠባ!

ወዳገሬ ልግባ

ወደአዲስ አበባ።

አይዞሽ ነፍሴ

ደረሰልሽ ገብሴ።" እያሉ ሆታ ያሰማሉ።

ከሌሊቱ አሥርና አሥራአንድ ሰዓት ሲሆን፣ በገጠር አካባቢ ያሉት ወደወንዝ ወርደው ሲታጠቡ፣ የከተሞቹ ደግሞ እቤታቸው ገላቸውን ይታጠባሉ። የመታጠቡ ምስጢርም ማንኛውንም መጥፎ ነገር ከአሮጌው ዘመን ጋር ለማስቀረትና አዲሱን ዘመን በንጽህና ለመቀበል ነው።

ልጆች በዋዜማው ዕለት ተሰባስበው ወደዱር በመሄድ አበባ ይቀጥፋሉ። አበባዎቹን ከእንግጫ ጋር እየጎነጎኑ የመልካም ምኞት መግለጫ ስጦታ ያዘጋጃሉ። በማግስቱም መስከረም አንድ ቀን በጧት ተነስተው ለቤተሰብ፣ ለወዳጅና ለዘመድ በስጦታ መልክ ያቀርባሉ። ልጆቹ የአበባ ስጦታ የሚያበረክቱት ለብሥራትና ለመልካም ምኞት መግለጫ ነው፤ "የብርሃን ዘመን መጥቷል፤ እንኳን ወደብርሃን ዘመን ተሸጋገራችሁ" ለማለት። ልጆቹ የአበባ ስጦታቸውን ሲያቀርቡ የክት ልብሳቸውን ይለብሳሉ፤ በህብረት ያዜማሉ። ወደቤት መቅረባቸውንም ለማሳወቅ፡-

“ሆ ብለን መጣን ሆ ብለን፣

እማማ አሉ ብለን፣

ሆ ብለን መጣን ሆ ብለን፣

አባባ አሉ ብለን፣

ሆ ብለን መጣን ሆ ብለን፣

ጋሼዬ አሉ ብለን” እያሉ ያዜማሉ።

የቤቱ ባለቤቶችም የልጆቹን መምጣት ሲሰሙ በደስታ ይቀበሏቸዋል። ልጆቹ ወደቤት ሲገቡ ደግሞ፡-

“እቴ አበባሽ እቴ አበባዬ፣

አዬ!

እቴ አበባዬ፣

እቴ አበባሽ ስትለኝ ከርማ፣

አዬ!

እቴ አባባዬ፣

ጥላኝ ሄደች ባምሌ ጨለማ።

አዬ!

እቴ አባባዬ

አዬ!

እቴ አበባዬ”

እያሉ በመቀባበል ይዘፍናሉ። በመቀጠልም ዜማ ይቀይሩና

አበባዬ ሆይ

ለምለም፣

ባልንጀሮቼ፣

ለምለም---”

በማለት አውራጅና ተቀባይ በመሆን በውብ ዜማ ይጨፍራሉ።

እንዲህ በህብረት እየጨፈሩ የመጡት ልጆች ልዩ ልዩ ገፀበረከት ይቀርብላቸዋል። ልጆቹም ስጦታ የለገሷቸው ሰዎች በተከታዩ ዓመት በህብት በልፅገውና ከብረው እንዲቆዩላቸው በመመኘት፡-

“ከብረው ይቆዩን ከብረው፣

ከዘመን ዘመን ደርሰው፣

ሠላሳ ጥጆች አስረው፣

ከብረው ይቆዩን ከብረው!”

እያሉ በዜማ መርቀው ስጦታቸውን ተቀብለው ይወጣሉ። በዚህ መልኩ ልጆቹ መልካም ምኞታቸውን ሲገልፁና ስጦታ ሲሰበስቡ ውለው ያገኙትን ተከፋፍለው በየቤታቸው ይከተታሉ።

(ማህተመሥላሴ ወልደመስቀል። 1959። *የኢትዮጵያ ባህል ጥናት።* ገጽ 15 *እና ከ6ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ።* 1996። ከገጽ 1-4 መጠነኛ ለውጥ ተደርጎ የተወሰደ።)

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. ካነበባችሁት ምንባብ ውስጥ ቁልፍ የሆኑ ቃላትን ለይታችሁ ጻፉ።

ለ. “የጎመን ምንቸት ውጣ፤ የገንፎ ምንቸት ግባ” የሚለው አባባል ምንን የሚገልጽ ይመስላችኋል?

ሐ. በአንዳንድ አካባቢ በእንቁጣጣሽ ዋዜማ አመሻሽ ላይ ችቦ የሚበራው ለምንድን ነው?

መ. ሰዎች በእንቁጣጣሽ ዋዜማ ገላቸውን የሚታጠቡት ለምንድን ነው?

ሠ. በእንቁጣጣሽ ዕለት ልጆች ስጦታ የሰጧቸውን ሰዎች ምን ብለው ይመርቋቸዋል?

ረ. ምንባቡ የፈጠረባችሁን ስሜት ለጓደኞቻችሁ ግለጹ።

## ቃላት

### ቃላትንና ሐረጋትን ከሁኔታዎች ጋር በማዛመድ ፍቺ መስጠት

#### ተግባር

የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት ከሁኔታዎች ጋር በማዛመድ ፍቻቸውን በጽሑፍ ግለጹ።

ምሳሌ፡-

እንቁጣጣሽ

1. "እዮሃ አበባዬ መስከረም ጠባዬ" ይባላል፤ ምክንያቱም ዛሬ እንቁጣጣሽ ነው።
2. መስከረም አንድ ቀን ልጆች አበባ ይዘው ወደእኛ ቤት ይመጣሉ፤ ምክንያቱም ቀኑ እንቁጣጣሽ ነው።
3. ሰዎች አመሻሽ ላይ ችቦ ይለኩሳሉ፤ ምክንያቱም እንቁጣጣሽ ነው።

   እንቁጣጣሽ "እንቁ"ና "ጣጣሽ" ከሚባሉ ሁለት ቃላት የተመሠረተ ሲሆን ትርጉሙም ውብ፣ ያማረ፣ አዲስ ቀን፣ ነገርግን ብዙ ዝግጅት የሚፈልግ፣ ብዙ ጣጣ ያለው ማለት ነው።

ሀ. የክት ልብስ
ለ. ዋዜማ
ሐ. ጥገት
መ. ብሥራት
ሠ. ምንቸት
ረ. እንግጫ
ሰ. ገፀበረከት

## መጻፍ

### ድርሰት መጻፍ

### ጅምር ሀሳብን መጨረስ

#### ተግባር 1

"እንቁጣጣሽ" በሚለው ምንባብ መሠረት

"አበባዬ ሆይ፣

ለምለም፣

ባልንጀሮቼ፣

ለምለም---”

ይህንን ጅምር ግጥም ጨርሳችሁ ጻፉና በክፍል ውስጥ አንብቡ።

### ተግባር 2

በክብረበዓላት ወይም በዐውዳመት ዕለት ከሚዜሙ ዜማዎች መካከል አንዱን ጻፉና በክፍል ውስጥ አንብቡ።

## የአጻጻፍ ሥርዓት

## ዓረፍተነገርን በትክክለኛ የአጻጻፍ ሥርዓት መጻፍ

### ተግባር

የቃላቱን ቅደምተከል በማስተካከል ዓረፍተነገሮችን እንደገና ጻፉ።

ሀ. ዕጽዋት ህይወት ያላቸው እንደእንስሳት ሁሉ ናቸው።

ለ. ከእንስሳት የሚለዩባቸውም ዕጽዋት ባህርያት አሏቸው።

ሐ. ምግብ ማዘጋጀታቸው የራሳቸውን ነው ከሚለዩባቸው ባህርያት አንዱ።

መ. ግን ማዘጋጀት አይችሉም የራሳቸውን ምግብ እንስሳት።

ሠ. ዕፅዋት ምግባቸውን ከአፈር፣ ከአየር፣ ከውኃና ከፀሐይ ብርሃን የሚያዘጋጁት ነው።

## 3ኛ ቀን

# አቀላጥፎ ማንበብ

## እንቁጣጣሽ

## ቅድመንባብ

### ተግባር

የሚከተሉትን የቅድመንባብ ጥያቄዎች በትክክል መልሱ።

ሀ. የእንቁጣጣሽ በዓል ከሌሎች በዓላት በምን ይለያል?

ለ. በእንቁጣጣሽ በዓል ዋዜማ ዕለት ችቦ አብሪዎች ምን እያሉ ያዜማሉ?

## ማንበብ

### ተግባር

"እንቁጣጣሽ" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ጥንድ ጥንድ በመሆን ዜማውን ጠብቃችሁ በፍጥነት አንብቡ።

## ማዳመጥ

### ረመዳን

### ቅድመማዳመጥ

### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

### ተግባር

የሚከተሉትን የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. በእናንተ አካባቢ የሚከበሩ ሃይማኖታዊ በዓላት ምን ምን ናቸው?

ለ. በሃይማኖታዊ በዓላቱ ዕለትስ ምን ምን ዓይነት ዝግጅቶች ይደረጋሉ?

### የማዳመጥ ሂደት

### መረዳትን ማረጋገጥና የምንባቡን ሀሳብ መገመት

### ተግባር

"ረመዳን" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ መምህራችሁ ያነቡላችኋል፤ ዋናና መዘርዝር ሀሳቦችን እየለያችሁ በማዳመጥ፣ በማዳመጥ ሂደት የሚጠየቁ ጥያቄዎችን በቃላችሁ መልሱ።

### አዳምጦ መረዳት

### ተግባር 1

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. የረመዳን ወር "ቅዱስ ወር" ተብሎ የሚጠራው ለምንድን ነው?

ለ. በረመዳን ወር የእስልምና እምነት ተከታዮች በመስጊድ ውስጥ የሚያሳልፉት ጊዜ ምን በመባል ይታወቃል?

ሐ. በኢድ አልፈጥር ዕለት ምዕመናን ችግረኞችን የሚረዱት ለምንድን ነው? በእናንተስ አካባቢ በሃይማኖታዊ በዓል ቀን ምን ይደረጋል?

መ. በኢድ አልፈጥር ዕለት ምዕመናኑ ምን ዓይነት ልብሶችን ይለብሳሉ?

ሠ. የጨረቃ መውጣትና የረመዳን ፆም ያላቸው ግንኙነት ምንድን ነው?

## ተግባር 2

ከሚከተሉት ቃላት ተገቢ የሆኑትን መርጣችሁ በደብተራችሁ ጻፉ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ማመስገን | ጣቅያ | ዘካ | ምንጣፍ |
| ዘካቱልማ | መጾም | ቀሚስ | ሂጃብ |
| ጀለብያ | ሶላት | መጸለይ | ካቱልፊጥር |




# ሰዋስው

## ጠቋሚ መስተአምርንና ወደረኛ መስተፃምርን መለየት

## ተግባር 1

የሚከተሉትን ጠቋሚ መስተአምሮች በመጠቀም በምሳሌው መሠረት ዓረፍተነገር ሥሩ።

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ያ | እነዚያ | ይህ | እነዚህ | ያቺ | እነሱ | እሱ | እሷ | ይቺ |

ምሳሌ

1. ያቺ ልጅ ጎበዝ ተማሪ ናት። "ያቺ" የሚለው ጠቋሚ መስተአምር ነው።
2. ይህ መጽሐፍ የራሴ ነው። "ይህ" የሚለው ጠቋሚ መስተአምር ነው።

## ተግባር 2

ተገቢ የሆኑትን መስተፃምሮች በክፍት ቦታዎቹ በማስገባት ዓረፍተነገሮቹን

አሟልታችሁ ጻፉ።

ምሳሌ

1. ሻይ <u>ወይም</u> ቡና አምጣልኝ።

2. መጽሐፍ ማንበብ<u>ና</u> ዋና መዋኘት እወዳለሁ።

ሀ. እናቴን ——— አባቴን በጣም እወዳለሁ።

ለ. በአካል ——— በስልክ መገናኘት አለብን።

ሐ. ሽማግሌው፣ ጨለማ ስለሆነ መብራት ——— ምርኩዝ ይዘዋል።

መ. በፈረስ ——— በበቅሎ መጓዝ ትችላለህ።

ሠ. ነፍሰጡሯ ወንድ ——— ሴት ልጅ ትወልዳለች።

ረ. መብራት ——— ውኃ ወደቤታችን ገባልን።

# ማንበብ

## ያልተፈታ ችግር

### ቅድመንባብ

### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

**ተግባር**

"ያልተፈታ ችግር" የሚለውን ምንባብ ከማንበባችሁ በፊት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. በአካባቢያችሁ የለቅሶ ሥርዓት የሚከናወነው እንዴት ነው?

ለ. በምንባቡ በተለየ ቀለም ተለይተው የተጻፉት ሀሳቦች ስለምን ይገልጻሉ?

ሐ. በሥዕሉ ላይ የሚታዩት ሰዎች ምን የሚያደርጉ ይመስላችኋል? ለምን?

### የማንበብ ሂደት

### ዋናና መዘርዝር ሀሳቦችን በመለየት ማንበብ

**ተግባር**

"ያልተፈታ ችግር" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ዋናና መዘርዝር ሀሳቦችን በመለየት በለሆሳስ አንብቡ።

# “ያልተፈታ ችግር”



በኢትዮጵያ በርካታ ባህላዊ ክንዋኔዎች አሉ። ከእነዚህ መካከል የለቅሶ ሥርዓት አንዱ ነው። የለቅሶ ሥርዓት ከቦታ ቦታ ይለያያል። ይሁን እንጂ በአብዛኛው በአማራ ክልል በሚከናወነው ባህላዊ የለቅሶ ሥርዓት ላይ ሀዘንተኞች አምርረው ሲያለቅሱ ይታያሉ። ብዙ ለቀስተኞች ይሰባሰባሉ፤ ለረዥም ሰዓትም ሲያስተዛዝኑ ይቆያሉ። ሞት ሲከሰት ማዘንና ማስተዛዘን ተገቢ ቢሆንም በለቅሶ ሥርዓቱ ላይ ግን ችግሮች ይታያሉ።

**የጤና ጉዳት**

- የደረት መቁሰል
- የሳንባ ሕመም
- የዓይን ብሌን መፍዘዝ
- ፊት መቁሰል
- የራስ ምታት

ለብዙ ቀናት የሚከናወነው ባህላዊ የለቅሶ ሥርዓት የሥራ ጊዜን በእጅጉ ይጎዳል። ሰዎች የተለያዩ ሁኔታዎችን በማስታወስ አጥብቀው ያለቅሳሉ። ወዳጅ ዘመድ እስኪሰባሰብ በሚል ሰበብ አስከሬን በማሳደር ሌሊቱን በሙሉ ሲያለቅሱ የሚያድሩ ብዙ ናቸው። በአንዳንድ አካባቢዎች ደግሞ ሥርዓተቀብር ከተፈጸመ በኋላ እንኳ የሚች ዕድር አባላት ለአንድ ሙሉ ቀን ያህል ሥራ ፈቶ መዋል አለ። የሚች ቤተሰብና የቅርብ ዘመድ ለሦስት ተከታታይ ቀናት ጧትጧት ወደመቃብሩ ቦታ በመሄድ ስለሚያለቅሱ ብዙ የሥራ ጊዜ ይባክናል።

ሀዘንተኞቹ በገበያ ቀናትና ህዝብ በሚሰባሰብባቸው ቦታዎች ላይ በመቀመጥ የሚመጡትን ለቅሶ ደራሾች እየተቀበሉ በማልቀስ የሚያባክኑት ጊዜም አለ። በሌላ በኩል ሀዘንተኞቹ ቀን መርጠው የቀጠሮ ለቅሶ ይጠራሉ። የቀጠሮ ለቅሶም ሁሉም ሰው በቀጠሮው ዕለት ተገኝቶ የሚለቀስበት ሥርዓት ነው። ይህ ሥርዓት ከመጀመሪያው የለቅሶ ዕለት በበለጠ ስለሚከናወን ብዙ ሰዎች የሥራ ጊዜያቸውን ያላግባብ ያባክናሉ።

ብዙ ሰዎች አምርረው በማልቀሳቸው የጤና ጉዳት ይደርስባቸዋል። ሀዘንተኞች የቅርብ ዘመድ ሲሞትባቸው ደረታቸውን ይደቃሉ፤ ጮኸው እያለቀሱ ደረታቸውን ስለሚመቱ በሳንባቸው ላይ ከፍተኛ ሕመም ይፈጥራሉ። ለጎን ውጋትና ለሌላ በሽታም ሊዳረጉ ይችላሉ። ጉንጫቸውንና ግንባራቸውንም በሻካራ ጨርቅ፣ በብርድ ልብስ ወይም በቡትቶ ጨርቅ በመላጥ እስኪደማ ድረስ የሚያቆስሉ አሉ፤ እንዲህ የሚያደርጉ ሰዎች የመረቀዘው ቁስል ሲለበልባቸው ይሰነብታል። ቁስሉ ከደረቀና ከተላጠም በኋላ የማይጠፋ ጠባሳ ጥሎባቸው ያልፋል። ለረጅም ጊዜም ያለገደብ ስለሚያነቡ የዓይን ብሌናቸው ይጎዳል፤ እይታቸውም ይደበዝዛል። ለከፍተኛ የራስ ምታትም ይጋለጣሉ። እንዲህ ዓይነቱ ጤናን የሚያውክ ተግባር የሚከናወነው በአብዛኛው በሴቶች ቢሆንም አልፎ አልፎ ወንዶችም ይፈፅሙታል።

> **የሥራ ጊዜን በአግባቡ አለመጠቀምና ተቀባይነት የሌለው ድግስ መደገስ ኢኮኖሚን ያናጋል።**

ባህላዊው የለቅሶ ሥርዓት በኢኮኖሚም ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አለው። በሀዘን ሰበብ የሟች ቤተሰቦች ለበርካታ ቀናት ያለሥራ ተቀምጠው ስለሚያሳልፉ ገቢያቸው ይቀንሳል። በእነዚህ ዕለቶች ምግብና መጠጥ በብዛት ተዘጋጅቶ ይቀርባል፤ ይበላል፤ ይጠጣል። እንደሟች የዕድሜ ሁኔታ ተዝካር ይዘጋጃል። ስለሆነም ከዕለተሞት ጀምሮ በሳልስት፣ በሰባት፣ በአርባ፣ በሰማንያ ቀን፣ በዓመት ወዘተ ለሟች መታሰቢያ ይደገሳል። የሚዘጋጀው ከልክ ያለፈ ድግስም የሰዎችን ኢኮኖሚ ያናጋል።

በአጠቃላይ እንዲህ ዓይነቱ ባህላዊ የለቅሶ ሥርዓት ጊዜን፣ ጤናንና ኢኮኖሚን በእጅጉ ሲጎዳ ቆይቷል። አሁንም እየጎዳ ይገኛል። ሰዎች እየወደቁ እየተነሱ፣ ደረት እየደቁ፣ ፊት እየነጩ ማልቀሳቸው ሟችን አያድንም። ረጅም ሰዓት ለሀዘን መቀመጥም ለሟች አይጠቅምም። ሀብትን ሊያባክን በሚችል መልኩ ከልክ ያለፈ የሙት መታሰቢያ ድግስ ማዘጋጀትም ዝና ሊሆን አይችልም። ስለሆነም የለቅሶ ሥርዓቱ ከፍተኛ ጉዳት ስላለው ገደብ ሊበጅለት ይገባል።

(አብክመ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ። 2000ዓ.ም.። *የባህል ልማት መስናክሎች ቅኝት*። ገጽ 11-14 ለውጥ ተደርጎበት የተወሰደ/)

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር 1

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. በቀጠሮ ለቅሶና በዕለት ለቅሶ መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

ለ. ከአራተኛው አንቀጽ በመነሳት ሰዎች ወዳጅ ዘመድ ሲሞቱባቸው የለቅሶ ሥርዓቱን እንዴት ማከናወን ያለባቸው ይመስላችኋል?

ሐ. አራተኛው አንቀጽ “ከፍተኛ ድግስ በመደገስ የሙት መታሰቢያ ማዘጋጀት ተገቢ አይደለም” የሚል ይመስላል፤ በዚህ ሀሳብ ትስማማላችሁ? ለምን?

መ. ቤተሰብ የሞተባቸው ሰዎች ባያለቅሱ ማህበረሰቡ ምን የሚላቸው ይመስላችኋል?

ሠ. “ጤናን የሚያውክ የለቅሶ ሥርዓት የሚከናወነው በአብዛኛው በሴቶች ቢሆንም አልፎአልፎ ወንዶችም ይፈጽሙታል” የሚለው አባባል “ወንዶች አያዝኑም” የሚል መልዕክት ያለው ይመስላችኋል? ለምን?

### ተግባር 2

የሚከተሉትን ባህላዊ ክንዋኔዎች ጥቅምና ጉዳት ዘርዝራችሁ ጻፉ።

| ባህላዊ ክንዋኔዎች | ጥቅም | ጉዳት |
|---|---|---|
| ለቅሶ | | |
| ሠርግ | | |
| የውርስ ጋብቻ | | |
| ክብረበዓላት | | |

## 5ኛ ቀን

## ቃላት

### በዓረፍተነገር ውስጥ ቃላትንና ሐረጋትን በተመሳሳያቸው መተካት

### ተግባር

ከሚከተሉት ቃላት ተገቢ የሆኑትን እየመረጣችሁ በዓረፍተነገር ውስጥ በተሠመረባቸው ቃላትና ሐረጋት ተኩ።

| | | |
|---|---|---|
| ሲከሰት | ስራፊተው | ገደብ |
| ሰበብ | ተዝካር | መታሰቢያ |
| አምርረው | ያናጋል | |

ሀ. በለቅሶው ዕለት ዘመዶቹ ከአንጀታቸው ሲያለቅሱ ዋሉ።

ለ. የዕድር አባላት አንድ ቀን ሙሉ ተቀምጠው ይውላሉ።

ሐ. የሞት አደጋ ሲያጋጥም የሟች ቤተሰብን ማፅናናት ያስፈልጋል።

መ. ሰዎች ሀዘናቸውንም ሆነ ደስታቸውን ወሰን ሊያበጁለት ይገባል።

ሠ. ለሙት ማስታወሻ ድግስ መደገስ ለማን ይጠቅማል?

ረ. ዘመድ እስኪሰበሰብ በሚል ምክንያት አስከሬን ማሳደር ጎጂ ልማድ ነው።

ሰ. በሞት ወቅት በድንኳን ውስጥ ለብዙ ቀናት መቀመጥ ኢኮኖሚን ያዛባል።

ሸ. በሞቱ ሰዎች ስም የሚዘጋጀው ድግስ ለአላስፈላጊ ወጪ ይዳረጋል።

## መጻፍ

### ድርሰት መጻፍ

### ከመነሻና ከማጠቃለያ ሀሳብ በመነሳት መዘርዝር ሀሳቦችን መጻፍ

#### ተግባር

የሚከተሉትን መነሻና ማጠቃለያ ሀሳቦች መሠረት በማድረግ መዘርዝር ሀሳቦችን (ሐተታ) ጻፉና ድርሰቱን አሟሉ።

"ድር ቢያብር…"

አንዲት ልጅ በክፍል ውስጥ ብቻዋን ቁጭ ብላ ታለቅሳለች። ተማሪዎቹ ለዕረፍት ወጥተዋል። ጓደኛዋ ቶሎ ተመልሳ ወደክፍል ገባች። "ምነው! ምን ሆነሻል?" አለቻት። ልጂቱም "አይ አንቺ! እኔማ ላገባ ተወስኖብኛል" ብላ ስቅስቅ ብላ አለቀሰች። "ማን ነው የወሰነብሽ? እስኪ ንገሪኝ!?" አለች ጓደኛዋ እልህ እየተናነቃት። ልጂቱም እናቷ መሆናቸውንና የጋብቻው ቀን መቆረጡን አስረዳቻት። ጓደኛዋም "አንቺ ገና የ15 ዓመት ልጃገረድ ነሽ፤ እናትሽም ሆኑ ሌሎች ሰዎች አስገድደው ሊድሩሽ አይችሉም" አለቻት።

የእረፍት ማብቂያ ደወል ተደወለ።______________________________

____________________________________________________

እናቷም ምንም እንኳን ባይማሩም የሰው ምክር ይሰማሉ፤ ማመዛዘንም ይችላሉ። በጉዳዩ ብዙ አላንገራገሩም፤ ጋብቻውን ለመሰረዝ ተስማሙ፤ ለማስተማር ቃል ገቡ። ልጅቷም ደስ አላት፤ መንታ መንታ ሆኖ የሚፈሰውን እንባዋን ጠራረገችና መምህሮቿንና የሴቶች፣ የሕፃናትና የወጣቶች ጽሕፈትቤት ተወካይዋን አቅፋ ሳመቻቸው።

## የአጻጻፍ ሥርዓት

### በዓረፍተነገር ውስጥ ዘዬ ቃላትን በመደበኛ ቃላት መተካት

#### ተግባር

በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ውስጥ ያሉትን ዘዬ ቃላት በመለየት በመደበኛ ቃላት ተኩ።

ሀ. አለሚቱ እንጀራውን በመሆዶ አስቀመጠች።

ለ. ወጡ አሻቦ ስለበዛበት የሚበላው ጠፋ።

ሐ. ቄጦ ስለበላ ምላሱን አቃጠለው።

መ. ቁርስ አልበልቶም መሰለኝ ከፍቶታል።

ሠ. ቅቤ ለማንጠር ዝቃቅቤ ገዛች።

ረ. ወጡን ከድስቱ በፊላና ጨለፈው።

ሰ. ሕፃኑን በአዲስ ቤሳ ላጨው።

ሸ. ልብሷን በመቁረጪት ቆረጠችው።

# 6ኛ ቀን

## አቀላጥፎ ማንበብ

### ያልተፈታ ችግር

### ቅድመንባብ

#### ተግባር

የሚከተለውን ጥያቄ በቃላችሁ መልሱ።

“ያልተፈታ ችግር” በሚል ርዕስ በቀረበው ምንባብ መሠረት የለቅሶ ሥርዓት የሚያስከትለውን ችግር ዘርዝራችሁ ተናገሩ።

## ማንበብ

### ተግባር

"ያልተፈታ ችግር" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ጥንድ ጥንድ በመሆን ርስበርስ እየተረዳዳችሁ አንብቡ።

## መናገር

## ውይይት ማካሄድ

### ተግባር

በሚከተሉት ሀሳቦች ላይ በመወያየት የደረሳችሁበትን የማጠቃለያ ሀሳብ በክፍል ውስጥ አቅርቡ።

ሀ. ጎጂ የሆነው የለቅሶ ሥርዓት እንዴት መሻሻል የሚችል ይመስላችኋል?

ለ. በሙታን መቃብር ላይ የሚሠሩ ሐውልቶች ተገቢ ናቸው ወይስ አይደሉም? ለምን?

## ሰዋስው

## በዓረፍተነገሩ ውስጥ ጠቋሚ መስተኣምርንና ወደረኛ መስተፃምርን መለየት

### ተግባር 1

በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ውስጥ ያሉትን ጠቋሚ መስተኣምሮች ለዩ።

ሀ. ያ መጽሐፍ በጣም ትልቅ ነው።

ለ. እነሱ ልጆች ተማሪዎቼ ናቸው።

ሐ. እነዚያን ሰዎች ታውቃቸዋለህ?

መ. ይህ ወንድሜ ያቺ ደግሞ እህቴ ናት።

ሠ. እሱን ተወውና ያን ደብተር ስጠኝ።

ረ. እሷ በግ የማን ናት?

ሰ. ያቺ መምህር በጣም ጎበዝ ናት።

### ተግባር 2

የሚከተሉትን ዓረፍተነገሮች ተገቢ ጠቋሚ መስተዓምሮችን ከቅንፍ ውስጥ በመምረጥ አሟሉ።

ሀ.______ አምና የተሸለመው ተማሪ የት ሄደ? (እሱ፣ያ)

ለ.______ ሰዎች መቼ ሄዱ? የማጫውታቸው ጉዳይ ነበረኝ። (እነዚያ፣ እነዚህ)

ሐ. ቱሪስቶች ______ ሀገር ይወዱታል፤ እኔም ልጎበኛት እሄዳለሁ። (ይቺን፣ ያቺን)

መ. _______ ወንበር ሰው ስለሌለው ና ቁጭ በል። (ይህ፣እሱ)

ሠ. _______ ወደቢሮ የምትሄደውን ልጅ ሮጠህ ጥራልኝ። (ያቺን፣ እሷን)

ረ. ______ ልጅ እንቅልፍ ስለወሰደው ተቀበለኝና አስተኛው (ያ፡ይህ)

## ተግባር 3

በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ውስጥ ያሉትን ወደረኛ መስተኣምሮች ለዩ።

ሀ. ጨረቃና ኮከብ የራሳቸው ብርሃን የላቸውም።

ለ. በቃላችሁ ወይም በጽሑፍ መልሱ።

ሐ. ስለጉዳዩ በስልክ ወይም በደብዳቤ ግለጽላት።

መ. አማርኛ ማወቅና አማርኛ መናገር የተለያዩ ናቸው።

ሠ. መብራት እስኪበራ ሻማ ወይም ኩራዝ እናብራ።

ረ. ሹመትና ሽረት የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ናቸው።

ሰ. የመንገዱን ግራ ጠርዝና የእግረኛ ማቋረጫን መስመር ተጠቀሙ።

## የቃላት ጥናት

### መነጠልና ማጣመር

**ተግባር**

የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት በመነጠልና በማጣመር አንብቡ።

| ነጣጥሎ ማንበብ | አጣምሮ ማንበብ |
|---|---|
| ሀ. አፈርሳታ-ው-ን | አፈርሳታውን |
| ለ. አለ-መግባባት-ኦች | አለመግባባቶች |
| ሐ. እንደ-ቅራኔ-ው | እንደቅራኔው |
| መ. በ-ሥነ-ምግባር-ኣቸው-ና | በሥነምግባራቸውና |
| ሠ. በ-ሚዛን-ኣዊ-ነት-ኣቸው | በሚዛናዊነታቸው |
| ረ. አለ-መስማማት-ኣቸው | አለመስማማታቸው |

## ማንበብ

### ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎች

### ቅድመንባብ

### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

**ተግባር**

ምንባቡን ከማንበባችሁ በፊት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. በአካባቢያችሁ ሰዎችን ወደግጭት የሚያስገቡ ጉዳዮች ምን ምን ናቸው? ግጭቶቹስ የሚፈቱት እንዴት ነው?

ለ. ሥዕሉን ተመልክታችሁ የተረዳችሁትን ተናገሩ?

## የማንበብ ሂደት

### ዋናና መዘርዝር ሀሳቦችን በመለየትና በማገናዘብ ማንበብ



### ተግባር

"ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎች" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ዋናና መዘርዝር ሐሳቦችን እየለያችሁ በለሆሳስ አንብቡ።

### ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎች

ሰዎች በማህበር ሲኖሩ በልዩ ልዩ ምክንያቶች ግጭት ውስጥ ሊገቡ ይችላሉ። የግጭቱ መጠን ይለያይ እንጂ፣ ሰዎች ባሉበት ቦታ ሁሉ ግጭት ይኖራል። ይሁን እንጂ ግጭቱን በወቅቱ በማስወገድ ሰላማዊና ጤናማ ህይወት መምራት ተገቢ ነው። ለዚህም ባህላዊ የግጭት መፍቻ መንገዶች አንድ አማራጭ ናቸው። ባህላዊ የግጭት ማስወገጃ ዘዴዎች የሚባሉት ቤተሰባዊ እርቅ፣ የዘመድ ዳኝነት፣ ሽምግልናና አፈርሳታ ናቸው።

በአንድ ቤተሰብ አባላት መካከል የሚፈጠር ግጭት በአብዛኛው በቤተሰብ አማካይነት መፍትሔ ሊያገኝ ይችላል። በልጆች፣ በልጆችና በወላጆች፣ በባልና በሚስት መካከል አለመግባባቶች ሲከሰቱ ቤተሰባዊ እርቅ ይካሄዳል። አብዛኛውን

ጊዜ የአስታራቂነትና የአስማሚነት ሚና የሚኖራቸው እናት፣ አባት ወይም በዕድሜ ከፍ ያሉ ልጆች ናቸው። ግጭቱ በባልና በሚስት መካከል ሲሆን ደግሞ በቅርብ የሚኖሩ የሥጋ ዘመዶች ሊጠሩ ይችላሉ። ጎረቤቶችም የሽምግልና ሥራ ይሠራሉ። በዘመድና በጎረቤት ሊፈታ ካልቻለ የዘመድ ዳኛ ወይም ሽማግሌዎች እንዲያዩት ይደረጋል።

ግጭቶች በዘመድ ዳኛ አማካይነት ይረግባሉ፤ መፍትሄም ያገኛሉ። የዘመድ ዳኛ ለሁለቱም ወገኖች የስጋ ዝምድና ያላቸው ዕድሜ ጠገብ አስታራቂ ናቸው። የዘመድ ዳኛ በጠበኞቹ ስምምነት ሊመረጡ ይችላሉ። ከዚያም የሁለቱን ጠበኞች ቃል ተራበተራ ያዳምጣሉ። ማብራሪያና ማስረጃም ይጠይቃሉ። ጉዳዩን በአግባቡ ከመረመሩ በኋላ ውሳኔ ይሰጣሉ፤ እንደጉዳዩ ክብደትና እንደቅራኔው ክረት የዘመድ ዳኛ ሌሎች ዘመዶችን በመጨመር አብረው እንዲሽመግሉ ያደርጋሉ። ከመካከላቸውም አንድ ሰው መርጠው ጉዳዩን ያስተናብራሉ።

ሽምግልና ሌላው የግጭት ማስወገጃ ዘዴ ነው።ሽምግልና በማህበረሰቡ ዘንድ ከፍተኛ ግምትና ተቀባይነት ይሰጠዋል። የሽማግሌዎች አባላት በሥነምግባራቸውና በሚዛናዊነታቸው በአካባቢው ሰው ዘንድ አክብሮት ያላቸው ሰዎች ይሆናሉ።ሽምግልና ብዙ ጊዜ በዕድሜ የገፉ ወይም በመካከለኛ ዕድሜ የሚገኙ ሰዎች ይወከሉበታል። ይሁን እንጂ ከዕድሜ ይልቅ ማህበራዊ ተቀባይነትን፣ ችሎታንና ተደማጭነትን ተመራጭ ሊያደርጉ ይችላሉ። ሽምግልና ግጭቱ ከሚመለከታቸው ወገኖች ገለልተኛነትን ስለሚጠይቅ ከዘመድ ዳኛ ይለያል። አንድን ግጭት ለመዳኘት ለሽምግልና የሚላኩ ሰዎች እንደጉዳዩ ክብደትና አስቸጋሪነት ሦስትና ከዚያ በላይ ሊሆኑ ይችላሉ። የሽምግልና ሂደት ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ጠበኞች በአንዳቸው አሳሳቢነት ሊጀመር ይችላል፤ ወይም ከጉዳዩ ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት በሌላቸው ገለልተኛ ሰዎች በሚቀርብ ጥያቄም ሊጀመር ይችላል። ሽምግልና አጥፊዎችን ይቀጣል፤ ተበዳዮች እንዲካሱ ያደርጋል፤ እርቅንና ሰላምን ያመጣል።

ሌላው ባህላዊ የግጭት ማስወገጃ ዘዴ አፈርሳታ ነው። አፈርሳታ ወይም አውጫጪኝ ማህበረሰብ በነቂስ ወጥቶ ወንጀለኛን የሚያውጣጣበት ሂደት ነው። አንድ ወንጀል ሲፈጸም የአካባቢው ኗሪዎች ወንጀሉን አለመስማታቸው ወይም በሌላ ሰው ሲፈጸም አለማየታቸውን በመሀላ ያረጋግጣሉ። ዘመናዊ የወንጀል ምርመራ ባልነበረበት ወቅት ወንጀል ሲፈጸም አፈርሳታ የሚመሩ ሰዎች የአካባቢውን ኗሪዎች ይሰበስባሉ። ከተሰበሰበው ህዝብ ፈንጠር ብለውም ይቀመጣሉ። ከዚያም የአካባቢው ኗሪዎች በተናጠል እየተነሱ ወንጀሉን የፈጸመውን አካል በምሥጢር ይጠቁማሉ። አፈርሳታውን የሚመሩት ሰዎችም የሚሰጣቸውን መረጃና ጥቆማ ትክክለኛነት በመስቀለኛ ጥያቄዎች ያረጋግጣሉ። በመጨረሻም የጠቋሚዎችን ማንነት ሳይገልጹ "ወንጀለኞችን ወፍ ነገረችን፤ ወንጀሉን የፈጸሙት እነገሌ ናቸው" በማለት በህዝብ ፊት ያጋልጣሉ። ወንጀለኞቹ ይመከራሉ፤ ይቀጣሉ። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን አፈርሳታ በዘመናዊ የወንጀል ምርመራ እየተተካ መጥቷል።

በአጠቃላይ ቤተሰባዊ እርቅ፣ የዘመድ ዳኝነት፣ ሽምግልናና አፈርሳታ ሰዎች ግጭቶችን የሚፈቱባቸው ዘዴዎች ናቸው። ዘዴዎቹ ለረዥም ዘመናት ሲያገለግሉ ቆይተዋል። ብዙዎቹ አሁንም እያገለገሉ ይገኛሉ። የተጣሉትን ለማስታረቅ፣ የተበደሉትን እንዲካሱ ለማድረግ፣ በማህበረሰብ ውስጥ ሰላምና ፍቅር ለማስፈን ዘዴዎቹ ከፍተኛ አስተዋጽዖ አላቸው። ስለሆነም በሳይንሳዊ መንገድ እየታገዙ ተጠናክረው ሊቀጥሉ ይገባል።

(አ.ብ.ክ.መ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ። 2001። *የባህል ልማት መሰናክሎች ቅኝት።* ገጽ 80-82 *መጠነኛ ለውጥ ተደርጎ የተወሰደ*)

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎች የተባሉት ምን ምን ናቸው? ለምንስ ባህላዊ ተባሉ?

ለ. አፈርሳታ ወይም አውጫጪኝ የሚከናወነው እንዴት ነው?

ሐ. በዘመድ ዳኝነትና በሽምግልና የግጭት ማስወገጃ ዘዴዎች መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

መ. ወላጆች በሚጋጩበት ጊዜ ልጆች ማስማማት የሚችሉ ይመስላችኋል? እንዴት?

ሠ. የግድያ ወንጀል የፈጸሙ ሰዎች በሽምግልና ቢታረቁ ስምምነቱ በሕግ የሚፀና ይመስላችኋል? ለምን?

ረ. በዘመናዊ የወንጀል ምርመራና በአውጫጪኝ መካከል ያለው አንድነትና ልዩነት ምንድን ነው?

ሰ. በአፈርሳታ ጊዜ አፈርሳታውን የሚመሩ ሰዎች ለወንጀለኞቹ "ወፍ ነገረችኝ" የሚሉት ለምንድን ነው?

# 8ኛ ቀን

## ቃላት

## ለቃላትና ለሐረጋት ፍቺ መስጠት

### ተግባር

ለሚከተሉት ቃላትና ሐረጋት በምንባቡ መሠረት ፍቻቸውን ጻፉ።

| | | |
|---|---|---|
| ሀ. ዕድሜ ጠገብ | መ. ነቂስ | ሰ. መስቀለኛ ጥያቄ |
| ለ. ክረት | ሠ. ካሳ | ሸ. አውጫጪኝ |
| ሐ. ማስተናበር | ረ. መሀላ | ቀ. ገለልተኛ |

## መጻፍ

### ድርሰት መጻፍ

### በዋናና በመዘርዝር ሀሳቦች አወቃቀር ስልት ድርሰት መጻፍ

#### ተግባር 1

ቀጥሎ "ይቅር ባይ" በሚል ርዕስ የቀረበውን ጽሑፍ መነሻ በማድረግ ባለሦስት አንቀጽ ድርሰት ጻፉ።

**ይቅር ባይ**

አቶ አስረስና አቶ ስሜነህ ጎረቤታሞች ናቸው። ባለፈው ወር የአቶ ስሜነህ በሬ የአቶ አስረስን ወይፈን ወግቶ ገደል አስገባባቸው። "በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ" እንዲሉ ሰሞኑን ደግሞ ጥቂሩ ውሻቸው የስድስት ዓመት ልጃቸውን ነከሰባቸው። በዚህ የተነሳ ሁለቱ ጎረቤታሞች ክፉኛ ተጣሉ። ይባስ ብለው አንዳቸው ባንዳቸው ላይ ሲዛቱ የሰፈር ሰዎች በመገላገል ለጊዜው ጠቡን አበረዱ።

አባባ ይታገሱም ከሠፈር ሽማግሌዎች አንዱ ናቸው። በአካባቢው የታወቁ፣ የብዙ ባለትዳሮችን ቤት ከመፍረስ ያዳኑ፣ በርካታ ሰዎችን ከግድያ ወንጀል ያተረፉ ብልህና ነገር አዋቂ ናቸው። __________________________________________________________________________________________________________________________________________

#### ተግባር 2

የሚከተሉትን ጥያቄዎች መሠረት በማድረግ በቡድን ሆናችሁ የወላጅ መምህር ህብረት (ወ.መ.ህ) በትምህርትቤታችሁ የሚፈጠሩ ችግሮችን እንዴት እንደሚፈቱ በመጠየቅ በክፍል ውስጥ በጽሑፍ አቅርቡ።

ሀ. የወ.መ.ህ አባላት ምን ምን ዓይነት ችግሮች ኣጋጠሟቸው?

ለ. የወ.መ.ህ አባላት ያጋጠሟቸውን ችግሮች የሚፈቱት እንዴት ነው?

### የአጻጻፍ ሥርዓት

### አርትኦት ማድረግ

**ተግባር**

“ይቅር ባይ” በሚል ርዕስ የጻፋችሑትን ድርሰት ርስበርስ በመተራረም የፊደል ግድፈትና የሥርዓተነጥብ አጠቃቀም ችግሮችን ለይታችሁ አውጡ።

## 9ኛ ቀን

## አቀላጥፎ ማንበብ

### ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴ

### ቅድመንባብ

**ተግባር**

“ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴ” በሚል ርዕስ ከቀረበው ምንባብ ውስብስብ ቃላትንና ሐረጋትን ለይታችሁ እያወጣችሁ አንብቡ።

### ማንበብ

**ተግባር**

“ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴ” በሚል ርዕስ ከቀረበው ምንባብ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት አንድ አንድ አንቀጽ አቀላጥፋችሁ አንብቡ።

## መናገር

### ውይይት ማካሄድ

**ተግባር**

የሚከተሉትን ሀሳቦች መነሻ በማድረግ በቡድን ተወያይታችሁ የደረሳችሁበትን የማጠቃለያ ሀሳብ በክፍል ውስጥ ተናገሩ።

ሀ. በቤተሰብ አባላት መካከል ግጭት ቢፈጠር ጉዳያቸው በዘመድ ዳኛ ቢታይ ይሻላል ወይስ በሽምግልና? ለምን?

ለ. ለግጭቶች መፍትሔ ለመስጠት ባህላዊ ሽምግልና ይሻላል ወይስ ፍርድቤት? ለምን?

## ሰዋስው

### በዓረፍተነገር ውስጥ ጠቋሚ መስተኣምርንና ወደረኛ መስተፃምርን መጠቀም

#### ተግባር 1

በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ውስጥ ያሉትን ጠቋሚ መስተኣምሮች ለይታችሁ ጻፉ።

ሀ. ያቺ ጎበዝ ተማሪ አንደኛ ወጣች።

ለ. ይህ ሰው ጤነኛ አይመስለኝም!

ሐ. ያ ሰውዬ ስሙን ነገረኝ።

መ. እነዚያ ተማሪዎች በየት በኩል ወጡ?

ሠ. እሷ ልጅ የታደሰ እህት ናት።

ረ. ጥፋተኞቹ እነዚህ ሳይሆኑ እነዚያ ናቸው።

#### ተግባር 2

የሚከተሉትን ጠቋሚ መስተኣምሮች በመጠቀም ዓረፍተነገር ሥሩ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ይህ | እነሱ | ይቺ | እሱ |

#### ተግባር 3

በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ውስጥ ባሉት ክፍት ቦታዎች ተስማሚ ወደረኛ መስተፃምሮችን ጻፉ።

ሀ. አባትህን —— እናትህን ተያዥ ማቅረብ አለብህ።

ለ. ፈተና ስለደረሰ ደብተራችንን —— መጽሐፋችንን ማንበብ ይገባናል።

ሐ. ጊዜው ብርድ ስለሆነ ሻይ —— ቡና እንጠጣ።

መ. ከአትክልት —— ከሥጋ የቱን ትመርጫለሽ?

ሠ. አጎቴ በመስከረም —— በጥር ሳይመጣ አይቀርም።



# ሴቶችን ማብቃት

## በትምህርት እኩልነትን ማስረጽ

ምዕራፍ 9

1ኛ ሳምንት 1ኛ ቀን

## የቃላት ጥናት

### መነጠልና ማጣመር

### ተግባር 1

የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት በመነጠልና በማጣመር አንብቡ።

| | ነጣጥሎ ማንበብ | አጣምሮ ማንበብ |
|---|---|---|
| ሀ | እንዲ-ሠሩ-አቸው | እንዲሠሯቸው |
| ለ | እንደ-አመለከቱ-ት | እንዳመለከቱት |
| ሐ | እንደ-አለ-አቸው | እንዳላቸው |
| መ | ሥርዓት-ትምህርት-ኦች-ም | ሥርዓተትምህርቶችም |
| ሠ | ሊፈጠር-ል-አቸው | ሊፈጠርላቸው |
| ረ | ተ-ደ-ን-ግ-ጓ-ል | ተደንግጓል |

### ተግባር 2

የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት ድምጽ በማሰማት አቀላጥፋችሁ አንብቡ።

ሀ. እንደሚጠበቅም

ለ. ለመመራመር

ሐ. ትምህርቶችም

መ. ስምምነቶች

ሠ. መንከባከብ

ረ. የሰደደውን

ሰ. እ.አ.አ. (እንደአውሮፖውያን አቆጣጠር)

ሸ. ዓ.ም. (ዓመተምሕረት)

## ማንበብ

## ሥርዓተጾታና ትምህርት

### ቅድመንባብ

### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

**ተግባር**

"ሥርዓተጾታና ትምህርት" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ከማንበባችሁ በፊት የሚከተሉትን የቅድመንባብ ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. በርዕሱ የተገለጹት ሁለት ጽንሰሀሳቦች ምን ምን ናቸው? ግንኙነታቸውስ ምንድን ነው?

ለ. ከምንባቡ ግራና ቀኝ በተለየ ቀለም የተጻፉት ዓረፍተነገሮች ዋና መልዕክት ምንድን ነው?

### የማንበብ ሂደት

### የተከታታይ ድርጊቶችን ግንኙነት በማስተዋል ማንበብ

**ተግባር**

ቀጥሎ "ሥርዓተጾታና ትምህርት" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ሀሳቦችን በድርጊት ቅደምተከተል እያደራጃችሁ በመረዳት በለሆሳስ አንብቡ።

## ሥርዓተጾታና ትምህርት

ሴቶች የማህበረሰቡ ግማሽ አካል ናቸው። ይሁን እንጂ በዓለም ካልተማሩ ሰዎች መካከል ከፍተኛውን ቁጥር የያዙት እነሱ ናቸው። "ሴት ወደማጀት፣ ወንድ ወደችሎት" በሚል የተሳሳተ ብሂል ሴቶች ከቤት እንዳይወጡ ተደርገው ቆይተዋል። ወንዶች ለመማር፣ ለማወቅ፣ ለመመራመር፣ ለአመራር ወዘተ እንደተፈጠሩ ተደርጎ ይታመናል። ቤት ማጽዳትና ማስዋብ፣ ምግብ ማብሰል፣ ልጅ መንከባከብ ወዘተ ደግሞ የሴቶች ሥራ እንደሆኑ ይታሰባል። በመሆኑም ወንዶች ወደትምህርትቤት ሲሄዱ ሴቶች እነሱ ብቻ እንዲሠሯቸው የግድ ባልሆኑ የቤት ውስጥ ሥራዎች ይጠመዳሉ። በዚህ የተነሳ ወንዶች ከሴቶች የተሻለ የመማር ዕድል አገኙ፣ ተጠቃሚም ሆኑ።

> **ሴቶች ሕፃናት እንደወንዶቹ ሁሉ የመማር መብት ስላላቸው እንዲማሩ እድል ሊፈጠርላቸው ይገባል!**

የሴቶችን እኩልነት ለማረጋገጥና ትምህርትን ለሁሉም ለማዳረስ የሚያስችሉ ዓለማቀፋዊ ስምምነቶች በተለያዩ ጊዜያት ተደርገዋል። እ.አ.አ. በ1981 ሴቶችና

ወንዶች እኩል የመማር መብት እንዳላቸው፣ እ.አ.አ. በ1990 ደግሞ ጾታ ሳይለይ ሁሉም ሕፃናት እኩል የመማር መብት እንዳላቸው ተወስኗል። በመሆኑም ሴቶች ሕፃናት እንደወንዶቹ ሁሉ የመማር መብት ስላላቸው እንዲማሩ ዕድል ሊፈጠርላቸው ይገባል። ለዚህም ሲባል እ.አ.አ. በ1995 በየትኛውም የትምህርት ደረጃ ሴቶችን ማግለል እንዲቆም፣ ሥርዓተትምህርቶችም ሁለቱንም ጾታዎች አማክለው እንዲዘጋጁና ሴቶች ቢማሩ የሚኖራቸውን ሚና እንዲያካትቱ ተደንግጓል። ይህንንም በማጠናከር እ.አ.አ. እስከ2005 ሁሉም ሕፃናት በተለይ ሴቶች በነፃ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት እንዲማሩ ግብ ተጥሏል። በተጨማሪም እ.አ.አ. እስከ2015 ድረስ በአንደኛና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤቶች የሥርዓተጾታን እኩልነት ማረጋገጥ እንደሚጠበቅም ስምምነት ላይ ተደርሷል።

**የሴቶች የትምህርት ዕድል ተጠቃሚነት ከወንዶቹ ጋር ሲነጻጸር እጅግ አናሳ ነው።**

በእነዚህ ስምምነቶች መሠረት ሀገራት በሥርዓተጾታ ላይ ያለውን የተዛባ አመለካከት ለመለወጥና ለማስተካከል ከፍተኛ ጥረቶችን አድርገዋል። በዚህም ምክንያት ትምህርትቤት በመግባትና ትምህርት በመጨረስ ረገድ በወንዶችና በሴቶች መካከል ልዩነቶች ቢኖሩም መጠነኛ መሻሻል ታይቷል። እ.አ.አ. ከ1990 ዓ.ም. ጀምሮ በትምህርት መስክ በሁሉም የዓለም ክፍሎች አጠቃላይ የሴቶች ተሳትፎ መጠን 10 በመቶ ጨምሯል። በአብዛኞቹ የዓለም ክፍሎች ደግሞ በመሠረታዊ ትምህርት የሴቶች የተሳትፎ መጠን ከወንዶች ጋር ተቀራራቢ ሆኗል። ይህም ሆኖ ግን አሁንም በትምህርት መስክ ያለውን የጾታ ልዩነት ለማስወገድ ተጨማሪ ጥረቶች ያስፈልጋሉ።

ኢትዮጵያ በሥርዓተጾታ ረገድ ያሉ ልዩነቶችን ለማስወገድ ጥረቶችን ብታደርግም ትምህርትን በተመለከተ በወንዶችና በሴቶች መካከል ሰፊ ልዩነቶች አሉ። በኢትዮጵያ በሴቶችና በወንዶች የትምህርት ተሳትፎ ላይ እ.አ.አ. በ2011፣ በ2012፣ በ2013 በተለያዩ ዓለማቀፍ ድርጅቶች ጥናቶች ተካሂደዋል። ጥናቶቹ እንዳመላከቱት ወንዶች ከሴቶች በተሻለ የትምህርት ዕድል ተጠቃሚ ሆነዋል። በኢትዮጵያ ማንበብና መጻፍ የሚችሉ ሴቶች 18 በመቶ ብቻ ሲሆኑ ወንዶቹ ግን 42 በመቶ ናቸው። ወደዩኒቨርሲቲ ከገቡት ተማሪዎች መካከል ሴቶቹ 24 በመቶ ብቻ ናቸው። በመሆኑም በሁለቱ ጾታዎች መካከል ያለውን የትምህርት ተሳትፎ ልዩነት ለማጥበብ በርካታ ተግባራት በመከናወን ላይ ናቸው። ይሁን እንጂ ለረጅም ጊዜ ሥር የሰደደውን ማህበራዊ አመለካከት ሙሉ በሙሉ ለመለወጥ ገና ብዙ ሥራ ይጠበቃል።

በአጠቃላይ ሴቶችንና ወንዶችን እኩል የማስተማር ልምድ በሁሉም የዓለም ክፍሎች የዳበረ አይደለም። በዚህ የተነሳ የሴቶች የትምህርት ተሳትፎ ከወንዶች እጅግ ያነሰ ነው። ይህም የሀገርን ዕድገት በከፍተኛ ደረጃ ይጎዳል። በማንኛውም

መስክ ሀገራዊ ዕድገት ለማምጣት የሴቶች ሚና ከፍተኛ ነው። ስለሆነም የተዛቡ ማህበራዊ አመለካከቶችን ማስወገድ ተገቢ ይሆናል። ሴቶችንና ወንዶችን እኩል ማስተማርም አስፈላጊና ወቅታዊ ጉዳይ ነው።

(ሲዳ። 2010። ኢዱኬሽን ጀንደር ኢኳሊቲ። ገጽ1-7 እና ኦክስፋም ኢትዮጵያ ካንትሪ ፕሮፋይል። 2013። ለውጥ ተደርጎ የተወሰደ)

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር 1

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. "ሴት ወደማጀት ወንድ ወደችሎት" የሚለው አባባል ምንን ይገልጻል? በአሁኑ ጊዜ ተቀባይነት ያለው ይመስላችኋል? ለምን?

ለ. "የሥርዓተጾታን እኩልነት ማረጋገጥ" ሲባል ምን ማለት ይመስላችኋል?

ሐ. ሴቶች ብቻ እንዲሠሯቸው የግድ ያልሆኑ የቤትሥራዎች የተባሉት ምን ምን ናቸው?

መ. በሴቶች ላይ ለረጅም ጊዜ ሥር የሰደደው የተሳሳተ ማህበራዊ አመለካከት ምንድን ነው?

ሠ. በአሁኑ ሰዓት ሴቶችን ለማበረታታት ምን ምን ተግባራት እየተከናወኑ ነው?

ረ. ከትምህርትቤት ባሻገር የሴቶች ተሳትፎ በምን በምን መስክ ሊረጋገጥ ይገባል ትላላችሁ?

### ተግባር 2

ቀጥሎ የቀረበውን ሠንጠረዥ በምንባቡ መሠረት በትክክል አሟሉ።

| ዓመተምሕረት (እ.አ.አ.) | ድንጋጌዎች |
|---|---|
| 1981 | ሴቶች ከወንዶች እኩል የመማር መብት እንዳላቸው ተደነገገ። |
| 1990 | |
| 1995 | |
| 2005 | |

# 2ኛ ቀን

## ቃላት

### ለቃላትና ለሐረጋት ዐውዳዊ ፍቺ መስጠት

**ተግባር**

ከምንባቡ ውስጥ ዘጠኝ ቁልፍ ቃላትንና ሐረጋትን ለይታችሁ በማውጣት ዐውዳዊ ፍቻቸውን ግለጹ።

## መጻፍ

### ድርሰት መጻፍ

### በተጋርቶ ድርሰት መጻፍ

**ተግባር 1**

የሚከተለውን መንደርደሪያ ዓረፍተነገር መነሻ በማድረግ በቡድን ሆናችሁ በተጋርቶ የተሟላ አንቀጽ ጻፉ።

- ሴቶች በትምህርት ከወንዶች እኩል እንዳይሳተፉ በርካታ እንቅፋቶች ያጋጥሟቸዋል።

**ተግባር 2**

በትምህርትቤታችሁ ያለውን የሥርዓተጾታ ክበብ አስተባባሪ በመጠየቅ የክበቡን የሥራ እንቅስቃሴ በሚመለከት ሦስት አንቀጾች ያሉት ድርሰት ጻፉና በክፍል ውስጥ አንብቡ።

### የአጻጻፍ ሥርዓት

### ቃላትን በተለያየ ቅርጽ መጻፍ

**ተግባር**

በሠንጠረዡ ውስጥ ያሉትን ቃላት በምሳሌው መሠረት ቅርጻቸውን በመቀያየር በደብተራችሁ ጻፉ።

| ቆረሰ | አቋረሰ | ማቋረስ | አቆራረስ |
|---|---|---|---|
| ገመሰ | | | |
| ከበበ | | | |
| በሰለ | | | |
| ቦደነ | | | |
| ለቀመ | | | |
| ሞገተ | | | |

## 3ኛ ቀን

# አቀላጥፎ ማንበብ

## ሥርዓተጾታና ትምህርት

### ቅድመንባብ

#### ተግባር

"ሥርዓተጾታና ትምህርት" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ከማንበባችሁ በፊት የሚከተሉትን የቅድመንባብ ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. በአሁኑ ጊዜ ሴቶችን ለማበረታታት ምን ምን ድጋፎች እየተደረጉ ናቸው?

ለ. "ሴቶችን ማስተማር ማህበረሰብን ማስተማር ነው" የሚለው አባባል የሚያስተላልፈው መልዕክት ምን ይመስላችኋል?

### ማንበብ

#### ተግባር

"ሥርዓተጾታና ትምህርት" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ አንድ አንድ አንቀጽ ድምጽ በማሰማት በየተራ አንብቡ።

## ማዳመጥ

## ትምህርት ለሴቶች

### ቅድመማዳመጥ

### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

#### ተግባር

የሚከተሉትን የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. ሴቶችን በትምህርት ማብቃት ጠቀሜታው ምንድን ነው?

ለ. በኢትዮጵያ ውስጥ በትምህርት ዘርፍ ተጽዕኖ ፈጣሪ (መልካም አርዓያ) ከሆኑ ሴቶች መካከል የምታስታውሷቸውን ጥቀሱ።

### የማዳመጥ ሂደት

#### ተግባር

ምንባቡን እያዳመጣችሁ በማዳመጥ ሂደት የሚቀርብላችሁን ጥያቄ በቃላችሁ መልሱ።

### አዳምጦ መረዳት

#### ተግባር 1

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. "የተማሩ እናቶች ካልተማሩ እናቶች ይልቅ ቤተሰባዊ ሰላምን ያሰፍናሉ" በሚለው ሀሳብ ትስማማላችሁ? እንዴት?

ለ. የተማሩ እናቶች አከታትለው ላለመውለድ የሚጠቀሙባቸው ዘዴዎች ምን ምን ናቸው?

ሐ. በትምህርትቤታችሁ የሥርዓተጾታ እኩልነትን የሚያሳዩ ተግባራት ምን ምን ናቸው?

መ. ከጥቂት አሥርት ዓመታት በፊት በተለያዩ የዓለም ክፍሎች ሴቶችን ማስተማር የተለመደ ያልነበረው ለምን ይመስላችኋል?

ሠ. እናቶች የተሻለ ገቢ ቢያገኙ እንዴት የሚጠቀሙበት ይመስላችኋል?

ረ. እናቶች የራሳቸው ገቢ ሳይኖራቸው ማግባታቸውና መውለዳቸው ምን ዓይነት ጉዳት የሚያስከትልባቸው ይመስላችኋል?

#### ተግባር 2

የሚከተለውን የቢጋር ሠንጠረዥ መሠረት በማድረግ የተማሩና ያልተማሩ እናቶች የሚመሳሰሉባቸውንና የሚለያዩባቸውን ባህርያት ግለጹ።

# እናቶች




## ሰዋስው

## አያያዦችን መጠቀም

### ተግባር

የሚከተሉትን አያያዦች በመጠቀም ዓረፍተነገሮችን አሟልታችሁ ጻፉ።

| ነገርግን | ስለዚህ | ምክንያቱም | ቢሆንም | አለበለዚያ |
|---|---|---|---|---|

ምሳሌ፡- የቤትሥራ ሠርቻለሁ፤ ስለዚህ በክፍል ውስጥ እሳተፋለሁ።

ሀ. ኳስ መጫወት እወዳለሁ፤ ——— እንድጫወት አይፈቀድልኝም።

ለ. የቤት ውስጥ ሥራ በዝቶብኛል፤——— ባለኝ ጊዜ አጠናለሁ።

ሐ. ከትምህርትቤት አትቅር፤——— የዕለቱ ትምህርት ያመልጥሀል።

መ. ገንዘብ ተልኮልኛል፤ ——— ወደባንክ መሄድ አለብኝ።

ሠ. ስለኢትዮጵያ ታሪክ ለማወቅ መጻሕፍት አንብቡ፤ ——— ትልልቅ ሰዎችን ጠይቁ።

ረ. ሥራነሽ አዲስ ልብስ ተገዝቶላታል፤———ደስተኛ አይደለችም።

## ማንበብ

### የትነበርሽ

**ቅድመንባብ**

**የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ**

**ተግባር**

ምንባቡን ከማንበባችሁ በፊት የሚከተሉትን የቅድመንባብ ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. አካል ጉዳተኛነት በማንኛውም መስክ ስኬታማ ከመሆን የሚያግድ ይመስላችኋል? ለምን?

ለ. በምንባቡ ውስጥ በተለየ ቀለም ተለይቶ በተጻፈው ሀሳብ መሠረት የባለታሪኳ ውሳኔ ፍላጎቷን ዳር ለማድረስ የሚጠቅማት ይመስላችኋል? ለምን?

**የማንበብ ሂደት**

**ተከታታይ ድርጊቶችን እየለዩ ማንበብ**

**ተግባር**

"የትነበርሽ" በሚል ርዕስ የቀረበውን ተራኪ ምንባብ ተከታታይ ድርጊቶችን እየለያችሁ በለሆሳስ አንብቡ።



## የትነበርሽ

የተወለደችው በ1975 ዓ.ም. አማራ ሳይንት አካባቢ ነው። ወላጆቿ በግብርና ሥራ የሚተዳደሩ ነበሩ። ሦስት ወር ሲሆናት ወላጆቿ ትዳራቸውን አፍርሰው በፍቺ በመለያየታቸው ከእናቷና ከአያቶቿ ጋር አደገች። አምስት ዓመት ሲሞላት ግን የዓይን ብርሃኗን አጣች። እናቷ ለዓይን ሕክምና ወደአዲስ አበባ ቢወስዷትም የተደረገላት ሕክምና ውጤት አልባ ሆነ። ስድስት ዓመት ሲሆናት እናቷ ወደሻሸመኔ የዓይነስውራን ካቶሊክ አዳሪ ትምህርትቤት ላኳት። ይቺ ሕፃን የትነበርሽ ንጉሴ ትባላለች።

**ለሰዎች መብት መከበር በነበራት ከፍተኛ ፍላጎት የተነሳ የሕግ ትምህርት ለማጥናት ወሰነች።**

የአንደኛ ደረጃ ትምህርቷንም የተከታተለችው በዚሁ ትምህርትቤት ነበር። በትምህርትቤቱ ውስጥ ከሚማሩ ሌሎች ዓይነስውራን ሕፃናት ጋር እየተጫወተችና በትምህርት እየተፎካከረች ልጅነቷን አሳለፈች። በወቅቱ ትምህርትቤቱ ይተዳደር የነበረው ዓይነስውር ሕፃናትን ለመንከባከብ በመጡ መነኩሲቶች ነበር። በመሆኑም ሴቶች ጠንካራና ውጤታማ መሪዎች መሆን እንደሚችሉ ከእነዚህ መነኩሲቶች ተማረች። በዚህ ትምህርትቤት ጥሩ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ክህሎትን አዳብራለች፣ ጠንካራ በራስ የመተማመን ስሜት ገንብታለች።

ስድስተኛ ክፍልን እንደጨረሰች በራስ የመተማመን ስሜቷን ይዛ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ለመማር ወደአዲስ አበባ ሄደች። እስከ12ኛ ክፍል በዳግማዊ ምኒልክ

ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤት ማየት ከሚችሉ ተማሪዎች ጋር ተማረች። በትምህርትቤቱ ውስጥ በነበራት ቆይታ የተለያዩ ክበባትን በመምራት ንቁ ተሳትፎ አደረገች። በትምህርትቤቱ የተማሪዎች መማክርት ምክትል ፕሬዚዳንት በመሆን ለሦስት ተከታታይ ዓመታት አገለገለች። የፀረአደንዛዥ ዕጽና የፀረኤች.አይ.ቪ. / ኤድስ ክበባት ሊቀመንበር በመሆንም ሠራች። በአጠቃላይ በዚሁ ትምህርትቤት ስድስት ያህል ክበባትን በኃላፊነት መርታለች።

የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን ስትጨርስ በዲግሪ መርሀግብር ለመማር ወደአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ገባች። ለሰዎች መብት መከበር በነበራት ከፍተኛ ፍላጎት የተነሳ የሕግ ትምህርት ለማጥናት ወሰነች። በሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤት የነበራትን ንቁ ተሳትፎ በዩኒቨርሲቲው ውስጥ አጠናክራ ቀጠለች። በዩኒቨርሲቲው የፀረኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ንቅናቄ የህዝብ ግንኙነት ኃላፊና ሊቀመንበር በመሆንም አገለገለች። በተጨማሪም ቀደምሲል “የሴቶች ክበብ”፣ አሁን “የሴት ተማሪዎች ማህበር” የተባለውን አቋቋመች፤ መራች። በኢትዮጵያ ሴት ዓይነስውራን ማህበር ውስጥ ለአራት ዓመታት በአመራርነት ሠርታለች። ከ20 የሚበልጡ ማህበራትን በበጎ ፈቃደኝነት አገልግላለች።

የትነበርሽ ሕግ በማጥናቷ ሰዎች እኩል መብቶች እንዳሏቸው ተረዳች። ለዚህም የአካል ጉዳተኛና የችግረኛ ሰዎችን መብቶች ለማስከበር ወሰነች። ለአካል ጉዳተኞችና ለተረሱ ወገኖች ተቆርቋሪ በመሆንም መሥራት ጀመረች። በ1998 ዓ.ም. በሕግ ትምህርት የመጀመሪያ ዲግሪዋን እንደጨረሰች የኢትዮጵያ የአካል ጉዳተኝነትና ልማት ማዕከልን በማቋቋም ሂደት በንቃት ተሳተፈች፤ ምኞቷን እውን ለማድረግም ጥረቷን ቀጠለች።

በማዕከሉ ውስጥ በተለያዩ የኃላፊነት ቦታዎች ላይ አገልግላለች፤ በርካታ ተግባራትንም አከናውናለች። ከ2004 ዓ.ም. ጀምራ የማዕከሉ ዋና ዳይሬክተር ሆና እየሠራች ነው። በሀገር ውስጥ ያለው ልማት አካል ጉዳተኞችን ያካተተ እንዲሆን ጥራለች። አዲስ የሚገነቡ ህንፃዎች ለአካል ጉዳተኞች ምቹ መሆን እንዳለባቸው ለሚያስገድደው የኢትዮጵያ የግንባታ ሕግ የተደራሽነት መመሪያ አርቅቃለች። ኢትዮጵያ፣ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት እ.አ.አ በ2006 ያወጣውን የአካል ጉዳተኞች መብት ስምምነት ተቀብላ እንድታጸድቅ በነበረው ቅስቀሳ ላይ ንቁ ተሳትፎ አድርጋለች። የአካል ጉዳተኞችን ኢኮኖሚያዊ አቅም በመገንባት ረገድ ውጤታማ ሥራ ሠርታለች። የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የአካል ጉዳተኝነት ፖሊሲ እንዲያወጣና ፖሊሲውን የሚያስፈፅም ማዕከል እንዲያቋቁም የራሷን አስተዋጽዖ አበርክታለች።

ልበብርሃኗ የትነበርሽ ባበረከተችው ከፍተኛ አስተዋጽዖ በሀገር አቀፍና በዓለም አቀፍ ደረጃ በርካታ ሽልማቶችን አግኝታለች። ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በማህበራዊ አገልግሎት የትምህርት መስክ ሁለተኛ ዲግሪዋን ይዛለች። ባለትዳርና የአንዲት ልጅ እናት የሆነችው ይቺ ወጣት አሁንም የተዘነጉ ወገኖቿ መብት እንዲከበር

በመታገል ላይ ትገኛለች። አካል ጉዳተኞች ጠንካሮችና ራዕያቸውን ማሳካት የሚችሉ መሆናቸውንም እያሳየች ነው።

(ከሚሪ ጄን ዋግሌይና ሳባ ገብረመድህን። 2007። *ተምሳሌት እፁብድንቅ ኢትዮጵያውያን ሴቶች። ገጽ 198-201 ለውጥ ተደርጎበት የተወሰደ*)

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር 1

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. የትነበርሽ ሕፃናትን ለመንከባከብ ከመጡት መነኩሲቶች የተማረችው ምንድን ነው?

ለ. የትነበርሽ የሕግ ትምህርት በማጥናቷ ለአካል ጉዳተኞችና ለችግረኞች ያበረከተችው አስተዋጽ™ ምንድን ነው?

ሐ. በትምህርትቤት በልዩ ልዩ ክበባት መሳተፍ ምን ጠቀሜታ ያስገኛል?

መ. ምንባቡ የፈጠረባችሁ ስሜት ምንድን ነው?

ሠ. በምንባቡ ሊተላለፍ የተፈለገው ዋና መልዕክት ምን ይመስላችኋል? እንዴት ይታወቃል?

### ተግባር 2

የትነበርሽ በ2ኛ ደረጃ ትምህርትቤት፣ በዩኒቨርሲቲና በሥራ ዓለም ያከናወነቻቸውን ጉልህ ተግባራት በደብተራችሁ ላይ ጻፉ።

| በ2ኛ ደረጃ ትምህርትቤት | በዩኒቨርሲቲ ደረጃ | በሥራ ዓለም |
|---|---|---|
| •<br>•<br>• | •<br>•<br>• | •<br>•<br>• |

## 5ኛ ቀን

## ቃላት

### በፍቺ ልዩ የሆነውን ቃል መለየት

### ተግባር

ከተሰጡት አማራጮች መካከል በምንባቡ መሠረት በፍቺ ልዩ የሆነውን ቃል ምረጡ።

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ሀ. እኩል | ለ. አቻ | ሐ. ተመጣጣኝ | መ. መሳ |
| 2 | ሀ. ራዕይ | ለ. ምኞት | ሐ. ስኬት | መ. ዓላማ |
| 3 | ሀ. መቆርቆር | ለ. መጸጸት | ሐ. መቆጨት | መ. መደመም |
| 4 | ሀ. ችሎታ | ለ. መስክ | ሐ. ሙያ | መ. ዘርፍ |
| 5 | ሀ. መፎካከር | ለ. መተናነቅ | ሐ. መወዳደር | መ. መነጻጸር |
| 6 | ሀ. አልቦ | ለ. ጥቂት | ሐ. ባዶ | መ. ምንም |
| 7 | ሀ. መወደስ | ለ. መታገዝ | ሐ. መረዳት | መ. መደገፍ |

## መጻፍ

### ድርሰት መጻፍ

### የራስን የህይወት ታሪክ መጻፍ

### ተግባር 1

የሚከተሉትን መሠረታዊ ሀሳቦች በመጠቀም የየራሳችሁን የህይወት ታሪክ ጽፋችሁ በክፍል ውስጥ አንብቡ።

**1. የውልደትና የቤተሰብ ሁኔታ**

ሙሉ ስም፣ የትውልድ ቦታና ጊዜ
የወላጆች ሙሉ ስም

**የራስ የህይወት ታሪክ**

**2. የአስተዳደግ ሁኔታ**

**3. የትምህርትቤት ህይወት**

የተገኙ ሽልማቶችና ምስጋናዎች (የተሳተፋችሁባቸው ክበባት)

**4. የወደፊት ህልም**

### ተግባር 2

የጻፋችሁትን የህይወት ታሪክ መረጃዎች በትክክል መካተታቸውንና በአግባቡ መደራጀታቸውን በማረጋገጥ ከልሳችሁ ጻፉ።

## የአጻጻፍ ሥርዓት

### የቃላትን ቅደምተከተል በማስተካከል ዓረፍተነገር መጻፍ

### ተግባር 1

ቃላትን በትክክለኛ ቅደምተከተላቸው አዋቅራችሁ ዓረፍተነገሮቹን አስተካክላችሁ ጻፉ።

ሀ. የታጠበውን/ልብስ/ዓለሙ/በልብስ ማስጫው ላይ/ አሰጣው።

ለ. ጣለችው/ወንድሟ/የገዛላትን/እርሳስ/ሶስና።

ሐ. ወርቂቱን/ነከሳት/ጥቁሩ ውሻ/ክፉኛ።

መ. ሕፃኑ/አደናቅፎት/ሰበረው/ስለወደቀ/ብርጭቆ/የያዘውን።

ሠ. የቴሌቪዥን/ድራማ/አሚናት/የማታውን/አልተመለከተችም።

ረ. ሠርተዋል/ሁሉም/ተማሪዎች/የቤትሥራውን/በጥሩ ሁኔታ።

ሰ. የወርቅ/አንደኛ/ሀብል/ስለወጣሁ/እናቴ/ሸለመችኝ።

ሸ. ቤት/ሰብረው/የሰረቁትን/ፖሊሱ/ያዛቸው/ሌቦች/ልብስ።

## 6ኛ ቀን

## አቀላጥፎ ማንበብ

### የትነበርሽ

### ቅድመንባብ

### ተግባር

"የትነበርሽ" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ አቀላጥፋችሁ ከማንበባችሁ በፊት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. የትነበርሽ የአንደኛ ደረጃ፣ የሁለተኛ ደረጃና የዩኒቨርሲቲ ትምህርቷን የተከታተለችው የት ነው?

ለ. የትነበርሽ የሠራችባቸውን የኃላፊነት ቦታዎች ግለጹ።

### ማንበብ

"የትነበርሽ" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ጥንድ ጥንድ ሆናችሁ በመረዳዳት አንድ አንድ አንቀጽ አንብቡ።

## መናገር

### ሀሳብን በንግግር መግለጽ

#### ተግባር

በሚከተሉት ሀሳቦች በቡድን በመወያየት የደረሳችሁባቸውን የማጠቃለያ ሀሳቦች በክፍል ውስጥ በንግግር አቅርቡ።

ሀ. የአካል ጉዳተኞች ውጤታማ እንዲሆኑ ከግለሰብ፣ ከማህበረሰብና ከመንግሥት ምን ይጠበቃል?

ለ. "አካል ጉዳተኞችን መንከባከብ ራስን መንከባከብ ነው" የሚለው አበባል ምን ማለት ይመስላችኋል? በምሳሌ አስረዱ።

## ሰዋስው

### አያያዦችን መጠቀም

#### ተግባር

ተስማሚ አያያዦችን ከቅንፉ ውስጥ በመምረጥ በክፍት ቦታው ጻፉ።

ሀ. ጎንደርን በጣም እወዳታለሁ፤ ——— ከባህር ዳር አትበልጥብኝም። (ቢሆንም፣ በመሆኑም)

ለ. እጇን ሳትታጠብ ምግብ አትበላም፤ —— አንዳንድ በሽታዎች ከንጽህና ጉድለት እንደሚመጡ ታውቃለች። (ይሁንና ምክንያቱም)

ሐ. እናቴ የእኔን ጥሩ ደረጃ ላይ መድረስ በጉጉት ትጠብቃለች፤——— ትምህርቴን ሌት ከቀን ጠንክሬ ማጥናት አለብኝ። (ምክንያቱም ስለዚህ)

መ. እኔ ደጋግሜ ነግሬያታለሁ፤——— ታናሿ ስለሆንኩ ምክሬን አትቀበልም። (በመሆኑም ነገርግን)

ሠ. ትዕግስት ይኑርህ፤ ——— ሁሉም ሲያልፍ ታያለህ። (እንጂ ወይም)

ረ. አሁን የጥናት ሰዓት ነው፤ ——— ቴሌቪዥኑ መዘጋት አለበት። (ሆኖም ስለዚህ)

ሰ. ብዙ ጊዜ በድሎኛል፤ ——— ወንድምነቱን አልክደውም። (ይሁንና፣ ስለሆነም)

## የቃላት ጥናት

### ውስብስብ ቃላትንና ሐረጋትን ማንበብ

የሚከተሉትን ውስብስብ ቃላትና ሐረጋት ድምጽ በማሰማት አንብቡ።

ሀ. ፓይለት

ለ. ቦይንግ

ሐ. ፎከር 50

መ. ዳሽ 8Q-400

ሠ. ቦይንግ 757፣ ቦይንግ 767

ረ. ቦይንግ 777፣ ቦይንግ 787

ሰ. ለካፒቴንነት

ሸ. ሜሪ-ጄን ዋግሌይ

## ማንበብ

### ፋና ወጊዋ ካፒቴን

### ቅድመንባብ

### ለአዳዲስ ቃላት ፍቺ መስጠት

**ተግባር**

የሚከተሉትን ቃላት ፍቺ በቃላችሁ ግለጹ።

ሀ. ካፒቴን

ለ. ፓይለት

ሐ. ሥነህንፃ

መ. ፋናወጊ

### ማንበብ ሂደት

### የድርጊቶችን ቅደምተከተል እየለዩ ማንበብ

**ተግባር**

“ፋና ወጊዋ ካፒቴን” በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ የድርጊቶችን ቅደምተከተል እየለያችሁ በለሆሳስ አንብቡ።

# ፋና ወጊዋ ካፒቴን




## አስተዳደግ

ህዳር 21 ቀን 1969 ዓ.ም. በባህር ዳር ከተማ ተወለደች። አራት ልጆች ላፈሩት ወላጆቿ የመጀመሪያ ልጅ ናት። ሦስት ዓመት ሲሞላት ቤተሰቦቿ ወደአዲስ አበባ ይዘዋት ሄዱ። ከዚያም የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቷን "አሳይ" በሚባል የህዝብ ትምህርትቤት ተማረች። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን ደግሞ በቦሌ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤት ተከታተለች። ወጣቷ አምሳለ ጓሉ እንደኛነው ትባላለች።

ወላጆቿ ከልጅነቷ ጀምረው በራሷ እንድትተማመን አድርገዋታል፤ ህልሟን እንድታሳካ አበረታተዋታል፤ ለትምህርቷም በቂ ድጋፍ አድርገውላታል። ሴትነቷ ወንዶች ከደረሱበት ደረጃ ከመድረስ እንደማያግዳት አስረድተዋታል። እንደዝንባሌዋ እንድትጓዝም አግዘዋታል። በመሆኑም ትምህርቷን በአግባቡ ተከታትላ ለከፍተኛ ትምህርት ወደዩኒቨርሲቲ ገባች።

## የከፍተኛ ትምህርትና ስልጠና

ከሐምሌ 1987 ዓ.ም. ጀምሮ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሥነህንፃ ትምህርት መማር ጀመረች። የአንደኛ ዓመት ተማሪ ሳለች የኢትዮጵያ አየር መንገድ የአብራሪዎች ማሠልጠኛ ትምህርትቤት ያዘጋጀውን የመግቢያ ፈተና ተፈተነች። ይሁን እንጂ ፈተናውን ባለማለፏ የመጀመሪያ ሙከራዋ ሳይሳካላት ቀረ። በዚህም ተስፋ ሳትቆርጥ የበለጠ ጥረት አደረገች። በዩኒቨርሲቲው የመጨረሻ ዓመት ተማሪ እያለች የመግቢያ ፈተናውን በድጋሚ ተፈተነችና አለፈች። ከዚያም ሐምሌ1992 ዓ.ም. ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በሥነህንፃ እንደተመረቀች የአብራሪነት ሥልጠናውን

ጀመረች።

አምሳለ አውሮፕላን አብራሪ የመሆን ፍላጎት ያደረባት ከልጅነቷ ጀምሮ ነው። አባቷ በየሳምንቱ ከእህቶቿ ጋር ወደአየር ማረፊያ እየወሰዱ አውሮፕላን ሲያርፍና ሲነሳ ያሳዩአት ነበር። በወቅቱ ግዙፎቹ አውሮፕላኖች ሰማዩን እየሰነጠቁ ሲከንፉ ማየቷ ልዩ ስሜት ፈጥሮባታል። የዘጠነኛ ክፍል ተማሪ ሳለች በሰፈሯ የሚኖሩትን ሁለት የበረራ ሠልጣኞች አለባበስ ስትመለከትም ሙያውን እጅግ ወደደችው።

ከሁለት ዓመት በኋላ ሥልጠናውን ጨርሳ ህዳር 1994 ዓ.ም. በረዳት አብራሪነት ተመረቀች። ለሰባት ዓመታት ያህል 4475 ሰዓታት አውሮፕላኖችን አበረረች። ከዚያም ከተለያዩ ምዘናዎችና ግምገማዎች በኋላ የካፒቴንነት (የዋና አብራሪነት) ሥልጠና ጀመረች። አስፈላጊውን የክህሎት ማጎልበቻ ሥልጠና በማጠናቀቋ በ2002 ዓ.ም. ካፒቴን ሆነች።

## የካፒቴንነት ሙያ

አምሳለ ስድስተኛዋ ኢትዮጵያዊ ሴት ፓይለት ስትሆን ለካፒቴንነት የበቃችው ግን እሷ ብቻ ናት። ሙሉ እመቤት እምሩ፣ አሰገደች አሰፋ፣ ሶፍያ ገዛኸኝ፣ ሀና ወልዴና እሌኒ ታደሰ ቀደምት ኢትዮጵያውያን ሴት ፓይለቶች ነበሩ። ይሁን እንጂ ስልጠናና መመዘኛ በማሟላት የዋና አብራሪነት ደረጃ ላይ አልደረሱም። አምሳለ ግን ብቃቷን አስመስክራ ለካፒቴንነት በቅታለች። በዚህም የልጅነት ህልሟን አሳክታ በሙያዋ ካፒቴንነት ደረጃ ላይ የደረሰች የመጀመሪያዋ ኢትዮጵያዊ ሴት ለመሆንም ችላለች። አምሳለ የሠለጠነችውም ሆነ የሠራችው በተለያዩ አውሮፕላኖች ነው። ከእነዚህ መካከል ፎከር 50፣ ዳሽ 8Q-400፣ ቦይንግ 757፣ ቦይንግ 767 ይገኙበታል።

## የወደፊት ህልም

ባለትዳርና የሦስት ልጆች እናት የሆነችው ካፒቴን አምሳለ በርካታ ህልሞች አሏት። ወደፊት በሞያዋ በመግፋት ቦይንግ 777፣ ቦይንግ 787 የመሳሰሉትን ትላልቅ አውሮፕላኖች በካፒቴንነት የማብረር ፍላጎት አላት። በቤተሰባዊ ህይወቷም ልጆቿ አድገውና ስኬታማ ሆነው የማየት ምኞት አላት። በአዲስ አበባና በሌሎች የክልል ከተሞች ለሚገኙ ተማሪዎች የህይወት ታሪኳን፣ ተሞክሮዋንና ስኬቷን በማጋራት የበኩሏን አስተዋጽዖ ማበርከት ትፈልጋለች። በዚህም ለአዲሱ ትውልድ በተለይም ለልጃገረዶች አርዓያ መሆን እንደምትችል ታምናለች። ሴቶችም ሆኑ ወንዶች ያለሙትን ለማሳካት እኩል መብትና ዕድል አግኝተው ማየትም ትናፍቃለች። ሴቶች በተሻለ የስኬት ጎዳና ተሰልፈውና ከጥገኝነት ተላቀው የማየት ተስፋም አላት። ለዚህ ደግሞ ራሷ ጥሩ ተምሳሌት እንደሆነች ርግጠኛ ናት።

(ሜሪ-ጄን ዋግሌይና ሳባ ገብረመድህን። 2007። *ተምሳሌት እፁብድንቅ ኢትዮጵያውያን ሴቶች።* ከሚለው ለውጥ ተደርጎበት የተወሰደ።)

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር 1

በምንባቡ መሠረት ድርጊቶችን ከተከናወኑበት ዓመተምህረት ጋር በጽሑፍ አዛምዱ።

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 1994 | 1969 | 1992 | 1987 | 2002 |

ሀ. በባህር ዳር ከተማ ተወለደች።

ለ. የሥነህንፃ ትምህርት መማር ጀመረች።

ሐ. በረዳት አብራሪነት ተመረቀች።

መ. ካፒቴን ሆነች።

ሠ. በሥነህንፃ ትምህርት ተመረቀች።

### ተግባር 2

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. የወላጆች ድጋፍ ለልጆች ስኬት ያለው ፋይዳ ምን ይመስላችኋል?

ለ. አምሳለ ከልጅነቷ ጀምሮ አውሮፕላን አብራሪ የመሆን ፍላጎት ያደረባት ለምንድን ነው?

ሐ. የሦስተኛው አንቀጽ ዋና ሀሳብ ምንድን ነው?

መ. አምሳለን ከሌሎች ቀደምት ሴት ፓይለቶች ልዩ የሚያደርጋት ምንድን ነው?

ሠ. የአምሳለ የወደፊት ህልም ምንድን ነው? የምታሳካው ይመስላችኋል?

## 8ኛ ቀን

## ቃላት

### ለቃላትና ለሐረጋት ዐውዳዊ ፍቺ መስጠት

### ተግባር 1

በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ለተሠመረባቸው ቃላትና ሐረጋት ዐውዳዊ ፍቺ ስጡ።

ሀ. ኃይለኛ ጉንፋን ስለያዛት ያለማቋረጥ <u>ሳለች</u>።

ለ. አፄ ቴዎድሮስ በሠሩት መልካም ሥራ ዘወትር ስማቸው <u>ሲነሳ</u> ይኖራል።

ሐ. የሀገሯን ዳር ድንበር በማስከበር ላይ እያለች ህይወቷ አለፈ።

መ. የሀገሬን መልክዓምድር ስጎበኝ ውስጤ በርካታ ይሞላል።

ሠ. ሰውን ያለሥራው መግፋት ህሊናን ያደማል።

ረ. ተማሪዎች በትምህርትቤታቸው ውስጥ ያለሙትን አትክልት አስጎበኙ።

## ተግባር 2

በሚከተሉት ቃላት የተለያየ ፍቺ ያላቸው ሁለት ሁለት ዓረፍተነገሮች መሥርቱ።

ሀ. ጠላ

ለ. መረቀ

ሐ. በጠበጠ

መ. ቀመቀመ

ሠ. ጠረጠረ

ረ. ሰፋ

ሰ. ሰማ

ሸ. አጠረ

ቀ. አማት

# መጻፍ

## ድርሰት መጻፍ

## ንዑሳን ርዕሶችን በመጠቀም ድርሰት መጻፍ

## ተግባር

የሚከተሉትን ንዑሳን ርዕሶችና ሀሳቦች በመጠቀም የክብር ዶክተር አርቲስት ጥላሁን ገሠሠን የህይወት ታሪክ ጻፉ።

## የግለሰብ የህይወት ታሪክ

### 1. የውልደትና የቤተሰብ ሁኔታ

- ሙሉ ስም፣ የትውልድ ቦታና ጊዜ
- ክብር ዶክተር አርቲስት ጥላሁን ገሠሠ ንጉሥ
- የእናት ስም፣ ወ/ሮ ጌጤ ጉርሙ
- የተወለደው መስከረም 19,1933 ዓ.ም. በደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን፣ በወሊሶ ከተማ

### 2. የሥራ ሁኔታ

- ትምህርትን ማቋረጥና በአዲስ አበባ፣ በሀገርፍቅር ቲያትር ቤት መቀጠር
- በክብር ዘበኛ የሙዚቃ ባንድ መቀጠር
- በብሔራዊ ቲያትር መቀጠር

### 3. የትምህርትቤት ህይወት

- የአንደኛ ደረጃ ትምህርት በወሊሶ ከተማ በራስ ጎበና ትምህርትቤት
- ከፍተኛ የሙዚቃ ፍቅር አደረበት ርዕሰመምህሩ በሙዚቃው እንዲገፋበት አበረታቱት።

### 4. ያበረከተው አስተዋጽዖ፣ ሽልማትና ህልፈተ ህይወት

- በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የክብር ዶክትሬት ድግሪ
- ከኢትዮጵያ ሥነጥበባትና መገናኛ ብዙኃን ድርጅት
- በተለያዩ ሀገራት በመዘዋወር የኢትዮጵያን ባህል ማስተዋወቅ
- በስኳር በሽታ መታመም
- ሚያዝያ 19/2001 ዓ.ም. በሞት መለየት

### የአጻጻፍ ሥርዓት

### ድርሰት አርሞና አስተካክሎ መጻፍ

**ተግባር**

በድርሰት መጻፍ ሥር የጻፉችሁትን የህይወት ታሪክ ከጓደኞቻችሁ ጋር በመለዋወጥ በሚከተሉት ነጥቦች መሠረት አርማችሁና አስተካክላችሁ ጻፉ።

- ንዑሳን ርዕሶችን መጠቀምና መግለጽ
- የቃላትን ፊደላት አለመግደፍ
- ሥርዓተነጥብን በተገቢ ቦታ መጠቀም

## 9ኛ ቀን

## አቀላጥፎ ማንበብ

**ፋናወጊዋ ካፒቴን**

### ቅድመንባብ

**ተግባር**

የሚከተሉትን የቅድመንባብ ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. አምሳለ ጓሉ ውጤታማ እንድትሆን የቤተሰቦቿ አስተዋጽ™ ምን ነበር?

ለ. ከአምሳለ ጓሉ የህይወት ታሪክ በመነሳት ስለሴቶች መማር ምን ማለት ይቻላል?

### ማንበብ

**ተግባር**

"ፋና ወጊዋ ካፒቴን" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ አንድ አንድ አንቀጽ የሬዲዮ ዜና አንባቢን በማስመሰል በፍጥነትና በትክክል አንብቡ።

## መናገር

### የወደፊት ምኞትን በንግግር መግለጽ

የሚከተሉትን ሀሳቦች መነሻ በማድረግ የወደፊት ምኞታችሁን በክፍል ውስጥ ተናገሩ።

- እናንተ ትምህርታችሁን ስትጨርሱ በምን የሙያ መስክ መሰማራት

ትፈልጋላችሁ? ለምን?

- የመረጣችሁትን የሙያ መስክ ለማግኘት ምን ጥረት እያደረጋችሁ ነው? ወደፊትስ ምን ይጠበቅባችኋል?

## ሰዋስው

### በአንቀጽ ውስጥ አያያዦችን መጠቀም

### ተግባር 1

የሚከተሉትን አያያዦች በተገቢ ቦታዎች በመጠቀም አንቀጹን የተሟላ አድርጉ።

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ሆኖም | ነገርግን | ወይም | በመሆኑም | እና | አለበለዚያ | ምክንያቱም |

ለአባቷ ሁለተኛም የመጨረሻም ልጅ ናት። አባቷ እሷ ጥሩ ደረጃ ላይ ደርሳ ማየት ይመኛሉ። "ተስፋዬ አንቺነሽ ልጄ!" የሚለውን የአባቷን ንግግር ሰንቃ ትምህርቷን መማር ጀመረች። ሌሊት ተነስታ ስታጠና ቅዝቃዜው ይቆረጥማታል፤ 1___ ጥናቷን ሳታቋርጥ እስኪነጋ ድረስ ታጠናለች። ጓደኞቿ አዲስ ልብስ፣ ዘመናዊ ቦርሳና ልዩ ልዩ ጌጣጌጦች ሲኖራቸው እሷ ግን ተመኝታ አታውቅም፤ 2___ የእሷ ራዕይ ጥሩ ውጤት አምጥታ ያለእናት ያሳደጓትን አባቷን ህልም እውን ማድረግ ነው። በርካታ ችግሮች ደርሰውባታል፤ 3___ አንዳቸውም ከጥረቷ ወደኋላ አላስቀሯትም። ሁሉንም በድል ተወጥታቸዋለች። ከ8ኛ-12ኛ ክፍል ድረስ በትምህርቷ የሚወዳደራት አልነበረም። የምታገኛቸው ሽልማቶች 4____ ምስጋናዎች ኃይል ሆነዋታል። ሳይንቲስት 5____ መሀንዲስ የመሆን ፍላጎት ነበራት። ጥረቷ ሁሉ ፍሬ አፍርቶ አሁን የዩኒቨርስቲ የምህንድስና ተማሪ ሆናለች። ዛሬም ከመቼውም በላይ ጠንክራ ታጠናለች። ቤተመጻሕፍት ታዘወትራለች፤ 6___ የእስካሁኑ ልፋቷና የአባቷ ቃል መና እንደሚቀርባት ታውቃለች። 7___ ሙሉ ጊዜዋንና ትኩረቷን በትምህርቷ ላይ ብቻ አድርጋ ወደስኬት እየገሰገሰች ትገኛለች።



# ተውኔት

## ምዕራፍ 10

### ትዕይንት

1ኛ ሳምንት 1ኛ ቀን

## የቃላት ጥናት

### ውስብስብ ቃላትንና ሐረጋትን ማንበብ

**ተግባር**

የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት ድምጽ በማሰማት አንብቡ።

ሀ. ኢያ ጓንጉል

ለ. ፕላስቲክ

ሐ. ታስረጂኛለሽ

መ. በመደርደሪያው

ሠ. ሲወርድ ሲዋረድ

ረ. ከእንግዲህ ወዲህ

ሰ. ኮስተር ብለው

ሸ. የራስ ቅሏን

## ማንበብ

### "ጅብ ነች" ትዕይንት 1

### ቅድመንባብ

### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

**ተግባር**

"ጅብ ነች" በሚል ርዕስ ከቀረበው ተውኔት ውስጥ ትዕይንት "1"ን ከማንበባችሁ በፊት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. ተውኔት ማለት ምን ማለት ነው? ምሳሌ መስጠት ትችላላችሁ?

ለ. ገፀባህርያት ማለት ምን ማለት ነው?

ሐ. ሥዕሉን ተመልከቱና የተረዳችሁትን ተናገሩ።

መ. "ጅብ ነች" የሚለው ርዕስ ምን እንደሚገልጽ ገምታችሁ ተናገሩ።

## የማንበብ ሂደት

### ተውኔት ማንበብ

### ተግባር

"ጅብ ነች" በሚል ርዕስ ከቀረበው ተውኔት፣ ትዕይንት "1"ን ገፀባህርያቱን ወክላችሁ ንግግራቸውን እያስመሰላችሁ ድምጽ በማሰማት አንብቡ።

**"ጅብ ነች ትዕይንት 1"**



በቤቱ ወለል ዙሪያ መደብ ይታያል። በመደቡ ላይ ደግሞ አጎዛዎች ጣል ጣል ተደርገዋል። ከመደቡ መካከል አንድ ትንሽ ጠረጴዛ የተቀደደ ኘላስቲክ ለብሷል። አንድ ወጣት ምግብ በመሶብ ቀርቦለት እየበላ ይታያል። በግድግዳው ላይ የቀኝ እጅ መዳፍ አሻራዎች በነጭ ቀለም አልፎ አልፎ ታትመዋል። በአንደኛው ጥግ ከግድግዳው ጋር ተያይዞ የተሠራ የዕቃ መደርደሪያ ይታያል። በመደርደሪያው ላይ የተለያየ መጠን ያላቸው ድስቶች፣ ሳህኖች፣ የውኃ ኩባያዎችና የወጥ ጭልፋዎች ይታያሉ። ከመደርደሪያው በስተቀኝ ደግሞ የውኃ ጀሪካኖች ተደርድረዋል።

**ወ/ሮ አሰገደች፡-** ብላ እንጂ ልጄ! ከእናት ቤት የተገኘውን ነው፤ አልጥምህ አለ እንዴ?

**አሰፋ፡-** አይ እማማ! አዲስ አበባም ስቆይ ከዚህ የጣፈጠ አላገኘሁ፤ ግን ሆዴ ሞላብኝ።

**ወ/ሮ አሰገደች፡-** <u>እንዳሻህ፤</u> ድካሙ ሲለቅህ ትበላለህ።

**አሰፋ፡-** (ተነስቶ እጁን ታጥቦ ወደበሩ አቅጣጫ ይሄዳል።)

**ወ/ሮ አሰገደች፡-** ምነው አሰፋ የት ልትሄድ ነው?

**አሰፋ፡-** አገሩን ልይ ብዬ ነው።

**ወ/ሮ አሰገደች፡-** ቆይ እንጂ፤ በኋላ ጥላው በረድ ሲል ነዋ ልጄ! በዚህ ጠራራ ፀሐይ ደግ አይደለም።

**አሰፋ፡-** ምን ይለኛል ብለሽ ነው?

**ወ/ሮ አሰገደች፡-** እንዴ! አይሆንም! ሽታው ... ደግሞ ምናምኑ ምን ይታወቃል ብለህ ነው? የኛ አገር እንዳዲሳባ አይደለም ልጄ። አተላው፣ አመዱ በየቦታው ነው የሚፈሰው። በዚህ ሰዓት ሽታው ደግ አይደለም።

**አሰፋ፡-** (የበሩን <u>መቃን</u> ተደግፎ ወደውጪ እየተመለከተ) እማ ያቺ ማን ናት?

(ረጅም ፀጉር ያላት አንዲት ወጣት በርቀት ትታያለች።)

**ወ/ሮ አሰገደች፡-** የቷ ልጄ?

**አሰፋ፡-** ያ...ያቺ!

**ወ/ሮ አሰገደች፡-** አሰፋ! በል ቀስ ብለህ ግባ...! ይቺን ልጅ ከእንግዲህ ወዲህ፣ ዓይንህ ፈፅሞ እንዳላያት ሁን።

**አሰፋ፡-** ምነው? ለምን እማማ?

**ወ/ሮ አሰገደች፡-** ቡዳ ነች! ልጄ። ያውም እንዲህ እንዳትመስልህ፤ ዋና ቀርጣፊዋ!

**አሰፋ፡-** (ነገሩን <u>በማቃለል</u> ሳቅ እያለ) አይ እማማ! አሁን ይ...ይቺ!

**ወ/ሮ አሰገደች፡-** (ኮስተር ብለው) አዎን እሷ። በዚህ መልኳ እያታለለች ነው ብዙውን ጀግና ያበላሸችው። እንግዲህ ስማና እረፈው፤ ማታማታ ጅብ ትሆናለች።

**አሰፋ፡-** (በማዘን ስሜት) እማማ! እንደዚህ አትበይ። እስኪ አስቢው እማማ! የሰው ልጅ እንዴት ጅብ መሆን ይችላል? እማማ ይህ <u>ሲወርድ ሲዋረድ</u> የመጣ ያገራችን <u>አፈታሪክ</u> ነው። ሰው፣ ማታ ጅብ ቀን ደግሞ ተመልሶ ሰው

ይሆናል ማለት የማይሆን ነገር ነው። በሳይንስ ትምህርታችንም ተቀባይነት የለውም።

**ወ/ሮ አሰገደች፦** (ይበልጥ ቱግ ብለው) ልጄ እንግዲህ ትሰማ እንደሆነ የወለድኩህ እኔ ነኝ፤ አንተ አይደለህም፤ ስማኝ! ጅብ ትሆናለች ስልህ ጅብ ትሆናለች ነው። ይህን የአንተን አትሆንም የሚለውን ትምህርት ለዚያው ለአዲሳባህ አድርገው።

**አሰፋ፦** (ድምፁን ከፍ አድርጎ) እሺ! አንቺ ጅብ መሆኗን እንዴት ታስረጂኛለሽ?

**ወ/ሮ አሰገደች፦** (በቁጣ) እንዴት ታስረጂኛለሽ ይላል! ይህ ሊያቅተኝ!? ምነው አሁን <u>በቀደምለት</u> ድፍን አገሬው አልተረዳውም እንዴ! አንድ <u>ወዳጇ</u> ነው አሉ፣ አልጋዋ ላይ በመድኀኒት አፍዝዛ አስተኝታው ሳለ እሷ ከጅቦቹ ጋር ስትጋልብ <u>አንግታ</u> ስትመለስ አውልቃ የደበቀችውን <u>የራስ ቅሏን</u> አግኝቶ አልደበቀውም! እሺ እሱም ይቅር፤ ሦስት ቀን ሙሉ አልመልስላት ብሎ በሯን ዘግታ ስታለቅስ አልከረመችም!?

እሺ እሱም ይቅር! አሁን ያየሽውን ፀጉሯን ራሱኑ ከነራስ ቅሏ ከሰውዬው እጅ ሰኞ ገበያ ውስጥ ሲዞር አላየነውም! ህም! ደግሞ እንዴት ታስረጂኛለሽ! ባየህ አገር ግልብጥ ብሎ ወጥቶ እግዚኦ ብሎ ለምኖት ነው የመለሰላት። (አየለች ከውጪ ወደውስጥ ስትገባ ትታያለች።) ምነው አንቺ አየለች? አትነግሪውም ለወንድምሽ? በይ እኮ! የስምየለሽን ፀጉር እወዳጇ እጅ አላየሽውም? እሷ በሯን ዘግታ ሦስት ቀን ሙሉ ስታለቅስ አልሰማሻትም?

**አየለች፦** አዎን ጋሼ። እማማ ያለችው ሁሉ እውነት ነው። ስምየለሽ ቡዳናት። ፀጉሯን አንድ ወዳጇ ሲያዞረው ሁላችንም አይተነዋል።

**አሰፋ፦** (ደንገጥ በማለት ለጥቂት ደቂቃዎች ዝም ብሎ ከቆየ በኋላ) ስንቱን ሰዓት በክርክር አሳለፍነው። እማማ አሁን ፀሀዩ በረድ ብሏል። ዘወር ዘወር ብዬ <u>ቀዬውን</u> አይቼ ልመለስ። (አሰፋ ሲወጣ ይታያል።)

**ወ/ሮ አሰገደች፦** (እደጅ ድረስ ተከትለውት እየወጡ) እንግዲህ እንዲያው አደራህን ልጄ! ወደዚያ ቤት ፊፅመህ ዝር እንዳትል።

**አሰፋ፦** እሺ እማማ!

**ወ/ሮ አሰገደች፦** አየለች! በይ እሱን ነጠላ አቀብዪኝና ከነአያ ጓንጉል ቤት ደርሰን እንምጣ።

**አየለች፦** (ለእናቷ ነጠላ ታቀብልና እናቷን ትከተላለች።)

(ታደሰ ሊበን። 1949። *መስከረም።* ከገጽ11-19 ለውጥ ተደርጎበት የተወሰደ)

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር 1

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. አሰፋ ምሳውን በልቶ ወደውጪ ሊሄድ ሲል እናቱ የከለከሉት ለምንድን ነው?

ለ. ወ/ሮ አሰገደች ስምየለሽን "ቡዳ ነች" ሲሉት፣ አሰፋ ነገሩን በማቃለል ሳቅ ያለው ለምን ይመስላችኋል?

ሐ. ወ/ሮ አሰገደች ስለስምየለሽ "ጅብ መሆን" ያቀረቡት ማስረጃ ምንድን ነው?

መ. በሳይንስ ትምህርት ተቀባይነት የሌለው ምንድን ነው? ለምን?

ሠ. ከወ/ሮ አሰገደችና ከአሰፋ ሀሳብ የትኛውን ትደግፋላችሁ? ለምን?

ረ. አሰፋ በስምየለሽ "ቡዳነት" የተስማማ ይመስላችኋል? እንዴት ይታወቃል?

ሰ. የአሰፋን ወይም የወ/ሮ አሰገደችን ሀሳብ ደግፋችሁ ተጨማሪ ምክንያት አቅርቡ፤

ሸ. ማን ያሸንፍ ይመስላችኋል? እናቱ ወይስ አሰፋ? እንዴት ይታወቃል?

### ተግባር 2

"በጅብ ነች" ተውኔት፣ ትዕይንት "1" መሠረት የሚከተለውን ሠንጠረዥ በተገቢ ሀሳብ አሟሉ።

| የታሪኩ መሰረታዊ ነገሮች | በታሪኩ መጀመሪያ | በታሪኩ መካከል | በታሪኩ መጨረሻ |
|---|---|---|---|
| ገፀባህርያት፣ | ጊዜው፣ ቦታው፣ ገፀባህርያት፣ መከራከሪያ ጉዳይ | አቢይ ግጭት | እልባት፣ መፍትሔ |
| መቼት (የታሪኩ ጊዜና ቦታ) | | | |
| ግጭት | | | |
| እልባት (መፍትሔ) | | | |

## 2ኛ ቀን

## ቃላት

### ለቃላትና ለሐረጋት ዐውዳዊ ፍቺ መስጠት

#### ተግባር 1

ለሚከተሉት ቃላትና ሐረጋት በምንባቡ መሠረት ዐውዳዊ ፍቻቸውን በጽሑፍ ግለጹ።

| | | |
|---|---|---|
| ሀ. ቀዬ | መ. ማቃለል | ሰ. በቀደምለት |
| ለ. መቃን | ሠ. የራስ ቅል | ሸ. ሲወርድ ሲዋረድ |
| ሐ. አንግታ | ረ. እንዳሻህ | ቀ. አፈታሪክ |

#### ተግባር 2

ለሚከተሉት ቃላት የመዝገበቃላት ፍቺ ስጡ።

| | | |
|---|---|---|
| ሀ. አጎዛ | መ. ጠራራ | ሰ. ጋሼ |
| ለ. አሻራ | ሠ. መቀርጠፍ | ሸ. አያ |
| ሐ. ማህተም | ረ. ማፍዘዝ | ቀ. ቡዳ |

## መጻፍ

### ድርሰት መጻፍ

### ገፀባህርያትን በድርጊታቸው ገምግሞ አንቀጽ መጻፍ

#### ተግባር

በተውኔቱ መሠረት አሰፋን በድርጊቱ ገምግማችሁ አንድ አንቀጽ ጻፉ፤ ግምገማችሁን በሚከተሉት ነጥቦች መሠረት አከናውኑ።

- የገፀባህርይ ድርጊት መገምገሚያ ቅጽ በመጠቀም በመጀመሪያው ረድፍ ውስጥ ገፀባህርዩ ያከናወናቸው ዋናዋና ድርጊቶች በሚለው ሥር አሰፋ ያከናወናቸውን ድርጊቶች በዝርዝር ጻፉ።
- "የእኔ አመለካከት/አስተያየት" በሚለው ሥር ደግሞ የአሰፋን ድርጊቶች በመደገፍ ወይም በመቃወም የራሳችሁን አመለካከት/አስተያየት በመዘርዘር ጻፉ።
- በመጨረሻም የገፀባህርይውን ድርጊቶችና የራሳችሁን አመለካከት/አስተያየት

በመጠቀም አንድ አንቀጽ ጻፉ።

- አንቀጹን ስትጽፉ አያያዥ ቃላትን (በመጀመሪያ፣ በመቀጠል፣ ከዚህም ባሻገር፣ ቢሆንም፣ የሆነሆኖ፣ እንዲሁም፣ ባጠቃላይ፣ በመጨረሻ፣ ወዘተ.) መጠቀማችሁን አረጋግጡ።

ገፀባህርይን መገምገሚያ ቅጽ

የገፀባህርዩ ስም፡- አሰፋ

| ገፀባህርዩ ያከናወናቸው ዋና ዋና ድርጊቶች | ስለገፀባህርዩ ድርጊቶች የግል አመለካከቴና አስተያየቴ |
|---|---|
| • | • |
| • | • |
| • | • |

## የአጻጻፍ ሥርዓት

## ድርሰትን መከለስ፣ ማረምና አስተካክሎ መጻፍ

### ተግባር

በ1ኛው ሳምንት፣ በ2ኛው ቀን በድርሰት መጻፍ ሥር የጻፋችሁትን አንቀጽ በሚከተሉት ነጥቦች መሠረት በማረም እንደገና አስተካክላችሁ ጻፉ።

- ተገቢ የሀሳብ አደረጃጀት አለው?
- አያያዥ ቃላቱ ዓረፍተነገሮቹን በተጠየቅ አስተሳስረዋል?
- ተገቢ ሥርዓተነጥቦች በተገቢ ቦታ አሉ?
- ከፊደላት ግድፈት ነጻ ነው?
- ባለቤትና ማሠሪያ አንቀጽ በፆታ፣ በጊዜ፣ በመደብ፣ በቁጥር---ስምምነት አላቸው?

## 3ኛ ቀን

# አቀላጥፎ ማንበብ

## "ጅብ ነች" ትዕይንት 1

### ቅድመንባብ

**ተግባር**

የሚከተሉትን የቅድመንባብ ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. "'ጅብ ነች' ትዕይነት 1" በሚለው ተውኔት ወ/ሮ አሰገደችና አሰፋ በሀሳብ ያልተስማሙበት ምክንያት ምን ይመስላችኋል?

ለ. አሰፋ እናቱን ማሳመን የቻለ ይመስላችኋል? ለምን?

### ማንበብ

**ተግባር**

"'ጅብ ነች' ትዕይንት 1" በሚል ርዕስ የቀረበውን ተውኔት ገፀባህርያቱን ወክላችሁ ንግግራቸውን በማስመሰል ጥንድ ጥንድ ሆናችሁ ድምጽ በማሰማት አንብቡ።

# ማዳመጥ

## ታማኝነት

### ቅድመማዳመጥ

### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

**ተግባር**

"ታማኝነት" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ከማዳመጣችሁ በፊት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. ታማኝነት ማለት ምን ማለት ነው? ቃሉን ከዚህ በፊት ሰምታችሁት ወይም ተጠቅማችሁበት ታውቃላችሁ? በምን አጋጣሚ?

ለ. ከርዕሱ ሥር ያለውን ሥዕል በመመልከት የተረዳችሁትን ግለጹ።

## የማዳመጥ ሂደት

## የሀሳቦችን የድርጊት ቅደምተከተል ግንኙነት እያደራጁ ማዳመጥ

### ተግባር

“ታማኝነት” በሚል ርዕስ የቀረበውን ተውኔት የሀሳቦችን የድርጊት ቅደምተከተል ግንኙነት በማደራጀት አዳምጡ።



## አዳምጦ መረዳት

### ተግባር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. ካሳና ምስክር የወደቀውን ቦርሳ ከማግኘታቸው በፊት የሚወያዩት ስለምን ነበር?

ለ. ካሳና ምስክር ባገኙት ቦርሳ ውስጥ ያለው ንብረት ምንድን ነው?

ሐ. ቦርሳውን ያገኛችሁት እናንተ ብትሆኑ ምን ታደርጉ ነበር? ለምን?

መ. ወድቆ የተገኘውን ቦርሳ ለፖሊስ መስጠት የሚያስፈልገው ለምንድን ነው?

ሠ. ምስክር “‘የሰው ገንዘብ ያጠፋል’ ትል ነበር አያቴ” ሲል ምን ማለቱ ይመስላችኋል?

ረ. ካሳና ምስክር ቦርሳውን እንዳገኙት መከራከር የጀመሩት በምን ምክንያት ነው?

ሰ. ካሳ ቦርሳውን ለፖሊስ ለመስጠት ባይስማማ ኖሮ ምስክር ምን የሚያደርግ ይመስላችኋል?

ሸ. ያዳመጣችሁት ተውኔት ዋና መልዕክት ምንድን ነው?

## ሰዋስው

### ቀጥተኛና ኢቀጥተኛ ተሳቢን መለየት

#### ተግባር 1

በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ውስጥ ቀጥተኛና ኢቀጥተኛ ተሳቢዎችን ለይታችሁ አመልክቱ።

ምሳሌ፡- “አስራት ለእህቱ ብር ላከላት።” በዚህ ዓረፍተነገር ውስጥ “ብር” የሚለው ቀጥተኛ ተሳቢ ሲሆን፣ “ለእህቱ” የሚለው ደግሞ ኢቀጥተኛ ተሳቢ ነው።

ሀ. አልማዝ ለአባቷ ደብዳቤ ጻፈች።

ለ. እህተ ለልጁ አሻንጉሊት ገዛችለት።

ሐ. ሻንበል ለእናቱ ምሥጢር ነገራት።

መ. ማህደር ለአባቷ ታሪክ አነበበችላቸው።

ሠ. መህቡባ ለወንድሟ መጻሕፍት ሰጠችው።

ረ. ዓለሙ ለጓደኛው ኳሷን ወረወረለት።

ሰ. ፀሐይ ለሰው ልጅ ብርሃኗን ትለግሳለች።

#### ተግባር 2

ቀጥተኛና ኢቀጥተኛ ተሳቢ ያላቸው አምስት ዓረፍተነገሮች ጻፉ።

## ማንበብ

### "ጅብ ነች ትዕይንት 2"

### ቅድመንባብ

### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

**ተግባር**

"ጅብ ነች" በሚል ርዕስ ከቀረበው ተውኔት ውስጥ ትዕይንት "2"ን ከማንበባችሁ በፊት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. ከ"ጅብ ነች ትዕይንት 1" ተውኔት የምታስታውሱትን ተናገሩ።

ለ. ተውኔቱ የሚቀጥል ቢሆን እንዴት ባለ ሁኔታ የሚቋጭ ይመስላችኋል?

### የማንበብ ሂደት

### የሀሳቦችን ድርጊታዊ ቅደምተከተል ግንኙነት በማስተዋል ማንበብ

**ተግባር**

"ጅብ ነች ትዕይንት 2" በሚል ርዕስ የቀረበውን ተውኔት የሀሳቦችን ድርጊታዊ ቅደምተከተል ግንኙነት በማስተዋል ጥንድ ጥንድ በመሆን አንብቡ።

### "ጅብ ነች ትዕይንት 2"

የአካባቢው መልክዓምድር ወጣ ገባ ነው። አልፎ አልፎ ዛፎች ይታያሉ። በስተምዕራብ አቅጣጫ ወንዝ ይገኛል። በስተምስራቅ ደግሞ የመኖሪያቤቶች ይታያሉ።

**ስምየለሽ፡-** (እንስራ ተሸክማ ወደወንዝ ትወርዳለች።)

**አሰፋ፡-** ይቺ... ቀን ላይ ያየኋት ልጅ አይደለች እንዴ! ታዲያ ምኗ ነው ጅብ ያሰኛት? ከእኛ በምን ትለያለች? እንዴትስ ጅብ መሆን ትችላለች? ይህ ፈፅሞ ሊሆን የማይችል ነገር ነው። ደግሞ እንዴት ታምራለች! ዛሬ የምታደርገውን ሁሉ ተደብቄ መከታተል አለብኝ። (በዛፎቹ መካከል ይደበቃል።)

**ስምየለሽ፡-** (ወንዝ ደርሳ እንስራዋን አውርዳ ፀጉሯን ከጭንቅላቷ ታወልቃለች።)



**አሰፋ፡-** (ወደልጅቷ እየተመለከተ በድንጋጤ ለብቻው ያወራል።) እግዚኦ!... እማማ ድረሽልኝ! ፀጉሯን አወለቀችው! እግዚኦ! ጅብ ልትሆን ነው! እግዚኦ! የራስ ቅሏ እንዴት ለስልሷል! ደግሞ መታጠብ ጀመረች እኮ! እንደገና ለበሰችው! ግን እንዴት ሊሆን ይችላል? ታዲያ ፀጉሯስ እንዴት ወለቀ?! አዎ! ዛሬ እውነቱን ማወቅ አለብኝ።

**ስምየለሽ፡-** (በምሬት ብቻዋን ታወራለች።) አሁንስ ስቃዬ በዛ፤ በሰው መሃል ብቻዋን የምትኖር ሴት ሆኜ እስከመቼ? እንስራ እንኳ የሚያሽክመኝ ሰው ልጣ! ወይ አለመታደል!

**አሰፋ፡-** እንዴት ያለ የምሬት ንግግር ነው? ልጅቷ ምን ሆነች! ለምን ሄጄ አላናግራትም! ጅብ ከሆነችም በማታ እንጂ በቀን አትሆንም። አዎ! ላናግራት። አንድ እውነት ይኖራት ይሆናል። ዩኒቨርሲቲ ገብቼ መማሬ ለምንድን ነው? (ተረጋግቶ ወደስምየለሽ እየተጠጋ) እንደምን ዋልሽ እህቴ?

**ስምየለሽ፡-** አ...አቤት።

**አሰፋ፡-** ከዚህ ሀገር ነው የምትኖሪው?

**ስምየለሽ፡-** ኑሮ አልከው! ከዚህ ኑሮስ ሞትን እመርጥ ነበር።

**አሰፋ፡-** ለምን?

**ስምየለሽ፡-** "ጅብ ነች" እያሉኝ (እንባዋ በአይኖቿ ይሞላል።)

**አሰፋ፡-** እንዴት?

**ስምየለሽ፡-** ታሪኬ ብዙ ነው።

**አሰፋ፡-** ማልቀሱን ተዪውና ንገሪኝ።

**ስምየለሽ፡-** (እንባዋን እየጠራረገች) ማንም አላወቀልኝም።

**አሰፋ፡-** ምኑን?

**ስምየለሽ፡-** ታሪኬን።

**አሰፋ፡-** ታሪክሽ ምንድን ነው?

**ስምየለሽ፡-** እናቴ እኔን እንደወለደችኝ አባቴ በመሞቱ ችግርና ረሀብ ክፉኛ አንገላታት። የሚላስ የሚቀመስ ስላልነበር እየዞረች ትለምን ነበር። አንድ ቀን በተወለድኩ በዓመቴ ብቻዬን ከቤት ውስጥ ዘግታብኝ እሷ ቃርሚያ ሄዳ ነበር። ለካስ ከተኛሁበት መደብ ሥር ረመጥ ኖሮ ተንከባልዬ በእናቴ ወድቄበት ራሴ በሞላ ተጠበሰ። እንዳጋጣሚ አንድ መንገደኛ ጩኸቴን ሰምቶ ባይደርስልኝና ባያተርፈኝ ኖሮ ነድጄ እቀር ነበር። ከዚያም እናቴ ይዛኝ አዲስ አበባ ገባች።

**አሰፋ፡-** (በታሪኳ ተመስጦ) እሺ! ከዚያስ?

**ስምየለሽ፡-** ከዚያማ ብዙ ሀኪሞች ዘንድ እየለመነች ደርሳ ራሴን አሳየቻቸው። ሁሉም ይሄ ፊፅሞ ተቃጥሏልና ሁለተኛ ፀጉር አያበቅልም አሏት። ትወደኝ ስለነበር ከአንደኛው ሀኪም እግር ሥር ወድቃ ምርር ብላ አለቀሰችበት። እሱም ትልቅ ስትሆን አምጫት ብሎ ቃል ገባላት። 15 ዓመት ሲሞላኝ በገባው ቃል መሠረት ይህን ፀጉር ሰጠኝ። እኔም ስታጠብም ሆነ ማታማታ ስተኛ እንዳይሰባበርብኝና እንዳያልቅብኝ አውልቄ አኖረዋለሁ።

**አሰፋ፡-** (አይኖቹ እንባ አዝለው) የሚያሳዝን ታሪክ አለሽ! ታዲያ "ጅብ ነች" የሚሉሽ ለምንድን ነው?

**ስምየለሽ፡-** አንድ ወቅት ወዳጄ የነበረ ሰው ፀጉሬን ማታ አውልቄ ካስቀመጥኩበት ያየዋል፤ እኔም ውኃ ልቀዳ ማልጄ ወደወንዝ ወርጄ ስለነበር፣ ቢፈልገኝ ያጣኛል። ይህን ጊዜ ፀጉሬን እቤት አስቀምጬ ጅብ የሆንኩ መሰለው። ላስረዳው ብሞክርም፣ "ጉድሽን ነው የማፈላው" ብሎ ፀጉሬን ገበያ ለገበያ ሲያዞረው ሰነበተ። "ጅብ ነች" እያለም ስሜን አጠፋው። በኋላ በሽማግሌዎች ተለምኖ መለሰልኝ። ይኸው ከዚያን ጊዜ ጀምሮ "ጅብ ነች" ተብዬ ብቻዬን

እኖራለሁ (ተንሰቅስቃ ታለቅሳለች።)

**አሰፋ፡-** (እንባውን ጠረገና) በቃ አታልቅሺ! ጅብ አይደለሽም፤ የሰው ልጅ ጅብ ሊሆን አይችልም። ፈፅሞ ሊሆን አይችልም። ከዚህ በኋላ "ጅብ ነች" የሚልሽ የለም። ለቤተሰቦቼም ሆነ ለማህበረሰቡ እውነቱን ላስረዳልሽ ቃል እገባልሻለሁ። አሁን ተረጋጊና እንስራሽን ተሸክመሽ ወደቤትሽ ሂጅ። ነገ እንገናኛለን። (እንስራዋን ያሸክማታል።)

**ስምየለሽ፡-** (እንስራዋን እየተሸከመች) እሺ!

(ታደሰ ሊበን። 1949። *መስከረም።* ከገጽ19-28 ለውጥ ተደርጎበት የተወሰደ)

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. ስምየለሽ በምሬት፣ "በሰው መሀል ብቻዋን የምትኖር ሴት ሆኜ እስከመቼ" ስትል ምን ማለቷ ነው?

ለ. አሰፋ የስምየለሽን "ጅብ" አለመሆን እንዴት ሊያምን ቻለ?

ሐ. ስምየለሽ ታሪኳን ለአሰፋ ባትነግረው ኖሮ የታሪኩ ፍፃሜ ምን የሚሆን ይመስላችኋል?

መ. ስምየለሽ ወደወንዝ ወረዳ ስትታጠብ አሰፋ የደነገጠው ለምንድን ነው?

ሠ. አሰፋ ስምየለሽን ቀርቦ ለማናገር የደፈረው እንዴት ነው?

ረ. የተውኔቱ ዋና መልዕክት ምንድን ነው።?

## 5ኛ ቀን

## ቃላት

## ለቃላትና ለሐረጋት ዐውዳዊ ፍቺ መስጠት

### ተግባር 1

በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ውስጥ ለተሠመረባቸው ሐረጋት ተመሳሳያቸውን ጻፉ።

ሀ. የሠራው ደባ <u>የተዳፈነ እሳት</u> ሆኖበት እረፍት ነሳው።

ለ. ዓይኖቿ <u>እንባ አዝለው</u> በማየቴ ልቤን ጨነቀው።

ሐ. አቶ ጋርጠው የሀሰት መታወቂያ የያዘችውን ሴት <u>ጉድሽን ነው የማፈላው</u>

በማለት ዛተባት።

መ. ሰውዬው ስለቀና <u>ስሜን አጠፋው</u>።

ሠ. አለቃዋ ባላጠፋችው ጥፋት ስለወቀሳት <u>ምርር ብላ</u> አለቀሰች።

## ተግባር 2

በሚከተሉት ቃላት ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የተለያየ ፍቺ ያላቸው ዓረፍተነገሮችን መሥርቱ።

ሀ. ሰምቶ

ለ. መደብ

ሐ. ተምሬ

መ. ቃል

ሠ. ማልጄ

ረ. ልጣ

## መጻፍ

## ድርሰት መጻፍ

## ጅምር ተውኔትን መጨረስ

## ተግባር

የሚከተለውን ተውኔት ከዚህ በታች በተሰጣችሁ መግቢያና ማጠቃለያ መሠረት አሟልታችሁ ጻፉ።

አሰፋ፡- በይ እንስራሽን አስቀምጠሽ እኛ ቤት እንድትመጪ! ለእናቴና ለእህቴ እውነቱን እንነግራቸዋለን። (አሰፋ ወደቤቱ ይሔዳል።)

ስምየለሽ፡- እሺ. እመጣለሁ።

ወ/ሮ አሰገደች፡- ይኸ ልጅ ብነግረው አልሰማ ብሎ እንደወጣ ቀረ! ቆይ ያገኛታል! ለነገሩማ ዕዳው የሚተርፈኝ ለኔ ነው።

አሰፋ፡- (ወደቤት ይገባል።)

**ወ/ሮ አሰገደች፡-** እንዳው ልጄ የት ሄደህ ነው እንዲህ የቆየኸው?

**አሰፋ፡-** እዚሁ ነበርኩ እኮ እማማ! የትም አልሄድኩ።

**ወ/ሮ አሰገደች፡-** ያቺ ልጅ አላገኘችህም አደል ልጄ?!

**አሰፋ፡-** የቷ ልጅ?!

**ወ/ሮ አሰገደች፡-** (ቆጣ ብለው) ጅቧ ናታ! ሌላ ማን ይሆናል?

**አሰፋ፡-** አይ እማማ! ቅድም ጅብ ናት፤ ቡዳ ናት ያልሽው እኮ ዝም ብለሽ ነው።

**ወ/ሮ አሰገደች፡-** (ራሳቸውን በሁለት እጃቸው ይዘው) እንደፈራሁት ያቺ ጉድ አገኘችህ ልጄ? አቤት! አቤት! አቤት!

**አሰፋ፡-** አዎ! ተገናኘን። ግን እናንተ እንደምትሉት ልጂቱ ጅብ አይደለችም።

**ወ/ሮ አሰገደች፡-** -----------------

**አሰፋ፡**------------------------------

**ወ/ሮ አሰገደች፡**------------------

**አሰፋ፡**-----------------------------

**ስምየለሽ፡**----------------------------

**ወ/ሮ አሰገደች፡**------------------

**አሰፋ፡**------------------------------

**ስምየለሽ፡**----------------------------

**ወ/ሮ አሰገደች፡-** ወይ ግሩም! የራስሽ ፀጉር'ኮ ነው የሚመስል! ሁላችንም ስናማሽ ሰንብተናል እኮ! ይህ ሁሉ ችግር እንደደረሰብሽ መች አወቅን ልጄ! አይዞሽ! ካሁን በኋላ ለእነአያ ጓንጉልና ለጎረቤቶቻችን ሁሉ አስረዳቸዋለሁ። አሁን እንጀራ ላቅርብና በልተሽ ትሂጃለሽ።

**አሰፋ፡-** የእጅ ውኃ ላቅርብ እማማ!

## የአጻጻፍ ሥርዓት

## በተውኔት ውስጥ ቅንፍ መጠቀም

### ተግባር

በሚከተለው የተውኔት ቅንጫቢ ውስጥ የገፀባህርያቱን ድርጊትና ውስጣዊ ስሜት ከንግግራቸው ለይታችሁ በቅንፍ አመልክቱ።

ምሳሌ፡- ኢሳይያስ፡- (ከኪሱ ፎቶ ያወጣል።) እስኪ ይሄን ፎቶ ልብ በለው (ይሰጠዋል።)

**ገዝሙ፡-** ካወቅህ ደህና፤ ሳታውቅ ነው ብዬ ተስፋ አድርጌ ነበር። ለጥቂት ሴኮንዶች ዝምታ ይሆናል።

**ደጀኔ፡-** ሲፈራ ሲቸር በመለማመጥ ወደተጫኔ ጠጋ ይልና ሊሊቱ ሊነጋ ነው፤ ወደቤትህ ብትሄድ ይሻላል።

**ተጫኔ፡-** እውነት ብለሃል እንሂድ። ወደገዝሙ ያመለክታል። ይኸን ተወው፤ የሚያሳዝነኝ ከሱ ጋር ስነታረክ ያባከንኩት ወርቅ ጊዜዬ ነው። እንደመሄድ ይልና በሩ ጋ ሲደርስ ወደገዝሙ ይመለሳል፤ አነጋገሩ በረድ ብሏል። ስማ ገዝሙ! የማደርስህ ቦታ እንዳለ አንዱ ጋ ልጣልህ፣ በማርሴዲዝ።

**ገዝሙ፡-** በእግር መሄድ መርጫለሁ። ይነሳና ወደልብስ መስቀያው ይሄዳል።

(ፈንታሁን እንግዳ። 1992። *የተውኔት ድርሰት አጻጻፍ ዘዴ*። ገጽ 69 የተወሰደ)

## 6ኛ ቀን

## አቀላጥፎ ማንበብ

### "ጅብ ነች" ትዕይንት 2

### ቅድመንባብ

**ተግባር**

የሚከተሉትን የቅድመንባብ ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ከ"ጅብ ነች" ትዕይንት 2 ተውኔት የምታስታውሱትን ተናገሩ።

### ማንበብ

### የገፀባህርያትን ንግግር አስመስሎ ማንበብ

**ተግባር**

በ"ጅብ ነች" ትዕይንት 2 የቀረበውን ተውኔት የገፀባህርያቱን ንግግር በማስመሰል ድምፅ በማሰማት በትክክል አንብቡ።

## መናገር

### ተውኔት መተወን

**ተግባር**

"ጅብ ነች" ትዕይንት 2 ተውኔትን፣ ገፀባህርያቱን ወክላችሁ በክፍል ውስጥ ተውኑ።

## ሰዋስው

### ቀጥተኛና ኢቀጥተኛ ተሳቢን መለየት

### ተግባር

ኢቀጥተኛና ቀጥተኛ ተሳቢዎችን በመጠቀም ክፍት ቦታዎችን በማሟላት ዓረፍተነገሮችን ጻፉ።

ምሳሌ፡- ዓለሙ ለአባቱ ኮት ሰጣቸው። "ለአባቱ" ኢቀጥተኛ ተሳቢ ሲሆን፣ "ኮት" ደግሞ ቀጥተኛ ተሳቢ ነው።

ሀ. አሚናት _____ ______ ነገረቻቸው።

ለ. አልማዝ _____ ______ ላከች።

ሐ. ካሳ ________ ______ ሸለማት።

መ. ሶስና _____ ______ አቀበለቻቸው።

ሠ. ሽምስያ _____ ______ አካፈለቻት።

ረ. ዓለም _____ ______ አሳየቻት።

## የቃላት ጥናት

### ውስብስብ ቃላትንና ሐረጋትን ማንበብ

**ተግባር**

የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት በፍጥነትና በትክክል አንብቡ።

ሀ. ስሪንጋዎችን

ለ. አንከሊስ

ሐ. የሚመረምርበት

መ. ያስገበግባችኋል

ሠ. ጀኔራል ወብሬሽን

ረ. ማስገንዘቢያዎች

ሰ. ካፖርቱን

ሸ. ዳማከሴ

ቀ. ይመዘምዘኝ

በ. ይገላግለኛል

## ማንበብ

**የመንደሩ መርፌ ወጊ**

### ቅድመንባብ

### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

**ተግባር**

"የመንደሩ መርፌ ወጊ" በሚል ርዕስ የቀረበውን ተውኔት ከማንበባችሁ በፊት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. ከተውኔቱ ርዕስ ምን ትረዳላችሁ?

ለ. ሥዕሉን ተመልክታችሁ የተረዳችሁትን ተናገሩ።

### የማንበብ ሂደት

### የገፀባህርያትን ቃለምልልስ ከገለጻው እየለዩ ማንበብ

**ተግባር**

"የመንደሩ መርፌ ወጊ" በሚል ርዕስ የቀረበውን ተውኔት የገፀባህርያትን ቃለምልልስ ከገለጻው እየለያችሁ አንብቡ።

# የመንደሩ መርፌ ወጊ



ከበረንዳው በአንደኛው ጥግ ከሣጠራ የተሠራ ጠረጴዛ ተቀምጧል። በጠረጴዛው ላይ ልዩ ልዩ የመድኀኒት ብልቃጦችና ጠርሙሶች ይታያሉ። ከሣጠራው ጠረጴዛ አለፍ ብሎ አንድ የእንጨት ወንበር አለ። የመንደሩ መርፌ ወጊ ሕመምተኞችን አጋድሞ የሚመረምርበት አግዳሚ ወንበርም በመጋረጃ ከለል ተደርጎ ይታያል።

ለመንደሩ መርፌ ወጊ እንደዘበኛም እንደነርስም የሚያገለግለው ገረመው በአሮጌ ቱታ ላይ ነጭ ካፖርት ደረቦ ከጠረጴዛው ላይ ያሉትን የመድኀኒት ብልቃጦችና የመርፌ መውጊያ ስሪንጋዎችን እየወለወለ በቦታ በቦታቸው ያስቀምጣል። ከቤቱ ፊትለፊት የተሰበሰቡት ሕመምተኞች ደግሞ ሲንጫጩ ይሰማሉ።

**ገረመው፡-** (በሽተኞችን ዝም ለማሰኘት በእጁ እያጨበጨበ) በሽተኞች እኔ በምነግራችሁ መሠረት “በሦስት ተርታ እንድትሰለፉ ትጠየቃላችሁ”። (በእጁ እያሳየ) እሺ! የመጀመሪያው ሰልፍ እዚያ ጋ ነው። ቆይ! ቆይ! እነማን እንደምትሰለፉ ሳልናገር ምን ያስገበግባችኋል? በመጀመሪያ <u>ጆሯችሁን ሰጥታችሁ</u> አዳምጡኝ። እሺ! ቁርጥማት፣ ችፌ፣ ስብራት፣ ቁስል፣ እከክ፣ ውጋት የታመማችሁ በሽተኞች እዚያ ጋ ተሰለፉ። ቀስ! ቀስ! ይደርሳችኋል። አይዟችሁ፤ መርፌ ሳይወጋ የሚሄድ ሰው የለም።

ሳናቃምስ አንሰዳችሁም። እሺ! በሁለተኛ ረድፍ መጋኛ፣ ምች፣ ወገብ ቆልፍ፣ አንከሊስ፣ አንገት አጥንን፣ እርጥብ ሳል፣ ደረቅ ሳል የያዘው ይሰለፍ። አልደግምም አደብ ገዝታችሁ አዳምጡ! (ጣቱን ቀስሮ) እናንተ የመጨረሻ አድርቆች ናችሁ። በመጨረሻም ዓይን ማዝ፤ የሥር መሸማቀቅ ያለባችሁና ጀኔራል ወብሬሽን የምትፈልጉ ተሰለፉ። አዎ፣ ፈታ ፈታ ብላችሁ ቁሙ!

(ከኪሱ የተጣጠፈ ወረቀት አውጥቶ እየዘረጋ) በሽተኞች! የሚከተሉትን ማስገንዘቢያዎች አነብላችኋለሁ፤ ልብ ብላችሁ አዳምጡ።

አንደኛ፡- በተከታታይ ሳያቋርጥ አሥር መርፌ ለተወጋ በሽተኛ አንድ መርፌ በነጣ እንመርቃለን።

ሁለተኛ፡- ለምርመራ ልብስ አናወልቅም የምትሉ ሴቶች በእጅጉ ተጠንቀቁ፤

ሦስተኛ፡- ለምርመራ ገንዘብ አንጠይቅም፤ በነጣ ነው። ለመርፌና ለከኒና ብቻ እናስከፍላለን።

አራተኛ፡- ሃኪሙ “ይበቃል” ብለው ትዕዛዝ እስካልሰጡ ድረስ መርፌ መወጋት ማቆም ክልክል ነው። የአንድ መርፌ ዋጋ አምስት ብርም ከእጃችሁ እንዳይለይ! አሁን ሐኪሙ መጥተዋል፤ የተቀመጣችሁ በሙሉ ተነሱ።

(ቢሰውር አልፎ አልፎ ሽበት ጣል ጣል ያደረገበት ሰውዬ ነበር። ነጭ ካፖርቱን አድርጎ፣ ጠቆር ያለ መነጽሩን ግንባሩ ላይ ሰክቶ፣ ሲጋራውን እያጨሰ የመኖሪያቤቱን በር ከፍቶ ወደበረንዳ ብቅ ይላል። በሽተኞች በጭብጨባና በእልልታ ይቀበሉታል።)

ገረመው፡- በተራችሁ መሠረት ከሦስቱም ሰልፍ አንዳንድ ተራበተራ አስገባለሁ፤ ተዘጋጁ። ከመጀመሪያው ሰልፍ ወንድም! ባለኮፍያ! አዎ አንተን ነው፤ ግባ። (ኮሰስ ያለ በሽተኛ ገብቶ መርፌ ወጊውን ዓይን ዓይን እያየ ይቆማል።)

ቢሰውር፡- (ከብልቃጡ መድኀኒት በመርፌው እየመጠጠ) ምን ዓይን ዓይኔን ታያለህ? ቀበቶህን ፈትተህ ሱሪህን አታወልቅም?

በሽተኛ፡- (ፊቱን ወደመርፌ ወጊው እንዳዞረ ሱሪውን ፈቶ ይቆማል።)

ቢሰውር፡- ወንድም የት ላይ ይመስልሃል መርፌ የምትወጋው? ሆድህ ላይ ይመስልሃል?

በሽተኛ፡- አይ! መቀመጫዬ ላይ ነው።

ቢሰውር፡- ታዲያ ዙርልኛ! ምን ዓይን ዓይኔን እያየህ ትገተራለህ... (በጥጥ አሻሽቶ መርፌውን እየወጋ) ኧረ ለመሆኑ ምንህን አሞህ ነው የመጣኸው?

በሽተኛ፡- የሰራ አካላቴን ያላምጠኛል፤ እንደገና በላብ ይጠምቀኛል።

ቢሰውር፡- ነው? እሱ ከሆነስ ፍቱን የሆነ መርፌ ነው የወጋሁህ። አይዞህ አሁን ትድናለህ። ስማ!

በሽተኛ፡- አቤት!

ቢሰውር፡- ዳማከሴ ፌልግና እሸት እያደረክ ከውኃ ጋር እየቀላቀልክ ጠጣበት፤ ግን እስክትድን ድረስ መርፌ አታቋርጥ።

በሽተኛ፡- እሺ!

ቢሰውር፡- ገረመው ቀጥል!

ባልቴቷ፡- (ሳል እያጣደፋቸው) በሰባ ሁለት ዓመቴ ደካማ ጉልበቴ እየተንቀጠቀጠ ከልጆቼ እኩል ቆሜ ወረፋ ልጠብቅ? ትንሽ አላሳዝናችሁም?

ቢሰውር፡- ተዋቸው! እስኪ ይግቡ ገረመው! እሺ ልብስዎን ገለብ አድርገው ይያዙት (ባልቴቷን ይወጋና በጥጥ አሻሽቶ) በቃዎት ልብሱን ይልቀቁት።

ባልቴቷ፡- እባክዎን በዚህኛው ታፋዬም አንድ ይድገሙኝ። በሽታዬ ሁለት ዓይነት ነው። ያስለኛል፤ ሆዴን ይቆርጠኛል። አሁን የወጉኝ ሳሉን ቢቀንስልኝ፣ ደግመው የሚወጉኝ ከሆድ ቁርጠቴ ይገላግለኛል።

ቢሰውር፡- የሁለት መርፌ ዋጋ አሥር ብር ይሆንብዎታላ!

ባልቴቷ፡- ይሁን፤ ግዴለዎትም ይድገሙኝ! ከጤናዬ አይብስ፤ ጨምሬ እከፍላለሁ!

ቢሰውር፡- መልሰው ገለብ ያድርጉት ልብስዎን። (ቀሚሳቸውን እንደገለበጡ በሌላው ታፋቸው ይወጋቸዋል።)

ባልቴቷ፡- እግዜር ይስጥዎ፤ ፈጣሪ አለሁ ይበልዎ፤ ታሞ የመጣ አይጣዎ። መቼም ያጅሬ መድኀኒት ፍቱን ነው። ገና ካሁኑ ሥራውን ጀመረ። ከዳሌዬ ጀምሮ እስከራስ ፀጉሬ ወደታችም እስከእግር ጥፍሬ ይመዘምዘኝ ገባ። እሰይ! ነፍሴ መለስ አለች። እንካ አሥር ብሩን (ለገረመው)። በረካ ሁኑልኝ።

ቢሰውር፡- አሜን አሜን።...

ገረመው፡- (ገረመው ወጣ ብሎ መለፈፉን ይቀጥላል። ወዲያው ድምፁን ያጠፋና ሲበር ይገባል።) ያንት ያለህ! እግዚኦ! እንዴት ያስፈራል! ከቻሉ እጅዎን ያውጡ ጌታዬ! ያምልጡ! እየመጡ ነው።

(የደንብ ልብስ የለበሱ ሦስት ፖሊሶች ሲመጡ ይታያሉ።)

( ፈንታሁን እንግዳ። 1990። *ዝክረተውኔት*። ከገጽ 88-101 መጠነኛ ለውጥ ተደርጎበት የተወሰደ።)

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር 1

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በተውኔቱ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. ገረመው በሽተኞችን ያሰለፋቸው ምንን መሠረት በማድረግ ነው? ተገቢ ይመስላችኋል?

ለ. "በተከታታይ ሳያቋርጥ አሥር መርፌ ለተወጋ በሽተኛ አንድ መርፌ በነፃ ይመረቅለታል" የሚለውን አባባል ገምግማችሁ ጻፉ።

ሐ. ቢሰውር በሽተኛውን መርፌ ከወጋው በኋላ ስለበሽታው ዓይነት መጠየቁ ትክክል ነው? ለምን?

መ. የመርፌ መውጊያ ስሪንጋዎች ተወልውለው መቀመጣቸው በታካሚዎች ላይ የሚያስከትለው ችግር ምንድን ነው?

ሠ. ባልቴቷ ሁለት መርፌ ከተወጉ በኋላ ከበሽታቸው የዳኑ ይመስላችኋል? ለምን?

ረ. የመንደሩ መርፌ ወጊ የመጨረሻ ዕጣ ፈንታ ምን ሊሆን ይችላል?

ሰ. የተውኔቱን ዋና መልዕክት በአምስት ዓረፍተነገሮች አጠቃላችሁ ጻፉ።

## 8ኛ ቀን

## ቃላት

### ጥቅል ቃላትን መዘርዘር፤ ዐውዳዊ ፍቺ መስጠት

### ተግባር 1

የሚከተለውን የቢጋር ሠንጠረዥ በተገቢ ቃላት አሟሉ።




## ተግባር 2

ለሚከተሉት ቃላትና ሐረጋት በምንባቡ መሠረት ፍቻቸውን በቃላችሁ ተናገሩ።

ሀ. ኮሰስ ያለ

ለ. የሰራ አካላቴ

ሐ. ጳማ ከሴ

መ. ወረፋ

ሠ. አጅሬ

ረ. በረካ

ሰ. ፍቱን

ሸ. ነጣ

ቀ. ሳናቃምስ

በ. ፈታ

ተ. ጆሯችሁን ሰጥታችሁ

ቸ. ጉልበቴ እየተንቀጠቀጠ

## መጻፍ

### ድርሰት መጻፍ

### ጅምር ተውኔትን መጨረስ

## ተግባር

የሚከተሉትን ሀሳቦች በመጠቀም ተውኔቱን ጨርሳችሁ ጻፉ።

- ፖሊሶቹ ወደቢሰውር ቤት ሲገቡ ቢሰውር የሚያከናውነው ድርጊት
- ፖሊሶቹ የሚወስዱት እርምጃ

- በሽተኞች የሚያከናውኗቸው ድርጊቶች
- በመጨረሻ ቢሰውር የተወሰደበት እርምጃ

**ቢሰውር፡-** (በድንጋጤ) እነማን ናቸው?

**ገረመው፡-** (ጋዋኑን እያወለቀ) ፖሊስ--- ፖሊሶች--- ፖሊሶች ናቸው!

**ቢሰውር፡-** (ወደቤት እየገባ) የት ደርሰዋል!? የት ደርሰዋል!? ስንት ናቸው!?

**ገረመው፡-** ከውጪ በር ላይ ደርሰዋል ጌታዬ! እስካሁንማ ግቢ ውስጥ ዘልቀው ይሆናል? (መርፌውንና የመድኀኒት ብልቃጦችን አሮጌ ካርቶን ውስጥ ይወረውራል።)

(ፖሊሶቹ በሽተኞችን አልፈው ወደቢሰውር ክፍል ደረሱና በሩን አንኳኩ።)

**ፖሊስ፡**--------------------------------

**ቢሰውር፡** -------------------------------

**ፖሊስ፡**------------------------------------

**ቢሰውር፡** -------------------------------

## የአጻጻፍ ሥርዓት

### ገላጭ ጽሑፍን ወደተውኔት መለወጥ

### ተግባር

የሚከተለውን ጽሑፍ ተጠቅማችሁ በጅምሩ መሠረት ወደተውኔት ለውጣችሁ ጻፉ።

አንድ ሰው ምግብ ለመመገብ ወደአንድ ምግብቤት ገባ። የምግብቤቱ አስተናጋጅ መጣና "ምንልታዘዝዎት?" አለ። ሰውዬውም "ሰላጣ በዘይት አምጣልኝ" አለው። አስተናጋጁ "እሺ ጌታዬ" ብሎ ከታዘዘ በኋላ ከወጥቤት ሰላጣውን ይዞ መጣ። ሰውዬውም አስተናጋጁን ትኩር ብሎ እያየ "ዘይቱስ" አለና ጠየቀው። አስተናጋጁም በመደናገጥ ይቅርታ ከጠየቀ በኋላ፣ ዘይቱን ለማምጣት ወደወጥቤት ሔደ። አስተናጋጁ ዘይቱን ይዞ ሲመጣ ሰውዬው ሰላጣውን በልቶ ጨርሶታል። በዚህ ጊዜ አስተናጋጁ "ጌታዬ ይቅርታ! ያለዘይት ሰላጣውን አስበላሁዎት አይደለም?" አለ። ሰውዬውም ዘይቱን ከአስተናጋጁ ተቀብሎ ጭልጥ አድርጎ ጠጣው። ወዲያውም መሬት ላይ መንከባለል ጀመረ። አስተናጋጁም በሁኔታው ተገርሞ "ለምን ይንከባለላሉ ጌታዬ?" አለው። ሰውዬውም ሆዱን እያሻሸ "ሰላጣው ከዘይቱ ጋር እንዲደባለቅ ነው" ብሎ መለሰለት።

(*ፈንታሁን እንግዳ።* 1990። *የተውኔት ድርሰት አጻጻፍ ዘዴ።* ከገጽ79 የተወሰደ)

(አንድ ሰው በአንድ ምግብቤት ውስጥ ምግብ ለመመገብ ተቀምጦ ይታያል።)

አስተናጋጁ፡- ምን ልታዘዝዎት?

ሰውዬው፡- ሰላጣ በዘይት አምጣልኝ።

አስተናጋጁ፡- እሺ ጌታዬ (ወደወጥቤት ይሂድና ሰላጣውን ያቀርባል።)

ሰውዬው፡- ---------

- 
- 
- 

9ኛ ቀን

## አቀላጥፎ ማንበብ

### የመንደሩ መርፌ ወጊ

**ቅድመንባብ**

**የገፀባህርያትን ንግግር አስታውሶ መናገር**

**ተግባር**

“የመንደሩ መርፌ ወጊ” ከሚለው ተውኔት ከገረመውና ከቢሰውር ንግግር የምታስታውሱትን አስመስላችሁ በቃላችሁ አቅርቡ።

**የማንበብ ሂደት**

**የገፀባህርያትን ቃለምልልስ ከገለጻው እየለዩ ማንበብ**

**ተግባር**

“የመንደሩ መርፌ ወጊ” በሚል ርዕስ የቀረበውን ተውኔት አምስት አምስት እየሆናችሁ ቃለምልልሱን ከገለጻው በመለየት ድምጽ በማሰማት አንብቡ።

## መናገር

### ተውኔትን መተወን

### ተግባር

"የመንደሩ መርፌ ወጊ" በሚል ርዕስ የቀረበውን ተውኔት በክፍል ውስጥ ተውኑ።

## ሰዋስው

### ባለቤትንና ተሳቢን መለየት

### ተግባር 1

ከሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ባለቤትና ተሳቢ የሆኑትን ቃላት/ሐረጋት ለይታችሁ ጻፉ።

ሀ. አልማዝ ወንድሟ የገዛላትን መጽሐፍ አነበበች።

ለ. ጎበዙ ልጅ ለመምህሩ ጥያቄ አቀረበ።

ሐ. እድሜ ጠገቧ አያቴ ለእናቴ አልቦ ሰጠቻት።

መ. አዲሷ ርዕሰመምህር ለተማሪዎቻቸው ምክር መከሩ።

ሠ. የውስጥ ደዌ ሀኪሙ ለበሽተኞቹ የተለያዩ መድኀኒቶችን አዘዙ።

ረ. የዕድሩ ሰብሳቢ ለሚመለከታቸው ሰዎች የሥራ ሪፖርት ላኩ።

### ተግባር 2

በሚከተሉት ቃላት ባለቤት፣ ቀጥተኛና ኢቀጥተኛ ተሳቢ ያሏቸው ዓረፍተነገሮች መሥርቱ።

ምሳሌ፡-

| መምህሯ | ለተማሪዎች | መጽሐፍ | አደለች |
|---|---|---|---|
| ↓ | ↓ | ↓ | ↓ |
| ባለቤት | ኢቀጥተኛ ተሳቢ | ቀጥተኛ ተሳቢ | ግስ |

ሀ. ነገረቻት

ለ. ሸለሙት

ሐ. ላከልሽ

መ. ሰጠ

ሠ. አጋራ

ረ. አቀበለ

# ሙዳየ ቃላት

**ሀሳብ ማጋራት** (Think-aloud)፡- በአርዓያነት እያነበቡ እያሉ በተወሰነ የጊዜ ልዩነት ቆም እያሉ ስለአንድ ነገር/ጉዳይ እንዴት እያሰብን እንደሆነ ለሌላ ሰው ሀሳብን ማካፈል፤

**መለየት/ማንበብ** (Decoding)፡- የተጻፉ ቃላትን (ጽሑፍን) ወደንግግር ቋንቋ ለመቀየር የፊደል ድምፅ ግንኙነትንና የቃላት ዕውቀትን መጠቀም፤

**መላልሶ ማንበብ** (Repeated reading)፡- በትክክለኛና በፍጥነት የማንበብ ችሎታን ለማጎልበት በግብረመልስ እየታገዙ ደጋግሞ የማንበብ ሂደት

**መልሶ ማንበብ** (Reread)፡- በማንበብ ሂደት ግልጽ ያልሆነ ጉዳይ ሲያጋጥም ሀሳቡን መረዳት እስኪቻል ድረስ ወደኋላ እየተመለሱ ማንበብ፤

**መልዕክት ሰጪ ንባብ** (Prosody)፡- አንድ ጽሁፍ በትክክለኛው ወይም በተገቢው የድምፅ ቅላፄ ማንበብ፤

**መምህር መር ንባብ** (Guided Reading)፡- ለደረጃው የቀረበውን ጽሑፍ በትክክል ማንበብ እንዲቻል መምህራን አንብበው በማሳየት ንባቡን የሚያስቀጥሉበት ሂደት፤

**መረዳት** (Comprehension)፡- የንግግርን ወይም የጽሑፍን ቋንቋ የመረዳትና ትርጉም የማግኘት ሂደት፤

**መነጠል** (Segmenting)፡- አንድን ሙሉ ቃል ወይም ሐረግ በተናጠላዊ ፊደሎች ወይም በአነስተኛ የቃል ክፍልፋዮች የመነጣጠል ሂደት

**መገመት** (prediction)፡- ከማንበብ/ከማዳመጥ በፊት ወይም በማንበብ/በማዳመጥ ሂደት ቀጥሎ ምን ሊመጣ ወይም ምን ሊሆን እንደሚችል መገመት፤ ስለገፀባህርያቱና ስለሴራው ድምዳሜ መስጠት፤

**የማዳመጥ ቃላት** (Listening vocabulary)፡- ሰዎች በንግግር ጊዜ አዳምጠው የሚረዷቸው ቃላት፤

**ማጠቃለል/ማሳጠር** (Summarizing)፡- የምንባብን አቢይ ሀሳብ ጨምቆ የማውጣት ሂደት፤

**ማጣመር** (blending)፡- በአነስተኛ ክፍልፋዮች ወይም ፊደሎች ተነጣጥሎ የቀረበን

ቃል በአንድ ላይ አጣምሮ የመናገር፣ የማንበብ ወይም የመጻፍ ሂደት፣

**ራስን የመከታተያ ስልት** (Self-checking strategy)፡- ተማሪዎች በሚያነቡበት ጊዜ መረዳታቸውን የሚያረጋግጡበት ብልሃት፣

**ቃላት በደቂቃ (ቃበደ)** (WPM)፡- በአንድ ደቂቃ በፍጥነት የተነበቡ ቃላት ብዛት፣ በአንድ ደቂቃ በትክክል የተነበቡ ቃላት ብዛት (WCPM ቃላት ትክክል በደቂቃ (ቃትበደ))፣ (የተማሪዎችን የማንበብ ብቃት ደረጃ ለመወሰን ያገለግላል::)

**ቃላት ትንተና** (Word analysis)፡- አንባቢዎች የተጻፉ ቃላትን በአነስተኛ ክፍልፋዮች ወይም ቅጥያዎች በመተንተን ለማንበብ የሚጠቀሙበት ስልት፣

**ቅጥያ** (Affix)፡- በቃል መጀመሪያ ወይም መጨረሻ የሚቀጠሉ ትርጉም አዘል ቅጥያዎች፣ (በቃል መጀመሪያ ሲቀጠሉ ቅድመአምድ ቅጥያ (Prefix)፣ በቃል መጨረሻ ሲቀጠሉ ድህረአምድ ቅጥያ (Suffix) ይባላሉ::)

**ቅጽበታዊነት** (Automaticity)፡- ፊደላትን፣ ድምጾችንና ቃላትን ያለችግር፣ ሳያመነቱ፣ ሳያወላውሉ፣ በቅጽበትና በትክክል የመለየትና የማንበብ ችሎታ፣

**ቀጥተኛ ጥያቄ** (Explicit question)፡- መልሱ በቀጥታ ከምንባብ ወይም ከንግግር የሚገኝ ጥያቄ ዓይነት፣

**ቃላትን መረዳት/ ማወቅ** (Word Recognition)፡- አንባቢዎች የተጻፉ ቃላትን ለመለየት የሚጠቀሙበት ስልት

**በማንበብ ሂደት መቆምና ማሰብ** (Stop and think)፡- በማንበብ ሂደት ምን እየተነበበ እንደሆነ ቆም ብሎ ማሰብ፣ ስለተነበበው ምንባብ ምንም ነገር ማስታወስ ካልተቻለ ወደፊት ከማንበብ ይልቅ ቆም ብሎ የተነበበውን ሀሳብ በአዕምሮ ለመረዳት መሞከር፣

**በቢጤ መማማር** (Peer tutoring)፡- ተማሪዎች ትምህርታዊ ክሂሎችን ርስበርስ የሚማማሩበት ሂደት

**የቢጋር ሠንጠረዥ** (Graphic organizer)፡- የሀሳብን ግንኙነት በሥዕል ወይም በግራፍ ወይም በሠንጠረዥ የማደራጃ ስልት፣

**በትብብር መማር** (Cooperative learning)፡- አንድን የትምህርት ይዘት በጋራ እየተረዳዱ የመማር ሂደት፣

**ቤት መምታት** (Rhyme)፡- በተመሣሣይ ፊደሎች/ድምጾች የሚጨርሱ ቃላት /

የግጥም ቤት/

**በጋራ ማንበብ** (Choral reading)፦ በርከት ያሉ ተማሪዎች አንድን ጽሑፍ በጋራ ሆነው ድምፅ በማሰማት የሚያነቡበት ስልት፣

**ተራኪ ጽሑፍ** (Narrative text)፦ ታሪክን በጊዜ ወይም በቦታ ወይም በድርጊት ቅደምተከተል የሚያሳይ የጽሑፍ መዋቅር

**የታሪክ መዋቅር** (Story structure)፦ እንደመቼት ፣ድርጊት፣ ሁነት፣ ችግርና መፍትሄ ያሉትን አላባውያን የሚያካትት የድርሰት መዋቅር

**ትክክለኛነት** (Accuracy)፦ አንድን ቃል ወይም ሐረግ ወይም ዓረፍተነገር ያለስህተትና ያለማወላወል የማንበብ ችሎታ፣

**ንባብን ወደፊት መቀጠል** (Read ahead)፦ አሻሚ ሀሳብ ሲያጋጥም ግልፅ እንዲሆን ወደፊት ያሉትን ዓረፍተነገሮች ማንበብ፤ የተወሰኑ ዓረፍተነገሮች ተነበው ሀሳቡ ግልፅ ካልሆነ ሌላ ስልት መፈለግ፣

**አመራማሪ ጥያቄዎች** (Implicit/inferential Questions)፦ ተማሪዎች በሚያነቡት/በሚያዳምጡት ጽሑፍ ውስጥ ያሉ መረጃዎችን ከቀደመ ዕውቀታቸው ጋር በማገናኘት መልስ የሚሰጡባቸው የአንብቦ/የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

**አስረጂ ጽሑፍ** (Expository text)፦ መረጃ ሰጪ የሆነ ጽሑፍ ሆኖ ስለአንድ ርዕሰጉዳይ ወይም እውነት ለማስተማር/ለማስረዳት የሚያገለግል ጽሑፍ፣

**አቀላጥፎ ማንበብ** (Fluency)፦ ፊደላትን፣ ቃላትንና ሐረጋትን በትክክል፣ በፍጥነትና መልዕክት ሰጭ በመሆነ መንገድ የማንበብ ችሎታ፣

**አንብቦ መረዳት** (Reading comprehension)፦ አንድ ጽሑፍ አንብቦ የመረዳትና ትርጉም የማግኘት ችሎታ፣

**አዕምሯዊ ምሥል** (Mental picture)፦ የገፀባህርያት፣ የቦታና የሁነቶች ገለፃን በተመለከተ በአዕምሮ ምሥል እየፈጠሩ ማንበብ፣

**አዳምጦ መረዳት** (Listening comprehension)፦ ንግግርን ወይም ጽሑፍን አዳምጦ መረዳትና ትርጉም የመስጠት ችሎታ፣

**የአጻጻፍ ስርዓት** (Writing convention)፦ የፊደላትን ቅርጽ፣ አሰዳደር፣ የአጻጻፍ አቅጣጫና የሥርዓተነጥብን አጠቃቀም የሚያሳይ የአጻጻፍ ሥርዓት፣

**ዋና ሀሳብ /አቢይ ሀሳብ/** (Main idea)፡- ከምንባብ ተጨምቆ የሚወጣ አቢይ ወይም ዋና ሀሳብ፣

**ዐውድ** (Context)፡- ለአንድ እንግዳ ቃል ፍቺ ፍንጭ የሚሰጡ ከቃሉ በፊት ወይም በኋላ የሚገኙ ቃላት፣ ሐረጋት ወይም ዓረፍተነገሮች፣

**ዘውግ** (Genre)፡- በልዩ መዋቅሩ ወይም ባህሪያቱ የሚታወቅ የጽሑፍ መዋቅር፤ ምሳሌ፡- ተውኔት፣ ገላጭ ድርሰት፣ ተራኪ ድርሰት፣

**ዘዬ** (dialect)፡- በንበት/በድምጽ፣ በቃል ወይም በሰዋስው የሚከሰት አካባቢያዊ የቋንቋ አጠቃቀም ልዩነት፣

**የጥንድ ንባብ** (partner reading)፡- በጥንድ ሆኖ ተራ በተራ የማንበብ ሂደት

**ጥያቄ መጠየቅ** (ask question)፡- ጥያቄ እየጠየቁ ማንበብ፣ ምንባቡን ለመረዳት ይጠቅማል። ለጥያቄዎች ምላሽ ማፈላለግ ያነበቡትን ለመረዳት ይረዳል፣

- ምንባቡ ስሜት ሰጥቶኛል?
- የማነበው ለምንድን ነው?
- ስለዚህ ምንባብ ምን የማውቀው ነገር አለኝ?
- ካነበብኩ በኋላ የምማረው ምንድን ነው?
- የዘለልኩት ነገር አለ?
- ምን ምን ጥያቄዎች አሉኝ?
- ስለምንባቡ ምን አስባለሁ? እስማማለሁ? ግራ ተጋብቻለሁ?
- ፍጥነቴን መቀነስ ነው ያለብኝ ወይስ መጨመር?

**የጽሑፍ መዋቅር** (text structure)፡- በጽሑፍ ውስጥ የይዘቶች አደረጃጀት

# ዋቢዎች

## ምዕራፍ 1


ማረው አለሙ። 2005። *በሳል ድርሰት ማስተማሪያ።* አዲስ አበባ፤ አልፋ አታሚዎች።

ሰይድ ይማም። (ዓ.ም. የሌለው)። "በከሚሴ ከተማ ዙሪያ በሚገኙ ገጠር ቀበሌዎች የወጣት ወንዶችና ሴቶች አለባበስና አጊያጊያጥ ፎክሎራዊ ገጽታ። " (ያልታተመ)።

ባየ ይማም። 1987። *የአማርኛ ሰዋስው።* ት.መ.ማ.ማ.ድ

-------------። 2002። *አጭርና ቀላል የአማርኛ ሰዋስው።* አዲስ አበባ፤ አልፋ አታሚዎች።


## ምዕራፍ 2


ሰለሞን ጥላሁንና ስምረት ገብረማርያም። 2000። *ደማቆቹ። አንዳንድ ታዋቂ ኢትዮጵያውንና ኢትዮጵያዊያት የህይወት ውልብታ።*

ቅዱስ ሀብት በላቸው። 2014። መጠነኛ ለውጥ ተደርጎ የተወሰደ

ከሳቴ ለገሰ። 1999። *የትግራይ ስፖርት እንቅስቃሴ ከየት ወዴት።* ኢትዮ ጥቁር አባይ አሳታሚዎች።

ፈንታሁን እንግዳ። 2000። *ታሪካዊ መዝገበሰብዕ ከጥንት እስከዛሬ።* አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት።


## ምዕራፍ 3


አንተነህ አወቀ። 2001። "የአማርኛ ስነቃል አጭር ቅኝት። " በአብክመ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ። *የአማራ ሕዝብ ባህልና ቋንቋ።* አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት።

አድማሱ ደስታ። 1980። *የማር እሸት።* አዲስ አበባ፤ ንግድ ማተሚያ ድርጅት።

ዘሪሁን አስፋው። 1992። *የሥነፅሁፍ መሠረታውያን።* አዲስ አበባ፤ ንግድ ማተሚያ ድርጅት።

የአብክመ ባህል፣ ቱሪዝምና ፓርኮች ልማት ቢሮ የባህል እሴቶችና ተቋማት ጥናት፣ ልማትና አጠቃቀም የስራ ሂደት። 2005። *የግብርና ግጥማዊ ስነቃል።* ባህር ዳር።

## ምዕራፍ 4

አሥራት አብርሃም። 2004። *ጎበዝ ተማሪ የመሆን ምስጢር።* አዲስ አበባ፤ ዚኤ ፕሪንቲንግ።

ዘሪሁን አስፋው። 1992። *የሥነጽሑፍ መሠረታውያን።* አዲስ አበባ፤ ንግድ ማተሚያ ድርጅት።

ጌታሁን አማረ። 1989። *የአማርኛ ሰዋስው በቀላል አቀራረብ።* አዲስ አበባ፤ አልፋ አታሚዎች።

## ምዕራፍ 5

የአማራ ብሔራዊ ክልል ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ። 1991። *የአማራ ክልልየቱሪስት መስህብ ሀብቶች።* አዲስ አበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።

ጌታቸው ደስታ። 1999። *ቱሪዝም በኢትዮጵያ።* አዲስ አበባ።

## ምዕራፍ 6

ከበደ ሚካኤል። 1999። *ታሪክና ምሣሌ። 2ኛ መጽሐፍ። ፯ኛ ዕትም።* አዲስ አበባ፤ ሜጋ አሳታሚና ማከፋፈያ ።

ደረጀ ገብሬ። 1996። *ተግባራዊ የጽሕፈት መመሪያ።* አዲስ አበባ፤ ንግድ ማተሚያ ድርጅት።

## ምዕራፍ 7

ሥርዓተትምህርት ዝግጅት ጥናትና ምርምር ኢንስቲትዩት። 1995። *የኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ትምህርት ለሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች።* አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት።

የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር እና የተባበሩት መንግሥታት በኢትዮጵያ። 2012። *በኢትዮጵያ በወንዶችና በሴቶች ልጆች ላይ መዋዕለ ንዋይ ማፍሰስ፦ ትናንት፣ ዛሬና ነገ።*

Federal HIV/AIDS prevention and control office Federal Ministry of Health. 2011. *HIV PREVENTION PACKAGE.* Addis Ababa.

## ምዕራፍ 8

ማህተመ ሥላሴ ወልደመስቀል። 1959። *የኢትዮጵያ ባህል ጥናት።* አዲስ አበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።

ዘነበ ወላ። 2000። *ልጅነት።* አዲስ አበባ።

የአብክመ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ። 2000። *የባህል ልማት መሰናክሎች ቅኝት።*

ባህር ዳር፤ (ያልታተመ)።

የአብክመ ትምህርት ቢሮ። 1996። *6ኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ።* አዲስ አበባ፤ ቦሌ ማተሚያ ቤት።

ይርጋ ኃይሉ። 2001። *"የአማራ ባህል ገጽታዎች። " በአብክመ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ። የአማራ ሕዝብ ባህልና ቋንቋ።* አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት።

## ምዕራፍ 9

ሜሪ-ጄንና ሳባ ገ/መድህን። 2007። *ተምሳሌት እፁብድንቅ ኢትዮጵያውያን ሴቶች።* አዲስ አበባ፤ ፀሐይ አሳታሚ ድርጅት።

CIDA. 2010. *Education GENDER EQUALITY*. Canada. cette publication

## ምዕራፍ 10

ማረው አለሙ። 2005። *በሳል ድርሰት ማስተማሪያ።* አዲስ አበባ፤ አልፋ አታሚዎች።

ባየ ይማም። 1986። *የአማርኛ ሰዋስው።* አዲስ አበባ፤ትመማማድ።

ታደሰ ሊበን። 1949። *መስከረም።* አዲስ አበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።

ፈንታሁን እንግዳ። 1990። *ዝክረተውኔት።* አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት።

ፈንታሁን እንግዳ። 1992። *የተውኔት ድርሰት አጻጻፍ ዘዴ።* አዲስ አበባ፤ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት።